# الإسلام - نبذة موجزة عن الإسلام
# )مشتملة على الأدلة) (للجمعية(
# እስልምና

# እስልምና

## ስለ እስልምና አጭር ገለፃ፤ በተከበረው ቁርአን እና በነብያዊ ሐዲሥ በመጣበት መልኩ

ይህ እስልምናን አጠር ባለ መልኩ የሚያስተዋውቅና የሚዳስስ አሳሳቢ መጽሐፍ ነው። መሰረታዊ ምንጮች ከሆኑት ከቅዱስ ቁርአን እና ከነብያዊ ሐዲሥ በመመርኮዝ ስለ (እስልምና) አሳሳቢ መሰረቶቹ፣ ስለ አስተምህሮቱ እንዲሁም ስለ መልካምነቱ የሚዳስስ አሳሳቢ ፅሁፍ ሲሆን፤ ኪታቡ ሙስሊምንም ይሁን ከሙስሊም ውጭ ያለ፤ በየትኛውም ጊዜ እና ቦታ የሚገኝ፤ በየትኛውም መስክም ይሁን በየትኛውም ሁኔታ የሚገኝን ለአቅመ ሃላፊነት የደረሰን ሁሉ የሚመለከት አሳሳቢ ኪታብ ነው።

(ከተከበረው ቁርአንና ከነብያዊ ፈለግ ማስረጃዎችን ያካተተ ቅጂ)

## 1- እስልምና ወደ ሰው ልጆች ሁሉ የተላከ የአላህ መልዕክት ነው። እንዲሁም ዘውታሪ የሆነ አምላካዊ የመጨረሻ መልዕክቱም ነው።

እስልምና ወደ ሰው ልጆች ሁሉ የተላከ የአላህ መልዕክት ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا كَآفَّةٗ لِّلنَّاسِ بَشِيرٗا وَنَذِيرٗا وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ}

{እንተንም ለሰዎች ሁሉ በሙላ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢሆን እንጂ አላክንህም። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም።} (ሰባእ፡ 28) ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{قُلْ يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنِّي رَسُولُ اللَّهِ إِلَيْكُمْ جَمِيعًا}

{(ሙሐመድ ሆይ!)፡- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ» በላቸው} [አል-አዕራፍ 158] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ قَدْ جَاءَكُمُ الرَّسُولُ بِالْحَقِّ مِن رَّبِّكُمْ فَآمِنُوا خَيْرًا لَّكُمْ ۚ وَإِن تَكْفُرُوا فَإِنَّ لِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ وَكَانَ اللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا}

እናንተ ሰዎች ሆይ! መልክተኛው እውነትን ከጌታችሁ አመጣላችሁ። እመኑም ለናንተ የተሻለ (ይኾናል)። ብትክዱም (አትጎዱትም)። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነውና። አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው። [ኒሳእ 170]

እስልምና ዘላለማዊ መለኮታዊ መልእክት ነው፤ እንዲሁም የመለኮታዊ መልእክቶች መደምደሚያም ነው።

{مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَا أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ اللَّهِ وَخَاتَمَ النَّبِيِّينَ ۗ وَكَانَ اللَّهُ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمًا}

"ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም። ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው። አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው።" [አልአሕዛብ 40]

## 2- እስልምና ለተወስኑ ነገዶች ወይንም ህዝቦች ብቻ የተወሰነ ሃይማኖት ሳይሆን አምላካዊ የሰው ልጆች ሁሉ ሃይማኖት ነው።

እስልምና ለተወስኑ ነገዶች ወይንም ህዝቦች ብቻ የተወሰነ ሃይማኖት ሳይሆን አምላካዊ የሰው ልጆች ሁሉ ሃይማኖት ነው። በታላቁ ቁርአን ውስጥ የመጀመርያው ትእዛዝ እንዲህ የሚለው የአላህ ቃል ነው፡-

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ اعْبُدُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُمْ وَالَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ}

"እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።" [(አል በቀራ፡21) ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ اتَّقُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَاحِدَةٍ وَخَلَقَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَبَثَّ مِنْهُمَا رِجَالًا كَثِيرًا وَنِسَاءً }

{እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርስዋም መቀናጆዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ።} [ኒሳእ 1] (የሁለቱንም መልካም ስራቸውን አላህ ይውደድላቸውና) ኢብኑ ዑመር ባስተላለፈው ሐዲሥ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መካን በከፈቱ ጊዜ እንዲህ የሚል ኹጥባ (ንግግር) ማድረጋቸው ተዘግቧል፡-

«يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّ اللَّهَ قَدْ أَذْهَبَ عَنْكُمْ عُبِّيَّةَ الجَاهِلِيَّةِ وَتَعَاظُمَهَا بِآبَائِهَا فَالنَّاسُ رَجُلَانِ: بَرٌّ تَقِيٌّ كَرِيمٌ عَلَى اللَّهِ وَفَاجِرٌ شَقِيٌّ هَيِّنٌ عَلَى اللَّهِ وَالنَّاسُ بَنُو آدَمَ

وَخَلَقَ اللَّهُ آدَمَ مِنْ تُرَابٍ قال الله:{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا ۚ إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ} [الحجرات:13] »

«እናንተ የሰው ልጆች ሆይ! አላህ የዘመነ ድንቁርናን መመፃደቅንና በወላጆቻቻው መኮፈስን ከእናንተ አስወግዶላችኋል። በመሆኑም ሰዎች ሁለት አይነት ብቻ ናቸው፤ ወይ ቸር የሆነ አላህን ፈሪ አላህም ዘንድ የተከበረ አለበለዚያም አመፀኛ የሆነ እድለቢስ አላህም ዘንድ የተዋረደ ነው። ሰዎች ሁሉ የአደም ልጆች ናቸው፤ አላህ ደግሞ አደምን ከአፈር ነው የፈጠረው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው። አላህ ግልጽን ዓዋቂ ውስጥንም ዓዋቂ ነው።} [አል-ሑጁራት 13] » ቲርሚዚይ ዘግበውታል (3270) እናም በታላቁ ቁርአን ትዕዛዛትም ይሁን በክቡር መልእክተኛው መመርያ ውስጥ ባህልም ሆነ ጎሳን ወይንም ዘርን ብቻ ነጥሎ የተደነገገ መመርያ አናገኝም።

## 3- እስልምና የአላህ ሰላት እና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና የቀደምት ነብያትንና መልእክተኞችን መልእክት ለማሟላት የመጣ መለኮታዊ መልእክት ነው።

እስልምና የአላህ ሰላት እና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና የቀደምት ነብያትንና መልእክተኞችን መልእክት ለማሟላት

የመጣ መለኮታዊ መልእክት ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ إِنَّا أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ كَمَا أَوْحَيْنَا إِلَىٰ نُوحٍ وَالنَّبِيِّينَ مِن بَعْدِهِ ۚ وَأَوْحَيْنَا إِلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ وَالْأَسْبَاطِ وَعِيسَىٰ وَأَيُّوبَ وَيُونُسَ وَهَارُونَ وَسُلَيْمَانَ ۚ وَآتَيْنَا دَاوُودَ زَبُورًا}

{እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን። ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስማዒልም፣ ወደ ኢስሓቅም፣ ወደ ያዕቆብም፣ ወደ ነገዶቹም፣ ወደ ዒሳም፣ ወደ አዩብም፣ ወደ ዩኑስም፣ ወደ ሃሩንና፣ ወደ ሱለይማንም አወረድን። ለዳውድም ዘቡርን ሰጠነው።} [ኒሳእ 163] እናም ይህ አላህ ለመልእክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የገለጠው ሃይማኖት ለቀደሙት ነቢያት የደነገገውንና እንዲከተሉትም ያዘዘበትን ሃይማኖት ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{شَرَعَ لَكُم مِّنَ الدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِ نُوحًا وَالَّذِي أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ وَمَا وَصَّيْنَا بِهِ إِبْرَاهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰ ۖ أَنْ أَقِيمُوا الدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُوا فِيهِ ۚ كَبُرَ عَلَى الْمُشْرِكِينَ مَا تَدْعُوهُمْ إِلَيْهِ ۚ اللَّهُ يَجْتَبِي إِلَيْهِ مَن يَشَاءُ وَيَهْدِي إِلَيْهِ مَن يُنِيبُ}

{ለእናንተ ከሃይማኖት ያንን በእርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ። ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በእርሱ ኢብራሂምን፣ ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ በእርሱም አትለያዩ ማለትን (ደነገግን)። በአጋሪዎቹ ላይ ያ ወደርሱ የምትጠራቸው ነገር ከበዳቸው። አላህ የሚሻውን ሰው ወደእርሱ (እምነት) ይመርጣል።

የሚመለስንም ሰው ወደርሱ ይመራል።} [አሽ-ሹራ 13] ይህ አላህ ለመልእክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የገለጠው ሃይማኖት ለቀደሙት ነቢያት የደነገገውንና እንዲከተሉትም ያዘዘበትን ሃይማኖት ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَالَّذِي أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ مِنَ الْكِتَابِ هُوَ الْحَقُّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ ۗ إِنَّ اللَّهَ بِعِبَادِهِ لَخَبِيرٌ بَصِيرٌ }

{ያም ከመጽሐፉ ወዳንተ ያወረድንልህ ከበፊቱ ላለው አረጋጋጭ ሲኾን እርሱ እውነት ነው። አላህ በርግጥ በባሮቹ ውስጠ ዐዋቂ ተመልካች ነው።} [ፋጢር 31]

## 4- ነብያቶች ሁሉ የአላህ ሰላት እና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና ሃይማኖታቸው አንድ ሲሆን መመርያ ድንጋጌያቸው ግን የተለያየ ነው።

ነብያቶች ሁሉ የአላህ ሰላት እና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና ሃይማኖታቸው አንድ ሲሆን መመርያ ድንጋጌያቸው ግን የተለያየ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَأَنزَلْنَا إِلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ الْكِتَابِ وَمُهَيْمِنًا عَلَيْهِ ۖ فَاحْكُم بَيْنَهُم بِمَا أَنزَلَ اللَّهُ ۖ وَلَا تَتَّبِعْ أَهْوَاءَهُمْ عَمَّا جَاءَكَ مِنَ الْحَقِّ ۚ لِكُلٍّ جَعَلْنَا مِنكُمْ شِرْعَةً وَمِنْهَاجًا ۚ وَلَوْ شَاءَ اللَّهُ لَجَعَلَكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَلَٰكِن لِّيَبْلُوَكُمْ فِي مَا آتَاكُمْ ۖ فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ ۚ إِلَى اللَّهِ مَرْجِعُكُمْ جَمِيعًا فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ }

{ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን። በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ። እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል። ከእናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን። አላህም በሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር። ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ (ለያያችሁ)። በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው። በእርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል።} [አል-ማኢዳህ 48] መልእክተኛው የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁንና እንዲህ ብለዋል፡-

«أَنَا أَوْلَى النَّاسِ بِعِيسَى ابْنِ مَرْيَمَ فِي الدُّنْيَا وَالْآخِرَةِ وَالْأَنْبِيَاءُ إِخْوَةٌ لِعَلَّاتٍ أُمَّهَاتُهُمْ شَتَّى وَدِينُهُمْ وَاحِدٌ»

«ለመርየም ልጅ ዒሳ ከሰው ልጆች ሁሉ በዱንያም በአኺራም በላጩ (ቅርብ ሰው) እኔ ነኝ፤ ነብያቶችም በእናት ተለያይተው በአባት እንደሚገናኙ ወንድማማቾች ናቸው፤ ሃይማኖታቸው አንድ ነው።» ቡኻሪይ ዘግበውታል (3443)

## 5- እስልምና የሚጣራው፡- ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ሱለይማን፣ ዳውድ፣ ዒሳ የአላህ ሰላት በእነርሱ ላይ ይስፈንና ~ሁሉም ነብያቶች ወደተጣሩበት ብቸኛ ጌታ፣ ፈጣሪ፣ ሲሳይ ለጋሽ፣ ህይወት ሰጭ ህይወት ነሺ፣ ንጉሰ

## ነገስት፣ የጉዳዮችም አስተናባሪ በሆነው አላህ ወደ ማመን ነው።

እስልምና የሚጣራው፦ ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ሱለይማን፣ ዳውድ፣ ዒሳ የአላህ ሰላት በእነርሱ ላይ ይስፈንና ~ሁሉም ነብያቶች ወደተጣሩበት ብቸኛ ጌታ፣ ፈጣሪ፣ ሲሳይ ለጋሽ፣ ህይወት ሰጭ ህይወት ነሺ፣ ንጉሰ ነገስት፣ የጉዳዮችም አስተናባሪ በሆነው አላህ ወደ ማመን ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ اذْكُرُوا نِعْمَتَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ ۚ هَلْ مِنْ خَالِقٍ غَيْرُ اللَّهِ يَرْزُقُكُم مِّنَ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ ۚ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ فَأَنَّىٰ تُؤْفَكُونَ }

{እናንተ ሰዎች ሆይ! በእናንተ ላይ (ያለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ፡፡ ከአላህ ሌላ ፈጣሪ አለን? ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣችሁ አለን? ከእርሱ በስተቀር አምላክ (ሰጪም) የለም፡፡ ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ፡፡} [ፋጢር 3]

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ مَن يَرْزُقُكُم مِّنَ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ أَمَّن يَمْلِكُ السَّمْعَ وَالْأَبْصَارَ وَمَن يُخْرِجُ الْحَيَّ مِنَ الْمَيِّتِ وَيُخْرِجُ الْمَيِّتَ مِنَ الْحَيِّ وَمَن يُدَبِّرُ الْأَمْرَ ۚ فَسَيَقُولُونَ اللَّهُ ۚ فَقُلْ أَفَلَا تَتَّقُونَ }

{«ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው ከሙትም ሕያውን የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን የሚያወጣስ ማን ነው ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው» በላቸው፡፡ «በእርግጥም አላህ ነው» ይሉሃል፡፡ «ታዲያ (ለምን

ታጋራላቸሁ) አትፈሩትምን» በላቸው፡፡} [ዩኑስ 31] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{أَمَّن يَبْدَأُ الْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُ وَمَن يَرْزُقُكُم مِّنَ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ ۗ أَإِلَٰهٌ مَّعَ اللَّهِ ۚ قُلْ هَاتُوا بُرْهَانَكُمْ إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ}

{ያ መፍጠርን የሚጀምር ከዚያም የሚመልሰው ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣችሁ አምላክ (ይበልጣልን ወይስ የሚያጋሩት) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን «እውነተኞች እንደኾናችሁ፤ አስረጃችሁን አምጡ» በላቸው፡፡} [አን-ነምል 64]

የአላህ ሰላም ይስፈንባቸውና ነብያቶችና መልእክተኞች ሁሉ የተላኩት አላህን በብቸኝነት ወደ ማምለክ ጥሪ እንዲያደርጉ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِي كُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَۖ فَمِنۡهُم مَّنۡ هَدَى ٱللَّهُ وَمِنۡهُم مَّنۡ حَقَّتۡ عَلَيۡهِ ٱلضَّلَٰلَةُۚ فَسِيرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَٱنظُرُواْ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُكَذِّبِينَ}

{በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ «አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል፡፡ ከእነሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አልለ፡፡ ከእነሱም ውስጥ በእርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አልለ፡፡ በምድርም ላይ ኺዱ፤ የአስተባባዮችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከቱ፡፡} [አን-ነሕል 36] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِي إِلَيْهِ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنَا فَاعْبُدُونِ}

{ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።} [አል-አንቢያእ 25] ኑሕ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸውን አላህ ነግሮናል፡-

{يَا قَوْمِ اعْبُدُوا اللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُ إِنِّي أَخَافُ عَلَيْكُمْ عَذَابَ يَوْمٍ عَظِيمٍ}

{ኑሕን ወደ ወገኖቹ በእርግጥ ላክነው። አላቸውም፡- «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ለእናንተ ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። እኔ በእናንተ ላይ የከባድ ቀንን ቅጣት እፈራላችኋለሁ።»} [አል አዕራፍ 59] የአላህ ኸሊል ኢብራሂም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸውን አላህ ነግሮናል፡-

{ وَإِبْرَٰهِيمَ إِذْ قَالَ لِقَوْمِهِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ وَٱتَّقُوهُ ۖ ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ}

{ኢብራሂምንም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። «አላህን ተገዙ ፍሩትም። ይህ የምታውቁ ብትሆኑ ለእናንተ በላጭ ነው።} [አል-ዓንከቡት 16] ነብዩ ሷሊሕ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አላህ እንደነገረን እንዲህ ብለዋል፡-

{قَالَ يَا قَوْمِ اعْبُدُوا اللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُ ۖ قَدْ جَاءَتْكُم بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ ۖ هَٰذِهِ نَاقَةُ اللَّهِ لَكُمْ آيَةً ۖ فَذَرُوهَا تَأْكُلْ فِي أَرْضِ اللَّهِ ۖ وَلَا تَمَسُّوهَا بِسُوءٍ فَيَأْخُذَكُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ}

{ወደ ሰሙድም ወንድማቸውን ሷሊህን ላክን። አላቸው «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ለእናንተ ምንም አምላክ የላችሁም። (እውነተኛ ለመኾኔ) ከጌታችሁ የኾነች

ምልክት በእርግጥ መጥታላችኋለች። ይህች ለእናንተ ተዓምር ስትኾን የአላህ ግመል ናትና ተዋት። በአላህ ምድር ውስጥ ትብላ፤ (ትጠጣም)። በክፉ አትንኳትም። አሰማሚ ቅጣት ይይዛችኋልና።»} [አል-አዐራፍ 73] ነብዩ ሹዐይብ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንም አላህ እንደነገረን እንዲህ ብለዋል፡-

{يَا قَوْمِ اعْبُدُوا اللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُ ۖ قَدْ جَاءَتْكُم بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ ۖ فَأَوْفُوا الْكَيْلَ وَالْمِيزَانَ وَلَا تَبْخَسُوا النَّاسَ أَشْيَاءَهُمْ وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا ۚ ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ}

{ወደ መድየንም (ምድያን) ወንድማቸውን ሹዓይብን (ላክን)፤ አላቸው፡- «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም። ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ በእርግጥ መጥታላችኋለች። ስፍርንና ሚዛንን ሙሉ። ሰዎችንም አንዳቾቻቸውን (ገንዘቦቻቸውን) አታጉድሉባቸው። በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ። ይህ ምእምናን እንደኾናችሁ ለእናንተ የተሻለ ነው።»} [አል-አዕራፍ 85]

ነብዩሏህ ሙሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንን አላህ መጀመርያውኑ እንዳናገራቸውም ጥሪት ይገባውና እንዲህ ነው ያለው፡-

{وَأَنَا اخْتَرْتُكَ فَاسْتَمِعْ لِمَا يُوحَىٰ (13) إِنَّنِي أَنَا اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنَا فَاعْبُدْنِي وَأَقِمِ الصَّلَاةَ لِذِكْرِي (14)}

{«እኔም መረጥኩህ፤ የሚወረድልህንም ነገር አዳምጥ።} 13

{«እኔ አላህ እኔ ነኝ ያለ እኔ አምላክ የለምና ተገዛኝ፡፡ ሶላትንም (በእርሷ) እኔን ለማውሳት ስገድ፡፡} 14 [ጧሃ 13-14] አላህ ስለ ነብዩሏህ ሙሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሲነግረን እንዲህ በሚል በአላህ ጥበቃ መፈለጋቸውን ነግሮናል፡-

{إِنِّي عُذْتُ بِرَبِّي وَرَبِّكُم مِّن كُلِّ مُتَكَبِّرٍ لَّا يُؤْمِنُ بِيَوْمِ الْحِسَابِ }

{ሙሳም «እኔ በምርመራው ቀን ከማያምን ትዕቢተኛ ሁሉ በጌታዬና በጌታችሁ ተጠበቅሁ» አለ፡፡} [ጋፊር 27] ነብዩሏህ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸውን አላህ እንዲህ ሲል ነግሮናል፡-

{ إِنَّ اللَّهَ رَبِّي وَرَبُّكُمْ فَاعْبُدُوهُ ۗ هَٰذَا صِرَاطٌ مُّسْتَقِيمٌ }

{«አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው፤ ስለዚህ ተገዙት፤ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው» (አላቸው)፡፡} [አሊ-ዒምራን 51] ነብዩሏህ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸውን አላህ እንዲህ ሲል ነግሮናል፡-

{ يَا بَنِي إِسْرَائِيلَ اعْبُدُوا اللَّهَ رَبِّي وَرَبَّكُمْ ۖ إِنَّهُ مَن يُشْرِكْ بِاللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ اللَّهُ عَلَيْهِ الْجَنَّةَ وَمَأْوَاهُ النَّارُ ۖ وَمَا لِلظَّالِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ }

{«የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታየንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፡፡ እነሆ በኣላሀ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፡፡ መኖርያቸውም እሳት ናት፡፡ ለበዳዮች ምንም ረዳቶች የላቸውም፡፡»} [አል ማእዳህ:72]

ኧረ እንደውም በተውራት (ኦሪት) እና በኢንጂልም (ወንጌል) ጭምር ጠንከር ባለ መልኩ የመጣው አላህን ብቻ ማምለክ ነው፡፡ በኦሪት ዘዳግም (6:4) ላይ ሙሴ እንዲህ

ማለታቸውን ነው የምናገኘው፡- {እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እ/ር አንድ እ/ር ነው።} በማርቆስ ወንጌልም (12:29) ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ በማለት የአምላክን አሃዳዊነት የሚያፀና ሆኖ ነው የምናገኘው፡- {ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፤ "ከትእዛዝ ሁሉ ፊተኛይቱ እስራኤል ሆይ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው"}

የላቀው አላህ ነብያቶች ሁሉ በዚህቸው እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ መላካቸውን ነው የነገረን። ይኸውም ወደ አላህ አሃዳዊነት ነው፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولًا أَنِ اعْبُدُوا اللَّهَ وَاجْتَنِبُوا الطَّاغُوتَ ۖ فَمِنْهُم مَّنْ هَدَى اللَّهُ وَمِنْهُم مَّنْ حَقَّتْ عَلَيْهِ الضَّلَالَةُ }

{በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ «አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል። ከእነሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አልለ። ከእነሱም ውስጥ በእርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አልለ። በምድርም ላይ ኺዱ፤ የአስተባባዮችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከቱ።} [አን-ነሕል 36] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡- {«ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸውን አያችሁን? ከምድር ምንን እንደ ፈጠሩ አሳዩኝ። ወይም በሰማያት ለእነርሱ (ከአላህ ጋር) መጋራት አላቸውን? (ያማልዱናል በማለታችሁ) እውነተኞች እንደ ኾናችሁ ከዚህ (ቁርኣን) በፊት የኾነን መጽሐፍ ወይም ከዕውቀት የኾነ ቅርስን አምጡልኝ» በላቸው።} [አል-አሕቃፍ 4] ሸይኽ ሰዕዲይ አላህ ይዘንላቸው እንዲህ ብለዋል፡-

"በዚህም ሙሽሪኮች (አጋሪዎች) ሽርካቸውን በተመለከተ ያቀረቡትን ክርክር (ሙግታቸው) በማስረጃ ወይም በበቂ መረጃ ላይ የተመሠረተ እንዳልሆነ ግልፅና የታወቀ ሆነ። ይልቁንም በተሳሳቱ ግምቶችና በተኮላሹ አመለካከቶች እንዲሁም በተመረዙ አእምሮዎች ላይ የተመሠረተ ነበር። የአቋማቸውንም ብልሽት ከሚያመላክቱህ ነገሮች መካከል ሁኔታዎቻቸውን በመከታተል፣ 'እውቀታቸውን' እና ተግባሮቻቸውን በመመርመር፣ (ይኸው ከአላህ ውጭ) ሲያመልኩት ሕይወታቸውን ያሳለፉለት አካል በዱኒያቸው ነው ወይንስ በአኼራቸው የፈየዳቸው?!" ተይሲሩል ከሪሙ ረሕማን: 779

## 6- ጥራት ይገባውና ከፍ ያለው አላህ ፈጣሪ እና ለአምልኮ ብቸኛው ተገቢ የሆነ ከእርሱም ሌላ አብሮት ሊመለክ የማይገባው ነው።

በብቸኝነት ሊመለክ የሚገባው አላህ ብቻ ነው። ከእርሱም ሌላ ማንም ሊመለክ አይገባውም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ اعْبُدُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُمْ وَالَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ (21) الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الْأَرْضَ فِرَاشًا وَالسَّمَاءَ بِنَاءً وَأَنزَلَ مِنَ السَّمَاءِ مَاءً فَأَخْرَجَ بِهِ مِنَ الثَّمَرَاتِ رِزْقًا لَّكُمْ ۖ فَلَا تَجْعَلُوا لِلَّهِ أَندَادًا وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ (22)}

{እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።}

{(እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤ ከሰማይም (ከደመና) ውሃን ያወረደ በርሱም ከፍሬዎች ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው። እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ።} [አል-በቀራህ 21-22] እኛንም ሆነ ከእኛ በፊት የነበሩትን ትውልዶች የፈጠረና ምድርን ምንጣፍ ያደረገልን፣ ከሰማይም ውሃን በማውረድ ሲሳያችንን ያፈራልን እርሱ ነው። አምልኮ የሚገባው እርሱ ብቻ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ اذْكُرُوا نِعْمَتَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ ۚ هَلْ مِنْ خَالِقٍ غَيْرُ اللَّهِ يَرْزُقُكُم مِّنَ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ ۚ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ فَأَنَّىٰ تُؤْفَكُونَ}

{እናንተ ሰዎች ሆይ! በእናንተ ላይ (ያለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ። ከአላህ ሌላ ፈጣሪ አለን? ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣችሁ አለን? ከእርሱ በስተቀር አምላክ (ሰጪም) የለም። ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ።} [ፋጢር 3] የሚፈጥርና ሲሳይንም የሚለግስ እርሱ ብቻ ነው አምልኮ የሚገባው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ذَٰلِكُمُ اللَّهُ رَبُّكُمْ ۖ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ خَالِقُ كُلِّ شَيْءٍ فَاعْبُدُوهُ ۚ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ وَكِيلٌ}

{ይህ ጌታችሁ አላህ ነው። ከእርሱ በቀር አምላክ የለም። ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው። ስለዚህም ተገዙት። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው።} [አል-አንዓም 102]

እናም ከአላህ ውጭ የሚመለክ ሁሉ ለአምልኮ ተገቢ ሆኖ አይደለም፤ ምክንያቱም በሰማይም ሆነ በምድር የአቶም

ክብደት ያክል ነገር ላይ እንኳ የበላይ ተቆጣጣሪነት የሌለው፣ በምንም መልኩ ለአላህ አጋር ወይንም ረዳት ሆነ አጋዥ የማይሆን፤ እንዴት ከአላህ ጋ ይጠራል?! እንዴትስ ለአላህ ተጋሪ ይደረጋል?! ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{قُلِ ادْعُوا الَّذِينَ زَعَمْتُم مِّن دُونِ اللَّهِ ۖ لَا يَمْلِكُونَ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ فِي السَّمَاوَاتِ وَلَا فِي الْأَرْضِ وَمَا لَهُمْ فِيهِمَا مِن شِرْكٍ وَمَا لَهُ مِنْهُم مِّن ظَهِيرٍ
}

{«እነዚያን ከአላህ ሌላ (አማልክት ብላችሁ) የምታስቧቸውን ጥሩ። በሰማያትም በምድርም ውስጥ የብናኝ ክብደት ያክል ምንንም አይችሉም። ለእነርሱም በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም። ከእነርሱም ለእርሱ ምንም አጋዥ የለውም፤» በላቸው።} [ሰበእ 22]

ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ ፍጥረታት የፈጠረና ያላንዳች ያስገኛቸውም ነው። የፍጥረታቱም መኖር ፈጣሪ ሞኖሩን፣ ጌትነቱና አምላክነቱ ማስረጃና አመላካች ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ إِذَا أَنتُم بَشَرٌ تَنتَشِرُونَ (20) وَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا لِّتَسْكُنُوا إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً وَرَحْمَةً ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ (21) وَمِنْ آيَاتِهِ خَلْقُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَاخْتِلَافُ أَلْسِنَتِكُمْ وَأَلْوَانِكُمْ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّلْعَالِمِينَ (22) وَمِنْ آيَاتِهِ مَنَامُكُم بِاللَّيْلِ وَالنَّهَارِ وَابْتِغَاؤُكُم مِّن فَضْلِهِ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَسْمَعُونَ (23) وَمِنْ آيَاتِهِ يُرِيكُمُ الْبَرْقَ خَوْفًا وَطَمَعًا وَيُنَزِّلُ مِنَ السَّمَاءِ مَاءً فَيُحْيِي بِهِ الْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَا ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ (24) وَمِنْ آيَاتِهِ أَن تَقُومَ السَّمَاءُ وَالْأَرْضُ بِأَمْرِهِ ۚ ثُمَّ إِذَا دَعَاكُمْ دَعْوَةً مِّنَ الْأَرْضِ إِذَا أَنتُمْ تَخْرُجُونَ (25) وَلَهُ مَن فِي

السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۖ كُلٌّ لَّهُ قَانِتُونَ (26) وَهُوَ الَّذِي يَبْدَأُ الْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُ وَهُوَ أَهْوَنُ عَلَيْهِ }

{እናንተንም ከዐፈር መፍጠሩ ከዚያም እናንተ ወዲያውኑ የምትበታተኑ ሰዎች መኾናችሁ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው።} (20)

{ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ።} (21)

{ሰማያትንና ምድርንም መፍጠሩ፣ የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁም መለያየት፣ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለዐዋቂዎች ተዓምራቶች አልሉበት።} (22)

{በሌሊትና በቀንም መተኛታችሁ፣ ከችሮታውም መፈለጋችሁ ከምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉበት።} (23)

{ብልጭታንም ፈሪዎችና ከጃዮች ስትሆኑ ለእናንተ ማሳየቱ፣ ከሰማይም ውሃን ማውረዱ፣ በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚያስቡ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልለበት።} (24)

{ሰማይና ምድርም (ያለምሰሶ) በትዕዛዙ መቆማቸው፣ ከዚያም (መልአኩ ለትንሣኤ) ከምድር ጥሪን በጠራችሁ ጊዜ

እናንተ ወዲያውኑ የምትወጡ መሆናችሁ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው።} (25)

{በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። ሁሉም ለእርሱ ታዛዦች ናቸው።} (26)

{እርሱም የመፍጠርን የሚጀምር ከዚያም የሚመልሰው ነው። እርሱም (መመለሱ) በእርሱ ሊዩ በጣም ገር ነው።} (27) [አር-ሩም 20-27]

ነምሩድ የጌታውን መኖር አስተባበለ፣ አላህ እንደነገረንም ነብዩሏህ ኢብራሂም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለውታል፡-

{قَالَ إِبْرَاهِيمُ فَإِنَّ اللَّهَ يَأْتِي بِالشَّمْسِ مِنَ الْمَشْرِقِ فَأْتِ بِهَا مِنَ الْمَغْرِبِ فَبُهِتَ الَّذِي كَفَرَ ۗ وَاللَّهُ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ }

{ኢብራሂም፡- «አላህ ፀሐይን ከምሥራቅ በኩል ያመጣል (አንተ) ከምዕራብ በኩል አምጣት» አለው። ያም የካደው ሰው ዋለለ፤ (መልስ አጣ) አላህም በዳዮች ሕዝቦችን አይመራም።} [አል-በቀራ 258] ነብዩሏህ ኢብራሂም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አላህን በተመለከተ የሚመራቸው፣ የሚመግባቸው፣ የሚያጠጣቸው፣ በታመሙም ጊዜ የሚያሽራቸው፣ የሚገድላቸውም ሆነ ህያው የሚያደርጋቸውም አላህ መሆኑን ማስረጃ አድርገው በማቅረብ ህዝባቸውን አስረድተውበታል። ልክ አላህ እንዲህ ብሎ ስለ እርሳቸው እንደነገረን፡-

{الَّذِي خَلَقَنِي فَهُوَ يَهْدِينِ (78) وَالَّذِي هُوَ يُطْعِمُنِي وَيَسْقِينِ (79) وَإِذَا مَرِضْتُ فَهُوَ يَشْفِينِ (80) وَالَّذِي يُمِيتُنِي ثُمَّ يُحْيِينِ (81) }

{«(እርሱ) ያ የፈጠረኝ ነው። እርሱም ይመራኛል።

«ያም እርሱ የሚያበላኝና የሚያጠጣኝ ነው።

«በታመምኩም ጊዜ እርሱ ያሽረኛል።

«ያም የሚገድለኝ ከዚያም ሕያው የሚያደርገኝ ነው።} [አሽ-ሹዓራእ 78-81] አላህ ነብዩሏህ ሙሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ከፊርዓውን ጋ የነበራቸውን ሙግት አስመልክቶ ሲነግረን እንዲህ እንዳሉት ነግሮናል።

{ الَّذِي أَعْطَىٰ كُلَّ شَيْءٍ خَلْقَهُ ثُمَّ هَدَىٰ}

{«ጌታችን ያ ለፍጥረቱ ነገርን ሁሉ (የሚያስፈልገውን) የሰጠ ከዚያም የመራው ነው» አለው።} [ጧሃ 50]

አላህ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ ለሰው ልጅ አግርቶ በፀጋው አካበበው። አላህን እንዲያመልኩ እና እንዳይክዱትም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{أَلَمْ تَرَوْا أَنَّ اللَّهَ سَخَّرَ لَكُم مَّا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ وَأَسْبَغَ عَلَيْكُمْ نِعَمَهُ ظَاهِرَةً وَبَاطِنَةً ۗ وَمِنَ النَّاسِ مَن يُجَادِلُ فِي اللَّهِ بِغَيْرِ عِلْمٍ وَلَا هُدًى وَلَا كِتَابٍ مُّنِيرٍ }

{አላህ በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ ለእናንተ ያገራላችሁ ጸጋዎቹንም ግልጽም ድብቅም ሲሆኑ የሞላላችሁ መሆኑን አታዩምን? ከሰዎችም ያለ ዕውቀትና ያለ መሪ፣ ያለግልጽ መጽሐፍም በአላህ የሚከራከር አልለ።} [ሉቅማን 20] አላህ በሰማይና ምድር ያለውን ሁሉ ለሰው ልጅ እንዳገራላቸው ሁሉ የሚጠቅመውን እውቀት እንዲማርና ወደ ጌታውም እንዲመራ መስሚያ፣ መመልከቻ

እና ልቦናንም በሚያስፈልገው ልክ አዘጋጅቶታል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَاللَّهُ أَخْرَجَكُم مِّن بُطُونِ أُمَّهَاتِكُمْ لَا تَعْلَمُونَ شَيْئًا وَجَعَلَ لَكُمُ السَّمْعَ وَالْأَبْصَارَ وَالْأَفْئِدَةَ ۙ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ }

{አላህም ከእናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ። ታመሰግኑም ዘንድ ለእናንተ መስሚያን ማያዎችንም ልቦችንም አደረገላችሁ።} [አን-ነሕል 78]

ሁሉን ቻይ የሆነው አላህ እነዚህን ዓለማት ሁሉ ፈጥሯል የሰውን ልጅም እንዲሁ ፈጥሯል እናም በሚፈልጉት አባላት እና ኃይሎች ሁሉ አዘጋጀው፣ ከዚያ የአላህን አምልኮ እና የምድር ግንባታ እንዲሠራ የሚረዳውን ሁሉ ሰጠው፣ ከዚያም ሰማይና ምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ ለእርሱ አስገዛ።

የላቀው አላህ እነዚህን ታላላቅ ፍጥረታት መፍጠሩን ግድ ለሚያስብለው መለኮታዊ ጌትነቱ ማስረጃ አደረገ። ጥራት ይገባውና እንዲህም ብሏል፦

{قُلْ مَنْ يَرْزُقُكُمْ مِنَ السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ أَمَّنْ يَمْلِكُ السَّمْعَ وَالْأَبْصَارَ وَمَنْ يُخْرِجُ الْحَيَّ مِنَ الْمَيِّتِ وَيُخْرِجُ الْمَيِّتَ مِنَ الْحَيِّ وَمَنْ يُدَبِّرُ الْأَمْرَ فَسَيَقُولُونَ اللَّهُ فَقُلْ أَفَلَا تَتَّقُونَ }

{«ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው ከሙትም ሕያውን የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን የሚያወጣስ ማን ነው ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው» በላቸው።

«በእርግጥም አላህ ነው» ይሉሃል። «ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ) አትፈሩትምን» በላቸው።} [ዩኑስ 31] ጥራት የተገባው የላቀው አል-ሓቅ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ أَرَأَيْتُمْ مَا تَدْعُونَ مِنْ دُونِ اللَّهِ أَرُونِي مَاذَا خَلَقُوا مِنَ الْأَرْضِ أَمْ لَهُمْ شِرْكٌ فِي السَّمَاوَاتِ ائْتُونِي بِكِتَابٍ مِنْ قَبْلِ هَذَا أَوْ أَثَارَةٍ مِنْ عِلْمٍ إِنْ كُنْتُمْ صَادِقِينَ}

{«ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸውን አያችሁን? ከምድር ምንን እንደ ፈጠሩ አሳዩኝ። ወይም በሰማያት ለእነርሱ (ከአላህ ጋር) መጋራት አላቸውን? (ያማልዱናል በማለታችሁ) እውነተኞች እንደ ኾናችሁ ከዚህ (ቁርኣን) በፊት የኾነን መጽሐፍ ወይም ከዕውቀት የኾነ ቅርስን አምጡልኝ» በላቸው።} [አል-አሕቃፍ 4] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ خَلَقَ السَّمَاوَاتِ بِغَيْرِ عَمَدٍ تَرَوْنَهَا وَأَلْقَىٰ فِي الْأَرْضِ رَوَاسِيَ أَن تَمِيدَ بِكُمْ وَبَثَّ فِيهَا مِن كُلِّ دَابَّةٍ وَأَنزَلْنَا مِنَ السَّمَاءِ مَاءً فَأَنبَتْنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوْجٍ كَرِيمٍ. هَٰذَا خَلْقُ اللَّهِ فَأَرُونِي مَاذَا خَلَقَ الَّذِينَ مِن دُونِهِ بَلِ الظَّالِمُونَ فِي ضَلَالٍ مُّبِينٍ}

{ሰማያትን ያለምታዩዋት አዕማድ (ምሰሶዎች) ፈጠረ። በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለ። በእርሷም ላይ ከተንቀሳቃሽ ሁሉ በተነ። ከሰማይም ውሃን አወረድን። በእርሷም ውስጥ ከመልካም ዓይነት ሁሉ አበቀልን። ይህ የአላህ ፍጡር ነው። እነዚያ ከእርሱ ሌላ ያሉት ምንን እንደፈጠሩ እስኪ አሳዩኝ። በእውነቱ በዳዮች በግልጽ ጥመት ውስጥ ናቸው።} [ሉቅማን 10-11] ጥራት የተገባው የላቀው አል-ሓቅ እንዲህ ብሏል፦

{ أَمْ خُلِقُوا مِنْ غَيْرِ شَيْءٍ أَمْ هُمُ الْخَالِقُونَ (35) أَمْ خَلَقُوا السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ بَلْ لَا يُوقِنُونَ (36) أَمْ عِندَهُمْ خَزَائِنُ رَبِّكَ أَمْ هُمُ الْمُصَيْطِرُونَ (37) }

{ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን?}

{ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም አያረጋግጡም።}

{ወይስ የጌታህ ግምጃ ቤቶች እነርሱ ዘንድ ናቸውን? ወይስ እነርሱ አሸናፊዎች ናቸውን?} [አጥ-ጡር 35-37] ሸይኽ ሰዕዲይ እንዲህ ብለዋል፦ "ይህ ለእውነታው እጅ ከመስጠት ውጪ ምናልባት ህሊና (አዕምሮ) እና ሃይማኖተ ቢስነትን ሊመርጡ ካልሆነ በቀር ማውገዝ በማይመቻቸው ማስረጃ ነው የሞገታቸው።" ተፍሲር ኢብኑ ሰዕዲይ: 816

## 7- በፍጠረተ አለሙ ያለውን ሁሉ የምናየውንም የማናየውንም ፈጣሪ አላህ ነው። ከእርሱ ውጪ ያለው ሁሉ ከፍጥረታቱ መካከል የሆነ ፍጡር ብቻ ነው። አላህ ሰማያትንና ምድርንም በሰባት ቀናት ፈጠረ።

በፍጠረተ አለሙ ያለው የምናየውንም የማናየውም ሁሉ ፈጣሪ አላህ ነው። ከእርሱም ውጭ ያለው ከፍጥረታቱ መካከል የሆነ ፍጡር ብቻ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ مَن رَّبُّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ قُلِ اللَّهُ ۚ قُلْ أَفَاتَّخَذْتُم مِّن دُونِهِ أَوْلِيَاءَ لَا يَمْلِكُونَ لِأَنفُسِهِمْ نَفْعًا وَلَا ضَرًّا ۚ قُلْ هَلْ يَسْتَوِي الْأَعْمَىٰ وَالْبَصِيرُ أَمْ هَلْ تَسْتَوِي الظُّلُمَاتُ وَالنُّورُ ۗ أَمْ جَعَلُوا لِلَّهِ شُرَكَاءَ خَلَقُوا كَخَلْقِهِ فَتَشَابَهَ الْخَلْقُ عَلَيْهِمْ ۚ قُلِ اللَّهُ خَالِقُ كُلِّ شَيْءٍ وَهُوَ الْوَاحِدُ الْقَهَّارُ }

{«የሰማያትና የምድር ጌታ ማን ነው» በላቸው። «አላህ ነው» በል። «ለነፍሶቻቸው ጥቅምንም ጉዳትንም የማይችሉትን ረዳቶች ከርሱ ሌላ ያዛችሁን» በላቸው። «ዕውርና የሚያይ ይስተካከላሉን ወይስ ጨለማዎችና ብርሃን ይስተካከላሉን ወይስ ለአላህ እንደርሱ አፈጣጠር የፈጠሩን ተጋሪዎች አደረጉለትና ፍጥረቱ በእነሱ ላይ ተመሳሰለባቸውን» በል፤ «አላህ ሁለመናውን ፈጣሪ ነው። እርሱም አንዱ አሸናፊው ነው» በል።} [ረዕድ: 16] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَيَخْلُقُ مَا لَا تَعْلَمُونَ}

{የማታውቁትንም ድንቅ ነገር ይፈጥራል።} [አን-ነሕል 8]

ሰማያትንና ምድርንም በሰባት ቀናት ፈጠረ። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ اسْتَوَىٰ عَلَى الْعَرْشِ ۚ يَعْلَمُ مَا يَلِجُ فِي الْأَرْضِ وَمَا يَخْرُجُ مِنْهَا وَمَا يَنزِلُ مِنَ السَّمَاءِ وَمَا يَعْرُجُ فِيهَا ۖ وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ ۚ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ }

{እርሱ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ፤ ከዚያም በዙፋኑ ላይ (ለሱ ክብር በሚስማማ መልኩ የተደላደለ ነው። በምድር ውስጥ የሚገባውን፣ ከእርሷም የሚወጣውን፣ ከሰማይም የሚወርደውን

በእርሷም ውስጥ የሚያርገውን ያውቃል። እርሱም የትም ብትኾኑ ከእናንተ ጋር ነው። አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው።} [አል-ሓዲድ 4] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدْ خَلَقْنَا السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ وَمَا مَسَّنَا مِن لُّغُوبٍ}

{ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ በእርግጥ ፈጠርን። ድካምም ምንም አልነካንም።} [ቃፍ 38]

## 8- ጥራት የተገባው አላህ በንግስናውም ሆነ በመፍጠሩ፤ በማስተናበሩም ሆነ በአምልኮው ተጋሪ የለውም።

ጥራት የተገባውና ከፍ ያለው አላህ የንጉሶች ሁሉ ንጉስ እርሱ ነው፤ በመፍጠር፣ በባለቤትነትም ይሁን በአስተናባሪነቱ ምንም አጋር የለውም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ أَرَأَيْتُم مَّا تَدْعُونَ مِن دُونِ اللَّهِ أَرُونِي مَاذَا خَلَقُوا مِنَ الْأَرْضِ أَمْ لَهُمْ شِرْكٌ فِي السَّمَاوَاتِ ۖ ائْتُونِي بِكِتَابٍ مِّن قَبْلِ هَٰذَا أَوْ أَثَارَةٍ مِّنْ عِلْمٍ إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ}

{«ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸውን አያችሁን? ከምድር ምንን እንደ ፈጠሩ አሳዩኝ። ወይም በሰማያት ለእነርሱ (ከአላህ ጋር) መጋራት አላቸውን? (ያማልዱናል በማለታችሁ) እውነተኞች እንደ ኾናችሁ ከዚህ (ቁርኣን) በፊት የኾነን መጽሐፍ ወይም ከዕውቀት የኾነ ቅርስን አምጡልኝ»

በላቸው።} [አል-አሕቃፍ 4] ሸይኽ ሰዕዲይ አላህ ይዘንላቸው እንዲህ ይላሉ፡- "ማለትም: ለእነዚያ ከአላህ ጋር ጣዖታትን ለሚያጋሩ የሚያጋሯቸው ጣኦታት ጥቅምም ይሁን ጉዳትን፣ ሞትም ይሁን ሕይወትን፣ ትንሣኤንም (መቀስቀስን) ምንም አይነት ነገርን እንደማይቆጣጠሩላቸው (ደካሞች መሆናቸውን) ንገራቸው። ጣኦቶቻቸው ከአምልኮ አንዳች ድርሻ እንደማይገባቸው በማብራራትም እንዲህ በላቸው፡- 'ከምድር ምንን እንደ ፈጠሩ አሳዩኝ። ወይም በሰማያት ለእነርሱ (ከአላህ ጋር) መጋራት አላቸውን?' ከሰማያትና ከምድር አካላት የሆነ ነገርን ፈጥረዋል? ተራሮችን ፈጠሩ? ወንዞችን አፈሰሱ? ለእንስሳ ህይወትን ሰጡ? ዛፎችን አብቅለዋልን? ወይስ እነዚህ ሲፈጠሩ አስተዋፆ ነበራቸው? ከነዚህም ውስጥ አንዳች ነገርን እንዳላደረጉ ሌላው ቀርቶ ራሳቸው እንኳ የማያስተባብሉት ነገር ነው። ይህ ደግሞ ማንም ከአላህ ውጭ የሚመለክ አምልኮቱ ውዳቅ ለመሆኑ ግልፅ የሆነ ቁርጥ ያለ አእምሯዊ ማስረጃ ነው።"

ከዚያም ሰማያዊ ማስረጃ አለመኖሩንም እንዲህ በማለት ገለፀ፤ ወደ ሽርክ ጥሪ የሚያደርግ {«እውነተኞች እንደ ሆናችሁ ከዚህ (ከቁርኣን) በፊት የሆነን መጽሓፍ ወይም ከዕውቀት የሆነ ቅርስን አምጡልኝ» በላቸው።} በዚሁ ጉዳይ የሚያዝ ከመልዕክተኞች የተወረሰ ነገር ካለ አምጡልኝ። እንደሚታወቀው ከየትኛውም የአላህ መልዕክተኛ ለዚህ ማስረጃ የሚሆንን ነገር ማምጣት አይችሉም። ይልቁንም ሁሉም መልእክተኞች ጥርት ባለ መልኩ ወደ ጌታቸው

አንድነት እንዳዘዙና ሽርክን እንደከለከሉ እርግጠኞች ነን፤ ከመልዕክተኞች የሚወረሰው ትልቁ እውቀትም ይኸው ነው። ተፍሲር ኢብኑ ሰዕዲይ: 779

ጥራት የተገባውና የላቀው አላህ እርሱ ነው ንጉሰ ነገስት፣ በንግስናውም አጋር የለውም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ قُلِ اللَّهُمَّ مَالِكَ الْمُلْكِ تُؤْتِي الْمُلْكَ مَن تَشَاءُ وَتَنزِعُ الْمُلْكَ مِمَّن تَشَاءُ وَتُعِزُّ مَن تَشَاءُ وَتُذِلُّ مَن تَشَاءُ ۖ بِيَدِكَ الْخَيْرُ ۖ إِنَّكَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ }

{(ሙሐመድ ሆይ!) በል፡- «የንግስና ባለቤት የኾንክ አላህ ሆይ! ለምትሻው ሰው ንግሥናን ትሰጣለህ። ከምትሻውም ሰው ንግሥናን ትገፍፋለህ። የምትሻውንም ሰው ታልቃለህ። የምትሻውንም ሰው ታዋርዳለህ። መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ (በችሎታህ) ነው፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና።»} [አሊ-ዒምራን 26] የላቀው አላህ ሙሉ ሥልጣን የእርሱ መሆኑ በእለተ ትንሳኤ ግልጽ እንደሚሆን እንዲህ ብሎ ገልፆልናል፡-

{ يَوْمَ هُم بَارِزُونَ ۖ لَا يَخْفَىٰ عَلَى اللَّهِ مِنْهُمْ شَيْءٌ ۚ لِّمَنِ الْمُلْكُ الْيَوْمَ ۖ لِلَّهِ الْوَاحِدِ الْقَهَّارِ }

{እነርሱ (ከመቃብር) በሚወጡበት ቀን በአላህ ላይ ከእነርሱ ምንም ነገር አይደበቅም። «ንግሥናው ዛሬ ለማን ነው?» (ይባላል፤)። «ለአሸናፊው ለአንዱ አላህ ብቻ ነው» (ይባላል)።} [ጋፊር: 16]

ጥራት የተገባው አላህ በንግስናውም ሆነ በመፍጠሩ፤ በማስተናበሩም ሆነ በአምልኮው ተጋሪ የለውም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَقُلِ الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي لَمْ يَتَّخِذْ وَلَدًا وَلَمْ يَكُن لَّهُ شَرِيكٌ فِي الْمُلْكِ وَلَمْ يَكُن لَّهُ وَلِيٌّ مِّنَ الذُّلِّ ۖ وَكَبِّرْهُ تَكْبِيرًا }

{«ምስጋና ለአላህ ለዚያ ልጅን ላልያዘው፣ ለእርሱም በንግሥናው ተጋሪ ለሌለው፣ ለእርሱም ከውርደት ረዳት ለሌለው ይገባው በልም። ማክበርንም አክብረው።»} [ኢስራእ: 111] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ الَّذِي لَهُ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَلَمْ يَتَّخِذْ وَلَدًا وَلَمْ يَكُن لَّهُ شَرِيكٌ فِي الْمُلْكِ وَخَلَقَ كُلَّ شَيْءٍ فَقَدَّرَهُ تَقْدِيرًا }

{(እርሱ) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና የእርሱ ብቻ የኾነ፣ ልጅንም ያልያዘ፣ በንግሥናውም ተጋሪ የሌለው፣ ነገሩንም ሁለ የፈጠረና በትክክልም ያዘጋጀው ነው።} [አል-ፉርቃን: 2] እርሱ የሁሉም ነገር ገዥ ነው፣ ጥራት ይገባውና ከእርሱው ውጭ ያለ ሁሉ ደግሞ የእርሱ ተገዥ ነው። ፈጣሪ እርሱ ነው፤ ከእርሱ ውጭ ያለው ሁሉ ደሞ የእርሱ ፍጡር ነው። ጉዳይንም ሁሉ የሚያስተናብረው እርሱ ነው። ስለዚህ እንዲህ ያለው ጌታ ነው ሊመለክ የሚገባው፤ ከእንዲህ ካለው ውጭ ማምለክም ህሊናቢስነትና ዲንንም ዱንያንም የሚያበላሽ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَقَالُوا كُونُوا هُودًا أَوْ نَصَارَىٰ تَهْتَدُوا ۗ قُلْ بَلْ مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا ۖ وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ }

«አይሁድን ወይም ክርስቲያኖችን ኹኑ፤ (ቅኑን መንገድ) ትመራላችሁና» አሉም። «አይደለም የኢብራሂምን ሃይማኖት ቀጥተኛ ሲኾን እንከተላለን፤ ከአጋሪዎችም አልነበረም» በላቸው። [አል-በቀራህ: 135] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَمَنْ أَحْسَنُ دِينًا مِّمَّنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ وَاتَّبَعَ مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا ۗ وَاتَّخَذَ اللَّهُ إِبْرَاهِيمَ خَلِيلًا}

{እርሱ መልካም ሠሪ ኾኖ ፊቱን ለአላህ ከሰጠና የኢብራሂምንም መንገድ ቀጥተኛ ሲኾን ከተከተለ ሰው ይበልጥ ሃይማኖቱ ያማረ ማን ነው አላህም ኢብራሂምን ፍጹም ወዳጅ አድርጎ ያዘው።} [ኒሳእ: 125] ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ ከቀናው የነብዩሏህ ኢብራሂም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ጎዳና ውጭ ሌላ ፈለግን የፈለገ ራሱን እንዳቄለ (እንዳሞኘ) ገለፀ፤ እንዲህም አለ፦ {ከኢብራሂምም ሕግጋት ነፍሱን ያቄለ ሰው ካልኾነ በስተቀር የሚያፈገፍግ ማነው? (የለም)፤ በቅርቢቱም ዓለም በእርግጥ መረጥነው። በመጨረሻይቱም ዓለም እርሱ ከመልካሞቹ ነው።} [አል-በቀራ: 130]

## 9- ጥራት የተገባው አላህ አልወለደም አልተወለደም ብጤም ሆነ አምሳያም የለውም።

ጥራት የተገባው አላህ አልወለደምም አልተወለደምም ብጤም ሆነ አምሳያም የለውም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ (1) اللَّهُ الصَّمَدُ (2) لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ (3) وَلَمْ يَكُن لَّهُ كُفُوًا أَحَدٌ (4)}

{በል «እርሱ አላህ አንድ ነው።}

{«አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው።}

{«አልወለደም፤ አልተወለደምም።}

{«ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም።»} [አል-ኢኽላስ: 1-4] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{رَّبُّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا فَاعْبُدْهُ وَاصْطَبِرْ لِعِبَادَتِهِ ۚ هَلْ تَعْلَمُ لَهُ سَمِيًّا}

{(እርሱ) የሰማያትና የምድር በሁለቱም መካከል ላለው ሁሉ ጌታ ነውና ተገዛው። እርሱን በመገዛትም ላይ ታገስ። ለእርሱ ሞክሼን ታውቃለህን?} [መርየም: 65] የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{فَاطِرُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا وَمِنَ الْأَنْعَامِ أَزْوَاجًا ۖ يَذْرَؤُكُمْ فِيهِ ۚ لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ ۖ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ}

{ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ነው። ከነፍሶቻችሁ ሴቶችን ከቤት እንስሳዎችም ዓይነቶችን (ወንዶችና ሴቶችን) ለእናንተ አደረገላችሁ። በእርሱ ያበዛችኋል። የሚመስለው ምንም ነገር የለም። እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።} [አሽ ሹራ፡ 11]

## 10- ጥራት የተገባውና ከፍ ያለው አላህ በአንዳች ፍጡራኑ ላይ የሚሰርፅም የሚዋሃድም አይደለም።

ጥራት የተገባውና የላቀው አላህ በአንዳች ፍጡራኑ ላይ የሚሰርፅም የሚዋሃድም አይደለም። ይህም አላህ የሁሉም ፈጣሪ እና ከርሱ ውጭ ያለው ሌላው ሁሉ ደግሞ ፍጡር በመሆኑ፤ እርሱ ዘልአለማዊ ሌላው ሁሉ ደግሞ በመጨረሻው ጠፊ በመሆኑ፤ የሁሉም ነገር ገዥው እርሱ ሌላው ሁሉ ደግሞ የእርሱ ተገዥ በመሆኑ፤ ጥራት ይገባውና አላህም በፍጡራኖቹ አይሰርፅም የትኛውም ፍጡርም በእርሱ የማይሰርፅበት በመሆኑ ነው። ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ ከሁሉም የበላይ የሆነ ታላቅ ነው። ከፍ ያለው አላህ በዒሳ ላይ ሰርጿል የሚሉትን ሲቃወማቸው እንዲህ ብሏል፡-

{لَّقَدْ كَفَرَ الَّذِينَ قَالُوا إِنَّ اللَّهَ هُوَ الْمَسِيحُ ابْنُ مَرْيَمَ ۚ قُلْ فَمَن يَمْلِكُ مِنَ اللَّهِ شَيْئًا إِنْ أَرَادَ أَن يُهْلِكَ الْمَسِيحَ ابْنَ مَرْيَمَ وَأُمَّهُ وَمَن فِي الْأَرْضِ جَمِيعًا ۗ وَلِلَّهِ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا ۚ يَخْلُقُ مَا يَشَاءُ ۚ وَاللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ}

{እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ። የመርየምን ልጅ አልመሲሕን እናቱንም በምድር ያለንም ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ ከአላህ ማዳንን የሚችል ማነው በላቸው። የሰማያትና የምድር የመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው። የሚሻውን

ይፈጥራል። አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።} [አል-ማኢዳህ: 17] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلِلَّهِ الْمَشْرِقُ وَالْمَغْرِبُ ۚ فَأَيْنَمَا تُوَلُّوا فَثَمَّ وَجْهُ اللَّهِ ۚ إِنَّ اللَّهَ وَاسِعٌ عَلِيمٌ (115) وَقَالُوا اتَّخَذَ اللَّهُ وَلَدًا ۗ سُبْحَانَهُ ۖ بَل لَّهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۖ كُلٌّ لَّهُ قَانِتُونَ (116) بَدِيعُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۖ وَإِذَا قَضَىٰ أَمْرًا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُ كُن فَيَكُونُ (117) }

{ምሥራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው (ፊቶቻችሁን) ወደ የትም ብታዞሩ የአላህ ፊት እዚያ ነው። አላህ ችሮታው ሰፊ ዐዋቂ ነውና።}

{አላህም ልጅ አለው አሉ። (ከሚሉት) ጥራት ተገባው። አይደለም በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነው። ሁሉም ለርሱ ታዛዦች ናቸው።}

{ሰማያትንና ምድርን ያለብጤ ፈጣሪ ነው፤ ነገርንም (ማስገኘት) በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው፡- «ኹን ነው፤» ወዲያውም ይኾናል።} [አል-በቀራህ: 115-117] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَقَالُوا اتَّخَذَ الرَّحْمَٰنُ وَلَدًا (88) لَّقَدْ جِئْتُمْ شَيْئًا إِدًّا (89) تَكَادُ السَّمَاوَاتُ يَتَفَطَّرْنَ مِنْهُ وَتَنشَقُّ الْأَرْضُ وَتَخِرُّ الْجِبَالُ هَدًّا (90) أَن دَعَوْا لِلرَّحْمَٰنِ وَلَدًا (91) وَمَا يَنبَغِي لِلرَّحْمَٰنِ أَن يَتَّخِذَ وَلَدًا (92) إِن كُلُّ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ إِلَّا آتِي الرَّحْمَٰنِ عَبْدًا (93) لَّقَدْ أَحْصَاهُمْ وَعَدَّهُمْ عَدًّا (94) وَكُلُّهُمْ آتِيهِ يَوْمَ الْقِيَامَةِ فَرْدًا (95) }

{«አልረሕማንም ልጅን ያዘ (ወለደ)» አሉ።}

{ከባድ መጥፎን ነገር በእርግጥ አመጣችሁ።}

{ከእርሱ (ከንግግራቸው) ሰማያት ሊቀደዱ፣ ምድርም ልትሰነጠቅ፣ ጋራዎችም ተንደው ሊወድቁ ይቃረባሉ።}

{ለአልረሕማን ልጅ አልለው ስለአሉ።}

{ለአልረሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም።}

{በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአልራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም።}

{በእርግጥ (በዕውቀቱ) ከቧቸዋል። መቁጠርንም ቆጥሯቸዋል።}

{ሁሉም በትንሣኤ ቀን ለየብቻ ኾነው ወደርሱ መጪዎች ናቸው።} [መርየም 88-95] አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ كُرۡسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۖ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفۡظُهُمَاۚ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ}

{አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ራሱን ቻይ ነው። ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም። በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው። ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል። በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)። መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ። ጥበቃቸውም አያቅተውም።

እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው።} [አል-በቀራህ: 255] የእርሱ ማንነት ይህ ሆኖ የፍጡራኑ ማንነት ሌላ እንዴት ነው ታድያ አንዱ በሌላው የሚሰርፀው?! እንዴትስ ልጅ አድርጎ ይይዘዋል?! እንዴትስ ከእርሱ ጋ ባላንጣ ያደርገዋል?!

## 11- ጥራት የተገባውና ከፍ ያለው አላህ ርህሩህና አዛኝ በመሆኑ መልዕክተኞችን ላከ መጽሐፍቶችንም አወረደ።

አላህም እጅግ በጣም ርኅሩኅና አዛኝ በመሆኑ ባሮቹን ከክህደትና ከሽርክ ጨለማ አውጥቶ ወደ ተውሒድና ቀና መመርያ ብርሃን ለማስገባት መልእክተኞችንም ላከ ኪታቦችንም አወረደ። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{هُوَ الَّذِي يُنَزِّلُ عَلَىٰ عَبْدِهِ آيَاتٍ بَيِّنَاتٍ لِّيُخْرِجَكُم مِّنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ ۚ وَإِنَّ اللَّهَ بِكُمْ لَرَءُوفٌ رَّحِيمٌ }

{እርሱ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ሊያወጣችሁ ያ ግልጾች የኾኑን አንቀጾች በበሪያው ላይ የሚያወርድ ነው። አላህም ለእናንተ በእርግጥ ርኅሩህ አዛኝ ነው።} [አል-ሓዲድ: 9]

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ }

{(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።} [አል-አንቢያእ: 107] ነብዩንም መሃሪውና እጅግ በጣም አዛኙ እርሱ መሆኑን ለአላህ ባርያዎች እንዲያሳውቁ አዘዛቸው፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ نَبِّئْ عِبَادِي أَنِّي أَنَا الْغَفُورُ الرَّحِيمُ}

{ባሮቼን እኔ መሓሪው አዛኙ እኔው ብቻ መሆኔን ንገራቸው።} [አል-ሒጅር: 49] ከርህሩህነቱ እና አዛኝነቱ አንፃር በባርያዎቹ ላይ ክፋትንም ይመክትላቸዋል መልካምንም ያስገኝላቸዋል፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَإِن يَمْسَسْكَ اللَّهُ بِضُرٍّ فَلَا كَاشِفَ لَهُ إِلَّا هُوَ ۖ وَإِن يُرِدْكَ بِخَيْرٍ فَلَا رَادَّ لِفَضْلِهِ ۚ يُصِيبُ بِهِ مَن يَشَاءُ مِنْ عِبَادِهِ ۚ وَهُوَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ}

{አላህም ጉዳትን ቢያደርስብህ ከእርሱ ሌላ ለእርሱ ገላጭ የለውም። በጎንም ነገር ቢሻልህ ለችሮታው መላሽ የለም። ከባሮቹ የሚሻውን በእርሱ ይለይበታል። እርሱም መሓሪ አዛኝ ነው።} [ዩኑስ: 107]

## 12- ጌታችን አላህ እጅግ በጣም አዛኙ በእለተ ትንሳኤ ፍጥረታትን የሚተሳሰብ ብቸኛው ጌታ ነው። የዚያኔ ሁሉንም ባጠቃላይ ከቀብራቸው እንዲቀሰቀሱ አድርጎ እያንዳንዱን ግለሰብ ከሰራው መልካምና ክፉ ስራው አንፃር ይመነዳዋል። አማኝ ሆኖ መልካምን የሰራ ዘውታሪ ፀጋ አለለት፤ የካደና መጥፎንም የሰራ ደግሞ በእለተ ትንሳኤ ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል።

ጌታችን አላህ እጅግ በጣም አዛኙ በእለተ ትንሳኤ ፍጥረታትን የሚተሳሰብ ብቸኛው ጌታ ነው። የዚያኔ ሁሉንም ባጠቃላይ ከቀብራቸው እንዲቀሰቀሱ አድርጎ

እያንዳንዱን ግለሰብ ከሰራው መልካምና ክፉ ስራው አንፃር ይመነዳዋል። አማኝ ሆኖ መልካምን የሰራ ዘውታሪ ፀጋ አለለት፤ የካደና መጥፎንም የሰራ ደግሞ በእለተ ትንሳኤ ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል። ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ ለፍጡራኑ ካለው ፍትሃዊነት፣ የላቀ ጥበብና እዝነትም አንፃር ይህንን ዓለም የሥራ ሀገር በማድረግ ሁለተኛውን ዓለም ደግሞ የምንዳ፣ የመተሳሰቢያና የሽልማት አገር አድርጎታል። ስለዚህም በጎ አድራጊው የበጎ አድራጎቱን ሽልማት እንዲያገኝ፤ ክፉ በዳይና ድንበር አላፊም የድንበር አላፊነቱንና የበደሉን ቅጣት እንዲያገኝ ይህን አደረገ። ይህንንም ከሞት የመቀስቀስ ጉዳይ የአንዳንዶች ነፍስ የማትቀበለው ስለሆነ ከሞት መነሳት የማያወላዳ እውነታ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎችንም አደረገ። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَمِنْ آيَاتِهِ أَنَّكَ تَرَى الْأَرْضَ خَاشِعَةً فَإِذَا أَنزَلْنَا عَلَيْهَا الْمَاءَ اهْتَزَّتْ وَرَبَتْ ۚ إِنَّ الَّذِي أَحْيَاهَا لَمُحْيِي الْمَوْتَىٰ ۚ إِنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ}

{አንተ ምድርን ደረቅ ኾና ማየትህም ከምልክቶቹ ነው። በእርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ (በቡቃያዎችዋ) ትላወሳለች። ትነፋለችም። ያ ሕያው ያደረጋት ጌታ በእርግጥ ሙታንን ሕያው አድራጊ ነው። እነርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።} [ፉሲለት: 39] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِن كُنتُمْ فِي رَيْبٍ مِّنَ الْبَعْثِ فَإِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ مِنْ عَلَقَةٍ ثُمَّ مِن مُّضْغَةٍ مُّخَلَّقَةٍ وَغَيْرِ مُخَلَّقَةٍ لِّنُبَيِّنَ لَكُمْ ۚ وَنُقِرُّ فِي الْأَرْحَامِ مَا نَشَاءُ إِلَىٰ أَجَلٍ مُّسَمًّى ثُمَّ نُخْرِجُكُمْ طِفْلًا ثُمَّ لِتَبْلُغُوا أَشُدَّكُمْ ۖ وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ وَمِنكُم مَّن يُرَدُّ إِلَىٰ أَرْذَلِ الْعُمُرِ لِكَيْلَا يَعْلَمَ مِن بَعْدِ عِلْمٍ

شَيْئًا ۚ وَتَرَى الْأَرْضَ هَامِدَةً فَإِذَا أَنزَلْنَا عَلَيْهَا الْمَاءَ اهْتَزَّتْ وَرَبَتْ وَأَنبَتَتْ مِن كُلِّ زَوْجٍ بَهِيجٍ}

{እናንተ ሰዎች ሆይ! ከመቀስቀስ በመጠራጠር ውስጥ እንደ ሆናችሁ (አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ)። እኛም ከዐፈር ፈጠርናችሁ፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ ከዚያም ከቁራጭ ሥጋ፣ ፍጥረትዋ ሙሉ ከሆነችና ሙሉ ካልሆነች (ችሎታችንን) ለናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ። የምንሻውንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በማሕፀን ውስጥ እናረጋዋለን። ከዚያም ሕፃን ሆናችሁ እናወጣችኋለን። ከዚያም ሙሉ ጥንካሬያችሁን ትደርሱ ዘንድ (እናሳድጋችኋለን)። ከእናንተም የሚሞት ሰው አልለ። ከእናንተም ከዕውቀት በኋላ ምንንም እንዳያውቅ ወደ ወራዳ ዕድሜ የሚመለስ ሰው አልለ። ምድርንም ደረቅ ሆና ታያታለህ። በእርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ ትላወሳለች። ትነፋፋለችም። ውበት ካለው ጎሳ ሁሉ ታበቅላለችም።} [አል-ሐጅ: 5] አላህ በዚህ አንቀፅ ውስጥ በትንሣኤ ቀን መቀስቀስን የሚያመለክቱ ሦስት አዕምሯዊ ማስረጃዎችን ጠቅሷል፤ እነርሱም፡-

1- የሰውን ልጅ አላህ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈጥረው ከአፈር ነው የፈጠረው፤ ታድያ ይህንን ከአፈር የፈጠረውን መልሶ አፈር ሲሆን አላህ በሻ ጊዜ ወደ ሕይወት ሊመልሰው ቻይ ነው።

2- ከወንዱ የዘር ፈሳሽ ሰው አድርጎ የፈጠረ ጌታ ከሞት በኋላም ሰው አድርጎ ወደ ሕይወት ሊመልሰው ቻይ ነው።

3- ምድር ከሞተች በኋላ በዝናብ ህያው ያደረገ የሰው ልጅንም ህያው ሊያደርገው ቻይ ነው። ይህች አንቀፅ ቁርአን ተአምራዊ ለመሆኑ እጅግ ግልፅ የሆነ ማስረጃ አቅፈለች። ምክንያቱም ይህች አንቀፅ ረዥም ካለመሆኗም ጋ ግን እጅግ በጣም አንገብጋቢ ለሆነ ጥያቄ ሶስት ፍንትው ያሉ አእምሯዊ ማስረጃዎች እንዴት አካትታለች።

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَوْمَ نَطْوِي السَّمَاءَ كَطَيِّ السِّجِلِّ لِلْكُتُبِ ۚ كَمَا بَدَأْنَا أَوَّلَ خَلْقٍ نُّعِيدُهُ ۚ وَعْدًا عَلَيْنَا ۚ إِنَّا كُنَّا فَاعِلِينَ}

{ለመጽሐፎች የሆኑ ገጾች እንደሚጠቀለሉ ሰማይን የምንጠቀልልበትን ቀን (አስታውስ)። የመጀመሪያን ፍጥረት እንደ ጀመርን እንመልሰዋለን። (መፈጸሙ) በእኛ ላይ የሆነን ቀጠሮ ቀጠርን። እኛ (የቀጠርነውን) ሠሪዎች ነን።} [አል-አንቢያእ: 104] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَضَرَبَ لَنَا مَثَلًا وَنَسِيَ خَلْقَهُ ۖ قَالَ مَن يُحْيِي الْعِظَامَ وَهِيَ رَمِيمٌ (78) قُلْ يُحْيِيهَا الَّذِي أَنشَأَهَا أَوَّلَ مَرَّةٍ ۖ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيمٌ}

{ለእኛም ምሳሌን አደረገልን። መፈጠሩንም ረሳ። «አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲኾኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?» አለ።}

{«ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል። እርሱም በፍጡሩ ሁሉ (ኹኔታ) ዐዋቂ ነው» በለው።} [ያሲን: 78] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ أَأَنتُمْ أَشَدُّ خَلْقًا أَمِ السَّمَاءُ ۚ بَنَاهَا (27) رَفَعَ سَمْكَهَا فَسَوَّاهَا (28) وَأَغْطَشَ لَيْلَهَا وَأَخْرَجَ ضُحَاهَا (29) وَالْأَرْضَ بَعْدَ ذَٰلِكَ دَحَاهَا (30) أَخْرَجَ مِنْهَا مَاءَهَا وَمَرْعَاهَا (31) وَالْجِبَالَ أَرْسَاهَا (32) }

{በፈጣጠር እናንተ ይበልጥ የበረታችሁ ናችሁን? ወይንስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት።} (27)

{ከፍታዋን አጓነ፤ አስተካከላትም።} (28)

{ሌሊቷንም አጨለመ። ቀንዋንም ገለጸ።} (29)

{ምድርንም ከዚህ በኋላ ዘረጋት።} (30)

{ውሃዋንና ግጦሿን ከእርሷ አወጣ።} (31)

{ጋራዎችንም አደለደላቸው።} (32) [አን-ናዚዓት: 27-32] በመሆኑም አላህ የሰውን ልጅ መፍጠር ሰማያትንና ምድርን በውስጣቸውም ያለውን ከመፍጠር ይበልጥ የሚከብድ እንዳልሆነ ግልፅ አደረገ። ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ጌታ የሰው ልጅን ድጋሚ መቀስቀሱ ሊሳነው አይችልም።

## 13- ከፍ ያለው አላህ አደምን ከፈጠረ በኋላ ዝርያዎቹ ከእርሱ በኋላ እንዲባዙ አደረገ። የሰው ልጆች ሁሉ አላህን በመፍራታቸው ካልሆነ በቀር በመሰረታዊ ማንነታቸው አንዱ

## ዝርያ ከሌላኛው ዝርያ አንዱ ህዝብ ከሌላኛው ህዝብ በማይበላለጥበት መልኩ እኩል ናቸው።

ከፍ ያለው አላህ አደምን ከፈጠረ በኋላ ዝርያዎቹ ከርሱ በኋላ እንዲባዙ አደረገ። የሰው ልጆች ሁሉ አላህን በመፍራታቸው ካልሆነ በቀር በመሰረታዊ ማንነታቸው አንዱ ዝርያ ከሌላኛው ዝርያ አንዱ ህዝብ ከሌላኛው ህዝብ በማይበላለጥበት መልኩ እኩል ናቸው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا ۚ إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ }

{እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው። አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው።} [አል-ሑጁራት: 13]

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَاللَّهُ خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ جَعَلَكُمْ أَزْوَاجًا ۚ وَمَا تَحْمِلُ مِنْ أُنثَىٰ وَلَا تَضَعُ إِلَّا بِعِلْمِهِ ۚ وَمَا يُعَمَّرُ مِن مُّعَمَّرٍ وَلَا يُنقَصُ مِنْ عُمُرِهِ إِلَّا فِي كِتَابٍ ۚ إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ }

{አላህም ከዐፈር፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ ፈጠራችሁ። ከዚያም ጎሳዎች አደረጋችሁ። ሴትም አታረግዝም አትወልድምም በዕውቀቱ ቢኾን እንጂ። ዕድሜው ከሚረዘምም አንድም አይረዘምም ከዕድሜውም አይጎደልም በመጽሐፉ ውስጥ ያለ ቢኾን

እንጂ። ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።} [ፋጢር: 11] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ الَّذِي خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ مِنْ عَلَقَةٍ ثُمَّ يُخْرِجُكُمْ طِفْلًا ثُمَّ لِتَبْلُغُوا أَشُدَّكُمْ ثُمَّ لِتَكُونُوا شُيُوخًا ۚ وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ مِن قَبْلُ ۖ وَلِتَبْلُغُوا أَجَلًا مُّسَمًّى وَلَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ }

{እርሱ ያ ከዐፈር ከዚያም ከፍትወት ጠብታ ከዚያም ከረጋ ደም የፈጠራችሁ ነው። ከዚያም ሕጻናት አድርጎ ያወጣችኋል። ከዚያም ጥንካሬያችሁን ትደርሱ ዘንድ፤ ከዚያም ሽማግሌዎች ትኾኑ ዘንድ (ያቆያችኋል)። ከእናንተም ውስጥ ከዚህ በፊት የሚሞት አልለ። (ይህንንም ያደረገው ልትኖሩና) የተወሰነ ጊዜንም ልትደርሱ ታውቁም ዘንድ ነው።} [ጋፊር: 67] እናም ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ አዳምን በአፈር (በአጽናፈ ዓለም) እንደ ፈጠረው ሁሉ በአጽናፈ ዓለም ሥርዓት ዒሳ (እየሱስን) እንደፈጠረ በግልጽ ተናግሯል። ከፍ አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ إِنَّ مَثَلَ عِيسَىٰ عِندَ اللَّهِ كَمَثَلِ آدَمَ ۖ خَلَقَهُ مِن تُرَابٍ ثُمَّ قَالَ لَهُ كُن فَيَكُونُ }

{አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው። ከዐፈር ፈጠረው። ከዚያም ለርሱ (ሰው) «ሁን» አለው፤ ሆነም።} [አሊ-ዒምራን: 59] በአንቀጽ ቁጥር (2) ላይ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሰዎች ሁሉ አላህን በመፍራታቸው ካልሆነ በቀር አንዱ ከሌላው በማይበላለጥበት መልኩ እኩል እንደሆኑ መግለፃቸውን ቀደም ብዬ ጠቅሻለሁ።

## 14- ሁሉ ልጅ በተፍጥሯዊው ሃይማኖት (እስልምና) ላይ ሆኖ ነው የሚወለደው።

ሁሉ ልጅ በተፍጥሯዊው ሃይማኖት (እስልምና) ላይ ሆኖ ነው የሚወለደው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا ۚ فِطْرَتَ اللَّهِ الَّتِي فَطَرَ النَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ اللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ }

{ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ። የአላህን ፍጥረት ያቺን አላህ ሰዎችን በእርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዟት)። የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም። ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች አያውቁም።} [አር-ሩም: 30] ሓኒፊያ የምትባለው ቀናዋ መንገድ የአላህ ልዩ ወዳጅ የሆኑት ነብዩሏህ ኢብራሂም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን መንገድ ነች። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ ثُمَّ أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ أَنِ اتَّبِعْ مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا ۖ وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ }

{ከዚያም ወደ አንተ የኢብራሂምን ሃይማኖት ቀጥተኛ ሲሆን ተከተል፤ ከአጋሪዎቹም አልነበረም ማለት አወረድን።} [አን-ነሕል: 123] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«مَا مِنْ مَوْلُودٍ إِلَّا يُولَدُ عَلَى الفِطْرَةِ فَأَبَوَاهُ يُهَوِّدَانِهِ أَوْ يُنَصِّرَانِهِ أَوْ يُمَجِّسَانِهِ كَمَا تُنْتَجُ البَهِيمَةُ بَهِيمَةً جَمْعَاءَ هَلْ تُحِسُّونَ فِيهَا مِنْ جَدْعَاءَ»

"ማንኛውም ልጅ የሚወለደው በተፈጥሯዊው ሃይማኖት (እስልምና) ላይ ሆኖ ነው ወላጆቹ አይሁድ ወይንም ክርስትያን አለዚያም እሳት አምላኪ ያደርጉታል እንጅ። ልክ

በተሟላ ተክለ ሰውነት እንደተወለደች እንስሳ ማለት ነው። በተሟላ ተክለሰውነት በተወለደች እንስሳ ነውር ይገኝባታልን?!" ከዚያም አላህ መልካም ስራውን ይውደድላትና አቡ ሁረይራ እንዲህ ይሉ ነበር፦

{فِطْرَةَ اللَّهِ الَّتِي فَطَرَ النَّاسَ عَلَيْهَالَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ اللَّهِ ذَلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ وَلَكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ }

{ወደ እውነት ተዘንባይ ሆነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ። የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በእርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዟት)። የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም። ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም።} [ሩም፡ 30] ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 4775 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«أَلَا إِنَّ رَبِّي أَمَرَنِي أَنْ أُعَلِّمَكُمْ مَا جَهِلْتُمْ مِمَّا عَلَّمَنِي يَوْمِي هَذَا كُلُّ مَالٍ نَحَلْتُهُ عَبْدًا حَلَالٌ وَإِنِّي خَلَقْتُ عِبَادِي حُنَفَاءَ كُلَّهُمْ وَإِنَّهُمْ أَتَتْهُمُ الشَّيَاطِينُ فَاجْتَالَتْهُمْ عَنْ دِينِهِمْ وَحَرَّمَتْ عَلَيْهِمْ مَا أَحْلَلْتُ لَهُمْ وَأَمَرَتْهُمْ أَنْ يُشْرِكُوا بِي مَا لَمْ أُنْزِلْ بِهِ سُلْطَانًا »

"በእውነቱ ጌታዬ በዚህ ቀን ያስተማረኝን እናንተ ግን የማታውቁትን እንዳስተምራችሁ አዘኛል። እንዲህ ብሏልም "ለባሪያየ የለገስኩት (ጠቃሚው) ሁሉ ሓላሉ ነው፤ ሸይጧን መጣባቸውና ከዲናቸው እንዲያፈነግጡ፣ እኔ የፈቀድኩላቸውን ከለከላቸው፣ እኔ ማስረጃ ላላወረድኩበትም ሽርክ ዳረጋቸው እንጅ እኔ ባርያዎቼን የፈጠርኳቸው በቀና ጎዳና ላይ አድርጌ ነው።" ሙስሊም ዘግበውታል 2865

## 15- ማንኛውም ሰው ሲወለድ ኋጢአተኛ ሆኖ ወይንም የሌላን ኋጢአት ወርሶ አይወለድም።

ማንኛውም ሰው ሲወለድ ኋጢአተኛ ሆኖ ወይንም የሌላን ኋጢአት ወርሶ አይወለድም። አላህ ስለ አደምም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የነገረን መለኮታዊውን ትእዛዝ ሲጥሱ እርሳቸውና ሚስታቸው ሐዋ (ሔዋን) ከዛፉ ሲበሉ በንስሃ ተፀፅተው ወደ አላህ መመለሳቸውንና መሀርታንም መጠየቃቸውን እንዲሁም አላህ መሀርታን የሚያስገኝላቸውን መልካም ቃላት አስተምሯቸው መሀርታንም እንደለገሳቸው ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَقُلْنَا يَا آدَمُ اسْكُنْ أَنتَ وَزَوْجُكَ الْجَنَّةَ وَكُلَا مِنْهَا رَغَدًا حَيْثُ شِئْتُمَا وَلَا تَقْرَبَا هَٰذِهِ الشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ الظَّالِمِينَ (35) فَأَزَلَّهُمَا الشَّيْطَانُ عَنْهَا فَأَخْرَجَهُمَا مِمَّا كَانَا فِيهِ ۖ وَقُلْنَا اهْبِطُوا بَعْضُكُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ ۖ وَلَكُمْ فِي الْأَرْضِ مُسْتَقَرٌّ وَمَتَاعٌ إِلَىٰ حِينٍ (36) فَتَلَقَّىٰ آدَمُ مِن رَّبِّهِ كَلِمَاتٍ فَتَابَ عَلَيْهِ ۚ إِنَّهُ هُوَ التَّوَّابُ الرَّحِيمُ (37) قُلْنَا اهْبِطُوا مِنْهَا جَمِيعًا ۖ فَإِمَّا يَأْتِيَنَّكُم مِّنِّي هُدًى فَمَن تَبِعَ هُدَايَ فَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ (38)}

{«አደም ሆይ! አንተ ከነሚስትህ በገነት ተቀመጥ፤ ከርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ፤ ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ ከበደለኞች ትኾናላችሁና» አልነም።}

{ከርሷም ሰይጣን አዳለጣቸው በውስጡም ከነበሩበት (ድሎት) አወጣቸው። «ከፊላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲኾን

ውረዱ፤ ለናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ (ሞታችሁ) ድረስ መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ» አልናቸው።}

{አደምም ከጌታው ቃላትን ተቀበለ። በርሱ ላይም (ጌታው ጸጸትን በመቀበል) ተመለሰለት፤ እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና።}

{«ሁላችሁም ኾናችሁ ከርሷ ውረዱ። ከኔም የኾነ መመሪያ ቢመጣላችሁ ወዲያውኑ መመሪያዬን የተከተለ ሰው በነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም» አልናቸው።} [አል-በቀራህ: 35-38] አላህ ለአደም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በንስሀቸው አማካኝነት መሀርታን እስከለገቻው ድረስ የኃጢአት ተሸካሚ የሚሆኑበት ምክንያት አይኖርም፤ ዝርያቸውም ቢሆኑ በተውባ የተገላገለውን ኋጢአት እነርሱ ወራሾቹ ሊሆኑ አይችሉም። በመሰረቱ ማንኛውም ግለሰብ የሌላውን ኋጢአት ተሸካሚ አይደለም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلَا تَكْسِبُ كُلُّ نَفْسٍ إِلَّا عَلَيْهَا ۚ وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزْرَ أُخْرَىٰ ۚ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُم مَّرْجِعُكُمْ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ }

{ነፍስም ሁሉ በራሷ ላይ እንጅ (ክፋን) አትሠራም። ተሸካሚም (ነፍስ) የሌላይቱን ሸክም (ኃጢአት) አትሸከምም። ከዚያም መመለሻችሁ ወደ ጌታችሁ ነው። ወዲያውም በእርሱ ትለያዩበት የነበራችሁትን ሁሉ ይነገራችኋል።»} [አል-አንዓም 164]

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{مَّنِ اهْتَدَىٰ فَإِنَّمَا يَهْتَدِي لِنَفْسِهِ ۖ وَمَن ضَلَّ فَإِنَّمَا يَضِلُّ عَلَيْهَا ۚ وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزْرَ أُخْرَىٰ ۗ وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبْعَثَ رَسُولًا }

{የተመራ ሰው የሚመራው ለራሱ ብቻ ነው። የተሳሳተም ሰው የሚሳሳተው (ጉዳቱ) በእርሷ ላይ ነው። ተሸካሚም (ነፍስ) የሌላይቱን ኃጢኣት አትሸከምም። መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም።} [አል-ኢስራእ 15] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزْرَ أُخْرَىٰ ۚ وَإِن تَدْعُ مُثْقَلَةٌ إِلَىٰ حِمْلِهَا لَا يُحْمَلْ مِنْهُ شَيْءٌ وَلَوْ كَانَ ذَا قُرْبَىٰ ۗ إِنَّمَا تُنذِرُ الَّذِينَ يَخْشَوْنَ رَبَّهُم بِالْغَيْبِ وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ ۚ وَمَن تَزَكَّىٰ فَإِنَّمَا يَتَزَكَّىٰ لِنَفْسِهِ ۚ وَإِلَى اللَّهِ الْمَصِيرُ }

{ኀጢአትን ተሸካሚም (ነፍስ) የሌላዋን ሸክም አትሸከምም። የተከበደችም (ነፍስ) ወደ ሸክሟ ብትጣራ (ተጠሪው) የቅርብ ዝምድና ባለቤት ቢኾንም እንኳ ከእርሷ አንዳችን የሚሸከምላት አታገኝም። የምታስጠነቅቀው እነዚያን ጌታቸውን በሩቅ የሚፈሩትን፣ ሶላትንም አስተካክለው ያደረሱትን ብቻ ነው። የተጥራራም ሰው የሚጥራራው ለራሱ ብቻ ነው። መመለሻም ወደ አላህ ብቻ ነው።} [ፋጢር 18]

## 16 - የሰው ልጆች የመፈጠራቸውም አላማ አላህን በብቸኝነት ለማምለክ ነው።

የሰው ልጆች የመፈጠራቸውም አላማ አላህን በብቸኝነት ለማምለክ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ }

{ጂኒን እና ሰዉንም እንዲገዙኝ እንጂ ለሌላ ነገር አልፈጠርኳቸዉም።} [አዝ-ዛሪያት 56]

## 17 - እስልምና የሰውልጆችን –ወንዶቹንም ሆነ ሴቶቹን- ክብርን አጎናፀፋቸው፤ ለተሟላ መብታቸውም ዋስትናውን አረጋገጠላቸው፤ በተቀሩት ምርጫዎች፣ ድርጊቶችም ሆኑ ክንውኖች ተጠያቂነትን አደረገባቸው፤ ራሱንም ይሁን ሌላን ለሚጎዱ ድርጊቶች የተጠያቂነት ኋላፊነት ጣለባቸው።

እስልምና የሰው ልጆችን –ወንዶቹንም ሆነ ሴቶቹን- ክብርን አጎናፀፋቸው፤ የላቀው አላህ ሰውን በምድር ላይ ምድራዊ ምትክ እንዲሆን ፈጠረ፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَائِكَةِ إِنِّي جَاعِلٌ فِي الْأَرْضِ خَلِيفَةً }

{(ሙሓመድ ሆይ) ጌታህ ለመላእክት፦ «እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤» ባለ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ፤} [አል-በቀራህ 30]

ይህ ክብር ሁለንተናዊና ለመላ የሰው ልጆች ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِي آدَمَ وَحَمَلْنَاهُمْ فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ وَرَزَقْنَاهُم مِّنَ الطَّيِّبَاتِ وَفَضَّلْنَاهُمْ عَلَىٰ كَثِيرٍ مِّمَّنْ خَلَقْنَا تَفْضِيلًا }

{የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው። በየብስና በባህርም አሳፈርናቸው።

ከመልካሞችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው። ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው።} [አል ኢስራእ፡ 70] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{لَقَدْ خَلَقْنَا الْإِنسَانَ فِي أَحْسَنِ تَقْوِيمٍ }

{ሰውንም በጣም በአማረ አቋም ላይ ፈጠርነው።} [አት-ቲን 4]

አላህ ሰው ራሱን ከአላህ ውጪ ላለ አካል አገልጋይ፣ ተከታይ ወይም ታዛዥ ከማድረግ ከልክሏል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَمِنَ النَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ اللَّهِ أَندَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ اللَّهِ ۖ وَالَّذِينَ آمَنُوا أَشَدُّ حُبًّا لِّلَّهِ ۗ وَلَوْ يَرَى الَّذِينَ ظَلَمُوا إِذْ يَرَوْنَ الْعَذَابَ أَنَّ الْقُوَّةَ لِلَّهِ جَمِيعًا وَأَنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعَذَابِ. إِذْ تَبَرَّأَ ٱلَّذِينَ ٱتُّبِعُواْ مِنَ ٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُواْ وَرَأَوُاْ ٱلْعَذَابَ وَتَقَطَّعَتْ بِهِمُ ٱلْأَسْبَابُ}

{ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባለንጣዎችን (ጣዖታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ሆነው የሚይዙ አልሉ። እነዚያ ያመኑትም አላህን በመውደድ (ከነርሱ) ይበልጥ የበረቱ ናቸው። እነዚያም የበደሉት ሰዎች ቅጣትን (በትንሣኤ ቀን) ባዩ ጊዜ ኀይል ሁሉ ለአላህ ብቻ መኾኑንና አላህም ቅጣቱ ብርቱ መኾኑን (በአዱኛ ዓለም) ቢያውቁ ኖሮ (ባላንጣዎችን በመያዛቸው በተጸጸቱ ነበር)።} [አል-በቀራህ 165-166] የላቀው አላህ በስህተት ላይ መሪዎችንና ተከታዮቻቸውን በእለተ ትንሣኤ የሚኖራቸው ሁኔታ አስመልክቶ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡-

{ قَالَ الَّذِينَ اسْتَكْبَرُوا لِلَّذِينَ اسْتُضْعِفُوا أَنَحْنُ صَدَدْنَاكُمْ عَنِ الْهُدَىٰ بَعْدَ إِذْ جَاءَكُم ۖ بَلْ كُنتُم مُّجْرِمِينَ (32) وَقَالَ الَّذِينَ اسْتُضْعِفُوا لِلَّذِينَ اسْتَكْبَرُوا بَلْ مَكْرُ اللَّيْلِ وَالنَّهَارِ إِذْ تَأْمُرُونَنَا أَن نَّكْفُرَ بِاللَّهِ وَنَجْعَلَ لَهُ أَندَادًا ۚ وَأَسَرُّوا النَّدَامَةَ لَمَّا رَأَوُا الْعَذَابَ وَجَعَلْنَا الْأَغْلَالَ فِي أَعْنَاقِ الَّذِينَ كَفَرُوا ۚ هَلْ يُجْزَوْنَ إِلَّا مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ (33) }

{እነዚያ የኮሩት ለእነዚያ ለተዋረዱት «ከትክክለኛው እምነት ከመጣላችሁ በኋላ እኛ ከለከልናችሁን? አይደለም (እናንተው) ከሓዲዎች ነበራችሁ» ይሏቸዋል፡፡}

{እነዚያም የተዋረዱት ለእነዚያ ለኮሩት «አይደለም፤ በአላህ እንድንክድና ለእርሱ ባላንጣዎችን እንድናደርግ ስታዙን (የከለከለን) የሌሊትና የቀን ዱለታችሁ ነው» ይላሉ፡፡ ቅጣቱንም ባዩ ጊዜ ጸጸትን ይገልጻሉ፡፡ በእነዚያም በካዱት አንገቶች ላይ እንዛዝሎችን እናደርጋለን፡፡ ይሠሩት የነበሩትን እንጂ ሌላን ይመነዳሉን?} [ሰባእ 32-33]

ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ በእለተ ትንሣኤ ከሚኖረው ፍጹም ፍትሓዊነትም አንፃር የስህተት ሰባኪዎች እና መሪዎች የራሳቸውንም የእነዚያ ባለማወቃቸው የተከተሏቸው ተከታዮቻቸውንም ኋጢአት ማሸከሙ ይገኝበታል፡፡ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{لِيَحْمِلُوا أَوْزَارَهُمْ كَامِلَةً يَوْمَ الْقِيَامَةِ ۙ وَمِنْ أَوْزَارِ الَّذِينَ يُضِلُّونَهُم بِغَيْرِ عِلْمٍ ۗ أَلَا سَاءَ مَا يَزِرُونَ}

{(ይህንንም የሚሉት) በትንሣኤ ቀን ኀጢኣቶቻቸውን በሙሉ ከእነዚያም ያለ ዕውቀት ኸነው ከሚያጠሟቸው

ሰዎች ኀጢአቶች ከፊሉን ሊሸከሙ ነው። ንቁ! የሚሸከሙት ኃጢኣት ምንኛ ከፋ!} [አን-ነሕል 25]

እስልምና ለሰው ልጅ በዚህኛውም በመጨረሻውም ዓለም ያለውን ሙሉ መብቱን ያረጋግጥለታል፤ እስልምና ለመላው የሰው ልጅ ካረጋገጠለት መብቶቹ መካከል እጅግ ታላቁ መብቱ አላህ በባሮቹ ላይ ያለውንና ባሮቹም እሱ ዘንድ ያላቸውን መብቶች ያሰወቀበት ነው።

فعَنْ مُعَاذٍ رضي الله عنه قَالَ: أَنَا رَدِيفُ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَقَالَ: «يَا مُعَاذُ» قُلْتُ: لَبَّيْكَ وَسَعْدَيْكَ ثُمَّ قَالَ مِثْلَهُ ثَلاَثًا: «هَلْ تَدْرِي مَا حَقُّ اللَّهِ عَلَى العِبَادِ» قُلْتُ: لاَ قَالَ: «حَقُّ اللَّهِ عَلَى العِبَادِ أَنْ يَعْبُدُوهُ وَلاَ يُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا» ثُمَّ سَارَ سَاعَةً فَقَالَ: «يَا مُعَاذُ» قُلْتُ: لَبَّيْكَ وَسَعْدَيْكَ قَالَ: "هَلْ تَدْرِي مَا حَقُّ العِبَادِ عَلَى اللَّهِ إِذَا فَعَلُوا ذَلِكَ: أَنْ لاَ يُعَذِّبَهُمْ »

ከሙዓዝ አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው በተላለፈ ሐዲሥ: አንድ ቀን ከነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ጋ በአንድ አህያ ተፈናጥጨ ሳለሁ: "ሙዓዝ ሆይ!" አሉኝ፤ እኔም "አቤት በደስታ" አልኳቸው፤ ከዚያም ራሡን ቃል ደጋገመው አሉና "አላህ በባርያዎቹ ላይ ያለውን መብት ታውቃለህን?" አሉኝ፤ እኔም "ኸረ አላውቅም" አልኳቸው፤ እሳቸውም "አላህ በባርያዎቹ ያለው መብት በእርሱ ምንንም ሳያጋሩ በብቸኝነት ሊያመልኩት ነው" አሉኝ፤ ከዚያም ትንሽ እንደተጓዙ መልሰው "ሙዓዝ ሆይ!" አሉኝ፤ እኔም "አቤት በደስታ" አልኩ፤ "ባርያዎችስ ያንን መብቱን ከተወጡ የማይቀጡበት የሆነውን መብታቸውን ታውቃለህን?" አሉኝ። "በጀሀነም እሳት (በዘውታሪነት) ላይቀጣቸው ነው።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6840

የእስልምና ሃይማኖት ለሰው ልጅ የሃይማኖቱን፣ የዝርያውን፣ የገንዘቡንና የክብሩን ዋስትና አረጋግጦለታል። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«فَإِنَّ اللَّهَ حَرَّمَ عَلَيْكُمْ دِمَاءَكُمْ وَأَمْوَالَكُمْ وَأَعْرَاضَكُمْ كَحُرْمَةِ يَوْمِكُمْ هَذَا فِي شَهْرِكُمْ هَذَا فِي بَلَدِكُمْ هَذَا»

"አላህ ልክ ይህው ያለንበትን ቀንና ሀገር እንዳከበረው፤ ደማችሁን፣ ንብረታችሁንና ክብራችሁንም ከልክሎ አስከብሮላችኋል።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6501 በእርግጥ ይህ ታላቅ ቃል ኪዳን የአላህ መልዕክተኛ ከመቶ ሺህ በላይ ሶሓቦች በተገኙበት የመሰናበቻው ሐጅ እለት ያወጁበት ነው። ይህንንም መልዕክት በመሰናበቻው ሐጅ እለተ እርድ (የውመ ነሕር) አፅንኦት ሰጥተውታል።

እስልምና የሰው ልጅ በምርጫዎቹም ሆነ በሌሎች ድርጊቶቹም ሁሉ እንዲሁም በአጠቃላይ እንቅስቃሴውም ጭምር ተጠያቂነትን ኋላፊነት አድርጎበታል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَكُلَّ إِنسَانٍ أَلْزَمْنَاهُ طَائِرَهُ فِي عُنُقِهِ ۖ وَنُخْرِجُ لَهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ كِتَابًا يَلْقَاهُ مَنشُورًا اقْرَأْ كِتَابَكَ كَفَىٰ بِنَفْسِكَ الْيَوْمَ عَلَيْكَ حَسِيبًا }

{ሰውንም ሁሉ በራሪውን (ሥራውን) በአንገቱ አስያዝነው። ለእርሱም በትንሣኤ ቀን የተዘረጋ ሆኖ የሚያገኘው የሆነን መጽሐፍ እናወጣለታለን።} [አል-ኢስራእ 13] አላህ ከአንድ ሰው ጋ ያያያዘው የትኛውም በጎም ይሁን መጥፎ ስራ ወደ ሌላ ወደ ማንም አይተላለፍም፤ በሌላው

ስራ እርሱ አይጠየቅም፤ በእርሱ ስራም ሌላው አይጠየቅም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا الْإِنسَانُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدْحًا فَمُلَاقِيهِ}

{አንተ ሰው ሆይ! አንተ ጌታህን (በሞት) እስከምትገናኝ ድረስ ልፋትን ለፊ ነህ፤ ተገናኚውም ነህ።} [አል-ኢንሺቃቅ 6] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ مَّنْ عَمِلَ صَٰلِحًا فَلِنَفْسِهِۦ ۖ وَمَنْ أَسَآءَ فَعَلَيْهَا ۗ وَمَا رَبُّكَ بِظَلَّٰمٍ لِّلْعَبِيدِ}

{መልካም የሠራ ሰው ለነፍሱ ነው። ያጠፋም ሰው በእርሷ ላይ ነው። ጌታህም ለባሮቹ በዳይ አይደለም።} [ፉሲለት 46]

እስልምና ራስንም ይሁን ሌላን ለሚጎዳ የትኛውም ድርጊት የተጠያቂነት ኋላፊነትን አድርጓል፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَمَن يَكْسِبْ إِثْمًا فَإِنَّمَا يَكْسِبُهُ عَلَىٰ نَفْسِهِ ۚ وَكَانَ اللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا}

{ኀጢአትንም የሚሠራ ሰው የሚሠራው ጥፋት በራሱ ላይ ነው። አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፤} [ኒሳእ 111] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ مِنْ أَجْلِ ذَٰلِكَ كَتَبْنَا عَلَىٰ بَنِي إِسْرَائِيلَ أَنَّهُ مَن قَتَلَ نَفْسًا بِغَيْرِ نَفْسٍ أَوْ فَسَادٍ فِي الْأَرْضِ فَكَأَنَّمَا قَتَلَ النَّاسَ جَمِيعًا وَمَنْ أَحْيَاهَا فَكَأَنَّمَا أَحْيَا النَّاسَ جَمِيعًا }

{በዚህ ምክንያት በእስራኤል ልጆች ላይ እነሆ ያለ ነፍስ (መግደል) ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት (ካልሆነ በስተቀር) ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤

ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ማለትን ጻፍን።} [አል-ማኢዳህ 32] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«لَا تُقْتَلُ نَفْسٌ ظُلْمًا إِلَّا كَانَ عَلَى ابْنِ آدَمَ الْأَوَّلِ كِفْلٌ مِنْ دَمِهَا لِأَنَّهُ كَانَ أَوَّلَ مَنْ سَنَّ الْقَتْلَ»

«አንዲትም ነፍስ በበደል እስከተገደለች ድረስ ለመጀመርያው የአደም ልጅ ከግድያው ድርሻ አለበት፤ ምክንያቱም ይግድያን ፈር ቀዳጅ እርሱው ነውና።» ሰሒሕ ሙስሊም 5150

## 18- እስልምና ወንዶችንና ሴቶችንም ከተጠያቂነት፣ ከቅጣት፣ ከምንዳም ሆነ ከሽልማት አንፃር እኩል አደረጋቸው።

እስልምና ወንዶችንና ሴቶችንም ከተጠያቂነት፣ ከቅጣት፣ ከምንዳም ሆነ ከሽልማት አንፃር እኩል አደረጋቸው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَمَن يَعْمَلْ مِنَ الصَّالِحَاتِ مِن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُولَٰئِكَ يَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ وَلَا يُظْلَمُونَ نَقِيرًا}

{ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ ከበጎ ሥራዎች አንዳችን የሚሠራም ሰው እነዚያ ገነትን ይገባሉ። በተምር ፍሬ ላይ ያለችን ነጥብ ያክል እንኳ አይበደሉም።} [ኒሳእ 124] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ مَنْ عَمِلَ صَالِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةً ۖ وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ }

{ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን። ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።} [አን-ነሕል 97] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{مَنْ عَمِلَ سَيِّئَةً فَلَا يُجْزَىٰ إِلَّا مِثْلَهَا ۖ وَمَنْ عَمِلَ صَالِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُولَٰئِكَ يَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ يُرْزَقُونَ فِيهَا بِغَيْرِ حِسَابٍ}

{«መጥፎን የሠራ ሰው ብጤዋን እንጅ አይምመነዳም። እርሱ ምእመን ኾኖ ከወንድ ወይም ከሴት በጎን የሠራም ሰው እነዚያ ገነትን ይገባሉ። በእርሷ ውስጥ ያለ ቁጥጥር ይመገባሉ።} [ጋፊር 40] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ الْمُسْلِمِينَ وَالْمُسْلِمَاتِ وَالْمُؤْمِنِينَ وَالْمُؤْمِنَاتِ وَالْقَانِتِينَ وَالْقَانِتَاتِ وَالصَّادِقِينَ وَالصَّادِقَاتِ وَالصَّابِرِينَ وَالصَّابِرَاتِ وَالْخَاشِعِينَ وَالْخَاشِعَاتِ وَالْمُتَصَدِّقِينَ وَالْمُتَصَدِّقَاتِ وَالصَّائِمِينَ وَالصَّائِمَاتِ وَالْحَافِظِينَ فُرُوجَهُمْ وَالْحَافِظَاتِ وَالذَّاكِرِينَ اللَّهَ كَثِيرًا وَالذَّاكِرَاتِ أَعَدَّ اللَّهُ لَهُم مَّغْفِرَةً وَأَجْرًا عَظِيمًا}

{ሙስሊሞች ወንዶችና ሙስሊሞች ሴቶች፣ ምእምናንና ምእምናትም፣ ታዛዦች ወንዶችና ታዛዦች ሴቶችም፣ እውነተኞች ወንዶችና እውነተኞች ሴቶችም፣ ታጋሾች ወንዶችና ታጋሾች ሴቶችም፣ አላህን ፈሪዎች ወንዶችና አላህን ፈሪዎች ሴቶችም፣ መጽዋቾች ወንዶችና መጽዋቾች ሴቶችም፣ ጿሚዎች ወንዶችና ጿሚዎች ሴቶችም፣ (ካልተፈቀደ ሥራ) ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች ወንዶችና ጠባቂ ሴቶችም፣ አላህን በብዙ አውሺዎች ወንዶችና አውሺዎች ሴቶችም፣ አላህ ለእነርሱ ምሕረትንና ታላቅን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል።} [አል-አሕዛብ 35]

## 19- እስልምና ሴትን ልጅ አከበረ፤ ሴቶቹን የወንዶቹ ክፋይ አድርጎም ቆጠረ፤ ወንድ እስከቻለ ድረስ ለሴት ይለግሳት ዘንድ ግዴታን ጣለበት፤ በመሆኑም አባት የሴት ልጁን ወጭ የመቻል ግዴታ አለበት፤ እናትም ወጭዋን ለመቻል የደረሰ ልጅ ካላት፤ ሚስትም ባሏ ወጭዋን ሊችሉ ግዴታ አለባቸው።

እስልምና ሴትን ልጅ የወንድ ልጅ ክፋይ አድርጎ ነው የሚቆጥራት። የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል:-

«إن النساء شقائق الرجال»

«ሴቶች የወንዶች ክፋይ ናቸው።» ቲርሚዚይ ዘግበውታል (113)

እስልምና ሴትን ልጅ ካላቀባቸው ጉዳዮች መካከል ችሎታው ያለው ወንድ ልጅ ያላት እናት ወንድ ልጇ ወጪዋን ሊችልላት ግዴታው መሆኑ ለዚህ አንድ ማሳያ ነው። የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል:-

«يَدُ الْمُعْطِي الْعُلْيَا أُمَّكَ وَأَبَاكَ وَأُخْتَكَ وَأَخَاكَ ثُمَّ أَدْنَاكَ أَدْنَاكَ»

«የሰጭ እጅ የበላይ ነው፤ ይበልጥ ተገቢዎቹም እናትህ፣ አባትህ፣ እህትህና ወንድምህ ከዚያም ባለው ቅርበት ልክ ይበልጥ ተገቢ ይሆናል።» ኢማም አሕመድ ዘግበውታል

ወላጆች ያላቸውን ደረጃ በማስመልከት በአላህ ፈቃድ አንቀፅ 29 ላይ ይመጣል።

እስልምና ሴትን ልጅ ካላቀባቸው ጉዳዮች መካከል ባሏ ችሎታው እስካለው ድረስ የሚስት ወጪዋን ሊችልላት በባሏ ላይ ግዴታው መሆኑ ለዚህ አንድ ማሳያ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{لِيُنفِقْ ذُو سَعَةٍ مِّن سَعَتِهِ ۖ وَمَن قُدِرَ عَلَيْهِ رِزْقُهُ فَلْيُنفِقْ مِمَّا آتَاهُ اللَّهُ ۚ لَا يُكَلِّفُ اللَّهُ نَفْسًا إِلَّا مَا آتَاهَا ۚ سَيَجْعَلُ اللَّهُ بَعْدَ عُسْرٍ يُسْرًا}

{የችሎታ ባለቤት ከችሎታው ይቀልብ። በእርሱም ላይ ሲሳዩ የተጠበበበት ሰው አላህ ከሰጠው ይቀልብ አላህ ነፍስን የሰጣትን እንጅ አያስገድድም። አላህ ከችግር በኋላ ምቾትን በእርግጥ ያደርጋል።} [አጥ-ጦላቅ 7]

وسَأَلَ النبيَ صلى الله عليه وسلم رَجُلٌ: مَا حَقُّ الْمَرْأَةِ عَلَى الزَّوْجِ؟ قَالَ: «تُطْعِمُهَا إِذَا طَعِمْتَ وَتَكْسُوهَا إِذَا اكْتَسَيْتَ وَلَا تَضْرِبِ الْوَجْهَ وَلَا تُقَبِّحْ»

አንድ ሰው ነብዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሚስት ከባሏ ስላላት መብቶች ጠየቃቸው፤ "ስትበላ ልታበላት፣ ስትለብስም ልታለብሳት ፊቷንም ላትመታት ላታነውራትም ነው።" በማለት መለሱለት። ኢማም አሕመድ ዘግበውታል የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሴቶች ከባሎቻቸው ሊያገኙ ስለሚገባቸው ከፊል መብቶቻቸው በማስመልከት እንዲህ ብለዋል፦

«وَلَهُنَّ عَلَيْكُمْ رِزْقُهُنَّ وَكِسْوَتُهُنَّ بِالْمَعْرُوفِ»

"ለእነርሱ የለት ጉርሳቸውንና ልብሳቸውን የመቻል እንዲሁም በመልካምም ልትናገሯቸው መብታቸው ነው።" ሰሒሕ ሙስሊም የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«كَفَى بِالْمَرْءِ إِثْمًا أَنْ يُضَيِّعَ مَنْ يَقُوتُ»

«አንድ ሰው ያለበትን ቤተሰባዊ የገንዘብ ኃላፊነት አለመወጣቱ ከወንጀል በቂው ነው።» ኢማም አሕመድ ዘግበውታል አል-ኸጧቢይ እንዲህ ብለዋል፡- "...ያለበት ቤተሰባዊ የገንዘብ ኋላፊነት..." ሲሉ ወጪያቸውን ሊችላቸው ግዴታው የሆነበት ማለታቸው ነው። በሌላ አገላለፅ ሶደቃ አወጣለሁ ለሚለው ሰው ወጪያቸውን ልትችላቸው ግዴታ ከሆኑብህ ቤተሰቦችህ ተርፎ ካልሆነ በቀር አጅርን ፈልገህበትም ሶደቃ አታድርግ እያሉት ነው። ምክንያቱም የእነርሱን ሐቅ ችላ በማለትህ ወንጀል ይሆንብሀልና ነው።

እስልምና ሴትን ካከበረባቸው ሁኔታዎች መካከል የአንዲትን ሴት ልጅ ወጪዋን ሊችላት ወላጅ አባቷ ላይ ግዴታ ማድረጉም ሌላው ማሳያ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَالْوَالِدَاتُ يُرْضِعْنَ أَوْلَادَهُنَّ حَوْلَيْنِ كَامِلَيْنِ ۖ لِمَنْ أَرَادَ أَن يُتِمَّ الرَّضَاعَةَ ۚ وَعَلَى الْمَوْلُودِ لَهُ رِزْقُهُنَّ وَكِسْوَتُهُنَّ بِالْمَعْرُوفِ}

{እናቶችም ልጆቻቸውን ሙሉ የሆኑን ሁለት ዓመታት ያጥቡ። (ይህም) ማጥባትን መሙላት ለሻ ሰው ነው። ለእርሱም በተወለደለት (አባት) ላይ ምግባቸውና ልብሳቸው

በችሎታው ልክ አለበት።} [አል-በቀራህ: 233] ልጅ የተወለደለት ወላጅ አባት ላይ ልጁን የማብላትና በጥሩ ሁኔታ የማልበስ ግዴታም እንዳለበት ግልፅ አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ فَإِنْ أَرْضَعْنَ لَكُمْ فَآتُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ }

{ለእናንተም (ልጆቻችሁን) ቢያጠቡላችሁ ምንዳዎቻቸውን ስጧቸው።} [አጥ-ጦላቅ: 6] የላቀው አላህ ልጅ እንዲጠባ የማድረግ ግዴታ ክፍያን በአባትየው ላይ አደረገ። ይህም የልጅን ወጭ ሊችል ግዴታውን በአባትየው ላይ መሆኑን እንዲሁም ልጅ የሚለው ደግሞ ሴት ልጅንም ሆነ ወንድ ልጅንም የሚያካትት ቃል ነው። በተከታዩ ሓዲሥ ደግሞ የእናትየውንም ሆነ የልጅየውን ወጪ የመቻል ኋላፊነት በቤቱ አባወራ ላይ መሆኑን እንረዳለን። ዓኢሻ መልካም ሥራዋን አላህ ይውደድላት ባስተላለፈችው ሓዲሥ፦ ሂንድ ለነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) "አባ ሱፍያን ስስታም ነው እኔ ደግሞ ከገንዘቡ ያስፈልገኛል።" ስትላቸው እሳቸውም እንዲህ አሏት፦

«خُذِي مَا يَكْفِيكِ وَوَلَدَكِ بِالْمَعْرُوفِ»

"ላንችም ለልጅሽም የሚበቃሽን ያህል በመልካም ሁኔታ ውሰጅ።" ቡኻሪ ዘግበውታል የተከበሩት ነቢይ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የሴት ልጆችን እና የእህቶችን ወጭያቸውን መቻል ያለውን ብልጫ እንዲህ በማለት አብራርተዋል፦

«مَنْ عَالَ ابْنَتَيْنِ أَوْ ثَلَاثَ بَنَاتٍ أَوْ أُخْتَيْنِ أَوْ ثَلَاثَ أَخَوَاتٍ حَتَّى يَبِنَّ أَوْ يَمُوتَ عَنْهُنَّ كُنْتُ أَنَا وَهُوَ كَهَاتَيْنِ. وَأَشَارَ بِأُصْبُعَيْهِ السَّبَّابَةِ وَالْوُسْطَى»

«በጋብቻ ወይንም በሞት እስኪለዩት ድረስ ሁለት ወይም ሦስት ሴት ልጆችን ወይንም ሁለት ወይም ሦስት እህቶችን ያሳደገ እኔና እሱ እንደነዚህ ነን በማለት በጠቋሚ ጣታቸውና በመሀል ጣታቸው አሳዩ።» ሲልሲለቱ ሶሒሓህ: 296

## 20- ሞት ብሎ ማለት ሙሉ በሙሉ አልቆ መጥፋት ማለት ሳይሆን ከስራ አለም ወደ ምንዳ አለም መሸጋገር ነው። ሞት አካልንም ሩሕንም የሚመለከት ነው። የሩሕ ሞት ስንል ግን ከአካል መለየቷን ማለታችን ነው። ከዚያም በእለተ ትንሳኤ ከተቀሰቀሱ በኋላ ሩሕ ወደ አካሏ ትመለሳለች። ሰው ከሞተ በኋላ ሩሑ ወደ ሌላ አካልም አትሸጋገርም ወደሌላም አካል አትሰርፅም።

ሞት ብሎ ማለት ለዘልአለሙ አልቆ መጥፋት ማለት አይደለም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ يَتَوَفَّاكُم مَّلَكُ الْمَوْتِ الَّذِي وُكِّلَ بِكُمْ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُمْ تُرْجَعُونَ}

{«በእናንተ የተወከለው መልአከ ሞት ይገድላችኋል። ከዚያም ወደ ጌታችሁ ትመለሳላችሁ» በላቸው።} ሰጅዳህ: 11 ሞት አካልንም ሩሕንም የሚመለከት ሲሆን የሩሕ ሞት ስንል ግን የሩሕ ከአካል መለየቷን ማለታችን ነው። ከዚያም

በእለተ ትንሳኤ ከተቀሰቀሱ በኋላ ሩሕ ወደ አካሏ ትመለሳለች። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ اللَّهُ يَتَوَفَّى الْأَنفُسَ حِينَ مَوْتِهَا وَالَّتِي لَمْ تَمُتْ فِي مَنَامِهَا ۖ فَيُمْسِكُ الَّتِي قَضَىٰ عَلَيْهَا الْمَوْتَ وَيُرْسِلُ الْأُخْرَىٰ إِلَىٰ أَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَآيَاتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ}

{አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል። ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፏ ጊዜ (ይወስዳታል)። ታዲያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል። ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቅቃታል። በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ምልክቶች አልሉበት።} ሩም: 42 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«إِنَّ الرُّوحَ إِذَا قُبِضَ تَبِعَهُ الْبَصَرُ»

«ሩሕ ስትያዝ አይንም ትከተላታለች።» ሙስሊም ዘግበውታል: 920 የሰው ልጅ ከሞት በኋላ ከስራ አለም ወደ ምንዳ አለም ይሸጋገራል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ إِلَيْهِ مَرْجِعُكُمْ جَمِيعًا ۖ وَعْدَ اللَّهِ حَقًّا ۚ إِنَّهُ يَبْدَأُ الْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُ لِيَجْزِيَ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ بِالْقِسْطِ ۚ وَالَّذِينَ كَفَرُوا لَهُمْ شَرَابٌ مِّنْ حَمِيمٍ وَعَذَابٌ أَلِيمٌ بِمَا كَانُوا يَكْفُرُونَ }

{ሁላችሁም ሆናችሁ መመለሻችሁ ወደ እርሱ ነው። (ይህም) የተረጋገጠ የአላህ ቃል ኪዳን ነው፤ እርሱ መፍጠርን ይጀምራል። ከዚያም እነዚያን ያመኑትንና መልካም የሠሩትን በትክክል ይመነዳ ዘንድ ይመልሰዋል። እነዚያ

የካዱትም ይክዱት በነበሩት ነገር ለነርሱ ከፈላ ውሃ የሆነ መጠጥና አሳማሚ ቅጣት አላቸው።} (ዩኑስ: 4)

ከሞት በኋላ ነፍስ ወደ ሌላ አካል አትዘዋወርም በሌላ አካልም ውስጥም አትሰርፅም። ወደ ሌላ አካል መስረፅ የሚባለው ሙግት በአእምሯዊም ሆነ በተጨባጩ ማስረጃ የሌለው ነው። ከነብያቶችም ዓለይሂሙ ሰላም ቢሆን ምንም አይነት የተረጋገጠ መሰረት የሌለው ተራ ሙግት ነው።

## 21- እስልምና በታላላቅ የእምነት መሰረቶች ወደ ማመን ይጣራል። እነኝህም፡ በአላህ ማመን፤ በመላእክቶች ማመን፤ በመለኮታዊ መጽሐፍት በነ ተውራት፣ ኢንጂል፣ ዘቡር –ከመበረዛቸው በፊት- ማመን እንዲሁም በቁርአን ማመን፤ የአላህ ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና በሁሉም ነብያቶች እና መልዕክተኞች ማመን እንዲሁም በመጨረሻቸውና የነብያቶችም የሩሱሎችም መደምደሚያ በሆኑት የአላህ መልዕክተኛ በሙሐመድ ማመን፤ በመጨረሻው ቀን ማመን –የዱንያ ህይወት ብቻ እንጂ ሌላ አለም የሌለ ቢሆን ኖሮ ህይወትም ሆነ ህልውና ጥርት ያለ

## ተላላነት በሆነ ነበር- በቀዷና በቀደር ማመን ላይ የተመሰረተ ነው።

እስልምና ሁሉም ነቢያትና መልእክተኞች ጥሪ ወዳደረጉበት ታላላቅ የእምነት መሰረቶች ወደ ማመን ነው የሚጣራው። እነኝህም፡-

አንደኛ: የዚህ ፍጥረተ ዓለም ሰማይ ጌታ፣ ፈጣሪ፣ ሲሳይ ለጋሽና ተቆጣጣሪ መሆኑንና እርሱ ብቻም አምልኮ የሚገባው መሆኑን፤ ከእርሱ ውጭ ያለውን ሁሉ ማምለክም ከንቱ መሆኑን፤ ከእርሱ ውጭ የሚመለኩት አማልክት ሁሉ ሐሰተኛ መሆናቸውን ስለዚህ አምልኮ ከእሱ በስተቀር ለሌላ ተገቢም አይደለም፤ አምልኮም ከእርሱ በስተቀር ትክክለኛ አምልኮ ሊሆንም አይችልም። በእርግጥ ለዚህ ያለንን ማስረጃ ከፍ ብለን ጠቅሰናል።

ጥራት የተገባውና የላቀው አላህ እነኝህን ታላላቅ መሰረቶችን በርከት ባሉ በተለያዩ የታላቁ ቁርአን አንቀጾች አውስቷቸዋል። ከእነኝህም መካከል ቀጣዮቹን የላቀው አላህ ንግግሮች ማየት እንችላለን፡-

{آمَنَ الرَّسُولُ بِمَا أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِ وَالْمُؤْمِنُونَ ۚ كُلٌّ آمَنَ بِاللَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن رُّسُلِهِ ۚ وَقَالُوا سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا ۖ غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ الْمَصِيرُ }

{መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖቹም (እንደዚሁ)። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል አንለይም» (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ። «ሰማን፤

ታዘዝንም፡፡ ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)፡፡ መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም፡፡} [አል-በቀራህ: 285]

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{لَّيْسَ الْبِرَّ أَن تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَٰكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَىٰ حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَىٰ وَالْيَتَامَىٰ وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ وَفِي الرِّقَابِ وَأَقَامَ الصَّلَاةَ وَآتَى الزَّكَاةَ وَالْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ إِذَا عَاهَدُوا ۖ وَالصَّابِرِينَ فِي الْبَأْسَاءِ وَالضَّرَّاءِ وَحِينَ الْبَأْسِ ۗ أُولَٰئِكَ الَّذِينَ صَدَقُوا ۖ وَأُولَٰئِكَ هُمُ الْمُتَّقُونَ}

{መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፡፡ በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን)፡፡ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡} [አል-በቀራህ: 177]

የላቀው አላህ በእነዚህ መርሆዎች ወደ ማመን የጠራ ሲሆን በእነሱም የሚክድ ሰው እጅግ በጣም የተሳሳተው መሆኑን ግልጽ አድርጓል፡፡ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا آمِنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ وَالْكِتَابِ الَّذِي نَزَّلَ عَلَىٰ رَسُولِهِ وَالْكِتَابِ الَّذِي أَنزَلَ مِن قَبْلُ ۚ وَمَن يَكْفُرْ بِاللَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَالًا بَعِيدًا}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ። በአላህና በመላእክቱም፣ በመጽሐፎቹም፣ በመልክተኞቹም፣ በመጨረሻውም ቀን፣ የካደ ሰው (ከእውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።} [ኒሳእ: 136] ከዑመር ኢብኑል ኸጧብ አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው በተላለፈ ሐዲሥ እንዲህ የሚል እናገኛለን፡-

(بَيْنَمَا نَحْنُ عِنْدَ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ذَاتَ يَوْمٍ إِذْ طَلَعَ عَلَيْنَا رَجُلٌ شَدِيدُ بَيَاضِ الثِّيَابِ شَدِيدُ سَوَادِ الشَّعَرِ لَا يُرَى عَلَيْهِ أَثَرُ السَّفَرِ وَلَا يَعْرِفُهُ مِنَّا أَحَدٌ حَتَّى جَلَسَ إِلَى النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَأَسْنَدَ رُكْبَتَيْهِ إِلَى رُكْبَتَيْهِ وَوَضَعَ كَفَّيْهِ عَلَى فَخِذَيْهِ وَقَالَ: يَا مُحَمَّدُ أَخْبِرْنِي عَنِ الْإِسْلَامِ فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «الْإِسْلَامُ أَنْ تَشْهَدَ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ وَتُقِيمَ الصَّلَاةَ وَتُؤْتِيَ الزَّكَاةَ وَتَصُومَ رَمَضَانَ وَتَحُجَّ الْبَيْتَ إِنِ اسْتَطَعْتَ إِلَيْهِ سَبِيلًا» قَالَ: صَدَقْتَ قَالَ: فَعَجِبْنَا لَهُ يَسْأَلُهُ وَيُصَدِّقُهُ قَالَ: فَأَخْبِرْنِي عَنِ الْإِيمَانِ قَالَ: «أَنْ تُؤْمِنَ بِاللهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَتُؤْمِنَ بِالْقَدَرِ خَيْرِهِ وَشَرِّهِ» قَالَ: صَدَقْتَ قَالَ: فَأَخْبِرْنِي عَنِ الْإِحْسَانِ قَالَ: «أَنْ تَعْبُدَ اللهَ كَأَنَّكَ تَرَاهُ فَإِنْ لَمْ تَكُنْ تَرَاهُ فَإِنَّهُ يَرَاكَ»

«ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዘንድ ሳለን ልብሱ በጣም ነጭ ፀጉሩ በጣም ጥቁር የሆነ ሰው ብቅ አለ። የመንገደኛ ምልክትም አይታይበትም ከኛ መካከልም የሚያውቀው

ሰውም የለም። ወደ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ተጠግቶ ጉልበቱን ከጉልበታቸው አስደግፎ ተቀመጠ። እጁንም ታፋው ላይ አደረገና "አንተ ሙሐመድ ሆይ! እስኪ ስለ ኢስላም ንገረኝ?" አላቸው። የአላህ መልዕክተኛም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) "ኢስላም ማለት በ'ላኢላሀ ኢለሏህ ሙሐመደን ረሱሉሏህ' የምስክርነት ቃልህን ልትሰጥ፣ ሶላት (ስርአቱን አሟልተህ) ልትሰግድ፣ ዘካን ልታወጣ፣ ረመዷንን ልትፆም፣ መንገዱን ከቻልክ ደግሞ ሐጅ ልታደርግ ነው።" አሉት። "እውነት ብለሃል" አላቸው። "ይጠይቀውና 'ትክክል ነህ' ይላቸዋል። ተገረምን!"» ይላል። «"ስለኢማን ንገረኝ እስኪ!" አላቸው። እርሳቸውም "በአላህ፣ በመላእክቶቹ፣ በኪታቦቹ፣ በመልእክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና ልታምንና በቀደርም ክፉውም ሆነ ደጉን ልታምን ነው።" አሉት። "እውነት ብለሃል!" አላቸው። "እስኪ ደሞ ስለ ኢሕሳን ንገረኝ!" አላቸው። እሳቸውም "አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው ነው፤ አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና።"» ሰሒሕ ሙስሊም 8 በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ጂብሪል (የአላህ ሰላም በእርሱ ላይ ይስፈን) ወደ መልእክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መጥቶ ስለ ዲን ደረጃዎች ማለትም ኢስላም፣ ኢማንና ኢሕሳንን በማስመልከት ጠየቃቸው። የአላህ መልዕክተኛም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ለጥያቄዎቹ መልስ ሰጥተው ለባልደረቦቻቸውም የመጣው ጂብሪል የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንደሆነና የመጣውም

ዲናቸውን ሊያስተምራቸው እንደነበር ነገሯቸው። ይሀው ነው አላህ በጂብሪል አማካኝነት በሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መልዕክተኝነት ወደ ሰው ልጆች የላከውና ከእርሳቸውም በኋላ የነብዩ ሱሓቦች ያሰራጩት እስልምና ማለት ይሀው ነው።

ሁለተኛ: በመላእክቶች ማመን ሲሆን እነርሱም በማይዳሰሰው አለም ያሉ አላህ የተወሰነ ሁኔታን አላብሶ የፈጠራቸው፤ የታላላቅ ሥራዎች ኋላፊነትም የሰጣቸው ናቸው። ከእነዚህ ታላላቅ የስራ ኋላፊነታቸው መካከልም መለኮታዊ ተልእኮን ወደ ነብያቶችና ረሱሎች ማድረሳቸው፤ ከመላእክቶችም እጅግ የተከበረው መላኢካው ጂብሪል የአላህ ሰላም በእርሱ ላይ ይስፈን ነው። ጂብሪል የአላህ ሰላም በእርሱ ላይ ይስፈን መለኮታዊ ወሕይ ይዞ ወደ መልእክተኞች ሲወርድ እንደነበር ከሚያመላክቱ ማስረጃዎች መካከል ተከታዩን የአላህ ቃል መጥቀስ ይቻላል፡-

{يُنَزِّلُ الْمَلَائِكَةَ بِالرُّوحِ مِنْ أَمْرِهِ عَلَىٰ مَن يَشَاءُ مِنْ عِبَادِهِ أَنْ أَنذِرُوا أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنَا فَاتَّقُونِ}

{ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ መላእክትን ከራእይ ጋር በፈቃዱ ያወርዳል (ከሓዲዎችን በቅጣት) አስጠንቅቁ፤ እነሆ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ ፍሩኝም ማለትን (አስታውቁ በማለት ያወርዳል)።} [ነሕል: 2] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَإِنَّهُ لَتَنزِيلُ رَبِّ الْعَالَمِينَ (192) نَزَلَ بِهِ الرُّوحُ الْأَمِينُ (193) عَلَىٰ قَلْبِكَ لِتَكُونَ مِنَ الْمُنذِرِينَ (194) بِلِسَانٍ عَرَبِيٍّ مُّبِينٍ (195) وَإِنَّهُ لَفِي زُبُرِ الْأَوَّلِينَ (196) }

{እርሱም (ቁርኣን) በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው።}

{እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) አወረደው}

{ከአስፈራሪዎቹ (ነቢያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)።}

{ግልጽ በኾነ ዐረብኛ ቋንቋ።}

{እርሱም (ቁርኣን) በቀድሞዎቹ መጻሐፍት ውስጥ (የተወሳ ነው)።} [አሽ-ሹዓራእ: 192-196]

ሶስተኛ: እንደ ተውራት፣ ኢንጂል፣ ዘቡር - ከመዛባታቸው በፊት - ባሉ መለኮታዊ መጻሕፍት ማመን እና በቁርአን ማመን፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا آمِنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ وَالْكِتَابِ الَّذِي نَزَّلَ عَلَىٰ رَسُولِهِ وَالْكِتَابِ الَّذِي أَنزَلَ مِن قَبْلُ ۚ وَمَن يَكْفُرْ بِاللَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَالًا بَعِيدًا}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ። በአላህና በመላእክቱም፣ በመጽሐፎቹም፣ በመልክተኞቹም፣ በመጨረሻውም ቀን፣ የካደ ሰው (ከእውነት) የራቀን

መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።} [ኒሳእ: 136] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{نَزَّلَ عَلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ وَأَنزَلَ التَّوْرَاةَ وَالْإِنجِيلَ (3) مِن قَبْلُ هُدًى لِّلنَّاسِ وَأَنزَلَ الْفُرْقَانَ ۗ إِنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا بِآيَاتِ اللَّهِ لَهُمْ عَذَابٌ شَدِيدٌ ۗ وَاللَّهُ عَزِيزٌ ذُو انتِقَامٍ (4) }

{ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት የሚያረጋግጥ ሲኾን መጽሐፉን (ቁርኣንን) ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ። ተውራትንና ኢንጂልንም አውርዷል።}

{(ከቁርኣን) በፊት ለሰዎች መሪ አድርጎ (አወረዳቸው)። ፉርቃንንም አወረደ። እነዚያ በአላህ ተዓምራቶች የካዱ ለእነርሱ ብርቱ ቅጣት አላቸው። አላህም አሸናፊ የመበቀል ባለቤት ነው።} [አሊ-ዒምራን: 3-4] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡهِ مِن رَّبِّهِۦ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَۚ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّن رُّسُلِهِۦۚ وَقَالُواْ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ غُفۡرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ }

{መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖቹም (እንደዚሁ)። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል አንለይም» (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ። «ሰማን፤ ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም።} [አል-በቀራህ: 285] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{قُلۡ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَمَآ أُنزِلَ عَلَيۡنَا وَمَآ أُنزِلَ عَلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَ وَٱلۡأَسۡبَاطِ وَمَآ أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَٱلنَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمۡ لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّنۡهُمۡ وَنَحۡنُ لَهُۥ مُسۡلِمُونَ}

{«በአላህ አመንን። በእኛ ላይ በተወረደውም (በቁርኣን)፣ በኢብራሂምና በኢስማዒልም፣ በኢስሓቅም፣ በያዕቆብም፣ በነገዶችም ላይ በተወረደው፤ ለሙሳና ለዒሳም ለነቢያትም ሁሉ ከጌታቸው በተሰጠው (አመንን)። ከእነርሱ መካከል አንድንም አንለይም። እኛ ለእርሱ ታዛዦች ነን» በል።} [አሊ-ዒምራን 84]

አራተኛ: በሁሉም ነብያቶችና መልእክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም ማመን። በሁሉም ነብያቶችና መልእክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም ማመን፤ ሁሉም ነብያቶችና ረሱሎችም ከአላህ የተሰጣቸውን ተልእኮ፣ ሃይማኖትና ድንጋጌ ለማድረስ ወደ ህዝቦቻቸው የተላኩ መሆናቸውንም ማመን ግዴታ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ قُولُوا آمَنَّا بِاللَّهِ وَمَا أُنزِلَ إِلَيْنَا وَمَا أُنزِلَ إِلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ وَالْأَسْبَاطِ وَمَا أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَمَا أُوتِيَ النَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ }

{«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም

ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ።} [አል-በቀራህ: 136] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ آمَنَ الرَّسُولُ بِمَا أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِ وَالْمُؤْمِنُونَ ۚ كُلٌّ آمَنَ بِاللَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن رُّسُلِهِ ۚ وَقَالُوا سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا ۖ غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ الْمَصِيرُ }

{መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖቹም (እንደዚሁ)። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል አንለይም» (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ። «ሰማን፤ ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም።} [አል-በቀራህ: 285] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ قُلْ آمَنَّا بِاللَّهِ وَمَا أُنزِلَ عَلَيْنَا وَمَا أُنزِلَ عَلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ وَالْأَسْبَاطِ وَمَا أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَالنَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ }

{«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ።} [አሊ-ዒምራን 84]

እንዲሁም በመደምደሚያቸውም ነብይ ማመን፤ ይህም የአላህ መልእክተኛ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የነቢያት እና የመልክተኞች ሁሉ

መደምደሚያ መሆናቸውንም ማመን ግዴታ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ إِذۡ أَخَذَ ٱللَّهُ مِيثَٰقَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ لَمَآ ءَاتَيۡتُكُم مِّن كِتَٰبٖ وَحِكۡمَةٖ ثُمَّ جَآءَكُمۡ رَسُولٞ مُّصَدِّقٞ لِّمَا مَعَكُمۡ لَتُؤۡمِنُنَّ بِهِۦ وَلَتَنصُرُنَّهُۥۚ قَالَ ءَأَقۡرَرۡتُمۡ وَأَخَذۡتُمۡ عَلَىٰ ذَٰلِكُمۡ إِصۡرِيۖ قَالُوٓاْ أَقۡرَرۡنَاۚ قَالَ فَٱشۡهَدُواْ وَأَنَا۠ مَعَكُم مِّنَ ٱلشَّٰهِدِينَ}

{አላህ የነቢያትን ቃል ኪዳን ከመጽሐፍና ከጥበብ ሰጥቻችሁ ከዚያም «ከእናንተ ጋር ላለው (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ መልክተኛ ቢመጣላችሁ በርሱ በእርግጥ እንደምታምኑበት በእርግጥም እንድትረዱት ሲል በያዘ ጊዜ (አስታውስ)። አረጋገጣችሁን በዚህም ላይ ኪዳኔን ያዛችሁምን» አላቸው። «አረጋገጥን» አሉ። «እንግዲያስ መስክሩ፤ እኔም ከእናንተ ጋር ከመስካሪዎቹ ነኝ» አላቸው።} [አሊ-ዒምራን 81]

እስልምና በሁሉም ነብያቶችና መልእክተኞች ማመንን እንዲሁም በመደምደሚያቸው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ማመንን ግዴታ አድርጓል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ يَا أَهْلَ الْكِتَابِ لَسْتُمْ عَلَىٰ شَيْءٍ حَتَّىٰ تُقِيمُوا التَّوْرَاةَ وَالْإِنجِيلَ وَمَا أُنزِلَ إِلَيْكُم مِّن رَّبِّكُمْ }

{«እናንተ የመጽሓፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታችሁም ወደእናንተ የተወረደውን እስከምታቆሙ (እስከምትሠሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም» በላቸው።} [አል-ማኢዳህ: 68] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ قُلْ يَا أَهْلَ الْكِتَابِ تَعَالَوْا إِلَىٰ كَلِمَةٍ سَوَاءٍ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا اللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِ شَيْئًا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضًا أَرْبَابًا مِّن دُونِ اللَّهِ ۚ فَإِن تَوَلَّوْا فَقُولُوا اشْهَدُوا بِأَنَّا مُسْلِمُونَ }

{የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ። (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው። እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው።} [አሊ-ዒምራን 64]

እንዲሁም በአንድም ነቢይ የካደ ደግሞ በነቢያት እና በመልክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም ሁሉ እንደካደ ነው። ለዚህም ነው አላህ በኑሕ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ህዝቦች ላይ የሰጠውን ፍርድ በማስመልከት እንዲህ ብሏል፡-

{ كَذَّبَتْ قَوْمُ نُوحٍ الْمُرْسَلِينَ }

{የኑሕ ሕዝቦች መልክተኞችን አስተባበሉ።} [አሽ-ሹዓራእ: 105] እንደሚታወቀው ነብዩሏህ ኑሕ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አንድም መልዕክተኛ አልቀደማቸውም። ነገር ግን ህዝባቸው እርሳቸውን ሲክዱ ይህ መካድ ነብያትንና መልክተኞችን ሁሉ መካድ ነበር። ምክንያቱም ጥሪያቸው አንድ ስለሆነ ግባቸውም አንድ ስለሆነ ነው።

አምስተኛ: የትንሣኤ ቀን በሆነው በመጨረሻው ቀን ማመን፤ በዚህ ዓለማዊ ሕይወት ፍፃሜ ላይ አላህ

መላኢካውን ኢስራፊልን ዐለይሂ ሰላም የድንጋጤ መለከት (ጥሩንባ) እንዲነፋ ያዝዛል፤ በዚያችም ድምፅ አማካኝነት አላህ እንዲቆይ ከሻለት በቀር ሁሉም በድንጋጤ ይሞታል።

{ وَنُفِخَ فِي الصُّورِ فَصَعِقَ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَمَن فِي الْأَرْضِ إِلَّا مَن شَاءَ اللَّهُ ۖ ثُمَّ نُفِخَ فِيهِ أُخْرَىٰ فَإِذَا هُمْ قِيَامٌ يَنظُرُونَ }

{በቀንዱም ይንነፋል። በሰማያት ውስጥ ያለው ፍጡርና በምድርም ውስጥ ያለው ፍጡር ሁሉ አላህ የሻው ሲቀር በድንጋጤ ይሞታል። ከዚያም በእርሱ ሌላ (መንነፋት) ይንነፋል። ወዲያውም እነርሱ (የሚሠራባቸውን) የሚጠባበቁ ኾነው ቋሚዎች ይኾናሉ።} [አዝ-ዙመር: 68] በሰማያት ሆነ በምድርም ያለው ሁሉ አላህ ከሻው በቀር በጠፋ ጊዜ አላህ ሰማያትንና ምድርንም ይጠቀልላል። ልክ በተከታዩ አንቀፅ እንዲህ እንዳለን፦

{يَوْمَ نَطْوِي السَّمَاءَ كَطَيِّ السِّجِلِّ لِلْكُتُبِ ۚ كَمَا بَدَأْنَا أَوَّلَ خَلْقٍ نُّعِيدُهُ ۚ وَعْدًا عَلَيْنَا ۚ إِنَّا كُنَّا فَاعِلِينَ }

{ለመጽሐፎች የኾኑ ገጾች እንደሚጠቀለሉ ሰማይን የምንጠቀልልበትን ቀን (አስታውስ)። የመጀመሪያን ፍጥረት እንደ ጀመርን እንመልሰዋለን። (መፈጸሙ) በእኛ ላይ የኾነን ቀጠሮ ቀጠርን። እኛ (የቀጠርነውን) ሠሪዎች ነን።} [አል-አንቢያእ: 104] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَمَا قَدَرُوا اللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِ وَالْأَرْضُ جَمِيعًا قَبْضَتُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ وَالسَّمَاوَاتُ مَطْوِيَّاتٌ بِيَمِينِهِ ۚ سُبْحَانَهُ وَتَعَالَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ }

{አላህንም በትንሣኤ ቀን ምድር በመላ ጭብጡ ስትኾን፤ ሰማያትም በኀይሉ የሚጠቀለሉ ሲኾኑ (ከርሱ ጋር

ሌላን በማጋራታቸው) ተገቢ ክብሩን አላከበሩትም። ከሚያጋሩት ጠራ፤ ላቀም።} [አዝ-ዙመር: 67] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«يطْوِي اللهُ عَزَّ وَجَلَّ السَّمَاوَاتِ يَوْمَ الْقِيَامَةِ ثُمَّ يَأْخُذُهُنَّ بِيَدِهِ الْيُمْنَى ثُمَّ يَقُولُ: أَنَا الْمَلِكُ أَيْنَ الْجَبَّارُونَ؟ أَيْنَ الْمُتَكَبِّرُونَ. ثُمَّ يَطْوِي الْأَرَضِينَ بِشِمَالِهِ ثُمَّ يَقُولُ: أَنَا الْمَلِكُ أَيْنَ الْجَبَّارُونَ؟ أَيْنَ الْمُتَكَبِّرُونَ؟»

"ልእለ ኋያሉ አላህ ሰማያትን ይጠቀልልና በቀኝ እጁ ይዞ: "እኔ ነኝ ንጉስ እብሪተኞቹ የት አሉ? ኩራተኞቹ የት አሉ?" ይላል። ከዚያም ምድሮቹንም በግራ እጁ ይጠቀልልና: "እኔ ነኝ ንጉስ እብሪተኞቹ የት አሉ? ኩረተኞቹስ የት አሉ?" ይላል። ሙስሊም ዘግበውታል

ከዚያም መላኢካውን ያዘውና መላኢካውም በድጋሚ ጥሩንባውን ይነፋል፤ ወዲያውም እነርሱ (የሚሠራባቸውን) የሚጠባበቁ ሆነው ቋሚዎች ይሆናሉ። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ثُمَّ نُفِخَ فِيهِ أُخْرَىٰ فَإِذَا هُمْ قِيَامٌ يَنظُرُونَ}

{ከዚያም በእርሱ ሌላ (መንነፋት) ይነፋል። ወዲያውም እነርሱ (የሚሠራባቸውን) የሚጠባበቁ ኾነው ቋሚዎች ይኾናሉ።} [አዝ-ዙመር: 68] አላህ ፍጥረታትን ከሞት ካስነሳቸው በኋላ ለሂሳብ ይሰበስባቸዋል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَوْمَ تَشَقَّقُ الْأَرْضُ عَنْهُمْ سِرَاعًا ذَٰلِكَ حَشْرٌ عَلَيْنَا يَسِيرٌ}

{የሚፈጥኑ ኾነው ምድር ከእነርሱ ላይ የምትሰነጣጠቅበት ቀን (የመውጫው ቀን ነው)። ይህ በእኛ ላይ ገር የኾነ መሰብሰብ ነው።} [ቃፍ: 44] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَوْمَ هُم بَارِزُونَ ۖ لَا يَخْفَىٰ عَلَى اللَّهِ مِنْهُمْ شَيْءٌ ۚ لِّمَنِ الْمُلْكُ الْيَوْمَ ۖ لِلَّهِ الْوَاحِدِ الْقَهَّارِ }

{እነርሱ (ከመቃብር) በሚወጡበት ቀን በአላህ ላይ ከእነርሱ ምንም ነገር አይደበቅም። «ንግሥናው ዛሬ ለማን ነው?» (ይባላል፤)። «ለአሸናፊው ለአንዱ አላህ ብቻ ነው» (ይባላል)።} [ጋፊር: 16] በዚህ ቀን የላቀው አላህ በሰዎች ሁሉ ላይ ይፈርዳል፤ የተጨቆኑ ሁሉ የጨቆነው አካል ይበቀላል (በደሉን ያካክሳል)፤ እያንዳንዱም በሰራው ይመነዳል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ الْيَوْمَ تُجْزَىٰ كُلُّ نَفْسٍ بِمَا كَسَبَتْ ۚ لَا ظُلْمَ الْيَوْمَ ۚ إِنَّ اللَّهَ سَرِيعُ الْحِسَابِ}

{«ዛሬ ነፍስ ሁሉ በሠራችው ሥራ ትምመነዳለች። ዛሬ በደል የለም። አላህ በእርግጥ ምርመራው ፈጣን ነው» (ይባላል)።} [ጋፊር: 17] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ اللَّهَ لَا يَظْلِمُ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ ۖ وَإِن تَكُ حَسَنَةً يُضَاعِفْهَا وَيُؤْتِ مِن لَّدُنْهُ أَجْرًا عَظِيمًا}

{አላህ የብናኝን ክብደት ያህል አይበድልም። መልካም ሥራ ብትኾንም ይደራርባታል። ከእርሱም ዘንድ ታላቅን ምንዳ ይሰጣል።} [ኒሳእ: 40] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ

ብሏል፡- {የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል።}

{وَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ شَرًّا يَرَهُ (8)}

{የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል።} [አዝ-ዘልዘላህ 7-8] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَنَضَعُ الْمَوَازِينَ الْقِسْطَ لِيَوْمِ الْقِيَامَةِ فَلَا تُظْلَمُ نَفْسٌ شَيْئًا ۖ وَإِن كَانَ مِثْقَالَ حَبَّةٍ مِّنْ خَرْدَلٍ أَتَيْنَا بِهَا ۗ وَكَفَىٰ بِنَا حَاسِبِينَ}

{በትንሣኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን። ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም። (ሥራው) የሰናፍጬ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርሷን እናመጣታለን። ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ።} [አል-አንቢያእ 47]

ከሞት ከመቀስቀስና በስራ ከመተሳሰብ በኋላ መመንዳት ይከተላል፤ በዚህም በጎን የሰራ የማይጠፋ ዘልአለማዊ ደስታ የሚያገኝ ሲሆን ክፉን የሰራና የካደ ደግሞ ቅጣቱን ያገኛል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{الْمُلْكُ يَوْمَئِذٍ لِّلَّهِ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ ۚ فَالَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ فِي جَنَّاتِ النَّعِيمِ (56) وَالَّذِينَ كَفَرُوا وَكَذَّبُوا بِآيَاتِنَا فَأُولَٰئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ مُّهِينٌ (57) }

{በዚያ ቀን ንግሥናው የአላህ ብቻ ነው። በመካከላቸው ይፈርዳል። እነዚያም ያመኑት መልካም ሥራዎችንም የሠሩት በመደሰቻ ገነቶች ውስጥ ናቸው።}

{እነዚያም የካዱት በአንቀጾቻችንም ያስተባበሉት እነዚያ ለእነርሱ አዋራጅ ቅጣት አላቸው።} [አል-ሐጅ: 56-57] እኛም የዚህች ዓለም ሕይወት ብቸኛ ህይወት ቢሆን ኖሮ

ሕይወትና ሕልውና የከንቱ ከንቱ ይሆን እንደነበር እናውቃለን። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ أَفَحَسِبْتُمْ أَنَّمَا خَلَقْنَاكُمْ عَبَثًا وَأَنَّكُمْ إِلَيْنَا لَا تُرْجَعُونَ }

{«የፈጠርናችሁ ለከንቱ መኾኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁን» (ለከንቱ የፈጠርናችሁ መሰላችሁን)} [አል-ሙእሚኑን: 115]

ስድስተኛ: በቀዷና ቀደር ማመን፤ ይኸውም የላቀው አላህ በዚህ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ የሆነውን እየሆነ ያለውንና ለወደፊትም የሚሆነውን ሁሉ ያውቃል፤ ይህንንም ሁሉ ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት እንደጻፈው ማመን ግዴታ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَعِندَهُ مَفَاتِحُ الْغَيْبِ لَا يَعْلَمُهَا إِلَّا هُوَ ۚ وَيَعْلَمُ مَا فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ ۚ وَمَا تَسْقُطُ مِن وَرَقَةٍ إِلَّا يَعْلَمُهَا وَلَا حَبَّةٍ فِي ظُلُمَاتِ الْأَرْضِ وَلَا رَطْبٍ وَلَا يَابِسٍ إِلَّا فِي كِتَابٍ مُّبِينٍ }

{የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው። ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም። በየብስና በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል። ከቅጠልም አንዲትም አትረግፍም የሚያውቃት ቢኾን እንጅ። ከቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልጽ በኾነው መጽሐፍ ውሰጥ (የተመዘገበ) ቢኾን እንጅ።} [አል-አንዓም: 59] አላህም በነገሩ ሁሉ በዕውቀት ያካበበ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{اللَّهُ الَّذِي خَلَقَ سَبْعَ سَمَاوَاتٍ وَمِنَ الْأَرْضِ مِثْلَهُنَّ يَتَنَزَّلُ الْأَمْرُ بَيْنَهُنَّ لِتَعْلَمُوا أَنَّ اللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ وَأَنَّ اللَّهَ قَدْ أَحَاطَ بِكُلِّ شَيْءٍ عِلْمًا}

{አላህ ያ ሰባትን ሰማያት የፈጠረ ነው። ከምድርም መሰላቸውን (ፈጥሮአል)፤ በመካከላቸው ትእዛዙ ይወርዳል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መኾኑን አላህም በነገሩ ሁሉ በዕውቀት ያካበበ መኾኑን በዕውቀት ያካበበ መኾኑን ታውቁ ዘንድ (ይህንን አሳወቃችሁ)።} [አጦላቅ: 12] እናም የላቀው አላህ ፍላጎት ሆኖ፤ መሽአው ታክሎበት፤ የፈጠረውም አላህ ሆኖ፤ እንዲሁም መንስኤዎቹንም አላህ አመቻችቶ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ ምንም ነገር አይከሰትም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{الَّذِي لَهُ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَلَمْ يَتَّخِذْ وَلَدًا وَلَمْ يَكُن لَّهُ شَرِيكٌ فِي الْمُلْكِ وَخَلَقَ كُلَّ شَيْءٍ فَقَدَّرَهُ تَقْدِيرًا }

{(እርሱ) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና የእርሱ ብቻ የኾነ፣ ልጅንም ያልያዘ፣ በንግሥናውም ተጋሪ የሌለው፣ ነገሩንም ሁለ የፈጠረና በትክክልም ያዘጋጀው ነው።} [አል-ፉርቃን: 2] ለዚህም አላህ ሰዎች የማይደርሱበት የሆነ ድካ የደረሰ ጥበብ አለው፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{حِكْمَةٌ بَالِغَةٌ ۖ فَمَا تُغْنِ النُّذُرُ}

{ሙሉ የኾነች ጥበብ (መጣቻቸው) ግን አስፈራሪዎቹ አያብቃቁም።} [አል-ቀመር: 5] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَهُوَ الَّذِي يَبْدَأُ الْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُ وَهُوَ أَهْوَنُ عَلَيْهِ وَلَهُ الْمَثَلُ الْأَعْلَى فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ}

{እርሱም ያ መፍጠርን የሚጀምር ከዚያም የሚመልሰው ነው። እርሱም (መመለሱ) በእርሱ ላይ በጣም

ገር ነው። ለእርሱም በሰማያትም በምድርም ከፍተኛ ባሕርይ (አንድነትና ለእርሱ ብጤ የሌለው መኾን) አልለው። እርሱም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።} [አር-ሩም: 27] የላቀው አላህ ራሱን በጥበብ የገለፀ ሲሆን ራሱንም አል-ሐኪም ብሎ ጠርቷል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{شَهِدَ اللَّهُ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَالْمَلَائِكَةُ وَأُولُو الْعِلْمِ قَائِمًا بِالْقِسْطِ ۚ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ}

{አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ። መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)። ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። አሸናፊው ጥበበኛው ነው።} [አሊ-ዒምራን 18] የላቀው አላህ ከነብዩ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ጋ በእለተ ትንሳኤ ከአላህ ጋ የሚያደርጉት ቃለ ምልልስ አስመልክቶ እንዲህ ብሎናል፦

{إِن تُعَذِّبْهُمْ فَإِنَّهُمْ عِبَادُكَ ۖ وَإِن تَغْفِرْ لَهُمْ فَإِنَّكَ أَنتَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ}

{«ብትቀጣቸው እነርሱ ባሮችህ ናቸው። ለነርሱ ብትምርም አንተ አሸናፊው ጥበበኛው ነህ» (ይላል)።} [አል-ማኢዳህ: 118] የላቀው አላህ ሙሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንን በጡር ተራራ አጠገብ ሆኖ ባናገራቸው ጊዜ እንዲህ ነበር ያለው።

{يَا مُوسَىٰ إِنَّهُ أَنَا اللَّهُ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ}

{«ሙሳ ሆይ! እነሆ እኔ አሸናፊው ጥበበኛው አላህ ነኝ።} [አን-ነምል: 9]

የተከበረውን ቁርአንንም በጥበብ ገልፆታል፤ እንዲህ ብሏል፦

{الر ۚ كِتَابٌ أُحْكِمَتْ آيَاتُهُ ثُمَّ فُصِّلَتْ مِن لَّدُنْ حَكِيمٍ خَبِيرٍ}

{አ.ለ.ረ (አሊፍ ላም ራ፤ ይህ ቁርኣን) አንቀጾቹ በጥንካሬ የተሰካኩ ከዚያም የተዘረዘሩ የሆነ መጽሐፍ ነው። ጥበበኛ ውስጠ ዐዋቂ ከሆነው ዘንድ (የተወረደ) ነው።} [ሁድ: 1] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ذَٰلِكَ مِمَّا أَوْحَىٰ إِلَيْكَ رَبُّكَ مِنَ الْحِكْمَةِ ۗ وَلَا تَجْعَلْ مَعَ اللَّهِ إِلَٰهًا آخَرَ فَتُلْقَىٰ فِي جَهَنَّمَ مَلُومًا مَّدْحُورًا}

{ይህ ጌታህ ከጥበቡ ወደ አንተ ካወረደው ነገር ነው። ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ አታድርግ የተወቀስክ የተባረርክ ኾነህ በገሀነም ውስጥ ትጣላለህና።} [አል-ኢስራእ: 39]

## 22- ነብያቶች ከአላህ በሚያደርሱት ተልእኳቸው ጥብቆች ናቸው፤ ህሊና ጋ ከሚጋጭም ሆነ ጥሩ ስነምግባር ከማይቀበለውም ነገር ሁሉም የተጠበቁ ናቸው፤ የአላህን ትእዛዞች ለባርያዎቹ የማድረስ ኋላፊነት የተሰጣቸው ነብያቶቹ ናቸው። ነብያቶች ለአላህ ብቻ ካሉት አምላካዊም ሆነ ጌታዊ ማንነት ድርሻ የላቸውም። ይልቅ እነርሱም እንደሌላው ሰው

## ሲሆኑ አላህ ተልእኮውን የሚገልፅላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው።

ነቢያትም ከአላህ የተሰጣቸውን በማስተላለፉ ረገድ ጥብቆች ናቸው፤ ምክንያቱም የላቀው አላህ ነብያቶቹን ሲልክ ከፍጥረታቱ ምርጦቹን መርጦ ነውና የሚልከው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{اللَّهُ يَصْطَفِي مِنَ الْمَلَائِكَةِ رُسُلًا وَمِنَ النَّاسِ ۚ إِنَّ اللَّهَ سَمِيعٌ بَصِيرٌ}

{አላህ ከመላእክት ውስጥ መልክተኞችን ይመርጣል። ከሰዎችም (እንደዚሁ)፤ አላህ ሰሚ ተመልካች ነው።} [አል-ሓጅ: 75] አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰٓ ءَادَمَ وَنُوحٗا وَءَالَ إِبۡرَٰهِيمَ وَءَالَ عِمۡرَٰنَ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ}

{አላህ አደምን፣ ኑሕንም፣ የኢብራሂምንም ቤተሰብ፣ የዒምራንንም ቤተሰብ በዓለማት ላይ መረጠ።} [አሊ-ዒምራን 33] አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ قَالَ يَٰمُوسَىٰٓ إِنِّي ٱصۡطَفَيۡتُكَ عَلَى ٱلنَّاسِ بِرِسَٰلَٰتِي وَبِكَلَٰمِي فَخُذۡ مَآ ءَاتَيۡتُكَ وَكُن مِّنَ ٱلشَّٰكِرِينَ}

{(አላህም) አለው፡- «ሙሳ ሆይ! እኔ በመልክቶቼና በማናገሬ በሰዎች ላይ መረጥኩህ። የሰጡህንም ያዝ። ከአመስጋኞቹም ሁን።»} [አል-አዕራፍ: 144] መልክተኞቹም የአላህ ሰላም በእነርሱ ላይ ይሁን በእነርሱ ላይ የሚወርደው መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) መሆኑን ያውቃሉም እና ደሞ ከወሕዩ ጋ መላእክት ሲወርዱም ይመለከታሉ።

{ عالِمُ الْغَيْبِ فَلَا يُظْهِرُ عَلَىٰ غَيْبِهِ أَحَدًا (26) إِلَّا مَنِ ارْتَضَىٰ مِن رَّسُولٍ فَإِنَّهُ يَسْلُكُ مِن بَيْنِ يَدَيْهِ وَمِنْ خَلْفِهِ رَصَدًا (27) لِّيَعْلَمَ أَن قَدْ أَبْلَغُوا رِسَالَاتِ رَبِّهِمْ وَأَحَاطَ بِمَا لَدَيْهِمْ وَأَحْصَىٰ كُلَّ شَيْءٍ عَدَدًا (28)}

{«(እርሱ) ሩቁን ምስጢር ዐዋቂ ነው። በምስጢሩም ላይ አንድንም አያሳውቅም።»}

{ከመልክተኛ ለወደደው ቢኾን እንጅ (ለሌላ አይገልጽም)። እርሱም ከስተፊቱም ከስተኋላውም ጠባቂዎችን ያደርግለታል።}

{እነርሱ ዘንድ ባለው ነገር ዕውቀቱ የከበበና ነገሩንም ሁሉ በቁጥር ያጠቃለለ ሲኾን የጌታቸውን መልክቶች ያደረሱ መኾናቸውን ያውቅ ዘንድ (ጠባቂ ያደርጋል)።} [አል-ጂን: 26-28] የላቀው አላህ ተልእኮውን እንዲያደርሱ አዟቸዋል፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا الرَّسُولُ بَلِّغْ مَا أُنزِلَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَ ۖ وَإِن لَّمْ تَفْعَلْ فَمَا بَلَّغْتَ رِسَالَتَهُ ۚ وَاللَّهُ يَعْصِمُكَ مِنَ النَّاسِ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الْكَافِرِينَ}

{አንተ መልክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወዳንተ የተወረደውን አድርስ። ባትሠራም መልክቱን አላደረስክም። አላህም ከሰዎች ይጠብቅሃል። አላህ ከሓዲዎችን ሕዝቦች አያቀናምና።} [አል-ማኢዳህ: 67] አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{رُّسُلًا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةُۢ بَعۡدَ ٱلرُّسُلِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمًا}

{ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)። አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።} [አን-ኒሳእ: 165]

መልክተኞቹም ዓለይሂሙ ሰላም አላህን አብዝተው የሚፈሩ በመሆናቸው አላህ ካወረደው ተልእኮ አንዳችም አይቀንሱም አንዳች አይጨምሩምም። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلَوْ تَقَوَّلَ عَلَيْنَا بَعْضَ الْأَقَاوِيلِ (44) لَأَخَذْنَا مِنْهُ بِالْيَمِينِ (45) ثُمَّ لَقَطَعْنَا مِنْهُ الْوَتِينَ (46) فَمَا مِنكُم مِّنْ أَحَدٍ عَنْهُ حَاجِزِينَ (47)}

{በእኛ ላይም ከፊልን ቃላት (ያላልነውን) በቀጠፈ ኖሮ}

{በኀይል በያዝነው ነበር።}

{ከዚያም ከእርሱ የልቡን ሥር (የተንጠለጠለበትን ጅማት) በቆረጥን ነበር።}

{ከእናንተም ውስጥ ከእርሱ ላይ ከልካዮች ምንም አይኖሩም።} [አል-ሓቃህ: 44-47] ኢብኑ ከሢር አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ብለዋል፡- ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡- ({በእኛ ላይም ከፊልን ቃላት (ያላልነውን) በቀጠፈ ኖሮ}) ማለትም: ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እነርሱ እንደሚሉት በእኛ ላይ ቀጥፎ፤ በተሰጠውም ተልእኮ ውስጥ ቢጨምር ወይንም ቢቀንስ፤ ወይንም ከራሱ ፈጥሮ አንድ ነገር ቢናገርና ወደኛም ቢያሳብብ - የሚያደርጉ አልነበሩም እንጂ - እኛ በቅጣት ባጣደፍናቸው ነበር። ለዚህም ነው አስከትሎ እንዲህ ያለው {በኀይል በያዝነው ነበር።} ስለ ትርጉሙ እንዲህ ተብሏል፡- በቀኝ በተበቀልነው ነበር ማለት ነው፤ ምክንያቱም የቀኝ አያያዝ ብርቱ ነውና። እንዲሁም በቀኙ በኩል በያዝነው ነበር ማለት ነውም ተብሏል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَإِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ ءَأَنتَ قُلۡتَ لِلنَّاسِ ٱتَّخِذُونِي وَأُمِّيَ إِلَٰهَيۡنِ مِن دُونِ ٱللَّهِۖ قَالَ سُبۡحَٰنَكَ مَا يَكُونُ لِيٓ أَنۡ أَقُولَ مَا لَيۡسَ لِي بِحَقٍّۚ إِن كُنتُ قُلۡتُهُۥ فَقَدۡ عَلِمۡتَهُۥۚ تَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِي وَلَآ أَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِكَۚ إِنَّكَ أَنتَ عَلَّٰمُ ٱلۡغُيُوبِ . مَا قُلۡتُ لَهُمۡ إِلَّا مَآ أَمَرۡتَنِي بِهِۦٓ أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبَّكُمۡۚ وَكُنتُ عَلَيۡهِمۡ شَهِيدٗا مَّا دُمۡتُ فِيهِمۡۖ فَلَمَّا تَوَفَّيۡتَنِي كُنتَ أَنتَ ٱلرَّقِيبَ عَلَيۡهِمۡۚ وَأَنتَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ}

አላህም፡- «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን» በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፡ ፡ «ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢየ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብየው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ። ግን አንተ ዘንዳ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዓዋቂ አንተ ብቻ ነህና» ይላል። «በእርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታየንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም። በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጣባበቂ ነበርኩ። ባነሳኸኝም ጊዜ አንተ በነሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ። አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ ዓዋቂ ነህ።» [አል-ማኢዳህ 116-117]

አላህ በነብያቶችና በሩሱሎች የአላህ ሰላትና ሰላም በሁሉም ላይ ይስፈን ካለው ፀጋ ተልእኳቸውን በሚያደርሱበት ማፅናቱ ይገኝበታል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{قَالَ إِنِّي أُشْهِدُ اللَّهَ وَاشْهَدُوا أَنِّي بَرِيءٌ مِمَّا تُشْرِكُونَ (54) مِنْ دُونِهِ فَكِيدُونِي جَمِيعًا ثُمَّ لَا تُنْظِرُونِ (55) إِنِّي تَوَكَّلْتُ عَلَى اللَّهِ رَبِّي وَرَبِّكُمْ مَا مِنْ دَابَّةٍ إِلَّا هُوَ آخِذٌ بِنَاصِيَتِهَا إِنَّ رَبِّي عَلَى صِرَاطٍ مُسْتَقِيمٍ}

{«… ከምታጋሩትም እኔ ንጹሕ መሆኔን መስክሩ» አላቸው። (54) ከእርሱ ሌላ (አማልክትን ከምታጋሩት ንጹህ ነኝ)። ሁላችሁም ሆናችሁ ተንኮልን ሥሩብኝ፤ ከዚያም አታቆዩኝ። (55)}

{«እኔ በጌታዬና በጌታችሁ በአላህ ላይ ተጠጋሁ። በምድር ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም እርሱ አናትዋን የያዛት ብትሆን እንጂ። ጌታዬ (ቃሉም ሥራውም) በቀጥተኛው መንገድ ላይ ነው» (አላቸው)።} [ሁድ 54-56] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَإِن كَادُوا لَيَفْتِنُونَكَ عَنِ الَّذِي أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ لِتَفْتَرِيَ عَلَيْنَا غَيْرَهُ ۖ وَإِذًا
لَّاتَّخَذُوكَ خَلِيلًا (73) وَلَوْلَا أَن ثَبَّتْنَاكَ لَقَدْ كِدتَّ تَرْكَنُ إِلَيْهِمْ شَيْئًا قَلِيلًا
(74) إِذًا لَّأَذَقْنَاكَ ضِعْفَ الْحَيَاةِ وَضِعْفَ الْمَمَاتِ ثُمَّ لَا تَجِدُ لَكَ عَلَيْنَا
نَصِيرًا (75)}

{እነሆ ከዚያም ወደ አንተ ካወረድነው ሌላን በእኛ ላይ ትዋሽ ዘንድ ሊፈትኑህ በእርግጥ ተቃረቡ። ያን ጊዜም ወዳጅ አድርገው በያዙህ ነበር።}

{ባላረጋንህም ኖሮ ወደነሱ ጥቂትን (ዝንባሌ) ልትዘነበል በእርግጥ በተቃረብክ ነበር።}

{ያን ጊዜ የሕይወትን ድርብ (ቅጣት) የሞትንም ድርብ (ቅጣት) ባቀመስንህ ነበር። ከዚያም ላንተ በኛ ላይ ረዳትን አታገኝም ነበር።} [አል-ኢስራእ 73-75] ይህና ከሱ በፊት የነበሩት አንቀጾች ቁርአን ከዓለማት ጌታ የተገለጠ ለመሆኑ ጠቋሚ ማስረጃዎች ናቸው፤ ምክንያቱም ከመልእክተኛው

ሙሐመድ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ቢሆን ኖሮ ይህን መሰሉ ለእሱ የተቅጣጨን ቃላት ባላካተተ ነበር።

ጥራት ይገባውና የላቀው አላህ መልዕክተኛውን ከሰዎች ይጠብቃቸዋልክ፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا الرَّسُولُ بَلِّغْ مَا أُنزِلَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَ ۖ وَإِن لَّمْ تَفْعَلْ فَمَا بَلَّغْتَ رِسَالَتَهُ ۚ وَاللَّهُ يَعْصِمُكَ مِنَ النَّاسِ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الْكَافِرِينَ}

{አንተ መልክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወዳንተ የተወረደውን አድርስ። በትሠራም መልክቱን አላደረስክም። አላህም ከሰዎች ይጠብቅሃል። አላህ ከሓዲዎችን ሕዝቦች አያቀናምና።} [አል-ማኢዳህ: 67] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَاتْلُ عَلَيْهِمْ نَبَأَ نُوحٍ إِذْ قَالَ لِقَوْمِهِ يَا قَوْمِ إِن كَانَ كَبُرَ عَلَيْكُم مَّقَامِي وَتَذْكِيرِي بِآيَاتِ اللَّهِ فَعَلَى اللَّهِ تَوَكَّلْتُ فَأَجْمِعُوا أَمْرَكُمْ وَشُرَكَاءَكُمْ ثُمَّ لَا يَكُنْ أَمْرُكُمْ عَلَيْكُمْ غُمَّةً ثُمَّ اقْضُوا إِلَيَّ وَلَا تُنظِرُونِ}

{የኑሕንም ወሬ በእነሱ ላይ አንብብላቸው። ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። «ሕዝቦቼ ሆይ! በእናንተ ውስጥ ብዙ ጊዜ መቆየቴ በአላህም ተዓምራት ማስታወሴ በእናንተ ላይ የከበደ ቢሆን፤ በአላህ ላይ ተጠግቻለሁ። ነገራችሁንም ከምታጋሩዋቸው (ጣዖታት) ጋር ሆናችሁ ቁረጡ። ከዚያም ነገራችሁ በእናንተ ላይ ድብቅ አይሁን (ግለጹት)። ከዚያም (የሻችሁትን) ወደእኔ አድርሱ። ጊዜም አትስጡኝ (ከምንም አልቆጥራችሁም)።»} [ዩኑስ: 71] ከፍ ያለው አላህ ነብዩሏህ ሙሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ለህዝባቸው ስላሏቸው ሲነግረን እንዲህ ብሏል፦ {«ጌታችን ሆይ! እኛ

በእኛ ላይ ክፋት በመሥራት መቸኮሉን ወይም ኩራትን መጨመሩን እንፈራለን» አሉ። (አላህም) አለ «አትፍሩ። እኔ በእርግጥ ከእናንተ ጋር ነኝና። እሰማለሁ፤ አያለሁም።} [ጧሀ: 45-46] የላቀው አላህ እርሱ ነብያቶቹንና መልዕክተኞቹን ጠላቶቻቸው ክፋትን እስከማያደርሱባቸው ድረስ እነርሱን እንደሚጠብቃቸው ግልፅ አደረገ። ጥራት የተገባውና የላቀው አላህ ያወረደው መልእክት (ወሕይም) እንዲሁ ጭማሪና ቅናሽ በማይደረግበት ልክ ጥበቃ እንደሚያደርለትም ነግሮናል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ}

{ቁርኣኑን እኛ ነው ያወረድነው፣እኛ ለሱ ጠባቂዎች ነን} [አል-ሒጅር: 9]

ነብያቶች ዓለይሂሙ ሰላም ህሊናንም ሆነ መልካም ስነምግባርን ከሚጣረስ ነገር ሁሉ የተጠበቁ ናቸው። ከፍ ያለው አላህ ነብዩን ሲያጥራራ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَإِنَّكَ لَعَلَى خُلُقٍ عَظِيمٍ}

{አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።} [አል-ቀለም: 4] ስለ እርሳቸው እንዲህም ብሏል፡-

{وَمَا صَاحِبُكُم بِمَجْنُونٍ}

{ነቢያችሁም በፍጹም ዕብድ አይደለም።} [አት-ተክዊር: 22] ይህም የሆነው ነብያቶቹ ዓለይሂሙ ሰላም ተልእኳቸውን ጥሩ በሆነ መልኩ በሚገባ ሊወጡ ዘንድ ነው። ነብያቶች ዓለይሂሙ ሰላም የተሰጣቸውን አምላካዊ

ተልእኳቸውን ላባርያዎቹ ከማርድስ ውጭ መለኮታዊም ይሁን አምላካዊ ድርሻ ኖሯቸው አይደለም። ይልቅ እነርሱ ማለት ልክ እንደ ሌላው የሰው ልጅ ብቻ ናቸው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قَالَتْ لَهُمْ رُسُلُهُمْ إِن نَّحْنُ إِلَّا بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ وَلَٰكِنَّ اللَّهَ يَمُنُّ عَلَىٰ مَن يَشَاءُ مِنْ عِبَادِهِ ۖ وَمَا كَانَ لَنَا أَن نَّأْتِيَكُم بِسُلْطَانٍ إِلَّا بِإِذْنِ اللَّهِ ۚ وَعَلَى اللَّهِ فَلْيَتَوَكَّلِ الْمُؤْمِنُونَ}

{መልክተኞቻቸው ለእነርሱ አሉ «እኛ ብጤያችሁ ሰው እንጂ ሌላ አይደለንም ግን አላህ ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ ይለግሳል። ለእኛም በአላህ ፈቃድ እንጂ ማስረጃን ልናመጣላችሁ አይገባንም። በአላህም ላይ ምእምናኖች ይጠጉ።} [ኢብራሂም: 11] የላቀው አላህ መልእክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ህዝባቸውን እንዲህ እንዲሉ ሲያዝ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ إِنَّمَا أَنَا بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰ إِلَيَّ أَنَّمَا إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَاحِدٌ ۖ فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَالِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا}

{«እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ። የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ። በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» በላቸው።} [አል-ከህፍ: 110]

## 23- እስልምና በታላላቅ መሰረቶች ባላቸው አምልኮ አላህን በብቸኝነት ወደ ማምለከ ጥሪ ያደርጋል፤ እነኝህም፦ ሶላት እርሷም መቆምና

**ማጎብደድ በግንባር መደፋትም (ሱጁድ) አላህን ማወደስና መማፀንንም ያካተተች ስትሆን በየዕለቱ እያንዳንዱ ግለሰብ አምስት ጊዜ የሚሰግዳት እንዲሁም በሰው ልጆች መካከል ያሉ ልዩነቶችንም የምታስወግድ ሃብታሙም ሆነ ድሃው መሪውም ሆነ ተመሪው በአንድ መስመር ገጥመው የሚሰግዷት ግዴታ ነች። ዘካ፡- አላህ ባስቀመጠው ጥቂት የገደብ መጠን በአመት አንድ ጊዜ ከሃብታም ንብረት ተቀንሶ ለድሃውና ለመሳሰሉት የምትሰጥ ግዴታ ነች። ፆም፡- በወርሃ ረመዷን የቀኑ ክፍለ ጊዜ ፆምን ከሚያፈርሱ ነገሮች ታቅቦ መዋል ሲሆን ነፍስን፣ ፍላጎትንና ትእግስትን የሚያሰለጥን ነው። ሐጅ፡- አቅም ባለው ሰው ላይ ሁሉ በእድሜ ልክ አንድ ጊዜ በተከበረው መካ የሚገኘውን የአላህን ቤት መጎብኘት ሲሆን በዚህ በስርአተ ሐጅ ሁሉም ወደ ፈጣሪ በመቅጣጨት እኩል በመሆናቸው ልዩነቶች እና መኮፈሻዎች ሁሉ ይወገዳሉ።**

እስልምና ታላላቅ በሆኑትም ሆነ በሌሎቹ አምልኮዎች አላህን ብቻ ወደ ማምለክ ነው ጥሪ የሚያደርገው። እነኝህን

ታላላቅ አምልኮዎች በሁሉም ነብያቶቹና መልዕክተኞቹ ዓለይሂሙ ሰላም ላይ ነው ግዴታ ያደረጋት። ከነኝህም ታላላቅ አምልኮዎች መካከል:-

አንደኛ: ሶላት በሌሎቹ ነብያቶችና መልዕክተኞችም ዓለይሂሙ ሶላቱ ወሰላም እንደተደገነገችው ሁሉ በeኛም ላይ የተደነገገች ግዴታ ነች። አላህ የeርሱ "ኸሊል" የሆነውን ወዳጁን ነብዩ ኢብራሂም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የአላህን ቤት ካዕባ ለዘዋሪዎች (ጠዋፍ አድራጊዎች) እና ለአጎንባሾችም ለሰጋጆችም እንዲያጠሩ አዟቸዋል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَإِذْ جَعَلْنَا الْبَيْتَ مَثَابَةً لِّلنَّاسِ وَأَمْنًا وَاتَّخِذُوا مِن مَّقَامِ إِبْرَاهِيمَ مُصَلًّى ۖ وَعَهِدْنَا إِلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ أَن طَهِّرَا بَيْتِيَ لِلطَّائِفِينَ وَالْعَاكِفِينَ وَالرُّكَّعِ السُّجُودِ}

{ቤቱንም ለሰዎች መመለሻና ጸጥተኛ ባደረግን ጊዜ (አስታውስ)። ከኢብራሂምም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ። ወደ ኢብራሂምና ወደ ኢስማዒልም ቤቴን ለዘዋሪዎቹና ለተቀማጮቹም ለአጎንባሾች ሰጋጆቹም አጥሩ ስንል ቃል ኪዳን ያዝን።} [አል-በቀራህ: 125] በሙሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ላይ ገና በመጀመርያው ጥሪ ነው ግዴታ ያደረገባቸው፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ إِنِّي أَنَا رَبُّكَ فَاخْلَعْ نَعْلَيْكَ ۖ إِنَّكَ بِالْوَادِ الْمُقَدَّسِ طُوًى (12) وَأَنَا اخْتَرْتُكَ فَاسْتَمِعْ لِمَا يُوحَىٰ (13) إِنَّنِي أَنَا اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنَا فَاعْبُدْنِي وَأَقِمِ الصَّلَاةَ لِذِكْرِي (14) }

{«እኔ ጌታህ እኔ ነኝ መጫሚያዎችህንም አውልቅ። አንተ በተቀደሰው ሸለቆ በጡዋ ነህና።}

{«እኔም መረጥኩህ፤ የሚወረድልህንም ነገር አዳምጥ።}

{«እኔ አላህ እኔ ነኝ ያለ እኔ አምላክ የለምና ተገዛኝ። ሶላትንም (በእርሷ) እኔን ለማውሳት ስገድ።} 14 [ጧሃ 12-14] መሲሑ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንም አላህ በሶላትና በዘካ እንዳዘዛቸው ተናግሯል፤ ልክ የላቀው አላህ እንደነገረን፦

{ وَجَعَلَنِي مُبَارَكًا أَيْنَ مَا كُنتُ وَأَوْصَانِي بِالصَّلَاةِ وَالزَّكَاةِ مَا دُمْتُ حَيًّا }

{«በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ አድርጎኛል። በሕይወትም እስካለሁ ሶላትን በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል።»} [መርየም: 31] ሶላት በእስልምና እያንዳንዱ በነፍስ ወከፍ ደረጃ በመቆም፣ በሩኩዕ (ማጎብደድ) እና በሱጁድ (በግንባር መደፋት)፤ አላህን በማውሳትና በማወደስ፤ አላህን በመማፀን በቀን አምስቴ የሚፈፅመው የፀሎት ስርአት ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ حَافِظُوا عَلَى الصَّلَوَاتِ وَالصَّلَاةِ الْوُسْطَىٰ وَقُومُوا لِلَّهِ قَانِتِينَ }

{በሶላቶች (በተለይ) በመካከለኛይቱም ሶላት ላይ ተጠባበቁ። ታዛዦች ኾናችሁም ለአላህ ቁሙ።} [አል-በቀራህ: 238] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦ {ሶላትን ከፀሐይ መዘንበል እስከ ሌሊት ጨለማ ድረስ ስገድ። የጎህንም ሶላት ስገድ። የጎህ ሶላት (መላእክት) የሚጣዱት ነውና።} [አል-

ኢስራእ: 78] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

(فَأَمَّا الرُّكُوعُ فَعَظِّمُوا فِيهِ الرَّبَّ عَزَّ وَجَلَّ وَأَمَّا السُّجُودُ فَاجْتَهِدُوا فِي الدُّعَاءِ فَقَمِنٌ أَنْ يُسْتَجَابَ لَكُمْ)

(በሩኩዕ ላይ ስትሆኑ ልእለ ኋያሉ አላህን አልቁ፤ በሱጁድ ስትሆኑ ግን በዱዓእ ተበራቱ ዱዓችሁ ተቀባይነት የማግኘት እድሉ ሰፊ ነውና።) ሰሒሕ ሙስሊም

ሁለተኛ: ዘካ በሌሎቹ ቀደምት ነብያቶችና መልዕክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም እንደተደረገችው ሁሉ በእኛም ላይ ግዴታ ሆናለች። እርሷም -አላህ በወሰናት መልኩ የተገደበች- ጥቂት የሆነች የገንዘብ መጠን ከሀብታሙ ገንዘብ ተቀንሳ ለድሀውና ለመሳሰሉት በአመት አንዴ የምትሰጥ ገንዘብ ነች። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ خُذْ مِنْ أَمْوَالِهِمْ صَدَقَةً تُطَهِّرُهُمْ وَتُزَكِّيهِم بِهَا وَصَلِّ عَلَيْهِمْ ۖ إِنَّ صَلَاتَكَ سَكَنٌ لَّهُمْ ۗ وَاللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ }

{ከገንዘቦቻቸው ስትኾን በእርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የኾነችን ምጽዋት ያዝ። ለነሱም ጸልይላቸው። ጸሎትህ ለእነሱ እርጋታ ነውና አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።} [አት-ተውባህ: 103] ነብያችን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሙዓዝን ወደ የመን በሚልኩበት ጊዜ እንዲህ ብለውታል፡-

«إِنَّكَ تَأْتِي قَوْمًا أَهْلَ كِتَابٍ فَادْعُهُمْ الَى شَهَادَةِ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَأَنِّي رَسُولُ اللهِ فَإِنْ هُمْ أَطَاعُوكَ لِذَلِكَ فَأَعْلِمْهُمْ أَنَّ اللهَ عَزَّ وَجَلَّ افْتَرَضَ عَلَيْهِمْ خَمْسَ صَلَوَاتٍ فِي كُلِّ يَوْمٍ وَلَيْلَةٍ فَإِنْ أَطَاعُوا لِذَلِكَ فَأَعْلِمْهُمْ أَنَّ اللهَ عَزَّ وَجَلَّ افْتَرَضَ عَلَيْهِمْ صَدَقَةً فِي أَمْوَالِهِمْ تُؤْخَذُ مِنْ أَغْنِيَائِهِمْ وَتُرَدُّ فِي فُقَرَائِهِمْ فَإِنْ

هُمْ أَطَاعُوكَ لِذَلِكَ فَإِيَّاكَ وَكَرَائِمَ أَمْوَالِهِمْ وَاتَّقِ دَعْوَةَ الْمَظْلُومِ فَإِنَّهَا لَيْسَ بَيْنَهَا وَبَيْنَ اللهِ عَزَّ وَجَلَّ حِجَابٌ»

"አንተ የምትሄድባቸው ሰዎች ከመጽሐፉ ባለቤት ወደሆኑ ህዝቦች ነው፤ በመሆኑም በ "ላ ኢላሃ ኢለሏህ" እና በኔም የአላህ መልዕክተኝነት እንዲመሰክሩ ጥሪ አድርግላቸው፤ ለዚህ ጥሪህ ተገቢውን ምላሽ ከሰጡህ ልእል ኋያሉ አላህ በየቀኑ አምስት ግዜ የምትሰገድ ሶላትን ግዴታ እንዳደረገባቸው አስተምራቸው፤ ለዚሁ ጥሪህም ተገቢውን ምላሽ ከሰጡህ ልእለ ኋያሉ አላህ በገንዘባቸው ላይ ከሀብታሞቻቸው ተይዞ ወደ ድሆቻቸው የምትመለስ የሆነችን ሶደቃ ግዴታ እንዳደረገባቸው አስተምራቸው፤ ለዚህም ተገቢውን ምላሽ ከሰጡህ አደራ ውድ ንብረቶቻቸውን ተጠንቀቅ፣ የተበዳይንም ዱዓእ ተጠንቀቅ ምክንያቱም በዱዓውና በአላህ መካከል ግርዶሽ የሌለበት ዱዓ ነው።" ቲርሚዚይ ዘግበውታል (625)

ሶስተኛ: ፆም የላቀው አላህ በቀደምት ነብያቶችና መልዕክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም ግዴታ እንዳደረገው ሁሉ በእኛም ላይ ግዴታ አድርጎታል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።} [አል-በቀራህ: 183]

ይኸውም: በወርሀ ረመዷን የቀኑ ክፍለ ጊዜ ፆምን ከሚያፈርሱ ነገሮች ታቅቦ መዋል ሲሆን፤ ፆም ነፍስን፣ ፍላጎትንም ሆነ ትእግስትን ያሰለጥናል። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«يَقُولُ اللَّهُ عَزَّ وَجَلَّ: الصَّوْمُ لِي وَأَنَا أَجْزِي بِهِ يَدَعُ شَهْوَتَهُ وَأَكْلَهُ وَشُرْبَهُ مِنْ أَجْلِي وَالصَّوْمُ جُنَّةٌ وَلِلصَّائِمِ فَرْحَتَانِ: فَرْحَةٌ حِينَ يُفْطِرُ وَفَرْحَةٌ حِينَ يَلْقَى رَبَّهُ»

"የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል: ፆም ለኔ ነውና እኔው ነኝ የምመነዳበት፤ ለኔው ብሎ ስሜቱን፣ መብሉንና መጠጡን ትቶልኛል፤ ፆም ጋሻ ነው፤ ለፆመኛም ሁለት ደስታ ያለው ሲሆን አንዱ ደስታ ፆሙን በሚያፈጥርበት ጊዜ ሌላኛው ደግሞ ጌታውን በሚገናኝበት ጊዜ ነው።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 7492

አራተኛ: ሐጅ አላህ በቀደምት ነብያቶችና መልዕክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም ላይ ግዴታ እንዳደረገው ሁሉ በእኛም ላይ ግዴታ አድርጎታል፤ ኸሊሉ ኢብራሂም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንን በሐጅ ጥሪ እንዲያደርጉ አላህ እንዲህ በማለት አዟቸዋል፡-

{وَأَذِّن فِي النَّاسِ بِالْحَجِّ يَأْتُوكَ رِجَالًا وَعَلَىٰ كُلِّ ضَامِرٍ يَأْتِينَ مِن كُلِّ فَجٍّ عَمِيقٍ}

{(አልነውም)፡- በሰዎችም ውስጥ በሐጅ ትዕዛዝ ጥራ። እግረኞች ከየሩቅ መንገድ በሚመጡ ከሲታ ግመሎችም ሁሉ ላይ ሆነው ይመጡሃልና።} [አል-ሓጅ: 27] የተከበረውን

ጥንታዊ ቤትን (ካዕባን) ለሐጅ አድራጊዎች እንዲያጠሩላቸው የላቀው አላህ እንዲህ በማለት አዟቸዋል፡-

{وَإِذْ بَوَّأْنَا لِإِبْرَاهِيمَ مَكَانَ الْبَيْتِ أَن لَّا تُشْرِكْ بِي شَيْئًا وَطَهِّرْ بَيْتِيَ لِلطَّائِفِينَ وَالْقَائِمِينَ وَالرُّكَّعِ السُّجُودِ }

{ለኢብራሂምም የቤቱን (የካዕባን) ስፍራ መመለሻ ባደረግንለት ጊዜ «በእኔ ምንንም አታጋራ፤ ቤቴንም ለሚዞሩትና ለሚቆሙበት ለሚያጎነብሱትና በግንባራቸውም ለሚደፉት ንጹሕ አድርግላቸው» (ባልነው ጊዜ አስታውስ)።} [አል ሐጅ 26]

ሐጅ: በተከበረችው መካ በሚገኘው የአላህ ቤት በመዘየር የተወሰኑ ክንውኖች የሚፈፀሙበት አቅም ባለው ሰው ላይ ሁሉ በእድሜ ልክ አንዴ ሊያደርገው ግዴታ የሆነ ስርአት ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلِلَّهِ عَلَى النَّاسِ حِجُّ الْبَيْتِ مَنِ اسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلًا ۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ اللَّهَ غَنِيٌّ عَنِ الْعَالَمِينَ }

{ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው። የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው።} [አሊ-ዒምራን 97] በሐጅ ስርአተ የአለም ሙስሊሞች ሁሉ ዒባዳቸውንም ጥርት ባለ መልኩ ጥራት ለተገባውና ለፈጣሪያቸው ብቻ የሚያደርጉ ሲሆኑ በአንድ ሜዳ ይሰባሰባሉ፤ ሐጅ አድራጊዎች ሁሉ የአምልኮ ስርአታቸውን ወጥ በሆነ መልኩ ማህበራዊና ስልጣኔ እንዲሁም የኑሮ ደረጃ ሳይለያቸው ይፈፅሙታል።

## 24- ኢስላማዊ አምልኮ ከሚለይባቸው መለያዎች መካከል ሁኔታውንም ሆነ ጊዜው ብሎም ቅድመ መስፈርቱን ሁሉ ያስቀመጠው አላህ ሲሆን ያደረሱት ስውግሞ የአላህ ሶለዋትና ሰላም ይስፈንባቸውና መልእክተኛው መሆናቸው ነው። ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬም ድረስ በመጨመሩም ሆነ በመቀነሱ የማንም ጣልቃ ገብነት የለበትም። እነኝህ ከፍ ብለን የጠቀስናቸው ታላላቅ አምልኮዎችም ቢሆኑ ነብያቶችም ሁሉ የተጣሩባቸው አምልኮዎች ናቸው።

ኢስላማዊ አምልኮ ከሚለይባቸው መለያዎች መካከል ሁኔታውንም ሆነ ጊዜውን ብሎም ቅድመ መስፈርቱን ሁሉ ያስቀመጠው አላህ ሲሆን ያደረሱት ደግሞ የአላህ ሶለዋትና ሰላም ይስፈንባቸውና መልእክተኛው መሆናቸው ነው። ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬም ድረስ በመጨመሩም ሆነ በመቀነሱ የማንም ጣልቃ ገብነት የለበትም። እነኝህ ከፍ ብለን የጠቀስናቸው ታላላቅ አምልኮዎችም ቢሆኑ ነብያቶችም ሁሉ የተጣሩባቸው አምልኮዎች ናቸው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ ٱلۡيَوۡمَ أَكۡمَلۡتُ لَكُمۡ دِينَكُمۡ وَأَتۡمَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ نِعۡمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ ٱلۡإِسۡلَٰمَ دِينٗاۚ}

{ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋየንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት

በኩል ወደድኩ።} [አል ማኢዳህ 3] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{فَٱسۡتَمۡسِكۡ بِٱلَّذِيٓ أُوحِيَ إِلَيۡكَۖ إِنَّكَ عَلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ}

{ያንንም ወደ አንተ የተወረደልህን አጥብቀህ ያዝ። አንተ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ነህና።} [አዝ-ዙኽሩፍ: 43] የላቀው አላህ ስለ ሶላት እንዲህ ብሏል፦

{فَإِذَا قَضَيْتُمُ الصَّلَاةَ فَاذْكُرُوا اللَّهَ قِيَامًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِكُمْ ۚ فَإِذَا اطْمَأْنَنتُمْ فَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ ۚ إِنَّ الصَّلَاةَ كَانَتْ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ كِتَابًا مَّوْقُوتًا}

{ሶላትንም በፈጸማችሁ ጊዜ ቆማችሁም ተቀምጣችሁም በጎኖቻችሁም ላይ ተጋድማችሁ አላህን አውሱ። በረጋችሁም ጊዜ ሶላትን (አሟልታችሁ) ስገዱ። ሶላት በምእምናን ላይ በጊዜያት የተወሰነች ግዴታ ናትና።} [አን-ኒሳእ 103] የላቀው አላህ ዘካ የሚሰጣቸውን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

{ إِنَّمَا ٱلصَّدَقَٰتُ لِلۡفُقَرَآءِ وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَٱلۡعَٰمِلِينَ عَلَيۡهَا وَٱلۡمُؤَلَّفَةِ قُلُوبُهُمۡ وَفِي ٱلرِّقَابِ وَٱلۡغَٰرِمِينَ وَفِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱبۡنِ ٱلسَّبِيلِۖ فَرِيضَةٗ مِّنَ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ}

{ግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድኾች፣ ለምስኪኖችም፣ በርሷም ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች፣ ልቦቻቸውም (በእስልምና) ለሚለማመዱት፣ ጫንቃዎችንም (በባርነት ተገዢዎችን) ነጻ በማውጣት፣ በባለ ዕዳዎችም፣ በአላህ መንገድም በሚሠሩ፣ በመንገደኛም ብቻ ነው። ከአላህ የተደነገገች ግዴታ ናት። አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ

ነው።} [አት-ተውባህ: 60] የላቀው አላህ ፆምን በተመለከተ እንዲህ ብሏል፦

{شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡفُرۡقَانِۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُۖ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٖ فَعِدَّةٞ مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۗ يُرِيدُ ٱللَّهُ بِكُمُ ٱلۡيُسۡرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ ٱلۡعُسۡرَ وَلِتُكۡمِلُواْ ٱلۡعِدَّةَ وَلِتُكَبِّرُواْ ٱللَّهَ عَلَىٰ مَا هَدَىٰكُمۡ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ}

{(እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች (አንቀጾች) ሲኾን ቁርኣን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው። ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው። በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የኾነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት። አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል። በእናንተም ችግሩን አይሻም። ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገግንላችሁ)።} [አል-በቀራህ: 185] የላቀው አላህ ሐጅን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

{ٱلۡحَجُّ أَشۡهُرٞ مَّعۡلُومَٰتٞۚ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلۡحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي ٱلۡحَجِّۗ وَمَا تَفۡعَلُواْ مِنۡ خَيۡرٖ يَعۡلَمۡهُ ٱللَّهُۗ وَتَزَوَّدُواْ فَإِنَّ خَيۡرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقۡوَىٰۖ وَٱتَّقُونِ يَٰٓأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ}

{ሐጅ (ጊዜያቱ) የታወቁ ወሮች ናቸው። በእነርሱም ውስጥ ሐጅን (እንዲሠራ) ነፍሱን ያስገደደ ሰው በሐጅ ውስጥ ሴትን መገናኘት ማመጽም ክርክርም የለም። ከበጎም ሥራ የምትሠሩትን ሁሉ አላህ ያውቀዋል። ተሰነቁም፤ ከስንቅም ሁሉ በላጬ ጥንቃቄ (አላህን መፍራት) ነው። የአእምሮዎችም ባለቤቶች ሆይ! ፍሩኝ።} [አል-በቀራህ: 197]

እነኚህ ታላላቅ አምልኮዎች ነብያቶች ሁሉ ጥሪ ያደረጉባቸው አምልኮዎች ናቸው።

## 25- የኢስላምን መልዕክት (ለዚህ ህዝብ ያደረሱት) የኢብራሂም ልጅ ኢስማዒል ዝርያ የሆኑት ነብዩ ሙሐመድ ቢን ዐብደሏህ ናቸው። በመካ እ. ኣ. አ. በ 571 ተልከው እዛው ተልእኮው የተሰጣቸው ሲሆን ወደ መዲና ሂጅራ አድርገዋል (ተሰደዋል)። ህዝባቸውንም በጣኦታዊ ጉዳያቸው አልተጋሯቸውም (ድጋፍ አልሰጡም)። ይልቅ ህዝባቸውን ይደግፉ የነበሩት በታላላቅ ስራዎች ላይ ነበር። ከመላካቸውም በፊት ባማረ ታላቅ ስነምግባር ላይ ነበሩ፤ ህዝቦቻቸውም አል አሚን (ታማኙ) ይሏቸው ነበር፤ እድሜያቸውም አርባ አመት በሞላ ጊዜ አላህ መልዕክተኛው አድርጎ ላካቸውና በታላላቅ ተአምራቶችም አጠነከራቸው፤ ይበልጥ ታላቁ ተዓምር የተከበረው ቁርአን ነው። ይኸውም የቁርአን ተአምርነት ከነብያቶች ተአምር ሁሉ እጅግ በጣም ታላቁ ተአምር ሲሆን ከነብያቶች ተአምር ሁሉ እስከዛሬ ድረስ የዘለቀውም ተአምር እርሱው ነው። አላህ ለእርሳቸው

**ዲኑን ባሟላላቸው ጊዜ መልእክተኛውም ተልእኳቸውን በተሟላ መልኩ ያደረሱ ሆነው እድሜያቸው 63 አመት በሞላ ጊዜ ከዚህ አለም በሞት ተለዩ። በነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከተማ መዲና ተቀበሩ። የአላህ መልእክተኛ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የነብያቶችና የመልእክተኞችም መጨረሻ ሲሆኑ አላህ የሰው ልጆችን ሁሉ ከጣኦታዊ የክህደትና የድንቁርና ጨለማዎች ወደ የተውሒድና የኢማን ብርሃን ሊያወጡ ላካቸው። አላህም በእርሱ ፈቃድ ወደ እርሱ የሚጣሩ መሆናቸው መሰከረላቸው።**

የኢስላምን መልዕክት (ለዚህ ህዝብ ያደረሱት) የኢብራሂም ልጅ ኢስማዒል ዝርያ የሆኑት ነብዩ ሙሐመድ ቢን ዐብደሏህ ናቸው። በመካ እ. ኣ. አ. በ 571 ተልከው እዛው ተልእኮው የተሰጣቸው ሲሆን ወደ መዲና ሂጅራ አድርገዋል (ተሰደዋል)። ህዝባቸውንም በጣኦታዊ ጉዳያቸው አልተጋሯቸውም (ድጋፍ አልሰጡም)። ይልቅ ህዝባቸውን ያግዙ የነበሩት በታላላቅ ስራዎች ነበር። ከመላካቸውም በፊት ባማረ ታላቅ ስነምግባር ላይ ነበሩ፤ ጌታችን አላህ በታላቅ ስነምግባር መሆናቸውን እንዲህ ብሎ ገልጿቸዋል፦

{وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ}

{አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ።} [አል-ቀለም 4] እድሜያቸው አርባ አመት ሲሞላቸው መልዕክተኛ አድርጎ በመላክ በታላላቅ ተአምራቶች አበርትቷቸዋል፤ ከተሰጣቸው እጅግ ታላቁ ተአምር የተከበረው ቁርአን ነው። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«مَا مِنَ الأَنْبِيَاءِ نَبِيٌّ إِلَّا أُعْطِيَ مَا مِثْلُهُ آمَنَ عَلَيْهِ البَشَرُ وَإِنَّمَا كَانَ الَّذِي أُوتِيتُ وَحْيًا أَوْحَاهُ اللَّهُ إِلَيَّ فَأَرْجُو أَنْ أَكُونَ أَكْثَرَهُمْ تَابِعًا يَوْمَ القِيَامَةِ»

«እያንዳንዱ ነቢይ ተአምራት የተሰጠው ሰዎች በሚያምኑለት በኩል ነው፤ እኔን ግን የተሰጠኝ አላህ የገለጠልኝ የሆነው መለኮታዊ መገለጥ (ወሕይ) ነው። ስለዚህም ተከታዮቼ በእለተ ትንሳኤ ከሌሎቹ ነቢያት ተከታዮች እንደሚበልጡ ተስፋ አደርጋለሁ።» ሰሒሑ አልቡኻሪ የተከበረው ቁርአን ከአላህ የሆነ ለመልዕክተኛው የተገለጠው ወሕይ ነው፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ ذَٰلِكَ الْكِتَابُ لَا رَيْبَ ۛ فِيهِ ۛ هُدًى لِّلْمُتَّقِينَ }

{ይህ መጽሐፍ (ከአላህ ለመሆኑ) ጥርጥር የለበትም፤ ለፈራህያን መሪ ነው።} [አል-በቀራህ: 2] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ الْقُرْآنَ ۚ وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ اللَّهِ لَوَجَدُوا فِيهِ اخْتِلَافًا كَثِيرًا}

{ቁርኣንን አያስተነትኑምን ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር።} [አን-ኒሳእ: 82] የላቀው አላህ የሰው ልጆችንና አጋንንቶችንም ጭምር

አምሳያውን ያመጡ እንደሁ ውርርድ አስገባቸው፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{قُل لَّئِنِ اجْتَمَعَتِ الْإِنسُ وَالْجِنُّ عَلَىٰ أَن يَأْتُوا بِمِثْلِ هَٰذَا الْقُرْآنِ لَا يَأْتُونَ بِمِثْلِهِ وَلَوْ كَانَ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ ظَهِيرًا}

{«ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርኣን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢሆንም እንኳ ብጤውን አያመጡም» በላቸው።} [አል-ኢስራእ: 88] ከዚያም ከቁርአን አምሳያ አስር ምእራፎችን ያመጡ ዘንድ በድጋሚ ውርርድ አስገባቸው፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ أَمْ يَقُولُونَ افْتَرَاهُ ۖ قُلْ فَأْتُوا بِعَشْرِ سُوَرٍ مِّثْلِهِ مُفْتَرَيَاتٍ وَادْعُوا مَنِ اسْتَطَعْتُم مِّن دُونِ اللَّهِ إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ }

{ይልቁንም «(ቁርኣንን) ቀጣጠፈው» ይላሉን፡- «እውነተኞች እንደሆናችሁ ብጤው የሆኑን ዐስር የተቀጣጠፉ ሱራዎች አምጡ። ከአላህም ሌላ የቻላችሁትን (ረዳት) ጥሩ» በላቸው።} [ሁድ: 13] ከዚያም ከቁርአን አምሳያ አንዲት ምእራፍን እንኳ ያመጡ ዘንድ ውርርድ አስገባቸው፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡- {በባሪያችንም ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ። እውነተኞችም እንደኾናችሁ ከአላህ ሌላ መስካሪዎቻችሁን ጥሩ።} [አል-በቀራህ: 23]

ከነብያቶች ተአምር ብቸኛው ዘላቂ ሆኖ እስከዛሬ ድረስ በመካከላችን ያለው የተከበረው ቁርአን ነው። የላቀው አላህ ለመልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ

ይሁን) ዲኑን ባሟላላቸውና እርሳቸውም ተልእኳቸውን በሚገባ ከተወጡ በኋላ እድሜያቸው ስድሳ ሶስት ሲሆን ሕይወታቸው አለፈ፤ በነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መዲና ተቀበሩ።

መልዕክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የነብያቶችና የረሱሎች መደምደሚያ ናቸው፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَا أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ اللَّهِ وَخَاتَمَ النَّبِيِّينَ ۗ وَكَانَ اللَّهُ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمًا }

{ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም። ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው። አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው።} [አል-አሕዛብ 40] አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና ከአቡ ሁረይራ በተዘገበ ሓዲሥ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«إِنَّ مَثَلِي وَمَثَلَ الأَنْبِيَاءِ مِنْ قَبْلِي كَمَثَلِ رَجُلٍ بَنَى بَيْتًا فَأَحْسَنَهُ وَأَجْمَلَهُ إِلَّا مَوْضِعَ لَبِنَةٍ مِنْ زَاوِيَةٍ فَجَعَلَ النَّاسُ يَطُوفُونَ بِهِ وَيَعْجَبُونَ لَهُ وَيَقُولُونَ هَلَّا وُضِعَتْ هَذِهِ اللَّبِنَةُ؟ قَالَ: فَأَنَا اللَّبِنَةُ وَأَنَا خَاتِمُ النَّبِيِّينَ»

«ከእኔ በፊት ከነበሩት ነቢያቶች አንፃር የኔ አምሳያ፤ ልክ በአንድ ጥግ ላይ ባለ የአንድ ጡብ ቦታ ብቻ ካልሆነ በቀር በሚያምር እና በተዋበ መልኩ ቤት እንደሠራ ሰው ነው። ሕዝቡ ወደዚያ ሄዶ እያየ ስለቤቱ ውበት በመደነቅ እንዲህ ይላሉ: 'አቤት! ይህ ጡብ በቦታው ቢቀመጥ ኖሮ እንዴት ነበር የሚያምረው!' ይላሉ። ስለዚህም ያ ቀረ የተባለው

ጡብ እኔ ነኝ፤ የነቢያትም መጨረሻቸው እኔ ነኝ።» ሰሒሕ ቡኻሪይ በወንጌልም መሰረት ዒሳ የነብዩን ሙሐመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መምጣት ሲያበስሩ እንዲህ ብለዋል፡- (ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣ የማእዘን ራስ ሆነ፤ ["ኢየሱስም እንዲህ ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን አላነበባችሁምን? አላቸው፤ " 'ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣ የማእዘን ራስ ሆነ፤ እግዚአብሔር ይህን አድርጎአል፤ ሥራውም ለዐይናችን ድንቅ ነው።" ማቴዎስ ወንጌል 21:42] በኦሪት ዘዳግም 18:18 ደግሞ ነብዩሏህ ሙሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸውን እናገኛለን ["ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌን በአፉ አደርጋለሁ፤ የማዘውንም ሁሉ ይነግራቸዋል።")

መልዕክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በቀና መመርያና በትክክለኛ ሃይማኖት አስታጥቆ ነበር የላካቸው፤ አላህም በቀናው ጎዳና ላይ መሆናቸውንና በአላህም ፈቃድ ወደ አላህ የሚጣራ መሆናቸውንም መስክሮላቸዋል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{لَّٰكِنِ اللَّهُ يَشْهَدُ بِمَا أَنزَلَ إِلَيْكَ ۖ أَنزَلَهُ بِعِلْمِهِ ۖ وَالْمَلَائِكَةُ يَشْهَدُونَ ۚ وَكَفَىٰ بِاللَّهِ شَهِيدًا}

{ግን አላህ ባንተ ላይ ባወረደው ይመሰክራል። በዕውቀቱ አወረደው። መላእክቱም ይመሰክራሉ። መስካሪም በአላህ በቃ።} [አን-ኒሳእ 166] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{هُوَ الَّذِي أَرْسَلَ رَسُولَهُ بِالْهُدَىٰ وَدِينِ الْحَقِّ لِيُظْهِرَهُ عَلَى الدِّينِ كُلِّهِ ۚ وَكَفَىٰ بِاللَّهِ شَهِيدًا}

{እርሱ ያ መልክተኛውን በመሪ መጽሐፍና በእውነተኛ ሃይማኖት በሃይማኖት ሁሉ ላይ ሊያልቀው የላከ ነው። መስካሪም በአላህ በቃ።} [አል-ፈትሕ 28] የሰው ልጆችን ከጣኦት፣ ክህደትና ድንቁርና ጨለማ ወደ ተውሒድና ኢማን ብርሀን ሊያወጡ ዘንድ በቀና መመርያ ላካቸው፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሎናል፦

{يَهْدِي بِهِ اللَّهُ مَنِ اتَّبَعَ رِضْوَانَهُ سُبُلَ السَّلَامِ وَيُخْرِجُهُم مِّنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ بِإِذْنِهِ وَيَهْدِيهِمْ إِلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ}

{አላህ ውዴታውን የተከተሉትን ሰዎች የሰላምን መንገዶች በእርሱ ይመራቸዋል። በፈቃዱም ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል። ወደ ቀጥተኛም መንገድ ይመራቸዋል።} [አል-ማኢዳህ 16] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{الر ۚ كِتَابٌ أَنزَلْنَاهُ إِلَيْكَ لِتُخْرِجَ النَّاسَ مِنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ بِإِذْنِ رَبِّهِمْ إِلَىٰ صِرَاطِ الْعَزِيزِ الْحَمِيدِ }

{አ.ለ.ረ (አሊፍ ላም ራ፤ ይህ ቁርአን) ሰዎችን በጌታቸው ፈቃድ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን አሸናፊ ምስጉን ወደ ኾነው። ጌታ መንገድ ታወጣ ዘንድ ወዳንተ ያወረድነው መጽሐፍ ነው።} [ኢብራሂም: 1]

## 26- ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ይዘውት የመጡት የእስልምና ድንጋጌ የአምላካዊ ተልእኮዎችና

**የጌታቻን አላህ ድንጋጌዎች መጨረሻ ነው። ይህችም የሙሉነት ድንጋጌ ስትሆን በውስጧም የሰው ልጆች ዲናዊም ሆነ ዱንያዊ መስተካከል የያዘች ነች። ይህች ሸሪዓ በመጀመርያ ደረጃ የሰው ልጆችን ሃይማኖት፣ ደማቸውንም፣ ንብረታቸውንም፣ አእምሯቸውንም፣ ዝርያቸውንም፣ ትጠብቅላቸዋለች። የቀደሙት ሸሪዓዎች ከፊሉ ከፊሉን ሲሽር እንደነበረው ሁሉ የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሸሪዓም ቀደምት ድንጋጌዎችን ሁሉ የምትሽር ነች።**

ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ይዘውት የመጡት የእስልምና ድንጋጌ የአምላካዊ ተልእኮዎችና የጌታቻን አላህ ድንጋጌዎች መጨረሻ ነው። አላህ ነብዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በላከበት ተልእኮ ነው ዲኑንም የሞላው፤ በሰው ልጆች ላይ የዋለውንም ፀጋ የተሟላ ያደረገው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا}

{ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።} [አል ማኢዳህ 3]

ይህች የሙሉነት ድንጋጌ ስትሆን በውስጧም የሰው ልጆች ዲናዊም ሆነ ዱንያዊ መስተካከል የያዘች ነች። ምክንያቱም የቀደምቶቹንም ድንጋጌ በተሟላ መልኩ አካታ ይዛለችና። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ إِنَّ هَٰذَا الْقُرْآنَ يَهْدِي لِلَّتِي هِيَ أَقْوَمُ وَيُبَشِّرُ الْمُؤْمِنِينَ الَّذِينَ يَعْمَلُونَ الصَّالِحَاتِ أَنَّ لَهُمْ أَجْرًا كَبِيرًا }

{ይህ ቁርኣን ወደዚያች እርሷ ቀጥተኛ ወደ ኾነችው መንገድ ይመራል። እነዚያንም በጎ የሚሠሩትን ምእመናን ለእነሱ ታላቅ ምንዳ ያላቸው መኾኑን ያበስራል።} [አል-ኢስራእ: 9] ነብዩ ይዘውት የመጡት የእስልምና ድንጋጌ በቀደሙት ህዝቦች ላይ የነበሩትን ሸክሞችንና (ከባባድ ህግጋቶችን) አንስታላቸዋለች። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{الَّذِينَ يَتَّبِعُونَ الرَّسُولَ النَّبِيَّ الْأُمِّيَّ الَّذِي يَجِدُونَهُ مَكْتُوبًا عِندَهُمْ فِي التَّوْرَاةِ وَالْإِنجِيلِ يَأْمُرُهُم بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَاهُمْ عَنِ الْمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ الطَّيِّبَاتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيْهِمُ الْخَبَائِثَ وَيَضَعُ عَنْهُمْ إِصْرَهُمْ وَالْأَغْلَالَ الَّتِي كَانَتْ عَلَيْهِمْ ۚ فَالَّذِينَ آمَنُوا بِهِ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَاتَّبَعُوا النُّورَ الَّذِي أُنزِلَ مَعَهُ ۙ أُولَٰئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ}

{ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት (በእርግጥ እጽፍለታለሁ)። በበጎ ሥራ ያዛቸዋል። ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል። መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል። መጥፎ ነገሮችንም በእነርሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከእነሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በእነርሱ ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) ያነሳላቸዋል። እነዚያም

በእርሱ ያመኑ ያከበሩትም የረዱትም ያንንም ከእርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ እነዚያ እነሱ የሚያድኑ ናቸው።} [አል-አዕራፍ: 157]

የእስልምና ድንጋጌ ቀደምት ድንጋጌዎችን ሁሉ የምትሽር ነች፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَأَنزَلْنَا إِلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ الْكِتَابِ وَمُهَيْمِنًا عَلَيْهِ ۖ فَاحْكُم بَيْنَهُم بِمَا أَنزَلَ اللَّهُ ۖ وَلَا تَتَّبِعْ أَهْوَاءَهُمْ عَمَّا جَاءَكَ مِنَ الْحَقِّ ۚ لِكُلٍّ جَعَلْنَا مِنكُمْ شِرْعَةً وَمِنْهَاجًا ۚ وَلَوْ شَاءَ اللَّهُ لَجَعَلَكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَلَٰكِن لِّيَبْلُوَكُمْ فِي مَا آتَاكُمْ ۖ فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ ۚ إِلَى اللَّهِ مَرْجِعُكُمْ جَمِيعًا فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ }

{ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን። በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ። እውነቱም ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል። ከእናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን። አላህም በሻ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር። ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ (ለያያችሁ)። በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው። በእርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል።} [አል-ማኢዳህ 48] ሸሪዓዎቹን ሁሉ ያካተተው ቅዱስ ቁርአን የመጣው ከእሱ በፊት የነበሩትን መለኮታዊ መጻሕፍት ለማረጋገጥ እና በእነርሱ ላይ ለመፍረድ እንዲሁም ለመሻርም ነው።

## ጥራት የተገባውና ከፍ ያለው አላህ መልዕክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ይዘውት ከመጡት ሃይማኖት ውጭ ሌላን ሃይማኖት አይቀበልም። በመሆኑም ከእስልምና ውጭ ያለን ሃይማኖት አድርጎ የያዘን አላህ አይቀበለውም።

ጥራትየተገባውና ከፍ ያለው አላህ መልዕክተኛው ሙሐመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከላካቸው በኋላ እርሳቸው ይዘውት ከመጡት ሃይማኖት ውጭ ሌላን ሃይማኖት አይቀበልም። በመሆኑም ከእስልምና ውጭ ያለን ሃይማኖት የፈለገ ሃይማኖቱን አላህ አይቀበለውም። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي الْآخِرَةِ مِنَ الْخَاسِرِينَ}

{ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው።} [አሊ-ዒምራን 85] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ إِنَّ الدِّينَ عِندَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ ۗ وَمَا اخْتَلَفَ الَّذِينَ أُوتُوا الْكِتَابَ إِلَّا مِن بَعْدِ مَا جَاءَهُمُ الْعِلْمُ بَغْيًا بَيْنَهُمْ ۗ وَمَن يَكْفُرْ بِآيَاتِ اللَّهِ فَإِنَّ اللَّهَ سَرِيعُ الْحِسَابِ}

{አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው። እነዚያም መጽሐፉን የተሰጡት ሰዎች በመካከላቸው ላለው

ምቀኛነት ዕውቀቱ ከመጣላቸው በኋላ እንጅ አልተለያዩም። በአላህም አንቀጾች የሚክድ አላህ ምርመራው ፈጣን ነው።} [አሊ-ዒምራን 19] [አር-ሩም: 30] ይኸው እስልምና ነው የነብዩሏህ ኢብራሂም የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን መንገድ፤ ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَمَن يَرْغَبُ عَن مِّلَّةِ إِبْرَاهِيمَ إِلَّا مَن سَفِهَ نَفْسَهُ ۚ وَلَقَدِ اصْطَفَيْنَاهُ فِي الدُّنْيَا ۖ وَإِنَّهُ فِي الْآخِرَةِ لَمِنَ الصَّالِحِينَ}

{ከኢብራሂምም ሕግጋት ነፍሱን ያቄለ ሰው ካልኾነ በስተቀር የሚያፈገፍግ ማነው? (የለም)፤ በቅርቢቱም ዓለም በእርግጥ መረጥነው። በመጨረሻይቱም ዓለም እርሱ ከመልካሞቹ ነው።} [አል-በቀራ: 130] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَمَنْ أَحْسَنُ دِينًا مِّمَّنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ وَاتَّبَعَ مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا ۗ وَاتَّخَذَ اللَّهُ إِبْرَاهِيمَ خَلِيلًا}

{እርሱ መልካም ሠሪ ኾኖ ፊቱን ለአላህ ከሰጠና የኢብራሂምንም መንገድ ቀጥተኛ ሲኾን ከተከተለ ሰው ይበልጥ ሃይማኖቱ ያማረ ማን ነው አላህም ኢብራሂምን ፍጹም ወዳጅ አድርጎ ያዘው።} [ኒሳእ: 125] የላቀው አላህ መልእክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ህዝባቸውን እንዲህ እንዲሉ አዟል፡-

{قُلْ إِنَّنِي هَدَانِي رَبِّي إِلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ دِينًا قِيَمًا مِّلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا ۚ وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ}

{«እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛን ሃይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲኾን የአብርሃምን

መንገድ መራኝ። እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበረም» በል።} [አል-አንዓም: 161]

**28- የተከበረው ቁርአን ከፍ ያለው አላህ ለመልዕክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በወሕይ መልኩ ያወረደለት መጽሐፍ የአላህ ቃል ነው። የእርሱን አምሳያ ወይንም ከአምሳያው የአንዷቷን ምእራፍ አምሳያ እንኳ እንዲያመጡ አላህ የሰው ልጆችንም ይሁን አጋንንቶችን ሁሉ ያፎካከረበት ነው። ማፎካከሩ ዛሬም ድረስ ያለ ነው። ይህ ታላቁ ቁርአን ብዙ እልፍ አእላፍ ሰዎችን የሚያሳስቡ በርካታ ጥያቄዎችን ይመልሳል። ይህ ታላቁ ቁርአን የወረደበት በሆነው የዐረብኛ ቋንቋ የአንዲት ሆሄ እንኳ መጨመር እና መቀነስ ሳይኖርበት እንደተጠበቀ ነው ያለው። ታትሞ የተሰራጨና ተአምራዊ ሲሆን መቅራቱም ሆነ የተተረጎመውን ማንበቡ የሚገባው የሆነ ታላቅ ኪታብ ነው። ልክ የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ፈለግ፣ አስተምህሮትና ታሪካቸውም የተጠበቀ እና በታማኝ ዘጋቢዎች ሰንሰለት ከትውልድ ወደ**

**ትውልድ እየተሸጋገረ እንዲሁም እሳቸው ሲናገሩበት በነበረው የዐረብኛ ቋንቋም የታተመ ብሎም ወደ በርካታ ቋንቋ የተተረጎመ እንደሆነው ሁሉ። የተከበረው ቁርአን እና የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሱና ለዲነል ኢስላም ህግጋትና ድንጋጌዎች ብቸኞቹ ምንጮች ናቸው። የእስልምና ምንጩ ራሳቸውን ወደ እርሱ ከሚያስጠጉ ግለሰቦች ተግባር ሳይሆን ከአምላካዊ ወሕይ ነው የሚያዘው፤ ማለትም ከተከበረው ቁርአንና ከነብያዊ ሱና።**

የተከበረው ቁርአን ከፍ ያለው አላህ ለመልዕክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በዐረብኛ ቋንቋ በወሕይ መልኩ ያወረደላቸው የአላህ ቃል ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَإِنَّهُ لَتَنزِيلُ رَبِّ الْعَالَمِينَ (192) نَزَلَ بِهِ الرُّوحُ الْأَمِينُ (193) عَلَىٰ قَلْبِكَ لِتَكُونَ مِنَ الْمُنذِرِينَ (194) بِلِسَانٍ عَرَبِيٍّ مُّبِينٍ (195)}

{እርሱም (ቁርኣን) በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው።}

{እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) አወረደው}

{ከአስፈራሪዎቹ (ነቢያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)።}

{ግልጽ በኾነ ዐረብኛ ቋንቋ።} [አሽ-ሹዓራእ: 192-195] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وَإِنَّكَ لَتُلَقَّى الْقُرْآنَ مِن لَّدُنْ حَكِيمٍ عَلِيمٍ }

{አንተም ቁርኣንን ጥበበኛና ዐዋቂ ከኾነው (ጌታህ) ዘንድ በእርግጥ ትስሰጣለህ።} [አን-ነምል: 6] ይኸው ቁርአን ቀደምት መለኮታዊ ኪታቦችን አረጋጋጭ ሆኖ ከአላህ የወረደ ኪታብ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَمَا كَانَ هَٰذَا الْقُرْآنُ أَن يُفْتَرَىٰ مِن دُونِ اللَّهِ وَلَٰكِن تَصْدِيقَ الَّذِي بَيْنَ يَدَيْهِ وَتَفْصِيلَ الْكِتَابِ لَا رَيْبَ فِيهِ مِن رَّبِّ الْعَالَمِينَ}

{ይህም ቁርኣን ከአላህ ሌላ (ከሆነ ፍጡር) የተቀጠፈ ሊሆን አይገባውም። ግን ያንን ከእርሱ በፊት ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥና በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን የሚዘረዝር በእርሱ ጥርጣሬ የሌለበት ሲሆን ከዓለማት ጌታ (የተወረደ) ነው።} [ዩኑስ: 37] እናም ታላቁ ቁርአን አይሁዶች እና ክርስቲያኖች በተለያዩባቸው ሀይማኖታዊ ጉዳዮች በአብዛኞቹ ላይ በዝርዝር ያብራራል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ هَٰذَا الْقُرْآنَ يَقُصُّ عَلَىٰ بَنِي إِسْرَائِيلَ أَكْثَرَ الَّذِي هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ }

{ይህ ቁርኣን በእስራኤል ልጆች ላይ የእነዚያን እነርሱ በእርሱ የሚለያዩበትን አብዛኛውን ይነግራል።} [አን-ነምል: 76] ታላቁ ቁርአን ጥራት ከተገባው አላህ፣ ከሀይማኖቱ እና ከምንዳውም ጋር የተዛመዱትን እውነታዎችን በማሳወቅ ረገድ ሁሉንም ሰዎች የሚያሳምኑ ማስረጃዎችንና ሙግቶችን አካቷል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدْ ضَرَبْنَا لِلنَّاسِ فِي هَٰذَا الْقُرْآنِ مِن كُلِّ مَثَلٍ لَّعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ}

{በዚህም ቁርኣን ውስጥ ለሰዎች ይገሠጹ ዘንድ ከየምሳሌው ሁሉ በእርግጥ አብራራን።} [አዝ-ዙመር 27] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ تِبْيَٰنًا لِّكُلِّ شَيْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ}

{መጽሀፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ፣ መሪም፣ እዝነትም፣ ለሙስሉሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው።} [አን ነሕል 89]

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ግራ የሚያጋቡ ብዙ አስፈላጊ ጥያቄዎችን ቅዱስ ቁርአን ይመልሳል። ቅዱስ ቁርአን አላህ ሰማያትን እና ምድርን እንዴት እንደፈጠረ ያሳያል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{أَوَلَمْ يَرَ الَّذِينَ كَفَرُوا أَنَّ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ كَانَتَا رَتْقًا فَفَتَقْنَاهُمَا ۖ وَجَعَلْنَا مِنَ الْمَاءِ كُلَّ شَيْءٍ حَيٍّ ۖ أَفَلَا يُؤْمِنُونَ }

{እነዚያም የካዱት ሰማያትና ምድር የተጣበቁ የነበሩና የለያየናቸው መኾናችንን አያውቁምን ሕያው የኾነንም ነገር ሁሉ ከውሃ ፈጠርን። አያምኑምን?!} [አል-አንቢያእ 30] አላህ የሰው ልጆችን ስለፈጠበረበትም ሁኔታ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِن كُنتُمْ فِي رَيْبٍ مِّنَ الْبَعْثِ فَإِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ مِنْ عَلَقَةٍ ثُمَّ مِن مُّضْغَةٍ مُّخَلَّقَةٍ وَغَيْرِ مُخَلَّقَةٍ لِّنُبَيِّنَ لَكُمْ ۚ وَنُقِرُّ فِي الْأَرْحَامِ مَا نَشَاءُ إِلَىٰ أَجَلٍ مُّسَمًّى ثُمَّ نُخْرِجُكُمْ طِفْلًا ثُمَّ لِتَبْلُغُوا أَشُدَّكُمْ ۖ وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ وَمِنكُم مَّن يُرَدُّ إِلَىٰ أَرْذَلِ الْعُمُرِ لِكَيْلَا يَعْلَمَ مِن بَعْدِ عِلْمٍ شَيْئًا ۚ وَتَرَى الْأَرْضَ هَامِدَةً فَإِذَا أَنزَلْنَا عَلَيْهَا الْمَاءَ اهْتَزَّتْ وَرَبَتْ وَأَنبَتَتْ مِن كُلِّ زَوْجٍ بَهِيجٍ }

{እናንተ ሰዎች ሆይ! ከመቀስቀስ በመጠራጠር ውስጥ እንደ ሆናችሁ (አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ)። እኛም ከዐፈር ፈጠርናችሁ፣ ከዚያም ከፍትወት ጠብታ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ ከዚያም ከቁራጭ ሥጋ፣ ፍጥረትዋ ሙሉ ከሆነችና ሙሉ ካልሆነች (ችሎታችንን) ለናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ። የምንሻውንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በማሕፀን ውስጥ እናረጋዋለን። ከዚያም ሕፃን ሆናችሁ እናወጣችኋለን። ከዚያም ሙሉ ጥንካሪያችሁን ትደርሱ ዘንድ (እናሳድጋችኋለን)። ከእናንተም የሚሞት ሰው አልለ። ከእናንተም ከዕውቀት በኋላ ምንንም እንዳያውቅ ወደ ወራዳ ዕድሜ የሚመለስ ሰው አልለ። ምድርንም ደረቅ ሆና ታያታለህ። በእርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ ትላወሳለች። ትነፋፋለችም። ውበት ካለው ጎሳ ሁሉ ታበቅላለችም።} [አል-ሓጅ: 5] የሰው ልጅ መመለሻ ወዴት እንደሆነ? ከዚህች ህይወት በኋላ የመልካም ሰሪ ምንዳው ምን እንደሆነ፤ የክፋ ሰሪስ ምንዳው ምን እንደሆነ? ለነዚህ ቁምነገሮች ማስረጃቸውን በአንቀፅ 20 አሳልፈናል፤ ይህስ ዓለም ድንገት የተከሰተ ነገር ነው? ወይስ ለታላቅ አላማ የተፈጠረ እና መሰል ጥያቄዎችን ይመልሳል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{أَوَلَمْ يَنظُرُوا فِي مَلَكُوتِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا خَلَقَ اللَّهُ مِن شَيْءٍ وَأَنْ عَسَىٰ أَن يَكُونَ قَدِ اقْتَرَبَ أَجَلُهُمْ ۖ فَبِأَيِّ حَدِيثٍ بَعْدَهُ يُؤْمِنُونَ}

{በሰማያትና በምድር ግዛት ውስጥ ከማንኛው ነገር አላህ በፈጠረውም ሁሉ የሞት ጊዜያቸውም በእርግጥ መቅረቡ

የሚፈራ መኾኑን አያስተውሉምን ከእርሱም (ከቁርኣን) ወዲያ በየትኛው ንግግር ያምናሉ።} [አል-አዕራፍ: 185] አላህ እንዲህ ብሏል፦

{أَفَحَسِبْتُمْ أَنَّمَا خَلَقْنَاكُمْ عَبَثًا وَأَنَّكُمْ إِلَيْنَا لَا تُرْجَعُونَ}

{«የፈጠርናችሁ ለከንቱ መኾኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁን» (ለከንቱ የፈጠርናችሁ መሰላችሁን)} [አል-ሙእሚኑን: 115]

ታላቁ ቁርአን በወረደበት ቋንቋው እንደተጠበቀ እስከዛሬ ድረስ አለ፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ}

{ቁርኣኑን እኛ ነው ያወረድነው፣እኛ ለሱ ጠባቂዎች ነን} [አል-ሒጅር: 9] በውስጡ ምንም ነገር አልጎደለም፤ ተቃርኖም ሆነ እንከን ወይንም መለወጥ ሊያጋጥመውም የማይችል ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ الْقُرْآنَ ۚ وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ اللَّهِ لَوَجَدُوا فِيهِ اخْتِلَافًا كَثِيرًا}

{ቁርኣንን አያስተነትኑምን ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር።} [አን-ኒሳእ: 82] ቁርአን ታትሞ ተሰራጭቶ ይገኛል። ለማንበብ፣ ለማዳመጥ ወይም ትርጉሞቹን ለመተርጎም የሚገባው የሆነ ታላቅ ተአምራዊ መጽሐፍም ነው። ልክ የመልክተኛው ሙሐመድ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሱና፣ እንዲሁም አስተምህሮታቸውና ታሪካቸው ተከታታይ በሆኑ ታማኝ ተራኪዎች መሠረት በቅብብሎሽ እየተላለፈ በህትመትም

ደረጃ ጭምር በመሰረታዊ የመልዕክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ቋንቋ ተጠብቆ ወደበርካታ ቋንቋም የተተረጎመ እንደሆነው ሁሉ ማለት ነው። ክቡር ቁርአን እና የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሱና ብቸኞቹ የእስልምና ህግጋትና ድንጋጌ ምንጮች ናቸው። እስልምና ከእርሱ ጋር ግንኙነት ካላቸው ግለሰቦች ተግባር አንፃር ሊወሰድ አይገባውም። ይልቁንም ፍፁም መለኮታዊ ከሆነ ወሕይ ነው ሊወሰድ የሚገባው - ይህውም ከታላቁ ቁርአን እና ከነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሱና ነው።

{ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِٱلذِّكۡرِ لَمَّا جَآءَهُمۡۖ وَإِنَّهُۥ لَكِتَٰبٌ عَزِيزٞ - لَّا يَأۡتِيهِ ٱلۡبَٰطِلُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَلَا مِنۡ خَلۡفِهِۦۖ تَنزِيلٞ مِّنۡ حَكِيمٍ حَمِيدٖ}

{እነዚያ በቁርኣን እርሱ አሸናፊ መጽሐፍ ሲሆን በመጣላቸው ጊዜ የካዱት (ጠፊዎች ናቸው)። ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም። ጥበበኛ ምስጉን ከኾነው ጌታ የተወረደ ነው።} [ፉሲለት: 41-42] የላቀው አላህ የነብዩ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለምን ሱና በማስመልከት ከአላህ የሆነ መገለጥ(ወሕይ) መሆኑን ሲነግረን እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمۡ عَنۡهُ فَٱنتَهُواْۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۖ إِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ}

{መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ። አላህንም ፍሩ። አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና።} [አል ሀሽር 7]

# 29- እስልምና ሙስሊም እንኳ ባይሆኑ ለወላጆች በጎ መዋልን ያዛል ስለልጆችም መልካሙን አደራ ያስተላልፋል።

እስልምና ለወላጆች በጎ መዋልን ያዛል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَقَضَىٰ رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوا إِلَّا إِيَّاهُ وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا ۚ إِمَّا يَبْلُغَنَّ عِندَكَ الْكِبَرَ أَحَدُهُمَا أَوْ كِلَاهُمَا فَلَا تَقُل لَّهُمَا أُفٍّ وَلَا تَنْهَرْهُمَا وَقُل لَّهُمَا قَوْلًا كَرِيمًا }

{ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፡- እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ። በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ። በአንተ ዘንድ ሆነው አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው። አትገላምጣቸውም። ለእነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው።} [አል-ኢስራእ: 23] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَوَصَّيْنَا الْإِنسَانَ بِوَالِدَيْهِ حَمَلَتْهُ أُمُّهُ وَهْنًا عَلَىٰ وَهْنٍ وَفِصَالُهُ فِي عَامَيْنِ أَنِ اشْكُرْ لِي وَلِوَالِدَيْكَ إِلَيَّ الْمَصِيرُ }

{ሰውንም በወላጆቹ (በጎ እንዲያደርግ) በጥብቅ አዘዝነው። እናቱ ከድካም በላይ በሆነ ድካም አረገዘችው። ጡት መጣያውም በሁለት ዓመት ውስጥ ነው። ለእኔም ለወላጆችህም አመስግን በማለት (አዘዝነው)። መመለሻው ወደኔ ነው።} [ሉቅማን:14] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَوَصَّيْنَا الْإِنسَانَ بِوَالِدَيْهِ إِحْسَانًا ۖ حَمَلَتْهُ أُمُّهُ كُرْهًا وَوَضَعَتْهُ كُرْهًا ۖ وَحَمْلُهُ وَفِصَالُهُ ثَلَاثُونَ شَهْرًا ۚ حَتَّىٰ إِذَا بَلَغَ أَشُدَّهُ وَبَلَغَ أَرْبَعِينَ سَنَةً قَالَ رَبِّ أَوْزِعْنِي أَنْ أَشْكُرَ نِعْمَتَكَ الَّتِي أَنْعَمْتَ عَلَيَّ وَعَلَىٰ وَالِدَيَّ وَأَنْ أَعْمَلَ

صَالِحًا تَرْضَاهُ وَأَصْلِحْ لِي فِي ذُرِّيَّتِي ۖ إِنِّي تُبْتُ إِلَيْكَ وَإِنِّي مِنَ الْمُسْلِمِينَ {

{ሰውንም በወላጆቹ በጎ መዋልን በጥብቅ አዘዝነው። እናቱ በችግር ላይ ኾና አረገዘችው። በችግርም ወለደችው። እርግዝናውና ከጡት መለያውም ሰላሳ ወር ነው። ጥንካሬውንም ወቅት በደረሰ ጊዜ (ከዚያ አልፎ) አርባ ዓመትንም በደረሰ ጊዜ «ጌታዬ ሆይ! ያችን በእኔ ላይና በወላጆቼ ላይ የለገስካትን ጸጋህን እንዳመሰግን የምትወደውንም መልካም ሥራ እንድሠራ ምራኝ። ዘሮቼንም ለእኔ አብጅልኝ። እኔ ወዳንተ ተመለስኩ። እኔም ከሙስሊሞ ነኝ» አለ።} [አል-አሕቃፍ: 15]

وعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ قَالَ: جَاءَ رَجُلٌ إِلَى رَسُولِ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَقَالَ: يَا رَسُولَ اللَّهِ مَنْ أَحَقُّ النَّاسِ بِحُسْنِ صَحَابَتِي؟ قَالَ: «أُمُّكَ» قَالَ: ثُمَّ مَنْ؟ قَالَ: «ثُمَّ أُمُّكَ» قَالَ: ثُمَّ مَنْ؟ قَالَ: «ثُمَّ أُمُّكَ» قَالَ: ثُمَّ مَنْ؟ قَالَ: «ثُمَّ أَبُوكَ»

አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና አቡ ሁረይራ ባስተላለፈው ሐዲሥ የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን)እንዲህ ብለዋል፦ አንድ ሰው ወደ ረሱል (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መጣና "ከማንም በላይ የእኔ ጥሩ አያያዝ የሚገባው ማነው? አላቸው፤ እርሳቸውም "እናትህ" አሉት፤ እሱም "ከዚያስ?" አላቸው፤ እርሳቸው "ከዚያም እናትህ" አሉት፤ "ከዚያስ?" አላቸው፤ እሳቸውም "ከዚያም እናትህ" አሉት፤ "ከዚያስ?" ሲላቸው "ከዚያም አባትህ" አሉት። ሰሒሕ ሙስሊም

ይህ ወላጆች በበጎ እንዲዋልላቸው የተላለፈ አደራ ሙስሊም ቢሆኑም ባይሆኑም ይመለከታቸዋል።

فعَنْ أَسْمَاءَ بِنْتِ أَبِي بَكْرٍ قَالَتْ: (قَدِمَتْ أُمِّي وَهِيَ مُشْرِكَةٌ فِي عَهْدِ قُرَيْشٍ وَمُدَّتِهِمْ إِذْ عَاهَدُوا النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ مَعَ ابْنِهَا فَاسْتَفْتَيْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَقُلْتُ: إِنَّ أُمِّي قَدِمَتْ وَهِيَ رَاغِبَةٌ، أَفَأَصِلُهَا؟ قَالَ: «نَعَمْ صِلِي أُمَّكِ»

ከአስማእ ቢንት አቢበክር በተላለፈ ሐዲሥ እንዲህ ብላለች፡- የቁረይሽ ሙሽሪኮች ከአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ጋር የሰላም ስምምነት ባደረጉበት ወቅት እናቴ ከልጇ ጋር በመሆን እኔን ለመጠየቅ መጣች እና እርሷ ሙሽሪክ ነበረች። በዚሁ ጉዳይ የአላህን መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) አማከርኳቸው (ፈትዋ /ብይን/ ጠየቅኳቸው) - “የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) እናቴ ወደ እኔ መጣች ከእኔ ጋ መቀራረብ (መልካም እንዳደርግላት) ትፈልጋለች፣ ከእሷ ጋር ዝምድናዬን ልቀጥልን?” አልኳቸው፤ እርሳቸውም “እንዴታ! ከእርሷ ጋር ጥሩ ግንኙነት ይኑርሽ (ዝምድናሽን ቀጥይ)” አሉኝ። ሰሒሕ ቡኻሪይ ይሁን እንጂ ወላጆች ልጃቸውን ከእስልምናው ወጥቶ ወደ ክህደት እንዲቀለበስ የሚጥሩ ከሆነ ግን በዚህ ጉዳይ ብቻ ሳይታዘዛቸው ሙእሚንነቱን ጠብቆ ይፀናል። በሌላው ጉዳይ ግን አሁንም ቢሆን በጎ ከመዋል ይወዳጃቸዋል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَإِن جَٰهَدَاكَ عَلَىٰٓ أَن تُشۡرِكَ بِي مَا لَيۡسَ لَكَ بِهِۦ عِلۡمٞ فَلَا تُطِعۡهُمَاۖ وَصَاحِبۡهُمَا فِي ٱلدُّنۡيَا مَعۡرُوفٗاۖ وَٱتَّبِعۡ سَبِيلَ مَنۡ أَنَابَ إِلَيَّۚ ثُمَّ إِلَيَّ مَرۡجِعُكُمۡ فَأُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ}

{ለአንተ በእርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር በእኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም አትታዘዛቸው፡፡ በቅርቢቱም ዓለም፤ በመልካም ሥራ ተወዳጃቸው፡፡ ወደእኔም የተመለሰን ሰው መንገድ ተከተል፡፡ ከዚያም መመለሻችሁ ወደእኔ ነው፡፡ ትሠሩት የነበራችሁትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፤ (አልነው)፡፡} [ሉቅማን: 15]

እስልምና ለአጋሪ ከሀድያን ቅርብ ቤተዘመዶች ቢሆኑም ባይሆኑም እስልምናን እስካልተዋጉ ድረስ ለእነርሱ በጎ መዋልን አይከለክልም፡፡ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ لَّا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَارِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ }

{ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፡፡ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና፡፡} [አል-ሙምተሒናህ: 8]

እስልምና ልጆችን በማስመልከትም መልካም በማድረግ ላይ አደራ ያላል፡፡ በእስልምና ወላጅ ስለ ልጆቹ ከታዘዘባቸው ጉዳዮች አጅግ ከባዱ ልጆቹን ስለ ጌታቸው ሐቅ ማስተማር ነው፡፡ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ለአጎታቸው ልጅ ለኢብኑ ዓባስ ረዲየሏሁ ዓንሁማ እንዲህ በማለት አስተምረውታል፦

«يَا غُلامُ أَوْ يَا غُلَيِّمُ أَلا أُعَلِّمُكَ كَلِمَاتٍ يَنْفَعُكَ اللهُ بِهِنَّ؟ فَقُلْتُ: بَلَى. فَقَالَ: "احْفَظِ اللهَ يَحْفَظْكَ احْفَظِ اللهَ تَجِدْهُ أَمَامَكَ تَعَرَّفْ إِلَيْهِ فِي الرَّخَاءِ يَعْرِفْكَ فِي الشِّدَّةِ وَإِذَا سَأَلْتَ فَاسْأَلِ اللهَ وَإِذَا اسْتَعَنْتَ فَاسْتَعِنْ بِاللهِ»

"አንተ ልጅ ሆይ! አላህ አንተን የሚጠቅምበት የሆኑ አንዳንድ ቃላትን እንዳስተምርህ አትፈልግምን? እንዴታ አልኳቸው፤ እርሳቸውም "አላህን ጠብቀው (ትዕዛዙን ጠብቅ) ይጠብቅሃል። አላህን ጠብቀው (ትዕዛዙን ጠብቅ) ከፊትህ ታገኘዋለህ። ከጠየቅክ አላህን ብቻ ጠይቅ። እርዳታንም ከፈለክ አላህን ብቻ እርዳኝ በለው።" አሕመድ ዘግበውታል: 4/287

አላህ ወላጆች ልጆቻቸውን በሃይማኖታዊም ሆነ በዓለማዊም ጉዳዮች ላይ የሚጠቅማቸውን እንዲያስተምሩ አዟቸዋል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ قُوٓا۟ أَنفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ نَارًا وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلْحِجَارَةُ عَلَيْهَا مَلَـٰٓئِكَةٌ غِلَاظٌ شِدَادٌ لَّا يَعْصُونَ ٱللَّهَ مَآ أَمَرَهُمْ وَيَفْعَلُونَ مَا يُؤْمَرُونَ}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ደንጋዮች ከኾነች እሳት ጠብቁ። በእርሷ ላይ ጨካኞች፣ ኀይለኞች የኾኑ መላእክት አልሉ። አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም። የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ።} [ሱረቱ ተሕሪም: 6] ከዐሊይ አላህ መልካም ሥራቸው ይውደድላቸው ተከታዩን የአላህ ቃል አስመልክቶ እንዲህ ብለዋል፦

{قُوا أَنفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ نَارًا}

{...ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን ... ጠብቁ።} "አርሟቸውም አስተምሯቸውም" ነው የሚለን። ነብዩ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) አባት ልጁን ሶላትን ተላምዶ

ያድግ ዘንድ ማስተማር እንዳለበት አዘዋል፤ እንዲህም ብለዋል፦

(مُرُوا أولاكمِ بالصلاةِ وهم أبناءُ سبعِ سِنينَ)

"ልጆቻችሁ እድሜያቸው ሰባት ዓመት ሲሆኑ በሶላት እዘዟቸው።" አቡ ዳውድ ዘግበውታል የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«كُلُّكُمْ رَاعٍ وَكُلُّكُمْ مَسْؤولٌ عَنْ رَعِيَّتِهِ الإِمَامُ رَاعٍ وَمَسْؤولٌ عَنْ رَعِيَّتِهِ وَالرَّجُلُ رَاعٍ فِي أَهْلِهِ وَهُوَ مَسْؤولٌ عَنْ رَعِيَّتِهِ وَالمَرْأَةُ رَاعِيَةٌ فِي بَيْتِ زَوْجِهَا وَمَسْؤولَةٌ عَنْ رَعِيَّتِهَا والخادمُ راعٍ في مالِ سيِّدِه ومسؤولٌ عن رعيَّتِه وكلُّكم راعٍ ومسؤولٌ عن رعيَّتِه»

"ሁላችሁም እረኛ ናችሁ ሁላችሁም ስለ ጠበቃችሁት ትጠየቃላችሁ። አባወራ (ወንድ ልጅ) በቤቱ ነዋሪዎች ላይ እረኛ ነው ስለጠበቀው ነገር ይጠየቃል። ሴት ልጅ የባሏን ቤት እና ልጆችን ጠባቂ እረኛ ነች በጠበቀችው ነገር ትጠየቃለች። አገልጋይ ባሪያም በጌታው ንብረት ላይ ጠባቂ እረኛ ነው ስለ ጠበቀው ይጠየቃል። ሁላችሁም እረኛ ናችሁ ሁላችሁም ስለጠበቃችሁት ትጠየቃላችሁ።" ሰሒሕ ኢብኑ ሒባን 4490

እስልምና ወላጅ አባት ለልጆቹም ሆነ ለቤተሰቡ የገንዘብ ጣጣቸውን እንዲችል አዟል። ስለዚህ ጉዳይ በአንቀፅ 18 ላይ በተወሰነ መልኩ አሳልፈናል። ነብዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የልጆችን ገንዘብ ነክ ጣጣ መቻል ያለውን በላጭነት ግልፅ አድርገዋል። እንዲህ ብለዋል፦

«أَفْضَلُ دِينَارٍ يُنْفِقُهُ الرَّجُلُ: دِينَارٌ يُنْفِقُهُ عَلَى عِيَالِهِ وَدِينَارٌ يُنْفِقُهُ الرَّجُلُ عَلَى دَابَّتِهِ فِي سَبِيلِ اللهِ وَدِينَارٌ يُنْفِقُهُ عَلَى أَصْحَابِهِ فِي سَبِيلِ اللهِ». قَالَ أَبُو

قِلَابَةَ: " وَبَدَأَ بِالْعِيَالِ ثُمَّ قَالَ أَبُو قِلَابَةَ: وَأَيُّ رَجُلٍ أَعْظَمُ أَجْرًا مِنْ رَجُلٍ يُنْفِقُ عَلَى عِيَالٍ صِغَارٍ يُعِفُّهُمْ أَوْ يَنْفَعُهُمُ اللهُ بِهِ وَيُغْنِيهِمْ"

"እጅግ በጣም ጥሩው ገንዘብ አንድ ሰው በቤተሰቡ ላይ የሚያወጣው፤ እና በአላህ መንገድ ለሚታገልበት እንስሳው ላይ የሚያወጣው እንዲሁም በአላህ መንገድ ላይ (ለተሰማሩ) ባልደረቦቻቸው የሚያወጣው ገንዘብ ነው።" አቡ ቂላባም እንዲህ ብለዋል፡- "ከቤተሰብ ጀምረ" አሉና ቀጥሎ አቡ ቂላባ እንዲህ አሉ፡- "ከእርሱ ለሚጠብቁ ሕጻናት የቤተሰቡ አባላት ከድህነት የሚጠብቃቸው ወይም በእርሱም ምክንያት አላህ የሚያጣቅማቸውና የሚያብቃቃቸው ከሆነ ስው የበለጠ አጅር ያለው ሰው ማነው?!።" ሰሒሕ ሙስሊም 994

## 30- እስልምና ከጠላት ጋር እንኳ በተግባርም ሆነ በንግግር ፍትሃዊ መሆንን ያዛል።

ጥራት የተገባውና የላቀ አላህ በባርያዎቹ መካከል በድርጊቱም ይሁን በአስተዳደሩ ውስጥ በፍትህና በእኩልነት የሚገለፅ ጌታ ነው። ባዘዘበትም ሆነ በከለከለበት በፈጠረውም ሆነ በወሰነው ነገር ላይ በቀናው (በቀጥተኛው) ጎዳና ያለ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{شَهِدَ اللَّهُ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَالْمَلَائِكَةُ وَأُولُو الْعِلْمِ قَائِمًا بِالْقِسْطِ ۚ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ}

{አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ። መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)። ከእርሱ

በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። አሸናፊው ጥበበኛው ነው።} [አሊ-ዒምራን 18] አላህ በፍትህ ያዛል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ أَمَرَ رَبِّي بِالْقِسْطِ}

{ጌታየ በማስተካከል አዘዘ።} [አል-አዕራፍ: 29] ነብያቶችና መልዕክተኞችም ሁሉ ፍትህን ይዘው ነው የመጡት፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{لَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلَنَا بِالْبَيِّنَاتِ وَأَنزَلْنَا مَعَهُمُ الْكِتَابَ وَالْمِيزَانَ لِيَقُومَ النَّاسُ بِالْقِسْطِ }

{መልዕክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን። ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሓፎችንና ሚዛንን ወደእነርሱ አወረድን።} [አል-ሓዲድ: 25] ሚዛን የተባለው በንግግርም ይሁን በተግባር ፍትሀዊ መሆን ነው።

እስልምና ከጠላት ጋር እንኳ በተግባርም ሆነ በንግግር ፍትሃዊ መሆንን ያዛል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُونُوا قَوَّامِينَ بِالْقِسْطِ شُهَدَاءَ لِلَّهِ وَلَوْ عَلَىٰ أَنفُسِكُمْ أَوِ الْوَالِدَيْنِ وَالْأَقْرَبِينَ ۚ إِن يَكُنْ غَنِيًّا أَوْ فَقِيرًا فَاللَّهُ أَوْلَىٰ بِهِمَا ۖ فَلَا تَتَّبِعُوا الْهَوَىٰ أَن تَعْدِلُوا ۚ وَإِن تَلْوُوا أَوْ تُعْرِضُوا فَإِنَّ اللَّهَ كَانَ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرًا}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በትክክል (ፍትሕ) ቀዋሚዎች በነፈሶቻችሁ ወይም በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ላይ ቢኾንም እንኳ ለአላህ መስካሪዎች ኹኑ። ሀብታም ወይም ድኻ ቢኾን አላህ በእነርሱ (ከእናንተ) ይበልጥ ተገቢ ነው። እንዳታደሉም ዝንባሌን አትከተሉ። ብታጠምሙም ወይም

(መመስከርን) ብትተው አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።} [አን-ኒሳእ: 135] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلَا يَجْرِمَنَّكُمْ شَنَآنُ قَوْمٍ أَن صَدُّوكُمْ عَنِ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ أَن تَعْتَدُوا ۘ وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَىٰ ۖ وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ ۖ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ}

{ከተከበረው መስጊድ ስለከለከሉዋችሁ ሰዎችን መጥላትም (በነሱ ላይ) ወሰን እንዳታልፉ አይገፋፋችሁ። በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ። ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፌ አትረዳዱ። አላህንም ፍሩ። አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና።} [አል-ማኢዳህ: 2] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُونُوا قَوَّامِينَ لِلَّهِ شُهَدَاءَ بِالْقِسْطِ ۖ وَلَا يَجْرِمَنَّكُمْ شَنَآنُ قَوْمٍ عَلَىٰ أَلَّا تَعْدِلُوا ۚ اعْدِلُوا هُوَ أَقْرَبُ لِلتَّقْوَىٰ}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ለአላህ ቀጥተኞች በትክክል መስካሪዎች ኹኑ። ሕዝበችንም መጥላት በለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ። አስተካክሉ። እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው። አላህንም ፍሩ። አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።} [አል-ማኢዳህ: 8] ለመሆኑ ግን በዛሬ ጊዜ በሰው ሰራሽ ሕጎችም ይሁን ወይም በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ እንዲህ ባለ መልኩ በራስ ላይም ይሁን በወላጆችና በዘመዶች እንዲሁም ከወዳጅም ጋ ይሁን ከጠላት ጋር የዚህን ያክል በእውነት ለመመስከርና እውነታዋን ለመናገር የሚችል መመርያ ይገኛል?!

ነብዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በልጆች መካከል ፍትሀዊነትን አዘዋል።

فعَنْ عَامِرٍ قَالَ: سَمِعْتُ النُّعْمَانَ بْنَ بَشِيرٍ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا وَهُوَ عَلَى المِنْبَرِ يَقُولُ: أَعْطَانِي أَبِي عَطِيَّةً فَقَالَتْ عَمْرَةُ بِنْتُ رَوَاحَةَ: لاَ أَرْضَى حَتَّى تُشْهِدَ رَسُولَ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَأَتَى رَسُولَ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَقَالَ: إِنِّي أَعْطَيْتُ ابْنِي مِنْ عَمْرَةَ بِنْتِ رَوَاحَةَ عَطِيَّةً فَأَمَرَتْنِي أَنْ أُشْهِدَكَ يَا رَسُولَ اللَّهِ قَالَ: «أَعْطَيْتَ سَائِرَ وَلَدِكَ مِثْلَ هَذَا؟» قَالَ: لاَ قَالَ: «فَاتَّقُوا اللَّهَ وَاعْدِلُوا بَيْنَ أَوْلاَدِكُمْ» قَالَ: فَرَجَعَ فَرَدَّ عَطِيَّتَهُ)

ከዓምር በተላለፈ ሓዲሥ ኑዕማን ቢን በሺር እንዲህ ሲል ሰምቸዋለሁ ይላል፤ "አባቴ ስጦታ ሰጠኝ ነገር ግን ዓምራ ቢንት ረዋሓ (እናቴ) "የአላህን መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ምስክር እንዲሆኑ ካላደረክ በቀር በዚህ አልስማማም" አለችኝ። ስለዚህም አባቴ ወደ አላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሄዶ ‹ከአምራ ቢንት ረዋሓ ለወለድኩት ልጄ ስጦታ አበረከትኩለት፤ እርሷም የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ምስክር ይሁኑልህ ብላ አዘዘችኝ!" አለ፤ እርሳቸውም "ለተቀሩት ልጆችህም ሰጥተሀልን?" አሉ፤ እርሱም "አይ" በማለት መለሰ። የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለምም) "አላህን ፍሩ በልጆቻችሁ መካከል ፍትሃዊ ሁኑ" አሉ። ከዚያ አባቴ ተመልሶ ስጦታውን መልሶ ወሰደ። ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 2587

ይህ የሆነው የሰዎች ጉዳይም ሆነ ሀገር ሊቀና የሚችለው በፍትህ ብቻ በመሆኑ ነው። ሰዎች በሃይማኖታቸው፣ በደማቸው፣ በዝርያቸው፣ በክብራቸው፣ በንብረታቸው፣

በመኖርያቸው በፍትህ ካልሆነ በቀር ደህንነት ሊሰማቸውም አይችልም። ስለዚህም ነበር ቁረይሾች ሙስሊሞችን ባጨናነቋቸው ጊዜ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ባልደረቦቻቸውን ወደ ሀበሻ ሂጅራ እንዲያደርጉ ያዘዟቸው። ይህንንም በሀበሻ ምድር ማንም የማይበደልበት ንጉስ አለ በሚል ምክንያት ነበር ያቆራኙት።

## 31- እስልምና ለፍጥረታቱ ሁሉ በጎ መዋልን የሚያዝ ሲሆን ወደ መልካም ስነምግባርና ወደ በጎ ስራዎችም ጥሪ ያደርጋል።

እስልምና ለፍጥረታት ሁሉ በጎ መዋልን ያዛል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُ بِالْعَدْلِ وَالْإِحْسَانِ وَإِيتَاءِ ذِي الْقُرْبَىٰ}

{አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል።} [አን-ነሕል: 90] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{الَّذِينَ يُنفِقُونَ فِي السَّرَّاءِ وَالضَّرَّاءِ وَالْكَاظِمِينَ الْغَيْظَ وَالْعَافِينَ عَنِ النَّاسِ ۗ وَاللَّهُ يُحِبُّ الْمُحْسِنِينَ}

{ለእነዚያ በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፣ ቁጭትንም ገቺዎች ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለኾኑት (ተደግሳለች)። አላህም በጎ ሠሪዎችን ይወዳል።} [አሊ-ዒምራን 134] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

« إنَّ اللَّهَ كَتَبَ الإحْسَانَ علَى كُلِّ شيءٍ، فَإِذَا قَتَلْتُمْ فأحْسِنُوا القِتْلَةَ، وإذَا ذَبَحْتُمْ فأحْسِنُوا الذَّبْحَ، وَلْيُحِدَّ أَحَدُكُمْ شَفْرَتَهُ، فَلْيُرِحْ ذَبِيحَتَهُ »

«አላህ ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ እንዲከናወን ወስኗል፤ ስለዚህ መግደል ካለባችሁ እንኳ በጥሩው ዘዴ ፈፅሙት (ስትገድሉ አገዳደላችሁን አሳምሩ)፤ እንስሳን ስታርዱ በጥሩ ሁኔታ እረዱ፤ ማለትም: እያንዳንዳችሁ ቢላዋን ይሳለው አድርጉ እና እንስሳውን በተቻለ መጠን ትንሽ ፋታ ስጡት።» ሰሒሕ ሙስሊም 1955

እስልምና ወደ መልካም ስነምግባርና ወደ በጎ ስራዎች ጥሪ ያደርጋል። የላቀው አላህ መልዕክተኛውን ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም በቀደምት ኪታቦች ሲገለፃቸው እንዲህ ብሏል፦

{الَّذِينَ يَتَّبِعُونَ الرَّسُولَ النَّبِيَّ الْأُمِّيَّ الَّذِي يَجِدُونَهُ مَكْتُوبًا عِندَهُمْ فِي التَّوْرَاةِ وَالْإِنجِيلِ يَأْمُرُهُم بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَاهُمْ عَنِ الْمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ الطَّيِّبَاتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيْهِمُ الْخَبَائِثَ وَيَضَعُ عَنْهُمْ إِصْرَهُمْ وَالْأَغْلَالَ الَّتِي كَانَتْ عَلَيْهِمْ ۚ فَالَّذِينَ آمَنُوا بِهِ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَاتَّبَعُوا النُّورَ الَّذِي أُنزِلَ مَعَهُ ۙ أُولَٰئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ}

{ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት (በእርግጥ እጽፍለታለሁ)። በበጎ ሥራ ያዛቸዋል። ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል። መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል። መጥፎ ነገሮችንም በእነርሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከእነሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በእነርሱ ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) ያነሳላቸዋል። እነዚያም

በእርሱ ያመኑ ያከበሩትም የረዱትም ያንንም ከእርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ እነዚያ እነሱ የሚያድኑ ናቸው።} [አል-አዕራፍ: 157] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«يَا عَائِشَةُ إِنَّ اللهَ رَفِيقٌ يُحِبُّ الرِّفْقَ وَيُعْطِي عَلَى الرِّفْقِ مَا لَا يُعْطِي عَلَى الْعُنْفِ وَمَا لَا يُعْطِي عَلَى مَا سِوَاهُ»

«አላህ በእርግጥ ርህሩህ ነው፤ ርህራሄን ይወዳል፤ በድርቅናም ሆነ በሌላም የማይሰጠውን በርህራሄ ግን ይሰጣል።» ሰሒሕ ሙስሊም 2593 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«إِنَّ اللَّهَ حَرَّمَ عَلَيْكُمْ: عُقُوقَ الأُمَّهَاتِ وَوَأْدَ البَنَاتِ وَمَنَعَ وَهَاتِ وَكَرِهَ لَكُمْ قِيلَ وَقَالَ وَكَثْرَةَ السُّؤَالِ وَإِضَاعَةَ المَالِ»

«የላቀው አላህ ለእናቶች አክብሮት የጎደለው (የመናቅ) ባህሪን ማሳየትን፣ ሴቶች ልጆቻችሁን በሕይወት እንዲቀብሩ ማድረግን፣ የሌሎችን ገንዘብ ነክ መብታቸውን ማቀብን ክልክል አድርጎታል። አሉ ተባለ ወሬ፣ መጠየቅ የማይገባችሁን ከሌሎች መጠየቅን እና ሀብትንን ማባከንን ከናንተ ይጠላል።» ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 2408 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«لَا تَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ حَتَّى تُؤْمِنُوا وَلَا تُؤْمِنُوا حَتَّى تَحَابُّوا أَوَلَا أَدُلُّكُمْ عَلَى شَيْءٍ إِذَا فَعَلْتُمُوهُ تَحَابَبْتُمْ؟ أَفْشُوا السَّلَامَ بَيْنَكُمْ»

«እስክታምኑ ድረስ ጀነትን አትገቡም፣ እርስ በርሳችሁም እስክትዋደዱ ድረስም እምነታችሁ ሙሉ አይሆንም። ታድያ ካደረጋችሁት እርስ በርሳችሁ የሚያዋዳችሁን ነገር አልንገራችሁምን? በመካከላችሁ ሰላምታን አብዙ (ሰላምን አሰራጩ)።» ሰሒሕ ሙስሊም 54

## 32- እስልምና እውነተኝነትን፣ አደራን መወጣትን፣ ጥብቅነትን፣ አይነ አፋርነትን፣ ጀግንነትን፣ ለጋስነትን፣ ቸርነትን፣ የተቸገረን መርዳትንና የወደመበትን መታደግን፣ የተራበን ማብላትን፣ መልካም ጉርብትናን፣ ዝምድና መቀጠልን፣ ለእንስሳት እንኳ ማዘንን በመሰሉ ምስጉን የሆኑ ስነምግባሮች ሁሉ ያዛል።

እስልምና ምስጉን በሆኑ ስነምግባሮች ያዛል፤ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል:-

(إِنَّمَا بُعِثْتُ لِأُتَمِّمَ صَالِحَ الْأَخْلَاقِ)

(እኔ የተላኩት የተስተካከለ ስነምግባርን ላሟላ ነው።) ሰሒሕ አል አዳቡል ሙፍረድ 207 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

(نَّ من أحبِّكم إليَّ ، وأقربِكم مني مجلسًا يومَ القيامةِ أحاسِنُكم أخلاقًا ، وإنَّ أبغضَكم إليَّ وأبعدَكم مني مجلسًا يومَ القيامةِ الثَّرثارونَ ، والمُتشدِّقونَ ، والمُتفيهقونَ ، قالوا : قد علِمْنا الثرثارونَ و المتشدِّقونَ ، فما المتفيهقونَ ؟ قال : المُتكبِّرونَ)

“በእለተ ትንሣኤ ከእናንተ ዘንድ በጣም የተወደደው እና ለኔም በጣም ቅርብ የሆነው በመልካም ሥነ ምግባር ከእናንተ በላጭ የሆነ ነው፤ ከእናንተ መካከል እኔ ዘንድ በጣም የተጠላውና ከእኔም የራቀው ደግሞ አሥ-ሠርሣሩን (ራሱን እያስጨነቀ ብዙ የሚያወራ)፣ አል-መተሸዲቁን (ያላቅሙ ተንጠራርቶ የሚያወራ)፣ አል-ሙተፈይቂሁን። ” ሶሓቦችም ጠየቁት-“የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኛ ስለ አሥ-ሠርሣሩን እና አል-ሙተሸዲቁንን አወቅናቸው፣ ግን አል ሙተፈይቂሁን ማን እንደሆኑ አላወቅንም” እሳቸውም “ትዕቢተኞች/ ኩራተኛ ሰዎች” በማለት መለሱ።" ሲልሲለቱ አስሶሒሓህ 791

وعَنْ عَبْدِ اللَّهِ بْنِ عَمْرٍو رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا قَالَ: " لَمْ يَكُنِ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَاحِشًا وَلاَ مُتَفَحِّشًا" وَكَانَ يَقُولُ: (إِنَّ مِنْ خِيَارِكُمْ أَحْسَنَكُمْ أَخْلاَقًا)

ዐብደሏህ ኢብን ዐምር እንዲህ ብለዋል፡- "ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዋልጌም አይደሉም ፀያፍ ቃልም አይወጣቸውም፤" እንዲህም ይሉ ነበር፡- "ከናንተ ምርጦቹ ስነ ምግባራቸው ይበልጥ ያማሩት ናቸው።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 3559 እነዚህና ሌሎች የቁርአን አንቀፆችና የሐዲሥ ማስረጃዎች ሁሉ እስልምና በመልካም ስነምግባርና በበጎ ስራ የሚያዝና የሚያበረታታ መሆኑን የሚያስረዱ።

እስልምና ከሚያዝባቸው ነገሮች መካከል እውነተኝነት ይገኝበታል፤ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

(عَلَيْكُمْ بِالصِّدْقِ فَإِنَّ الصِّدْقَ يَهْدِي إِلَى الْبِرِّ وَإِنَّ الْبِرَّ يَهْدِي إِلَى الْجَنَّةِ وَمَا يَزَالُ الرَّجُلُ يَصْدُقُ وَيَتَحَرَّى الصِّدْقَ حَتَّى يُكْتَبَ عِنْدَ اللهِ صِدِّيقًا)

"እውነተኝነት ላይ አደራችሁን፤ እውነት ወደ መልካም ሥራ ይመራል፣ መልካም ሥራ ደግሞ ወደ ጀነት ይመራል፤ አንድ ሰው እውነትን መናገር እስከቀጠለ እና እውነትንም ዓላማው እስካደረገ ድረስ በአላህ ፊት እውነተኛ ሆኖ ይመዘገባል።" ሰሒሕ ሙስሊም 2607

እስልምና ከሚያዝባቸው ነገሮች መካከል አደራን መወጣት ይገኝበታል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُكُمْ أَن تُؤَدُّوا الْأَمَانَاتِ إِلَىٰ أَهْلِهَا}

{አላህ አደራዎቻችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንዳታደርሱ ያዛችኋል።} [ኒሳእ: 58]

እስልምና ከሚያዝባቸው ነገሮች መካከል ጥብቅነት ይገኝበታል፤ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«ثلاثة حق على الله عونهم: وذكر منهم: والناكح الذي يريد العفاف»

"ሶስቱን አላህ ሊረዳቸው ዋስትና አላቸው፤ ከነኝህም መካከል ጥብቅነትን ፈልጎ ትዳር የሚመሰርትን ጠቀሱ።" ሱነኑ ቲርሚዚይ 1655 ከነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ዱዓዎች መካከል እንዲህ ይሉ ነበር፦

«اللهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْهُدَى وَالتُّقَى وَالْعَفَافَ وَالْغِنَى»

"አላህ ሆይ ቅን መንገድ ምራቻን፣ ላንተ የሚገባ መፍራትን (ተቅዋ)፣ ጥብቅነትን እና መብቃቃትን እጠይቅሀለሁ።" ሰሒሕ ሙስሊም 2721

እስልምና ከሚያዝባቸው ነገሮች መካከል ሐያእ (አይነ አፋርነት) ይገኝበታል፤ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«الْحَيَاءُ لَا يَأْتِي إِلَّا بِخَيْرٍ»

"ሐያእ ይዞ የሚመጣው ኸይርን ብቻ ነው።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6117 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«لِكُلِّ دِينٍ خُلُقٌ وَخُلُقُ الْإِسْلَامِ الْحَيَاءُ»

"ለሁሉም ሃይማኖት የየራሱ ስነምግባር አለው፤ እስልምና የሚያላብሰው ሐያእን ነው።" በይሀቂይ በሹዐቡል ኢማን የሐዲሡን ሙሉ ሰነድ ዘግበውታል 6/2619

እስልምና ከሚያዝባቸው ነገሮች መካከል ጀግንነት ይገኝበታል፤ ከአነስ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ የሚል ተላልፏል፦

«كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَحْسَنَ النَّاسِ وَأَشْجَعَ النَّاسِ وَأَجْوَدَ النَّاسِ وَلَقَدْ فَزِعَ أَهْلُ المَدِينَةِ فَكَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ سَبَقَهُمْ عَلَى فَرَسٍ»

"ነቢዩ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ከሰዎች ሁሉ ደፋር እና ለጋስም ነበሩ። አንድ ጊዜ የመዲና ሰዎች በቁረይሾች ምክንያት በፍርሃት በተዋጡ ጊዜ ነቢዩ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ግን ፊት ለፊት ቀድመው ነው የነበሩት።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 2820 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም

በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከፈሪነት በአላህ ሲጠበቁ እንዲህ ይሉ ነበር፡-

«اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الجُبْنِ»

"አላህ ሆይ! እኔ ከፈሪነት ባንተ እጠበቃለሁ።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6374

እስልምና ከሚያዝባቸው ነገሮች መካከል ቸርነትና ለጋስነት ይገኝበታል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{مَّثَلُ الَّذِينَ يُنفِقُونَ أَمْوَالَهُمْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ كَمَثَلِ حَبَّةٍ أَنبَتَتْ سَبْعَ سَنَابِلَ فِي كُلِّ سُنبُلَةٍ مِّائَةُ حَبَّةٍ ۗ وَاللَّهُ يُضَاعِفُ لِمَن يَشَاءُ ۗ وَاللَّهُ وَاسِعٌ عَلِيمٌ }

{የእነዚያ ገንዘቦቻቸውን በአላህ መንገድ የሚለግሱ ሰዎች (ልግስና) ምሳሌ በየዘለላው ሁሉ መቶ ቅንጣት ያለባቸውን ሰባት ዘለላዎች እንደ አበቀለች አንዲት ቅንጣት ብጤ ነው። አላህም ለሚሻው ሰው (ከዚህ በላይ) ያነባብራል። አላህም ችሮታው ሰፊ ዐዋቂ ነው።} [አል-በቀራህ: 261] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ስነምግባራቸው ቸርነት ነበር፤ ከኢብኑ ዓባስ ረዲየሏሁ ዓንሁ እንዲህ የሚል ተላልፏል፡-

«كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَجْوَدَ النَّاسِ بِالْخَيْرِ وَكَانَ أَجْوَدُ مَا يَكُونُ فِي رَمَضَانَ حِينَ يَلْقَاهُ جِبْرِيلُ وَكَانَ جِبْرِيلُ عَلَيْهِ السَّلاَمُ يَلْقَاهُ كُلَّ لَيْلَةٍ فِي رَمَضَانَ حَتَّى يَنْسَلِخَ يَعْرِضُ عَلَيْهِ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ الْقُرْآنَ فَإِذَا لَقِيَهُ جِبْرِيلُ عَلَيْهِ السَّلاَمُ كَانَ أَجْوَدَ بِالْخَيْرِ مِنَ الرِّيحِ المُرْسَلَةِ»

"ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከሰዎች ሁሉ እጅግ በጣም ለጋስ ነበሩ፤ በይበልጥ ደግሞ በወርሀ ረመዷን ጂብሪል ሲመጣ የበለጠ ለጋስ ይሆኑ ነበር። ጂብሪል

በረመዳን በየምሽቱ ከእርሳቸው ጋር ቁርአንን ለመከለስ ያገኛቸው ነበር። የዚህ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ከተላከች ነፋስ የበለጠ ለጋስ ነበሩ።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 1902

እስልምና ከሚያዝባቸው መልካም ስነምግባሮች መካከል የተቸገረን መርዳትንና የወደመበትን መታደግን፣ የተራበን ማብላትን፣ መልካም ጉርብትናን፣ ዝምድና መቀጠልን፣ ለእንስሳት እንኳ ማዘንን በመሰሉ ምስጉን ስነምግባሮች ይገኙበታል።

فعَنْ عَبْدِ اللَّهِ بْنِ عَمْرٍو رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُمَا أَنَّ رَجُلًا سَأَلَ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: أَيُّ الإِسْلاَمِ خَيْرٌ؟ قَالَ: «تُطْعِمُ الطَّعَامَ وَتَقْرَأُ السَّلاَمَ عَلَى مَنْ عَرَفْتَ وَمَنْ لَمْ تَعْرِفْ»

ዐብደሏህ ኢብኑ ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁማ ባስተላለፈው ሐዲሥ አንድ ሰው ነብዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ሲል ጠየቃቸው: "የትኛው እስልምና ይበልጣል?" እርሳቸውም፦ "ሚስኪንን የምታበላበትና ለምታውቀውም ለማታውቀውም ሰላምታን የምታበዛበት።" አሉት። ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 12 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«بَيْنَمَا رَجُلٌ يَمْشِي بِطَرِيقٍ اشْتَدَّ عَلَيْهِ العَطَشُ فَوَجَدَ بِئْرًا فَنَزَلَ فِيهَا فَشَرِبَ ثُمَّ خَرَجَ فَإِذَا كَلْبٌ يَلْهَثُ يَأْكُلُ الثَّرَى مِنَ العَطَشِ فَقَالَ الرَّجُلُ: لَقَدْ بَلَغَ هَذَا الكَلْبَ مِنَ العَطَشِ مِثْلُ الَّذِي كَانَ بَلَغَ بِي فَنَزَلَ البِئْرَ فَمَلأَ خُفَّهُ ثُمَّ أَمْسَكَهُ بِفِيهِ فَسَقَى الكَلْبَ فَشَكَرَ اللَّهُ لَهُ فَغَفَرَ لَهُ» قَالُوا: يَا رَسُولَ اللَّهِ وَإِنَّ لَنَا فِي البَهَائِمِ أَجْرًا؟ فَقَالَ: «نَعَمْ فِي كُلِّ ذَاتِ كَبِدٍ رَطْبَةٍ أَجْرٌ»

ነቢዩ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል - “አንድ ሰው በመንገድ ላይ እያለ በጣም ተጠምቶ ነበር፣ እዚያም አንድ ጉድጓድ ገጠመው። ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ወርዶ ጠጥቶ ሲወጣ አንድ ውሻ እጅግ ወኃ ከመጠማቱ የተነሳ መሬቱን የሚልስ ውሻ አስተዋለ፤ ሰውየውም (ለራሱ)፦ “ይህ ውሻ እንደ እኔ በጥም እየተሰቃየ ነው” አለ። ስለዚህ እንደገና ወደ ጉድጓዱ ወርዶ ጫማውን በውሃ ሞልቶ አውጥቶ አጠጣው። አላህ ለዚያ ተግባር አመስግነውና እና (ወንጀሉን ማረለት) ይቅር አለው። ሶሐቦችም - “የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ሆይ! እንስሳትን (በመንከባከባችን) ለእኛ ምንዳ አለን? ሲሉ ጠየቁ። "እርሳቸውም “አዎን! ማንኛውንም ሕያው (ፍጡር) በመንከባከብ ምንዳ አለ” ሲሉ መለሰ። ሰሒሕ ኢብኑ ሒባን 544 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«السَّاعِي عَلَى الأَرْمَلَةِ وَالمِسْكِينِ كَالْمُجَاهِدِ فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَوِ القَائِمِ اللَّيْلَ الصَّائِمِ النَّهَارَ»

"ለመበለቲቱ (ባላቸው ለሞተባቸው) እና ችግረኞችን (ለመርዳት) የሚታገል ሰው በአላህ መንገድ እንደሚታገል ወይም በሌሊት ቆሞ እየሰገደ በቀን እየፆመ እንደሚኖር ሰው ነው።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 5353

እስልምና የዝምድና መብቶችን አረጋግጦ ዝምድናን መቀጠልንም ግዴታ ያደርጋል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{النَّبِيُّ أَوْلَىٰ بِالْمُؤْمِنِينَ مِنْ أَنفُسِهِمْ ۖ وَأَزْوَاجُهُ أُمَّهَاتُهُمْ ۗ وَأُولُو الْأَرْحَامِ بَعْضُهُمْ أَوْلَىٰ بِبَعْضٍ فِي كِتَابِ اللَّهِ مِنَ الْمُؤْمِنِينَ وَالْمُهَاجِرِينَ إِلَّا أَن تَفْعَلُوا إِلَىٰ أَوْلِيَائِكُم مَّعْرُوفًا ۚ كَانَ ذَٰلِكَ فِي الْكِتَابِ مَسْطُورًا}

{ነቢዩ በምእምናን ከነፍሶቻቸው ይበልጥ ተገቢ ነው። ሚስቶቹም እናቶቻቸው ናቸው። የዝምድና ባለቤቶችም ከፊላቸው በከፊሉ (ውርስ) በአላህ መጽሐፍ ውስጥ ከምእምናንና ከስደተኞቹ ይልቅ የተገባቸው ናቸው። ግን ወደ ወዳጆቻችሁ (በኑዛዜ) መልካምን ብትሰሩ (ይፈቀዳል)። ይህ በመጽሐፉ ውሰጥ የተመዘገበ ነው።} [አል-አሕዛብ: 6]

ዝምድናን ትስስር ከማቋረጥ አስጠንቅቋል ምድርን ከማበላሸት ጋር ከማገናኘት አቆራኝቶታል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{فَهَلْ عَسَيْتُمْ إِن تَوَلَّيْتُمْ أَن تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ وَتُقَطِّعُوا أَرْحَامَكُمْ (22) أُولَٰئِكَ الَّذِينَ لَعَنَهُمُ اللَّهُ فَأَصَمَّهُمْ وَأَعْمَىٰ أَبْصَارَهُمْ (23) }

{ብትሸሹም በምድር ላይ ማበላሸትን ዝምድናችሁንም መቁረጥን ከጀላችሁን?}

{እነዚህ እነዚያ አላህ የረገማቸው፣ ያደነቆራቸውም፣ ዓይኖቻቸውንም ያወራቸው ናቸው።} [ሙሓመድ: 22-23]

የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል: "ዝምድናን የሚቆርጥ ሰው ጀነት አይገባም።" ሰሒሕ ሙስሊም 2556 መቀጠሉ ግዴታ የሚሆነው ዝምድና፡- ወላጆች፣ ወንድሞች፣ እህቶች፣ በአባትም በእናትም በኩል ያሉ አጎቶችና በአባትም በእናትም በኩል ያሉ አክስቶች ናቸው።

እስልምና የጎረቤትን መብት ከህዷ ቢሆን እንኳን ያረጋግጣል (እንዲጠበቅ ያዛል)፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا ۖ وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا وَبِذِي الْقُرْبَىٰ وَالْيَتَامَىٰ وَالْمَسَاكِينِ وَالْجَارِ ذِي الْقُرْبَىٰ وَالْجَارِ الْجُنُبِ وَالصَّاحِبِ بِالْجَنبِ وَابْنِ السَّبِيلِ وَمَا مَلَكَتْ أَيْمَانُكُمْ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ مَن كَانَ مُخْتَالًا فَخُورًا}

{አላህንም ተገዙ። በእርሱም ምንንም አታጋሩ። በወላጆችና በቅርብ ዝምድና ባለቤትም፣ በየቲሞችም፣ በምስኪኖችም፣ በቅርብ ጎረቤትም፣ በሩቅ ጎረቤትም፣ በጎን ባልደረባም፣ በመንገደኛም፣ እጆቻችሁም ንብረት ባደረጓቸው (ባሮች)፣ መልካምን (ሥሩ)፤ አላህ ኩራተኛ ጉረኛ የኾነን ሰው አይወድም።} [አን-ኒሳእ: 36] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

(مَا زَالَ جِبْرِيلُ يُوصِينِي بِالْجَارِ حَتَّى ظَنَنْتُ أَنَّهُ سَيُوَرِّثُهُ)

"ጂብሪል ጉርብትናን በማስመልከት ውርስም ይገባዋል ይለኛ ይሆን እስክል ድረስ እኔን አደራ ከማለት አልተወገደም።" ሰሒሕ አቢ ዳውድ 5152

## 33- እስልምና ከሚጠጣም ሆነ ከሚበላ ነገር ጥሩውን (መልካም የሆነውን) ፈቅዷል፤ ልቦናንም ሆነ አካልን እንዲሁም መኖርያ ስፍራን ንፁህ ማድረግን አዟል፤ የአላህ ሰላትና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈን ነብያቶችም

## እንዳዘዙት ሁሉ ጋብቻን የተፈቀደ አድርጓል፤ እነርሱ በጥሩ ነገር ሁሉ የሚያዙ ናቸውና።

እስልምና ከሚበላም ሆነ ከሚጠጣ ነገር ጥሩ የሆነውን ሁሉ ፈቅዷል፤ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّ اللَّهَ طَيِّبٌ لَا يَقْبَلُ إِلاَّ الطَّيِّب وإِنَّ اللَّهَ أَمَرَ الْمُؤْمِنِينَ بِمَا أَمَرَ بِهِ الْمُرْسَلِينَ قَالَ تعالى: {يَا أَيُّهَا الرُّسُلُ كُلُوا مِنَ الطَّيِّبَاتِ وَاعْمَلُوا صَالِحًا إِنِّي بِمَا تَعْمَلُونَ عَلِيمٌ} وَقَالَ تعالى: {يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُلُوا مِنْ طِيِّبَاتِ مَا رَزَقْنَاكُمْ واشكروا لله إن كنتم إياه تعبدون} الآية قَالَ: ثُمَّ ذَكَرَ الرَّجُلَ يُطِيلُ السَّفَرَ أَشْعَثَ أَغْبَرَ يَمُدُّ يَدَيْهِ إِلَى السَّمَاءِ: يَا رَب يَا رَبِّ وَمَطْعَمُهُ حَرَامٌ وَمَلْبَسُهُ حَرَامٌ وَمَشْرَبُهُ حَرَامٌ وَغُذِّيَ بِالْحَرَامِ فَأَنَّى يُسْتَجَابُ لِذَلِكَ؟!»

እናንተ ሰዎች ሆይ! አላህ መልካም ነው፤ መልካሙን ብቻ ነው የሚቀበለው። አላህ መልእክተኞቹን ባዘዘበት ነገር አማኞችንም አዟል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡- "እናንተ መልክተኞች ሆይ! ከተፈቀዱት ምግቦች ብሉ። በጎ ሥራንም ሥሩ። እኔ የምተሠሩትን ሁሉ ዓዋቂ ነኝ።" እንዲህም ብሏል፡- "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮች ብሉ። ለአላህም እርሱን ብቻ የምትገዙ እንደሆናችሁ አመስግኑ።" (የሐዲሡ አስተላላፊ ሓዲሡን እንዲህ በማለት ቀጠለ) "ከዚያም ፀጉሩ የተንጨባረረ እና አቧራማ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ረጅም ጉዞ ስለሚያደርግ ሰው አወሱ፤ (ይህ ሰው ምግቡ፣ መጠጡና ልብሱ ከሐራም በሆነበት ሁኔታ) “ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ!” እያለ እጆቹን ወደ ሰማይ ዘርግቶ ይለምናል፤ የሚበላው ሓራም! የለበሰው ሓራም!

የሚጠጣው ሐራም! ሁለመናው በሐራም የተገነባ ሆኖ ሳለ አላህ እንዴት ዱዓውን ሊቀበለው ይችላል!? ሰሒሕ ሙስሊም 1015 ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{قُلْ مَنْ حَرَّمَ زِينَةَ اللَّهِ الَّتِي أَخْرَجَ لِعِبَادِهِ وَالطَّيِّبَاتِ مِنَ الرِّزْقِ ۚ قُلْ هِيَ لِلَّذِينَ آمَنُوا فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا خَالِصَةً يَوْمَ الْقِيَامَةِ ۗ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ الْآيَاتِ لِقَوْمٍ يَعْلَمُونَ}

«የአላህን ጌጥ ያችን ለባሮቹ የፈጠራትን ከሲሳይም ጥሩዎቹን እርም ያደረገ ማን ነው» በላቸው። «እርሷ በትንሣኤ ቀን ለእነዚያ ላመኑት ብቻ ስትኾን በቅርቢቱ ሕይወት ተገቢያቸው ናት» በላቸው። እንደዚሁ ለሚያውቁ ሕዝቦች አንቀጾችን እናብራራለን።» [አል-አዕራፍ: 32]

እስልምና የልብን፣ የአካልንና የቤት ንፅህናን አዟል፤ ለዚህም ጋብቻን ፈቅዷል፣ ልክ በዚህ መልኩ ነቢያትና ሩሱሎችን የአላህ ሰላትና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈን አዟል፤ እነርሱ መልካም ነገሮችን ሁሉ ያዛሉና። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَاللَّهُ جَعَلَ لَكُمْ مِنْ أَنْفُسِكُمْ أَزْوَاجًا وَجَعَلَ لَكُمْ مِنْ أَزْوَاجِكُمْ بَنِينَ وَحَفَدَةً وَرَزَقَكُمْ مِنَ الطَّيِّبَاتِ أَفَبِالْبَاطِلِ يُؤْمِنُونَ وَبِنِعْمَتِ اللَّهِ هُمْ يَكْفُرُونَ}

{አላህም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ለእናንተ ሚስቶችን አደረገ። ለእናንተም ከሚስቶቻችሁ ወንዶች ልጆችን፣ የልጅ ልጆችንም አደረገላችሁ። ከመልካሞችም ጸጋዎች ሰጣችሁ። ታድያ በውሸት (በጣኦት) ያምናሉን በአላህም ጸጋ እነሱ ይክዳሉን} [አን-ነሕል: 72] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَثِيَابَكَ فَطَهِّرْ (4) وَالرُّجْزَ فَاهْجُرْ (5) }

{ልብስህንም አጥራ።}

{ጣዖትንም ራቅ።} [አል-ሙደሢር: 4-5] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

(لَا يَدْخُلُ الْجَنَّةَ مَنْ كَانَ فِي قَلْبِهِ مِثْقَالُ ذَرَّةٍ مِنْ كِبْرٍ. قَالَ رَجُلٌ: إِنَّ الرَّجُلَ يُحِبُّ أَنْ يَكُونَ ثَوْبُهُ حَسَنًا وَنَعْلُهُ حَسَنَةً قَالَ: إِنَّ اللهَ جَمِيلٌ يُحِبُّ الْجَمَالَ الْكِبْرُ بَطَرُ الْحَقِّ وَغَمْطُ النَّاسِ)

"በልቡ ውስጥ የሰናፍጭ ቅንጣትክብደት ያክል ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም። አንድ ሰው (ከሱሓቦች መካከል) እንዲህ አለ - "በእርግጥ አንድ ሰው ልብሱ ጥሩ እንዲሆን፣ ጫማውም ጥሩ እንዲሆኑ ይወዳል።" ሲላቸው ነቢዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ አሉት - "በእርግጥ አላህ ውብ ነው ውበትንም ይወዳል። ኩራት ማለት እውነትን አለመቀበልና ሰውን መናቅ ነው።" ሰሒሕ ሙስሊም 91

## 34- እስልምና በአላህ ማጋራት፣ ክህደት፣ የጣኦት አምልኮ፣ በአላህ ላይ ያለ እውቀት መናገር፣ ልጅን መግደል፣ ክቡር የሆነችውን የሰውን ልጅ ነፍስ ማጥፋት፣ በምድር ላይ ማበላሸት፣ ድግምት፣ ግልፅም ይሁን ድብቅ ብልግና፣ ዝሙት፣ ግብረሶዶም፣ ወለድ መብላትንም ከልክሏል፣ የበከተን ስጋ፣ ለጣኦታትና ለቅርፃ ቅርፅ ተብሎ የታረደን ስጋ

**እና የአሳማ ስጋን መብላት እና ሌሎችም ርኩስና ቆሻሻን ሁሉ ከልክሏል፤ ወላጁን ያጣን (የቲም) ልጅ ንብረት መብላት፣ ሚዛንና መለኪያን ማዛባት፣ ዝምድና መቁረጥን የመሰሉ የሐራም (እርም) ነገሮች መሰረት የሆኑትን ይከለክላል። ሁሉም ነብያቶችም እነዚህ የተዘረዘሩት የተከለከሉ ሐራም መሆናቸው ላይ ይስማማሉ።**

እስልምና በአላህ ማጋራት፣ ክህደትንና ጣኦት አምላኪነትን፣ ስለ አላህ ያለበቂ እውቀት መናገር፣ ልጆችን መግደልን መሰል የሆኑ የሐራም መሰረቶችን ከልክሏል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ تَعَالَوۡاْ أَتۡلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمۡ عَلَيۡكُمۡۖ أَلَّا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗاۖ
وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُم مِّنۡ إِمۡلَٰقٖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُكُمۡ وَإِيَّاهُمۡۖ وَلَا تَقۡرَبُواْ ٱلۡفَوَٰحِشَ مَا
ظَهَرَ مِنۡهَا وَمَا بَطَنَۖ وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ ذَٰلِكُمۡ
وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ وَلَا تَقۡرَبُواْ مَالَ ٱلۡيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ حَتَّىٰ
يَبۡلُغَ أَشُدَّهُۥۚ وَأَوۡفُواْ ٱلۡكَيۡلَ وَٱلۡمِيزَانَ بِٱلۡقِسۡطِۖ لَا نُكَلِّفُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَاۖ وَإِذَا
قُلۡتُمۡ فَٱعۡدِلُواْ وَلَوۡ كَانَ ذَا قُرۡبَىٰۖ وَبِعَهۡدِ ٱللَّهِ أَوۡفُواْۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ
تَذَكَّرُونَ}

{«ኑ፤ ጌታችሁ በእናንተ ላይ እርም ያደረገውን ነገር (በእርሱም ያዘዛችሁን) ላንብብላችሁ» በላቸው። «በእርሱ (በአላህ) ምንንም ነገር አታጋሩ። ለወላጆችም በጎን ሥራ (ሥሩ)። ልጆቻችሁንም ከድህንት (ፍራቻ) አትግደሉ። እኛ እናንተንም እነርሱንም እንመግባችኋለንና። መጥፎ

ሥራዎችንም ከእርሷ የተገለጸውንም የተደበቀውንም ሁሉ አትቅረቡ። ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በሕግ ቢኾን እንጅ አትግደሉ። ይህን ታውቁ ዘንድ (አላህ) በእርሱ አዘዛችሁ።»}

{«የየቲምንም ገንዘብ ብርታቱን (አካለ መጠን) እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በኾነች ኹኔታ እንጅ አትቅረቡ። ስፍርንና ሚዛንንም በትክክሉ ሙሉ። ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድም። በተናገራችሁም ጊዜ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢኾንም እንኳ (እውነትን በመናገር) አስተካክሉ። በአላህም ቃል ኪዳን ሙሉ። እነሆ ትገሰጹ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ።»} [አል-አንዓም: 151-152] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{قُلْ إِنَّمَا حَرَّمَ رَبِّيَ الْفَوَاحِشَ مَا ظَهَرَ مِنْهَا وَمَا بَطَنَ وَالْإِثْمَ وَالْبَغْيَ بِغَيْرِ الْحَقِّ وَأَن تُشْرِكُوا بِاللَّهِ مَا لَمْ يُنَزِّلْ بِهِ سُلْطَانًا وَأَن تَقُولُوا عَلَى اللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ}

{«ጌታዬ እርም ያደረገው መጥፎ ሥራዎችን፣ ከርሷ የተገለጸውንና የተደበቀውን ኃጢአትንም፣ ያላግባብ መበደልንም፣ በርሱም ማስረጃ ያላወረደበትን (ጣዖት) በአላህ ማጋራታችሁን፣ በአላህም ላይ የማታውቁትን መናገራችሁን ብቻ ነው» በላቸው።} [አል-አዕራፍ: 33]

እስልምና የተከበረች ነፍስ ማጥፋትን ሐራም (እርም) አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۗ وَمَن قُتِلَ مَظۡلُومٗا فَقَدۡ جَعَلۡنَا لِوَلِيِّهِۦ سُلۡطَٰنٗا فَلَا يُسۡرِف فِّي ٱلۡقَتۡلِۖ إِنَّهُۥ كَانَ مَنصُورٗا}

{ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ። የተበደለም ኾኖ የተገደለ ሰው ለዘመዱ (በገዳዩ ላይ) በእርግጥ ስልጣንን አድርገናል። በመግደልም ወሰንን አይለፍ፤ እርሱ የተረዳ ነውና።} [አል-ኢስራእ: 33] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَالَّذِينَ لَا يَدْعُونَ مَعَ اللَّهِ إِلَٰهًا آخَرَ وَلَا يَقْتُلُونَ النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ وَلَا يَزْنُونَ ۚ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ يَلْقَ أَثَامًا }

{እነዚያም ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የማይገዙት፣ ያችንም አላህ እርምም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ የማይገድሉት፣ የማያመነዝሩትም ናቸው። ይህንንም የሚሠራ ሰው ቅጣትን ያገኛል።} [አል-ፉርቃን: 68]

እስልምና በምድር ላይ ብክለትን (ብልሹነት መፍጠርን) ሐራም አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا}

{በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ።} [አል-አዕራፍ: 56]

وقال الله تعالى مخبراً عن النبي شعيب عليه السلام أن قال لقومه: {يَا قَوْمِ اعْبُدُوا اللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُ ۖ قَدْ جَاءَتْكُم بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ ۖ فَأَوْفُوا الْكَيْلَ وَالْمِيزَانَ وَلَا تَبْخَسُوا النَّاسَ أَشْيَاءَهُمْ وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا ۚ ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ}

ነብዩሏህ ሹዐይብ ለህዝባቸው እንዲህ ማለታቸውን የላቀው አላህ በዚህ መልኩ ነግሮናል፦

{ወደ መድየንም (ምድያን) ወንድማቸውን ሹዓይብን (ላክን)፤ አላቸው፦ «ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ

በቀር ምንም አምላክ የላችሁም። ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ በእርግጥ መጥታላችኋለች። ስፍርንና ሚዛንን ሙሉ። ሰዎችንም አንዳቾቻቸውን (ገንዘቦቻቸውን) አታጉድሉባቸው። በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ። ይህ ምእምናን እንደኾናችሁ ለእናንተ የተሻለ ነው።»} [አል-አዕራፍ 85]

እስልምና ድግምትን ሐራም አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَأَلْقِ مَا فِي يَمِينِكَ تَلْقَفْ مَا صَنَعُوٓاْۖ إِنَّمَا صَنَعُواْ كَيْدُ سَٰحِرٖۖ وَلَا يُفْلِحُ ٱلسَّاحِرُ حَيْثُ أَتَىٰ}

{«በቀኝ እጅህ ያለቻውንም በትር ጣል። ያንን የሠሩትን ትውጣለችና። ያ የሠሩት ሁሉ የድግምተኛ ተንኮል ነውና። ድግምተኛም በመጣበት ስፍራ ሁሉ አይቀናውም» (አልን)።} [ጧሀ: 69] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«اجْتَنِبُوا السَّبْعَ المُوبِقَاتِ قَالُوا: يَا رَسُولَ اللَّهِ وَمَا هُنَّ؟ قَالَ: الشِّرْكُ بِاللَّهِ وَالسِّحْرُ وَقَتْلُ النَّفْسِ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالحَقِّ وَأَكْلُ الرِّبَا وَأَكْلُ مَالِ اليَتِيمِ وَالتَّوَلِّي يَوْمَ الزَّحْفِ وَقَذْفُ المُحْصَنَاتِ المُؤْمِنَاتِ الغَافِلاَتِ»

"ሰባቱ የሰው ልጆችን አጥፊዎች በመባል የታወቁ ከባድ ኃጢአቶችን ተጠንቀቁ (ሰባት አጥፊ ወንጀሎችን ተጠንቀቁ)፤ (ሰሐቦችም) የአላህ መልእክተኛ ሆይ ምን ምን ናቸው? አሉ። እርሳቸውም፦ በአላህ ማጋራት፥ ድግምት፥ አላህ ክልክል ያደረጋትን ነፍስ ያለ አግባብ ማጥፋት፥ የየቲሞችን (ወላጅ አባታቸው የሞተባቸውን ታዳጊዎችን)

ገንዘብ መብላት፣ ወለድ (አራጣ) መብላት፣ ከተፋፋመ ጦርነት ማፈግፈግ፣ ጥብቅ (ንፁህ) የሆኑ ሴቶችን በዝሙት ማነወር (መወንጀል) ናቸው።" አሉ። ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6857

እስልምና ድብቅም ግልፅም የሆነ ብልግናን፣ ግብረ ሶዶማዊነትን ሐራም አድርጓል፤ ይህንን በማስመልከትም በዚሁ ቅፅ መጀመርያ አካባቢ ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ የቁርአን ማስረጃዎችን አሳልፈናል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَذَرُوا مَا بَقِيَ مِنَ الرِّبَا إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ (278) فَإِن لَّمْ تَفْعَلُوا فَأْذَنُوا بِحَرْبٍ مِّنَ اللَّهِ وَرَسُولِهِ ۖ وَإِن تُبْتُمْ فَلَكُمْ رُءُوسُ أَمْوَالِكُمْ لَا تَظْلِمُونَ وَلَا تُظْلَمُونَ (279)}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። ከአራጣም የቀረውን ተዉ። አማኞች እንደኾናችሁ (ተጠንቀቁ)።}

{(የታዘዛችሁትን) ባትሠሩም ከአላህና ከመልክተኛው በኾነች ጦር (መወጋታችሁን) ዕወቁ። ብትጸጸቱም ለእናንተ የገንዘቦቻችሁ ዋናዎች አሏችሁ። አትበድሉም አትበደሉምም።} [አል-በቀራህ: 278-279] አላህ የአራጣን የሚበላ ሰው ላይ የዛተበትን ያክል የትኛውም አመፀኛ ላይ አልዛተም፤ ይህም የሆነው በአራጣ ምክንያት የሃይማኖቶች፣ የአገራት፣ የገንዘብ እና የሕይወት ውድመት ስላለ ነው።

እስልምና የበከተ ስጋ፣ ለጣኦት የታረደን እና የአሳማ ስጋ መብላትን ሐራም አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{حُرِّمَتْ عَلَيْكُمُ الْمَيْتَةُ وَالدَّمُ وَلَحْمُ الْخِنزِيرِ وَمَا أُهِلَّ لِغَيْرِ اللَّهِ بِهِ وَالْمُنْخَنِقَةُ وَالْمَوْقُوذَةُ وَالْمُتَرَدِّيَةُ وَالنَّطِيحَةُ وَمَا أَكَلَ السَّبُعُ إِلَّا مَا ذَكَّيْتُمْ وَمَا ذُبِحَ عَلَى النُّصُبِ وَأَن تَسْتَقْسِمُوا بِالْأَزْلَامِ ۚ ذَٰلِكُمْ فِسْقٌ }

{በክት፣ ፈሳሽ ደምም፣ የእሪያ (አሣማ) ሥጋም፣ በርሱ ከአላህ (ስም) ሌላ የተነሳበትም፣ የታነቀችም፣ ተደብድባ የተገደለችም፣ ተንከባላ የሞተችም፣ በቀንድ ተውግታ የሞተችም፣ ከርሷ አውሬ የበላላትም (ከእነዚህ በህይወት ደርሳችሁ) ያረዳችሁት ብቻ ሲቀር ለጣዖታትም የታረደው በአዝላምም ዕድልን መፈለጋችሁ በእናንተ ላይ እርም ተደረገ።} [አል ማኢዳህ 3]

እስልምና አስካሪ መጠጥንም ሆነ ነጃሳና ቆሻሻ ነገራቶችን ሁሉ መጠጣትን ሐራም አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنَّمَا الْخَمْرُ وَالْمَيْسِرُ وَالْأَنصَابُ وَالْأَزْلَامُ رِجْسٌ مِّنْ عَمَلِ الشَّيْطَانِ فَاجْتَنِبُوهُ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ (90) إِنَّمَا يُرِيدُ الشَّيْطَانُ أَن يُوقِعَ بَيْنَكُمُ الْعَدَاوَةَ وَالْبَغْضَاءَ فِي الْخَمْرِ وَالْمَيْسِرِ وَيَصُدَّكُمْ عَن ذِكْرِ اللَّهِ وَعَنِ الصَّلَاةِ ۖ فَهَلْ أَنتُم مُّنتَهُونَ (91)}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው። (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና።}

{ሰይጣን የሚፈልገው በሚያሰክር መጠጥና በቁማር በመካከላችሁ ጠብንና ጥላቻን ሊጥል አላህን ከማውሳትና ከስግደትም ሊያግዳችሁ ብቻ ነው። ታዲያ እናንተ (ከእነዚህ) ተከልካዮች ናችሁን (ተከልከሉ)።} [አል-ማኢዳህ: 90-91]

በአንቀፅ ቁጥር (31) ላይ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በተውራትና ኢንጂል ካላቸው መገለጫ መካከል ቆሻሻ ነገርን ሁሉ የሚከለክል መሆኑን ጠቅሰን አሳልፈናል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ الَّذِينَ يَتَّبِعُونَ الرَّسُولَ النَّبِيَّ الْأُمِّيَّ الَّذِي يَجِدُونَهُ مَكْتُوبًا عِندَهُمْ فِي التَّوْرَاةِ وَالْإِنجِيلِ يَأْمُرُهُم بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَاهُمْ عَنِ الْمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ الطَّيِّبَاتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيْهِمُ الْخَبَائِثَ وَيَضَعُ عَنْهُمْ إِصْرَهُمْ وَالْأَغْلَالَ الَّتِي كَانَتْ عَلَيْهِمْ ۚ}

{ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት (በእርግጥ እጽፍለታለሁ)። በበጎ ሥራ ያዘቸዋል። ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል። መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል። መጥፎ ነገሮችንም በእነርሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከእነሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በእነርሱ ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) ያነሳላቸዋል። እነዚያም በእርሱ ያመኑ ያከበሩትም የረዱትም ያንንም ከእርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ እነዚያ እነሱ የሚያድኑ ናቸው።} [አል-አዕራፍ: 157]

እስልምና (የተከበረች) የየየቲምን ገንዘብ መብላትን ሐራም አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَآتُوا الْيَتَامَىٰ أَمْوَالَهُمْ ۖ وَلَا تَتَبَدَّلُوا الْخَبِيثَ بِالطَّيِّبِ ۖ وَلَا تَأْكُلُوا أَمْوَالَهُمْ إِلَىٰ أَمْوَالِكُمْ ۚ إِنَّهُ كَانَ حُوبًا كَبِيرًا}

{የቲሞችንም ገንዘቦቻቸውን ስጡ። መጥፎውንም በመልካሙ አትለውጡ። ገንዘቦቻቸውንም ወደ ገንዘቦቻችሁ (በመቀላቀል) አትብሉ እርሱ ታላቅ ኃጢአት ነውና።} [አን-ኒሳእ: 2] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ الَّذِينَ يَأْكُلُونَ أَمْوَالَ الْيَتَامَىٰ ظُلْمًا إِنَّمَا يَأْكُلُونَ فِي بُطُونِهِمْ نَارًا ۖ وَسَيَصْلَوْنَ سَعِيرًا}

{እነዚያ የየቲሞችን ገንዘብ በመበደል የሚበሉ በሆዶቻቸው ውስጥ የሚበሉት እሳትን ብቻ ነው። እሳትንም በእርግጥ ይገባሉ።} [አን-ኒሳእ: 10]

እስልምና በመለኪያና በሚዛን ማዛነፍን ሐራም አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَيْلٌ لِّلْمُطَفِّفِينَ (1) الَّذِينَ إِذَا اكْتَالُوا عَلَى النَّاسِ يَسْتَوْفُونَ (2) وَإِذَا كَالُوهُمْ أَو وَّزَنُوهُمْ يُخْسِرُونَ (3) أَلَا يَظُنُّ أُولَٰئِكَ أَنَّهُم مَّبْعُوثُونَ (4)}

{ለሰላቢዎች ወዮላቸው።}

{ለእነዚያ ከሰዎች ባስሰፈሩ ጊዜ የሚያስሞሉ።}

{ለእነርሱም (ለሰዎቹ) በሰፈሩ ወይም በመዘኑላቸው ጊዜ የሚያጎድሉ (ለኾኑት)።}

{እነዚያ እነርሱ ተቀስቃሾች መኾናቸውን አያውቁምን?} [አል-ሙጠፊፊን: 1-4]

እስልምና ዝምድና መቁረጥን ሐራም አድርጓል። ይህንንም በማስመልከት በአንቀፅ ቁጥር (31) ላይ ይህንን የሚያመላክቱ የቁርአንና የሓዲሥ ማስረጃዎችን እንዲሁም ነብያቶችና ሩሱሎችም ሁሉ እነኚህ ነገራቶች ሐራም

መሆናቸው ላይ ሙሉ ስምምነት እንዳላቸው ጠቅሰን አሳልፈናል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

## 35- እስልምና እንደ ውሸት፣ ማታለል፣ መካድ፣ ክፋትን ማመርቀዝ፣ ምቀኝነት፣ መጥፎ ተንኮል፣ ስርቆት፣ ድንበር ማለፍንና ሰዎችን መበደልን ከመሰሉ የተወገዙ ስነምግባሮችና መጥፎ ማንነቶች ሁሉ ይከለክላል።

እስልምና ከተወገዙ ባህሪዎች ይከለክላል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَلَا تُصَعِّرۡ خَدَّكَ لِلنَّاسِ وَلَا تَمۡشِ فِي ٱلۡأَرۡضِ مَرَحًاۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخۡتَالٖ فَخُورٖ}

{«ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር። በምድርም ላይ ተንበጥርረህ አትሂድ። አላህ ተንበጥራሪን ጉረኛን ሁሉ አይወድምና።} [ሉቅማን: 18] የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል:-

« إنَّ من أحبِّكم إليَّ وأقربِكم منِّي مجلسًا يومَ القيامةِ أحاسنَكُم أخلاقًا وإنَّ أبغضَكم إليَّ وأبعدَكم منِّي مجلسًا يومَ القيامةِ الثَّرثارونَ والمتشدِّقونَ والمتفَيهِقون قالوا يا رسولَ اللَّهِ قد علِمنا الثَّرثارونَ والمتشدِّقونَ فما المتفَيهِقونَ قالَ المتكبِّرونَ »

"በእለተ ትንሣኤ ከእናንተ ዘንድ በጣም የተወደደው እና ለኔም በጣም ቅርብ የሆነው በመልካም ሥነ ምግባር ከእናንተ በላጭ የሆነ ነው፤ ከእናንተ መካከል እኔ ዘንድ በጣም የተጠላውና ከእኔም የራቀው ደግሞ አሥ-ሠርሣሩን

(ራሱን እያስጨነቀ ብዙ የሚያወራ)፣ አል-መተሸዲቁን (ያላቅሙ ተንጠራርቶ የሚያወራ)፣ አል-ሙተፈይቂሁን። " ሶሓቦችም ጠየቁት-"የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኛ አሡ-ሠርሣሩን እና አል-ሙተሸዲቁንን አወቅናቸው፣ ግን አል ሙተፈይቂሁን ማን እንደሆኑ አላወቅንም" እሳቸውም "ትዕቢተኞች /ኩራተኛ/ ሰዎች" በማለት መለሱ።" ሲልሲለቱ ሶሒሓህ: 791

እስልምና ውሸትንም ይከለክላል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል:-

{ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِي مَنْ هُوَ مُسْرِفٌ كَذَّابٌ}

{አላህ ያንን እርሱ ድንበር አላፊ ውሸታም የኾነውን አይመራምና።} [ጋፊር: 28] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል:-

«وَإِيَّاكُمْ وَالْكَذِبَ فَإِنَّ الْكَذِبَ يَهْدِي إِلَى الْفُجُورِ وَإِنَّ الْفُجُورَ يَهْدِي إِلَى النَّارِ وَمَا يَزَالُ الرَّجُلُ يَكْذِبُ وَيَتَحَرَّى الْكَذِبَ حَتَّى يُكْتَبَ عِنْدَ اللهِ كَذَّابًا»

"ውሸትን ተጠንቀቁ፤ ውሸት ወደ ትእቢት ይመራል፣ ትብኢት ደግሞ የሚመራው ወደ ጀሀነም ነው፤ አንድ ሰው ውሸት በመናገር ላይ እስከዘወተረ እና ውሸንም በመምረጥ እስከቀጠለ ድረስ በአላህ ፊት ውሸታም ሆኖ ይመዘገባል።" ሰሒሕ ሙስሊም 2607 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል:-

«آيَةُ الْمُنَافِقِ ثَلاَثٌ: إِذَا حَدَّثَ كَذَبَ وَإِذَا وَعَدَ أَخْلَفَ وَإِذَا اؤْتُمِنَ خَانَ»

"የሙናፊቅ ምልክቱ ሶስት ነው፤ ሲናገር ይዋሻል፣ ቃል ሲገባ ቃሉን ያፈርሳል፣ ሲታመን ይክዳል።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6095

እስልምና ማጭበርበርን ሐራም (እርም) አድርጓል።

وجاء في الحديث أن رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ مَرَّ عَلَى صُبْرَةِ طَعَامٍ فَأَدْخَلَ يَدَهُ فِيهَا فَنَالَتْ أَصَابِعُهُ بَلَلًا فَقَالَ: «مَا هَذَا يَا صَاحِبَ الطَّعَامِ؟» قَالَ أَصَابَتْهُ السَّمَاءُ يَا رَسُولَ اللهِ قَالَ: أَفَلَا جَعَلْتَهُ فَوْقَ الطَّعَامِ كَيْ يَرَاهُ النَّاسُ مَنْ غَشَّ فَلَيْسَ مِنِّي»

በሓዲሡ እንዲህ የሚል ተላልፎ እናገኛለን፦ የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) በአንድ ወቅት በእህል ክምር እያለፉ እጃቸውን ወደ ውስጥ ሲያስገቡ ጣታቸው ትንሽ እርጥበት ተሰማቸውና “የእህሉ ባለቤት ሆይ ይህ ምንድን ነው?” ሲሉ ጠየቁት። እርሱም “የአላህ መልእክተኛ ሆይ ዝናብ አግኝቶት ነው።” ሲል መለሰ። እርሳቸውም "ታድያ (እርጥበቱን ክፍል) ሰዎች እንዲያዩት በእህሉ ላይ ለምን አላስቀመጥከውም?፤ ያታለለ ከእኔ አይደለም" አሉ። ሰሒሕ ሙስሊም 102

እስልምና ሰዎችን መሸወድ፣ ተንኮልንና ማታለልን ሐራም አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَخُونُوا اللَّهَ وَالرَّسُولَ وَتَخُونُوا أَمَانَاتِكُمْ وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ }

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህንና መልክተኛውን አትክዱ። አደራዎቻችሁንም እናንተ እያወቃችሁ አትክዱ።} [አል-አንፋል: 27] አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ ٱلَّذِينَ يُوفُونَ بِعَهۡدِ ٱللَّهِ وَلَا يَنقُضُونَ ٱلۡمِيثَٰقَ}

{እነዚያ በአላህ ቃል ኪዳን የሚሞሉ የጠበቀውንም ኪዳን የማያፈርሱ ናቸው።} [አር-ራዕድ: 20] የአላህ

መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሰራዊታቸው ሲዘምቱ እንዲህ ይሏቸው ነበር፡-

«اغْزُوا وَلَا تَغُلُّوا وَلَا تَغْدِرُوا وَلَا تَمْثُلُوا وَلَا تَقْتُلُوا وَلِيدًا»

"ዝመቱ! ምርኮን አትሸፍጡ፣ አትካዱ፣ አካል ጉዳተኛ ወይንም የሞተን አስከሬን አታንገላቱ፣ ታዳጊ ልጅንም አትግደሉ።" ሰሒሕ ሙስሊም 1731 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«أَرْبَعٌ مَنْ كُنَّ فِيهِ كَانَ مُنَافِقًا خَالِصًا وَمَنْ كَانَتْ فِيهِ خَصْلَةٌ مِنْهُنَّ كَانَتْ فِيهِ خَصْلَةٌ مِنَ النِّفَاقِ حَتَّى يَدَعَهَا: إِذَا اؤْتُمِنَ خَانَ وَإِذَا حَدَّثَ كَذَبَ وَإِذَا عَاهَدَ غَدَرَ وَإِذَا خَاصَمَ فَجَرَ»

"አራት (ባሕርያት) በእርሱ ላይ ያለበት ሰው ጥርት ያለ ሙናፊቅ ሆኗል፤ ከአራቱ ባህሪዎች ውስጥ አንዱ ያለበት ደግሞ እስካልተወውና እስከሚያቆም ድረስ አንድ የሙናፊቅ ባህሪ ይኖረዋል፡- ሲያምኑት ይክዳል፣ ሲናገር ይዋሻል፣ ቃል ኪዳን ሲገባ ቃሉን ያፈርሳል፣ ሲከራከር ያፈነግጣል።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 34

እስልምና ምቀኝነትን ይከለክላል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{أَمْ يَحْسُدُونَ النَّاسَ عَلَىٰ مَا آتَاهُمُ اللَّهُ مِن فَضْلِهِ ۖ فَقَدْ آتَيْنَا آلَ إِبْرَاهِيمَ الْكِتَابَ وَالْحِكْمَةَ وَآتَيْنَاهُم مُّلْكًا عَظِيمًا}

{ይልቁንም ሰዎችን (ሙሐመድን) አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ላይ ይመቀኛሉን ለኢብራሂምም ቤተሰቦች መጽሐፍንና ጥበብን በእርግጥ ሰጠን ታላቅንም ንግሥና

ሰጠናቸው።} [አን-ኒሳእ: 54] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَدَّ كَثِيرٌ مِّنْ أَهْلِ الْكِتَابِ لَوْ يَرُدُّونَكُم مِّن بَعْدِ إِيمَانِكُمْ كُفَّارًا حَسَدًا مِّنْ عِندِ أَنفُسِهِم مِّن بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُمُ الْحَقُّ ۖ فَاعْفُوا وَاصْفَحُوا حَتَّىٰ يَأْتِيَ اللَّهُ بِأَمْرِهِ ۗ إِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ}

{ከመጽሐፉ ባለቤቶች ብዙዎች እውነቱ ከተገለጸላቸው በኋላ ከነፍሶቻቸው በኾነው ምቀኝነት ከእምነታችሁ በኋላ ከሓዲዎች አድርገው ሊመልሱዋችሁ ተመኙ። አላህም ትዕዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ይቅርታ አድርጉ፤ እለፏቸውም። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ከሃሊ ነውና።} [አል-በቀራህ: 109] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«دَبَّ إِلَيْكُمْ دَاءُ الأُمَمِ قَبْلَكُمْ: الحَسَدُ وَالبَغْضَاءُ هِيَ الحَالِقَةُ لَا أَقُولُ تَحْلِقُ الشَّعَرَ وَلَكِنْ تَحْلِقُ الدِّينَ وَالَّذِي نَفْسِي بِيَدِهِ لَا تَدْخُلُوا الجَنَّةَ حَتَّى تُؤْمِنُوا وَلَا تُؤْمِنُوا حَتَّى تَحَابُّوا أَفَلَا أُنَبِّئُكُمْ بِمَا يُثَبِّتُ ذَلِكَ لَكُمْ؟ أَفْشُوا السَّلَامَ بَيْنَكُمْ»

"ከናንተ በፊት የነበረው የቀደምቶች በሽታ፣ ቅናትና ጥላቻ ወደናንተ መጣ። ጥላቻ "መላጩ" (አጥፊ) ነው። እኔ ፀጉር ይላጫል አይደለም የምላችሁ ይልቁንም የሃይማኖታዊ ቁርጠኝነት መላጫ (አጥፊ) ነች። ነፍሴ በእጁ በሆነችው እምላለሁ፦ እስክታምኑ ድረስ ጀነት አትገቡም፤ እርስ በርሳችሁም እስክትዋደዱ ድረስ አታምኑም። ያንን ለማሳካት የሚረዳዎችሁን ነገር አልነግራችሁምን? ሰላምታ በመካከላችሁ አብዙ (አሰራጩ)።" ሱነኑ ቲርሚዚይ 2510

እስልምና ክፉ ተንኮልን ሐራም (እርም) አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَكَذَٰلِكَ جَعَلْنَا فِي كُلِّ قَرْيَةٍ أَكَابِرَ مُجْرِمِيهَا لِيَمْكُرُوا فِيهَا ۖ وَمَا يَمْكُرُونَ إِلَّا بِأَنفُسِهِمْ وَمَا يَشْعُرُونَ}

{እንደዚሁም በየከተማይቱ በውስጧ ያሴሩ ዘንድ የተንኮለኞችዋን ታላላቆች አደረግን። በነፍሶቻቸውም ላይ እንጅ በሌላ ላይ አያሴሩም፤ ግን አያውቁም።} [አል-አንዓም: 123] የላቀው አላህ አይሁዶች መሲሑ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንን ለመግደል አሲረው እንደነበርና ነገር ግን በአፀፋው አላህ እነርስኑ እንዳታለላቸው እንዲሁም መጥፎ ተንኮል በባለቤቱ ላይ ብቻ እንደሚደርስ ግልፅ አድርጓል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{فَلَمَّا أَحَسَّ عِيسَىٰ مِنْهُمُ الْكُفْرَ قَالَ مَنْ أَنصَارِي إِلَى اللَّهِ ۖ قَالَ الْحَوَارِيُّونَ نَحْنُ أَنصَارُ اللَّهِ آمَنَّا بِاللَّهِ وَاشْهَدْ بِأَنَّا مُسْلِمُونَ (52) رَبَّنَا آمَنَّا بِمَا أَنزَلْتَ وَاتَّبَعْنَا الرَّسُولَ فَاكْتُبْنَا مَعَ الشَّاهِدِينَ (53) وَمَكَرُوا وَمَكَرَ اللَّهُ ۖ وَاللَّهُ خَيْرُ الْمَاكِرِينَ (54) إِذْ قَالَ اللَّهُ يَا عِيسَىٰ إِنِّي مُتَوَفِّيكَ وَرَافِعُكَ إِلَيَّ وَمُطَهِّرُكَ مِنَ الَّذِينَ كَفَرُوا وَجَاعِلُ الَّذِينَ اتَّبَعُوكَ فَوْقَ الَّذِينَ كَفَرُوا إِلَىٰ يَوْمِ الْقِيَامَةِ ۖ ثُمَّ إِلَيَّ مَرْجِعُكُمْ فَأَحْكُمُ بَيْنَكُمْ فِيمَا كُنتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ (55)}

{ዒሳ ከነርሱ ክህደት በተሰማውም ጊዜ፡- «ወደ አላህ (ተጨምረው) ረዳቶቼ እነማን ናቸው» አለ፤ ሐዋርያት፡- «እኛ የአላህ ረዳቶች ነን፤ በአላህ አምነናል፤ እኛም ትክክለኛ ታዛዦች መኾናችንን መስክር» አሉ።}

{«ጌታችን ሆይ! ባወረድኸው አመንን፤ መልክተኛውንም ተከተልን፤ ከመስካሪዎችም ጋር መዝግበን» (አሉ)።}

{(አይሁዶችም) አደሙ አላህም አድማቸውን መለሰባቸው። አላህም ከአድመኞች ሁሉ በላጭ ነው።}

{አላህም ባለ ጊዜ (አስታውስ)። ዒሳ ሆይ! እኔ ወሳጂህ ወደ እኔም አንሺህ ነኝ። ከነዚያም ከካዱት ሰዎች አጥሪህ ነኝ እነዚያንም የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ። ከዚያም መመለሻችሁ ወደእኔ ነው። በርሱ ትለያዩበትም በነበራችሁት ነገር በመካከላችሁ እፈርዳለሁ።} [አሊ-ዒምራን: 52-55] የላቀው አላህ የነብዩ ሷሊሕ (ዓለይሂ -ሰላም) ህዝቦች በተንኮል ሊገድሏቸው ሲያሴሩ አላህም በእነርሱ ላይ አሴረባቸውና መላ ህዝቦቹን አጠፋቸው።የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قَالُوا تَقَاسَمُوا بِاللَّهِ لَنُبَيِّتَنَّهُ وَأَهْلَهُ ثُمَّ لَنَقُولَنَّ لِوَلِيِّهِ مَا شَهِدْنَا مَهْلِكَ أَهْلِهِ وَإِنَّا لَصَادِقُونَ (49) وَمَكَرُوا مَكْرًا وَمَكَرْنَا مَكْرًا وَهُمْ لَا يَشْعُرُونَ (50) فَانظُرْ كَيْفَ كَانَ عَاقِبَةُ مَكْرِهِمْ أَنَّا دَمَّرْنَاهُمْ وَقَوْمَهُمْ أَجْمَعِينَ (51) }

{«እርሱንና ቤተሰቦቹን ሌሊት ልንገድል ከዚያም ለዘመዱ የቤተሰቦቹን ጥፋት (መገደላቸውን) አላየንም፤ እኛም እውነተኞች ነን ልንል በአላህ ተማማሉ» አሉ።} (49)

{ተንኮልንም መከሩ። እነርሱም የማያወቁ ሲኾኑ በተንኮላቸው አጠፋናቸው።} (50)

{የተንኮላቸውም መጨረሻ እንዴት እንደነበረ እኛ እነርሱንም ሕዝቦቻቸውንም በሙሉ እንዴት እንዳጠፋናቸው ተመልከት።} [አን-ነምል: 49-51]

እስልምና ስርቆትን ሐራም አድርጓል፤ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«لاَ يَزْنِي الزَّانِي حِينَ يَزْنِي وَهُوَ مُؤْمِنٌ وَلاَ يَسْرِقُ حِينَ يَسْرِقُ وَهُوَ مُؤْمِنٌ وَلاَ يَشْرَبُ حِينَ يَشْرَبُهَا وَهُوَ مُؤْمِنٌ وَالتَّوْبَةُ مَعْرُوضَةٌ بَعْدُ»

‹‹ዝሙትን የሚፈጽም ሰው ዝሙትን በሚፈጽምባት ቅፅበት አማኝ ሆኖ አይሠራም፤ ሌባም ሌብነቱን በሚፈጽምበት ቅጽበት አማኝ ሆኖ አይሰርቅም እንዲሁም አስካሪ መጠጥ ጠጪም መጠጡን በሚጠጣበት ቅፅበት አማኝ ሆኖ አይጠጣም። የተውባ በር ከዚያም በኋላ ክፍት ነች።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6810

እስልምና ድንበር ማለፍን ይከለክላል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُ بِالْعَدْلِ وَالْإِحْسَانِ وَإِيتَاءِ ذِي الْقُرْبَىٰ وَيَنْهَىٰ عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ وَالْبَغْيِ ۚ يَعِظُكُمْ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ }

{አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል። ከአስከፊም (ከማመንዘር)፣ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል። ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል።} [አን-ነሕል: 90] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«إنَّ الله أوحى إليَّ أن تَواضَعُوا حتى لا يَبغِي أحدٌ على أحدٍ ولا يفخَرَ أحدٌ على أحدٍ»

“አላህ ማንም ሰው ሌላው ላይ ድንበር እስከማይተላለፍና አንዱ በሌላው ላይ እስከማይመፃደቅ ድረስ ትሑት መሆን እንዳለባችሁ ለእኔ ወሕይ (መለኮታዊ ራእይ) አውርዶልኛል።" ሰሒሕ አቢ ዳውድ 4895

እስልምና በደልንም ይከለክላል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ ٱلظَّـٰلِمِينَ}

{አላህ በዳዮችን አይወድም።} [አሊ-ዒምራን 57] የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلظَّـٰلِمُونَ}

{እነሆ በዳዮች አይሰካላቸውም።} [አል-አንዓም: 21] የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلظَّـٰلِمِينَ أَعَدَّ لَهُمْ عَذَابًا أَلِيمًۢا}

{በዳዮችንም (ዝቶባቸዋል)። ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣትን አዘጋጅቶላቸዋል።} [አል-ኢንሳን: 31] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«ثَلَاثَةٌ لَا تُرَدُّ دَعْوَتُهُمْ: الْإِمَامُ الْعَادِلُ وَالصَّائِمُ حَتَّى يُفْطِرَ وَدَعْوَةُ الْمَظْلُومِ تُحْمَلُ عَلَى الْغَمَامِ وَتُفْتَحُ لَهَا أَبْوَابُ السَّمَاوَاتِ وَيَقُولُ الرَّبُّ عَزَّ وَجَلَّ: وَعِزَّتِي لَأَنْصُرَنَّكَ وَلَوْ بَعْدَ حِينٍ»

«ሶስቱ ዓይነት ሰዎች ዱዓቸው ተመላሽ አይሆንም፤ ፍትሀዊ መሪ፣ ፆመኛ እስኪያፈጥርና የተበዳይ ዱዓእ ናቸው። ከደመናዎች በላይ ከፍ ትላለች፤ እናም የሰማይ በሮች ይከፈቱላትና ልእለ ኋያሉ አምላክ "ቢዘገይ እንኳ

እንደምረዳሽ በልቅናየ እምላለሁ።" ይላል።» ሙስሊም (2749) ሰነዱን አጠር አድርገው ትንሽ ቢለያይም ዘግበውታል፤ ቲርሚዚይ (2526) ከተወሰነ ልዩነት ጋ ዘዘግበውታል፤ አሕመድ (8043) ዘግበውታል ይህ የተጠቀሰው የቃላት አወቃቀር የአሕመድ ዘገባ ነው። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሙዓዝን ወደ የመን በላኩት ጊዜ ካሉት መካከል፡-

«وَاتَّقِ دَعْوَةَ الْمَظْلُومِ فَإِنَّهُ لَيْسَ بَيْنَهُ وَبَيْنَ اللَّهِ حِجَابٌ»

"የተበዳይን ዱዓእ ተጠንቀቅ ምክንያቱም በርሱና በአላህ መካከል ምንም ግርዶሽ የለምና።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 1496 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«أَلَا مَن ظَلَم مُعاهِداً أو انتَقصَهُ أو كلَّفَهُ فوقَ طاقَتِهِ أو أخَذَ منهُ شيئاً بِغيرِ طِيبِ نَفسٍ فأنا حَجِيجُهُ يوم القيامةِ»

"ተጠንቀቁ ባለ ውልን (ሙዓሂድ) ቢበድለው ወይም መብቱን ቢቀንስበት ወይም ከአቅሙ በላይ እንዲሠራ ቢያስገድደው ወይም ያለ እርሱ ፈቃድ ማንኛውንም ነገር ቢወስድበት በፍርድ ቀን ራሴ እፋረደዋለሁ።" ሱነን አቢ ዳውድ: 3052 እስልምና እንደሚታየው እያንዳንዱን መጥፎ ባህሪ፤ ኢ-ፍትሀዊ ወይንም አምባገነናዊ መስተጋብርን ሐራም አድርጓል።

## 36- እስልምና ወለድ፣ የሰዎች ጉዳት፣ መሸወድ፣ ሰዎችን መበደል፣ ማጭበርበር ካለበትም ሆነ ማህበራዊም ይሁን ህዝባዊ

## ወይንም ግለሰባዊ ጉዳት ወደ ማምጣት ሊያደርስ የሚችልን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን ይከለክላል።

እስልምና ወለድ፣ የሰዎች ጉዳት፣ መሸወድ፣ ሰዎችን መበደል፣ ማጭበርበር ካለበትም ሆነ ማህበራዊም ይሁን ህዝባዊ ወይንም ግለሰባዊ ጉዳት ወደማምጣት ሊያደርስ የሚችልን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን ይከለክላል። በዚህ አንቀጽ መጀመሪያ ላይ አራጣ፣ ኢፍትሃዊነትን፣ ማጭበርበር ወይም ብክለትን በምድር ላይ የሚከለክሉ የቁርኣን አንቀጾችን እና ሐዲሶችን ጠቅሰን አሳልፈናል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል:-

{وَالَّذِينَ يُؤْذُونَ الْمُؤْمِنِينَ وَالْمُؤْمِنَاتِ بِغَيْرِ مَا اكْتَسَبُوا فَقَدِ احْتَمَلُوا بُهْتَانًا وَإِثْمًا مُّبِينًا}

{እነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚያስከፉ በቅርቢቱ ዓለም በመጨረሻይቱም አላህ ረግሟቸዋል። ለእነርሱም አዋራጅን ቅጣት ደግሶላቸዋል።} [አል-አሕዛብ: 58] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{مَّنْ عَمِلَ صَالِحًا فَلِنَفْسِهِ ۖ وَمَنْ أَسَاءَ فَعَلَيْهَا ۗ وَمَا رَبُّكَ بِظَلَّامٍ لِّلْعَبِيدِ}

{መልካም የሠራ ሰው ለነፍሱ ነው። ያጠፋም ሰው በእርሷ ላይ ነው። ጌታህም ለባሮቹ በዳይ አይደለም።} [ፉሲለት: 46]

وجاء في السنة: «أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَضَى أَنْ لَا ضَرَرَ وَلَا ضِرَارَ»

በነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አስተምህሮ እንዲህ የሚል መጥቷል፡- "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መጉዳትም መጎዳትም የለም ብለው ወስነዋል።" ሱነን አቢ ዳውድ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

« مَن كانَ يُؤْمِنُ باللَّهِ والْيَومِ الآخِرِ فلا يُؤْذِي جارَهُ، ومَن كانَ يُؤْمِنُ باللَّهِ والْيَومِ الآخِرِ فَلْيُكْرِمْ ضَيْفَهُ، ومَن كانَ يُؤْمِنُ باللَّهِ والْيَومِ الآخِرِ فَلْيَقُلْ خَيْرًا، أوْ لِيَسْكُتْ. وفي روايةٍ: فَلْيُحْسِنْ إلى جارِهِ. »

"በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ ጎረቤቱን አያስቸግር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ እንግዳውን ያክብር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን መልካምን ይናገር አሊያም ዝም ይበል።" በሌላ ዘገባ "ለጎረቤቱ በጎ ይዋልላቸው።" ሰሒሕ ሙስሊም 47 የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«عُذِّبَتِ امْرَأَةٌ فِي هِرَّةٍ سَجَنَتْهَا حَتَّى مَاتَتْ فَدَخَلَتْ فِيهَا النَّارَ لَا هِيَ أَطْعَمَتْهَا وَسَقَتْهَا إِذْ هِيَ حَبَسَتْهَا وَلَا هِيَ تَرَكَتْهَا تَأْكُلُ مِنْ خَشَاشِ الْأَرْضِ»

"አንዲት ሴት እስክትሞት ድረስ ባሰረቻት ድመት ምክንያት በጀሀነም እሳት ተቀጣች። ወይ አላበላቻትና አላጠጣቻት ወይም ደግሞ ከምድር ትላትል ለቃቅማ ትበላ ዘንድ አልለቀቀቻት።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 3482 ይህ እንግዲህ ድመትን ላስቸገረ ሰው ከሆነ ታዲያ ሰዎችን ላስቸገረ ሰውስ እንዴት ሊሆን ነው? ከኢብኑ ዑመር በተላለፈ ሐዲሥ እንዲህ የሚል እናገኛለን፡- የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም

በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሚንበር ላይ ወጥተው ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ አሉ፡-

(يَا مَعْشَرَ مَنْ أَسْلَمَ بِلِسَانِهِ وَلَمْ يُفْضِ الإِيمَانُ إِلَى قَلْبِهِ لاَ تُؤْذُوا الْمُسْلِمِينَ وَلاَ تُعَيِّرُوهُمْ وَلاَ تَتَّبِعُوا عَوْرَاتِهِمْ فَإِنَّهُ مَنْ تَتَبَّعَ عَوْرَةَ أَخِيهِ الْمُسْلِمِ تَتَبَّعَ اللَّهُ عَوْرَتَهُ وَمَنْ تَتَبَّعَ اللَّهُ عَوْرَتَهُ يَفْضَحْهُ وَلَوْ فِي جَوْفِ رَحْلِهِ قَالَ: وَنَظَرَ ابْنُ عُمَرَ يَوْمًا إِلَى البَيْتِ أَوْ إِلَى الكَعْبَةِ فَقَالَ: مَا أَعْظَمَكِ وَأَعْظَمَ حُرْمَتَكِ وَالمُؤْمِنُ أَعْظَمُ حُرْمَةً عِنْدَ اللهِ مِنْكِ)

"እምነት በልባችሁ ሳይደርስ ኢስላምን በምላሳችሁ የተቀበላችሁ ሆይ! ሙስሊሞችን አትጎዱ ፣ አትሳደቡ (አታነውሯቸው)፣ ነውራቸውን አትከታተሉ። የሙስሊሙን ወንድሙን ነውር የሚከታተል ሰው አላህ ነውሩን ይከታተለዋል፤ አላህ ነውሩን የተከታተለበት ሰው ደግሞ በቤቱ ጓዳ ውስጥ ቢሆን እንኳ የሠራውን ነውር ያጋልጥበታል። ኢብኑ ዑመር አንድ ቀን ወደ አላህ ቤት ወይም ወደ ካዕባ ተመለከተና እንዲህ አለ፡- "ምንኛ ታላቅ ነህ፤ ክብርህስ ምንኛ ታላቅ ነው፤ (ነገር ግን) አላህ ዘንድ ግን የአንድ አማኝ ክብር ከአንተ እጅግ የበለጠ ነው።) ቲርሚዚይ ዘግበውታል (2032)፤ እንዲሁም ኢብኑ ሒባን (5763) የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

(مَنْ كَانَ يُؤْمِنُ بِاللَّهِ وَاليَوْمِ الآخِرِ فَلاَ يُؤْذِ جَارَهُ وَمَنْ كَانَ يُؤْمِنُ بِاللَّهِ وَاليَوْمِ الآخِرِ فَلْيُكْرِمْ ضَيْفَهُ وَمَنْ كَانَ يُؤْمِنُ بِاللَّهِ وَاليَوْمِ الآخِرِ فَلْيَقُلْ خَيْرًا أَوْ لِيَصْمُتْ)

"በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ ጎረቤቱን አያስቸግር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ እንግዳውን ያክብር፤

በአላህና በመጨረሻው ቀን መልካምን ይናገር አሊያም ዝም ይበል።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6018

وعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: " هَلْ تَدْرُونَ مَنِ الْمُفْلِسُ؟ " قَالُوا: الْمُفْلِسُ فِينَا يَا رَسُولَ اللهِ مَنْ لَا دِرْهَمَ لَهُ وَلَا مَتَاعَ. قَالَ: " إِنَّ الْمُفْلِسَ مِنْ أُمَّتِي مَنْ يَأْتِي يَوْمَ الْقِيَامَةِ بِصِيَامٍ وَصَلَاةٍ وَزَكَاةٍ وَيَأْتِي قَدْ شَتَمَ عِرْضَ هَذَا وَقَذَفَ هَذَا وَأَكَلَ مَالَ هَذَا فَيُقْعَدُ فَيَقْتَصُّ هَذَا مِنْ حَسَنَاتِهِ وَهَذَا مِنْ حَسَنَاتِهِ فَإِنْ فَنِيَتْ حَسَنَاتُهُ قَبْلَ أَنْ يَقْضِيَ مَا عَلَيْهِ مِنَ الْخَطَايَا أُخِذَ مِنْ خَطَايَاهُمْ فَطُرِحَتْ عَلَيْهِ ثُمَّ طُرِحَ فِي النَّارِ)

አቢ ሁረይራ ባስተላለፉት ሐዲሥ የአላህ መልዕክተኛ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም፡- "ያጣ የነጣ ድኻ የሚባለው ማን ነው?" ብለው ጠየቁ፤ ሶሓቦችም የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እኛ ዘንድ ያጣ የነጣ ድኻ የሚባለው ገንዘብም ሆነ የሚጠቃቀምበት እቃ የሌለው ነው በማለት መለሱ። የአላህ መልዕክተኛ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለምም እንዲህ አሉ። "ከህዝቦቼ መካከል ያጣ የነጣ ድኻ ማለት የቂያማ ቀን የሶላት፣ የፆምና የዘካን አጅር አከማችቶ ይመጣል፤ ነገር ግን አንዱን ክብሩን በስድብ ተዳፍሮታል፤ አንዱን ደሞ ዘልፎታል፤ የአንዱን ገንዘቡን በልቶበታል፤ ታድያ እርሱ እያየ ለዚህኛው (ለበደለው ሰው) ከአጅሩ ይቀነስለታል፤ ለዚህኛም ከአጅሩ ተቀንሶ ይሰጠዋል፤ በመጨረሻም የበደላቸው ሰዎች (ካሳቸው) ጉዳያቸው ከማለቁ በፊት አጅሩ ሲያልቅ ከወንጀላቸው እየተቀነሰ ወደ እርሱ ወንጀል ይነባበርለትና ወደ ጀሀነም ይወረወራል።" ሙስሊም ዘግበውታል (2581)፤ ቲርሚዚይም (2418)፤ አሕመድም (8029) ዘግበውታል ይህ የቃላት አሰካክም የእርሳቸው ነው።

የአለህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

(كَانَ عَلَى الطَّرِيقِ غُصْنُ شَجَرَةٍ يُؤْذِي النَّاسَ فَأَمَاطَهَا رَجُلٌ فَأُدْخِلَ الْجَنَّةَ) "አንድ ሰው (መሀል) መንገድ ላይ የነበረችን ሰዎችን የምታስቸግርን ዛፍ በማስወገዱ ጀነት ገባ።" ቡኻሪይ መልዕክቱን ዘግበውታል (652)፤ ሙስሊምም እንዲሁ (1914)፤ ኢብኑ ማጃህ (3682) እና አሕመድም (10432) ዘግበውታል የቃላት አሰካክም የሁለቱ ነው፤ ሰዎችን የሚያስቸግርን ነገር ማስወገድ ጀነት የሚያስገባ ከሆነ ሰዎችን የሚስቸግርንና ህይወታቸውንም የሚያበላሽንስ ነገር ማስወገድ ከሆነ (ምንዳው) እንዴት ሊሆን ነው?

## 37- እስልምና የመጣው አእምሮን ለመጠበቅ እና አስካሪ መጠጥ መጠጣትን ከመሰሉ እርሱን ከሚያበላሹ ነገሮች በመከልከል ነው። እስልምና የአዕምሮንም ደረጃ ከፍ በማድረግ የፍርድ ማብሰልሰያ አድርጎ ከአጉል እምነትም ሆነ ከጣዖት አምልኮ ጭንቅ ገላገለው። በመሆኑም በእስልምና አንዱን የማህበረሰብ ክፍል ከሌላው የሚለዩ ምስጢሮች ወይም ፍርዶች የሉም፤ ሁሉም ፍርዶቹ እና ህጎቹ ጤናማ ከሆኑ አእምሮዎችም ጋር የሚስማሙ

## ናቸው፤ እነርሱም ከፍትህና ጥበብ ጋ የሚገጠሙ ናቸው።

እስልምና አዕምሮንለመጠበቅ ነው የመጣው፤ ደረጃውንም ከፍ አድርጎታል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{إِنَّ السَّمْعَ وَالْبَصَرَ وَالْفُؤَادَ كُلُّ أُولَٰئِكَ كَانَ عَنْهُ مَسْئُولًا }

{መስሚያ፣ ማያም፣ ልብም እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከእነሱ ተጠያቂ ነውና።} [አል-ኢስራእ: 36] በመሆኑም ማንም ሰው የአእምሮውን ጤናማነት መጠበቅ ግዴታው ነው፤ ለዚህም ሲባል ነው እስልምና አልኮልን እና አደንዛዥ ዕፅን የከለከለው። የአስካሪ መጠጥ ሐራምነትን በአንቀፅ (34) ላይ ጠቅሰናል፤ በርካታ የቁርአን አንቀፆች በተከታዩ ቃል ነው የሚጠናቀቁት፡-

{لَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ}

{...ታውቁ ዘንድ።} [አል-በቀራህ: 242] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَمَا الْحَيَاةُ الدُّنْيَا إِلَّا لَعِبٌ وَلَهْوٌ ۖ وَلَلدَّارُ الْآخِرَةُ خَيْرٌ لِّلَّذِينَ يَتَّقُونَ ۗ أَفَلَا تَعْقِلُونَ }

{የቅርቢቱም ሕይወት ጨዋታና ላግጣ እንጅ ሌላ አይደለችም። የመጨረሻይቱም አገር (ገነት) ለእነዚያ ለሚጠነቀቁት በጣም በላጭ ናት። አታውቁምን} [አል-አንዓም: 32] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ إِنَّا أَنزَلْنَاهُ قُرْآنًا عَرَبِيًّا لَّعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ }

{እኛ (ፍቹን) ታውቁ ዘንድ ዐረብኛ ቁርኣን ሲሆን በእርግጥ አወረድነው።} [ዩሱፍ: 2] የላቀው አላህ መመሪያና ጥበብ ሊጠቅሙ የሚችሉት የእውቀት ሰዎች (የአዕምሮ ባለቤቶች) ብቻ እንደሆነና እነርሱም የአስተዋይ ልቦና ባለቤቶች መሆናቸውን ግልፅ አድርጓል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يُؤْتِي الْحِكْمَةَ مَن يَشَاءُ ۚ وَمَن يُؤْتَ الْحِكْمَةَ فَقَدْ أُوتِيَ خَيْرًا كَثِيرًا ۗ وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّا أُولُو الْأَلْبَابِ }

{ለሚሻው ሰው ጥበብን ይሰጣል፤ ጥበብንም የሚስሰጥ ሰው ብዙን መልካም ነገር በእርግጥ ተሰጠ። የአእምሮዎች ባለቤቶች እንጂ (ሌላው) አይገሰጽም።} [አል-በቀራህ: 269]

ለዚህም ነው እስልምና ኋላፊነት ለመስጠት ወሳኙን ነገር አእምሮ ያደረገው፤ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«رُفِعَ الْقَلَمُ عَنْ ثَلَاثٍ: عَنِ النَّائِمِ حَتَّى يَسْتَيْقِظَ وَعَنِ الصَّبِيِّ حَتَّى يَحْتَلِمَ وَعَنِ الْمَجْنُونِ حَتَّى يَعْقِلَ»

"(እያንዳንዱን ሥራቸውን የሚዘግበው) ብዕር ከሶስት ዓይነት ሰዎች ተነስቶላቸዋል፤ የተኛ ሰው እስኪነቃ፤ ታዳጊ ህፃን ለአቅመ አዳም (ሄዋን) እስኪደርስና እብድ አእምሮው እስኪሰራ ድረስ።" ቡኻሪይ ከሓዲሥ ቁጥር (5269) በፊት በማያጠራጥር መልኩ ዘግበውታል፤ አቡዳውድ ሓዲሡን በተቀጣጠለ ሰንሰለት ዘግበውታል(4402) ይህ የቃላት አሰካክም የሳቸው ነው፤ ቲርሚዚይም (1423)፤ ነሳኢይም በሱነኑል ኩብራ (7346)፤ አሕመድም (956) ከተወሰነ ልዩነት

ጋ፤ ኢብኑ ማጃህም (2042) ላይ አጠር ባለ መልኩ ዘግበውታል። ከእንቶፈንቶ ከባባድ ህግጋትና ጣኦታዊነትም ነጻ አውጥቶታል፤ ቀደምት ህዝቦች ከእንቶፈንቷቸው ጋ ያላቸውን ቁርኝትና ከአላህ የመጣ እውነታን አሻፍረኝ ማለታቸውን አስመልክቶ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَكَذَٰلِكَ مَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ فِي قَرْيَةٍ مِّن نَّذِيرٍ إِلَّا قَالَ مُتْرَفُوهَا إِنَّا وَجَدْنَا آبَاءَنَا عَلَىٰ أُمَّةٍ وَإِنَّا عَلَىٰ آثَارِهِم مُّقْتَدُونَ}

{(ነገሩ) እንደዚሁም ነው። ከበፊትህ በማንኛይቱም ከተማ ውስጥ አስፈራሪን አልላክንም፤ ቅምጥሎችዋ እኛ አባቶቻችንን በሃይማኖት ላይ አገኘን፤ እኛም በፈለጎቻቸው ላይ ተከታዮች ነን ያሉ ቢኾኑ እንጅ።} [አዝ-ዙኽሩፍ: 23] ነብዩሏህ ኢብራሂም ለህዝቦቹ እንዲህ ማለታቸውን የላቀው አላህ በዚህ መልኩ ነግሮናል፦

{مَا هَٰذِهِ التَّمَاثِيلُ الَّتِي أَنتُمْ لَهَا عَاكِفُونَ (52) قَالُوا وَجَدْنَا آبَاءَنَا لَهَا عَابِدِينَ (53) }

{«ይህቺ ቅርጻ ቅርጽ ይቺ እናንተ ለእርሷ ተገዢዎች የኾናችሁት ምንድን ናት» ባለ ጊዜ (መራነው)።} (52)

{«አባቶቻችንን ለእርሷ ተገዢዎች ኾነው አገኘን» አሉት።} (53) [አል-አንቢያእ: 52-53] ስለዚህም እስልምና መጥቶ ሕዝቡ ጣዖት አምልኮንና ከአባቶቹና ከአያቶቹ የወረሰውን አጉል እምነትም በመተው የሩሱሎችን ፈለግ እንዲከተሉ አዘዘ።

በእስልምና የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ብቻ የሚለዩበት ሚስጥራትና ህግጋቶች የሉም።

سُئل علي بن أبي طالب رضي الله عنه وهو ابن عم رسول الله صلى الله عليه وسلم وزوج ابنته: أَخَصَّكُمْ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ بِشَيْءٍ؟ فَقَالَ: «مَا خَصَّنَا رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ بِشَيْءٍ لَمْ يَعُمَّ بِهِ النَّاسَ كَافَّةً إِلَّا مَا كَانَ فِي قِرَابِ سَيْفِي هَذَا قَالَ: فَأَخْرَجَ صَحِيفَةً مَكْتُوبٌ فِيهَا: لَعَنَ اللهُ مَنْ ذَبَحَ لِغَيْرِ اللهِ وَلَعَنَ اللهُ مَنْ سَرَقَ مَنَارَ الْأَرْضِ وَلَعَنَ اللهُ مَنْ لَعَنَ وَالِدَهُ وَلَعَنَ اللهُ مَنْ آوَى مُحْدِثًا»

የረሱል የአጎት ልጅና የልጃቸው ባል የሆኑት ዐልይ (አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው) እንዲህ ተብለው ተጠይቀው ነበር - የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ለእናንተ (የነብዩ ቤተሰቦች) ብቻ በሆነ ነገር ለይተዋችኋልን?" እርሳቸውም "በዚህ በሰይፌ ሰገባ ውስጥ ባለው ካልሆነ በስተቀር ለሌሎች ሰዎች ሁሉ ሳይናገር ለእኛ ብቻ የሆነን ነገር ለይተው አልነገሩንም።" በማለት እንዲህ የሚል ፅሁፍ የተፃፈበትን ወረቀት አወጡ - “ከአላህ ውጪ ላለ አካል ያረደ አላህ ይርገመው፣ የቦታ ድንበር ጠቋሚዎችን የሰረቀን (ሰርቆ የወሰደ) አላህ ይርገመው፣ ወላጁን የረገመ አላህ ይርገመው፤ በዲናችን አዲስ ፈሊጥ ያመጣን ሰው ከለላ የሰጠን አላህ ይርገመው።” ሰሒሕ ሙስሊም 1978 የእስልምና ውሳኔዎች እና ህጎች ሁሉ ጤናማ አእምሮ ካለው ጋ እንዲሁም ከፍትህና ከጥበብ ጋ የሚገጥሙ ናቸው።

## 38- ሐሰተኛ ሃይማኖቶች ተከታዮቻቸው በውስጣቸው ያሉትን እርስ በርስ መጣረሶች እና አዕምሯቸው የማይቀበሏቸውን ጉዳዮች ካልተረዱ የሃይማኖቱ አባቶች ሃይማኖትን ከምክንያታዊነት በላይ ነው ብለው

**ተከታዮቻቸውን ያታልላሉ። አእምሮም ሀይማኖትን መረዳትና መገንዘብን ለመቻል እድሉ የለውም ይሏቸዋል። እስልምና ግን ሃይማኖትን ለአእምሮ ጎዳና የሚያበራለት ብርሃን እንደሆነ አድርጎ የሚቆጥር ሲሆን የሐሰት ሃይማኖቶች ግን ፍላጎታቸው ሰው አእምሮውን ትቶ እነሱን እንዲከተል ነው። እስልምና ታድያ ሰው የነገሮችን እውነታ ባሉበት ተጨባጭ ያውቅ ዘንድ አዕምሮውን እንዲያነቃ ይፈልጋል።**

ሐሰተኛ ሃይማኖቶች ተከታዮቻቸው በውስጣቸው ያሉትን እርስ በርስ መጣረሶች እና አዕምሯቸው የማይቀበሏቸውን ጉዳዮች ካልተረዱ የሃይማኖቱ አባቶች ሃይማኖትን ከምክንያታዊነት በላይ ነው ብለው ተከታዮቻቸውን ያታልላሉ። አእምሮም ሀይማኖትን መረዳትና መገንዘብን ለመቻል እድሉ የለውም ይሏቸዋል። እስልምና ግን ሃይማኖትን ለአእምሮ ጎዳና የሚያበራለት ብርሃን እንደሆነ አድርጎ የሚቆጥር ሲሆን የሐሰት ሃይማኖቶች ግን ፍላጎታቸው ሰው አእምሮውን ትቶ እነሱን እንዲከተል ነው። እስልምና ታድያ ሰው የነገሮችን እውነታ ባሉበት ተጨባጭ ያውቅ ዘንድ አዕምሮውን እንዲያነቃ ይፈልጋል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል:-

{ وَكَذَٰلِكَ أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ رُوحًا مِّنْ أَمْرِنَا ۚ مَا كُنتَ تَدْرِي مَا الْكِتَابُ وَلَا الْإِيمَانُ وَلَٰكِن جَعَلْنَاهُ نُورًا نَّهْدِي بِهِ مَن نَّشَاءُ مِنْ عِبَادِنَا ۚ وَإِنَّكَ لَتَهْدِي إِلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ }

{እንደዚሁም ወደ አንተ ከትእዛዛችን ሲኾን መንፈስን (ቁርኣንን) አወረድን። መጽሐፉም እምነቱም ምን እንደኾነ የምታውቅ አልነበርክም። ግን (መንፈሱን) ከባሮቻችን የምንሻውን ሰው በእርሱ የምንመራበት ብርሃን አደረግነው። አንተም ወደ ቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ ትመራለህ።} [አሽ-ሹራ: 52] መለኮታዊው ወሕይ (ራእይ) ጤናማ አእምሮዎች ለማወቅ እና ለማመን የሚመኙት ወደ ሆነው እውነታ የሚመሩ ማስረጃዎችን እና ሙግቶችን ጭምር አካትቷል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَا أَيُّهَا النَّاسُ قَدْ جَاءَكُم بُرْهَانٌ مِّن رَّبِّكُمْ وَأَنزَلْنَا إِلَيْكُمْ نُورًا مُّبِينًا}

{እናንተ ሰዎች ሆይ! ከጌታችሁ ዘንድ በእርግጥ አስረጅ መጣላችሁ፤ ወደእናንተም ገላጭ የኾነን ብርሃን (ቁርኣንን) አወረድን።} [አን-ኒሳእ: 174] የላቀው አላህ የሰው ልጅ በመመሪያ፣ በእውቀትና በእውነት ብርሃን እንዲኖር ይፈልጋል፤ ሰይጣኖች እና አምባገነኖች ግን ሰው በክህደት፣ በድንቁርናና በስህተት ጨለማ ውስጥ ሆኖ እንዲቆይ ነው የሚፈልጉት። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{اللَّهُ وَلِيُّ الَّذِينَ آمَنُوا يُخْرِجُهُم مِّنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ ۖ وَالَّذِينَ كَفَرُوا أَوْلِيَاؤُهُمُ الطَّاغُوتُ يُخْرِجُونَهُم مِّنَ النُّورِ إِلَى الظُّلُمَاتِ}

{አላህ የእነዚያ ያመኑት ሰዎች ረዳት ነው። ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል። እነዚያም የካዱት ረዳቶቻቸው

ጣዖታት ናቸው። ከብርሃን ወደ ጨለማዎች ያወጧቸዋል። እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፤ እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው።} [አል-በቀራህ: 257]

## 39- እስልምና ትክክለኛ እውቀትን ያልቃል። ስሜትን ከመከተል የጠራ የሆነ ሳይንሳዊ ምርምርን ያበረታታል። ስለ ራሳችንም ሆነ በዙሪያችን ስላለው ፍጥረተ ዓለም በተመለከተ እንድናስተነትን ጥሪ ያደርጋል። እናም ትክክለኛ የሳይንስ ምርምር ውጤቶች ከእስልምና ጋር አይጋጩም።

እስልምና ትክክለኛ የሆነን ምርምር ያበረታታል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{يَرْفَعِ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا مِنكُمْ وَالَّذِينَ أُوتُوا الْعِلْمَ دَرَجَاتٍ ۚ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ }

{አላህ ከናንተ እነዚያን ያመኑትንና እነዚያንም ዕውቀትን የተሰጡትን በደረጃዎች ከፍ ያደርጋል። አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ ዓዋቂ ነው።} [አል ሙጃዲላ 11] አላህ በታላቅ ጉዳይ ላይ የሊቃውንቱን ምስክርነት ከእርሱ ምስክርነትና ከመላእክቱ ምስክርነት ጋር አቆራኝቶ ገልጿል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{شَهِدَ اللَّهُ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَالْمَلَائِكَةُ وَأُولُو الْعِلْمِ قَائِمًا بِالْقِسْطِ ۚ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ }

{አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ። መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)። ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። አሸናፊው ጥበበኛው ነው።} [አሊ-ዒምራን 18] ይህም የእውቀት ባለቤቶች በእስልምና ውስጥ ያላቸውን ደረጃ ያሳያል፤ የላቀው አላህ ነቢዩ ሙሐመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከእውቀት በስተቀር ጨምርልኝ እንዲሉ ያዘዘበት ሌላ ነገር የለም። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَقُل رَّبِّ زِدْنِي عِلْمًا }

{"ጌታየ ሆይ! እውቀትንም ጨምርልኝ" በል።} [ጧሀ: 114] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«مَنْ سَلَكَ طَرِيقًا يَلْتَمِسُ فِيهِ عِلْمًا سَهَّلَ اللَّهُ لَهُ طَرِيقًا إِلَى الْجَنَّةِ وَإِنَّ الْمَلَائِكَةَ لَتَضَعُ أَجْنِحَتَهَا رِضًا لِطَالِبِ الْعِلْمِ وَإِنَّ طَالِبَ الْعِلْمِ يَسْتَغْفِرُ لَهُ مَنْ فِي السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ حَتَّى الْحِيتَانِ فِي الْمَاءِ وَإِنَّ فَضْلَ الْعَالِمِ عَلَى الْعَابِدِ كَفَضْلِ الْقَمَرِ عَلَى سَائِرِ الْكَوَاكِبِ إِنَّ الْعُلَمَاءَ وَرَثَةُ الْأَنْبِيَاءِ إِنَّ الْأَنْبِيَاءَ لَمْ يُوَرِّثُوا دِينَارًا وَلَا دِرْهَمًا إِنَّمَا وَرَّثُوا الْعِلْمَ فَمَنْ أَخَذَهُ أَخَذَ بِحَظٍّ وَافِرٍ»

«እውቀትን ፍለጋ መንገድን የጀመረ አላህ ወደ ጀነት የሚወስደውን መንገድ ያገራለታል። መላእክት ለእውቀት ፈላጊ በሚያደርገው ነገር ተደስተው ክንፋቸውን ዝቅ ያደርጉለታል። በሰማይና በምድር ያለውም ሁሉ ለእውቀት ፈላጊ ምህረትን ይለምኑለታል። በባህር ውስጥ ያለ ዓሳ እንኳን ሳይቀር። አንድ ዓሊም ከዐቢድ (አምልኮ ብቻ ከሚፈጽም ሰው) አንፃር ያለው በላጭነት ልክ ጨረቃ

ከሌሎች የሰማይ ከዋክብት አንፃር እንዳላት ብልጫ የላቀ ነው። ሊቃውንት የነቢያት ወራሾች ናቸው፤ ነቢያቶች ደግሞ ዲናር ወይንም ዲርሃም አይደለም ያወረሱት፤ ይልቁንም እውቀትን ነውያወረሱት። ያህንን የጨበጠ ሰው ትልቅ ድርሻን ነው የጨበጠው።» አቡ ዳውድ (3641)፤ ቲርሚዚይ (2682)፤ ኢብኑ ማጀህ (223) ዘግበውታል ይህ ያቃላት አወቃቀርም የዚሁ ዘገባ ነው፤ አሕመድ (21715) ዘግበውታል።

እስልምና ከስሜታዊነት ነፃ የሆነ ሳይንሳዊ ምርምርን ያበረታታል፤ በእኛና በዙሪያችን ስላለው ፍጥረተ ዓለም ወደማሰብና ወደማስተንተንም ይጋብዛል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{سَنُرِيهِمْ آيَاتِنَا فِي الْآفَاقِ وَفِي أَنفُسِهِمْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمْ أَنَّهُ الْحَقُّ ۗ أَوَلَمْ يَكْفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ شَهِيدٌ}

{እርሱም (ቁርኣን) እውነት መኾኑ ለእነርሱ እስከሚገለፅላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን። ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ መኾኑ አይበቃቸውምን?} [ፉሲለት: 53] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{أَوَلَمْ يَنظُرُوا فِي مَلَكُوتِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا خَلَقَ اللَّهُ مِن شَيْءٍ وَأَنْ عَسَىٰ أَن يَكُونَ قَدِ اقْتَرَبَ أَجَلُهُمْ ۖ فَبِأَيِّ حَدِيثٍ بَعْدَهُ يُؤْمِنُونَ}

{በሰማያትና በምድር ግዛት ውስጥ ከማንኛው ነገር አላህ በፈጠረውም ሁሉ የሞት ጊዜያቸውም በእርግጥ መቅረቡ

የሚፈራ መኾኑን አያስተውሉምን ከእርሱም (ከቁርኣን) ወዲያ በየትኛው ንግግር ያምናሉ።} [አል-አዕራፍ: 185] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{أَوَلَمْ يَسِيرُوا فِي الْأَرْضِ فَيَنظُرُوا كَيْفَ كَانَ عَاقِبَةُ الَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ ۚ كَانُوا أَشَدَّ مِنْهُمْ قُوَّةً وَأَثَارُوا الْأَرْضَ وَعَمَرُوهَا أَكْثَرَ مِمَّا عَمَرُوهَا وَجَاءَتْهُمْ رُسُلُهُم بِالْبَيِّنَاتِ ۖ فَمَا كَانَ اللَّهُ لِيَظْلِمَهُمْ وَلَٰكِن كَانُوا أَنفُسَهُمْ يَظْلِمُونَ}

{በምድር ላይ አይኼዱምና የእነዚያን ከበፊታቸው የነበሩትን ሰዎች ፍጻሜ እንዴት እንደነበረ አይመለከቱምን? በኀይል ከእነርሱም ይበልጥ የጠነከሩ ነበሩ። ምድርንም አረሱ። (እነዚህ) ከአለሟትም የበዛ አለሟት። መልዕክተኞቻቸውም በተዓምራቶች መጡባቸው፤ (አስተባበሉምና ጠፉ)። አላህም የሚበድላቸው አልነበረም፤ ግን ነፍሶቻቸውን ይበድሉ ነበሩ።} [አር-ሩም: 9]

የሳይንስ ትክክለኛ ሳይንሳዊ ውጤቶች ከእስልምና ጋር አይጋጩም። ቁርአን ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመታት በፊት ትክክለኛ ዝርዝሮችን የጠቀሰበትን እና ዘመናዊ ሳይንስ ዘግይቶ የደረሰበትን አንድ ምሳሌ እንጠቅሳለን። ሽል በእናቱ ማህፀን ውስጥ ያለውን ሂደት በማስመልከት የሳይንስ ምርምር ውጤቶች በታላቁ ቁርአን ውስጥ ካለው ፅንሰ - ሀሳብ ጋር ሙሉ በሙሉ የተስማማ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ وَلَقَدْ خَلَقْنَا الْإِنسَانَ مِن سُلَالَةٍ مِّن طِينٍ (12) ثُمَّ جَعَلْنَاهُ نُطْفَةً فِي قَرَارٍ مَّكِينٍ (13) ثُمَّ خَلَقْنَا النُّطْفَةَ عَلَقَةً فَخَلَقْنَا الْعَلَقَةَ مُضْغَةً فَخَلَقْنَا الْمُضْغَةَ

عِظَامًا فَكَسَوْنَا الْعِظَامَ لَحْمًا ثُمَّ أَنشَأْنَاهُ خَلْقًا آخَرَ ۚ فَتَبَارَكَ اللَّهُ أَحْسَنُ الْخَالِقِينَ (14)}

{በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው።} (12)

{ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው።} (13)

{ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን። የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን። ቁራጯንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን። አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው። ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረትን አድርገን አስገኘነው። ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ።} [አል-ሙእሚኑን: 12-14]

## 40- በአላህ አምነው ለታዘዙትና መልእክተኞቹንም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እውነት ብለው የተቀበሉትን ካልሆነ በቀር አላህ ከማንም ስራውን አይቀበለውም ለመልካም ስራውም አኺራ ላይ አይመነዳውም። የደነገገውንም ካልሆነ በቀር የትኛውንም አምልኮ አይቀበለም። የሰው ልጅ በአላህ ከካደ በኋላ አላህ መልካም ይመነዳኛል ብሎ እንዴት ያስባል?! ማንኛውም ሰው ቢሆን በሁሉም ነብያቶች ብሎም በነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የአላህ

## መልእክተኛነት አምኖ ካልተገኘ አላህ እምነቱን አይቀበለውም።

በአላህ አምነው ለታዘዙትና መልእክተኞቹንም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እውነት ብለው የተቀበሉትን ካልሆነ በቀር አላህ ከማንም ስራውንም አይቀበለውም፤ ለመልካም ስራውም አኺራ ላይ አይመነዳውም። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{مَّن كَانَ يُرِيدُ الْعَاجِلَةَ عَجَّلْنَا لَهُ فِيهَا مَا نَشَاءُ لِمَن نُّرِيدُ ثُمَّ جَعَلْنَا لَهُ جَهَنَّمَ يَصْلَاهَا مَذْمُومًا مَّدْحُورًا (18) وَمَنْ أَرَادَ الْآخِرَةَ وَسَعَىٰ لَهَا سَعْيَهَا وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُولَٰئِكَ كَانَ سَعْيُهُم مَّشْكُورًا (19) }

{ቻኳይቱን ዓለም (በሥራው) የሚፈልግ ሰው ለእርሱ በርሷ ውስጥ የሻነውን (ጸጋ) ለምንሻው ሰው እናስቸኩልለታለን። ከዚያም ለእርሱ ገሀነምን (መኖሪያ) አድርገንለታል። ተወቃሽ ብራሪ ኾኖ ይገባታል።}

{መጨረሻይቱንም ዓለም የፈለገ ሰው እርሱ አማኝ ኾኖ ለርሷ (ተገቢ) ሥራዋን የሠራም ሰው እነዚህ ሥራቸው የተመሰገነ ይኾናል።} [አል-ኢስራእ: 18-19] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{فَمَن يَعْمَلْ مِنَ الصَّالِحَاتِ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَا كُفْرَانَ لِسَعْيِهِ وَإِنَّا لَهُ كَاتِبُونَ }

{እርሱ ያመነ ኾኖ ከበጎ ሥራዎች ማንኛውንም የሚሠራም ሰው፤ ምንዳውን አይነፈግም። እኛም ለእርሱ መዝጋቢዎች ነን።} [አል-አንቢያእ: 94] አላህ ከአምልኮ የሚቀበለው የደነገገውን ብቻ ነው። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ فَمَن كَانَ يَرْجُو لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَالِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا }

{የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ። በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» [አል-ከህፍ: 110] ስለዚህ የትኛውም ድርጊት አላህ የደነገገውና ድርጊት ፈፃሚውም ድርጊቱን በሚፈፅምበት ጊዜ የአላህን ውዴታ ብቻ ፈልጎበት ካልሆነ፤ እንዲሁም ሰውየው በነቢያቱና በመልእክተኞቹ ዓለይሂሙ ሰላም የሚያምን አማኝ ሆኖ ካልሆነ በቀር ድርጊቱም ፅድቅ እንደማይሆን ግልፅ አድርጓል። ከዚህ ውጭ ለሆነማ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَقَدِمْنَا إِلَىٰ مَا عَمِلُوا مِنْ عَمَلٍ فَجَعَلْنَاهُ هَبَاءً مَّنثُورًا }

{ከሥራም ወደ ሠሩት እናስባለን። የተበተነ ትቢያም እናደርገዋለን።} [አል-ፉርቃን: 23] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ وُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ خَاشِعَةٌ (2) عَامِلَةٌ نَّاصِبَةٌ (3) تَصْلَىٰ نَارًا حَامِيَةً (4) }

{ፊቶች በዚያ ቀን ተዋራጆች ናቸው።} (2)

{ሠሪዎች ለፊዎች ናቸው።} (3)

{ተኳሳን እሳት ይገባሉ።} (4) [አል-ጋሺያህ: 2-4] እነዚህ ፊቶች ከስራ አንፃር የተናነሱና ያሉና ቀጥ ያሉ ነበሩ፤ ነገር ግን ስራቸው በአላህ መመሪያ ሳይሆን ሲቀር፤ መመለሻቸውን አላህ እሳት አደረገው። ምክንያቱም አላህ ያልደነገገውን ከመስራት አልታቀቡም ነበርና፤ ይልቁንም በሐሰት አምልኮ ታመልክና የሐሰት ሃይማኖቶችን የሚፈጥሩላቸውን

የጥመት ራሶችንም (መሪዎችን) ይከተሉ ነበርና ነው። አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የፅድቅ ስራ የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ይዘውት የመጡትን የሚገጥም የሆነው ነው። የሰው ልጅ ታድያ በአላህ እየካደ እንዴት የአላህን ምንዳ ይከጅላል?

በሁሉም ነብያቶችና ነብዩ ሙሐመድም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ይዘውት በመጡት ተልእኮ አምኖ ካልሆነ በቀር የማንም እምነት አላህ ዘንድ ተቀባይነት አያገኝም። ለዚህም የሚሆኑ የተወሰኑ ማስረጃዎችን በአንቀፅ (20) አሳልፈናል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{آمَنَ الرَّسُولُ بِمَا أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِ وَالْمُؤْمِنُونَ ۚ كُلٌّ آمَنَ بِاللَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن رُّسُلِهِ ۚ وَقَالُوا سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا ۖ غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ الْمَصِيرُ}

{መልክተኛው ከጌታው ወደ ርሱ በተወረደው አመነ። ምእምኖቹም (እንደዚሁ)። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጻሕፍቱም፣ በመልክተኞቹም ከመልክተኞቹ «በአንድም መካከል አንለይም» (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ። «ሰማን፤ ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምሕረትህን (እንሻለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው» አሉም።} [አል-በቀራህ: 285]

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا آمِنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ وَالْكِتَابِ الَّذِي نَزَّلَ عَلَىٰ رَسُولِهِ وَالْكِتَابِ الَّذِي أَنزَلَ مِن قَبْلُ ۚ وَمَن يَكْفُرْ بِاللَّهِ وَمَلَائِكَتِهِ وَكُتُبِهِ وَرُسُلِهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَالًا بَعِيدًا}

{እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው በዚያም በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ። በአላህና በመላእክቱም፣ በመጽሐፎቹም፣ በመልክተኞቹም፣ በመጨረሻውም ቀን፣ የካደ ሰው (ከእውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።} [ኒሳእ: 136] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَإِذْ أَخَذَ اللَّهُ مِيثَاقَ النَّبِيِّينَ لَمَا آتَيْتُكُم مِّن كِتَابٍ وَحِكْمَةٍ ثُمَّ جَاءَكُمْ رَسُولٌ مُّصَدِّقٌ لِّمَا مَعَكُمْ لَتُؤْمِنُنَّ بِهِ وَلَتَنصُرُنَّهُ ۚ قَالَ أَأَقْرَرْتُمْ وَأَخَذْتُمْ عَلَىٰ ذَٰلِكُمْ إِصْرِي ۖ قَالُوا أَقْرَرْنَا ۚ قَالَ فَاشْهَدُوا وَأَنَا مَعَكُم مِّنَ الشَّاهِدِينَ }

{አላህ የነቢያትን ቃል ኪዳን ከመጽሐፍና ከጥበብ ሰጥቻችሁ ከዚያም «ከእናንተ ጋር ላለው (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ መልክተኛ ቢመጣላችሁ በርሱ በእርግጥ እንደምታምኑበት በእርግጥም እንድትረዱት ሲል በያዘ ጊዜ (አስታውስ)። አረጋገጣችሁን በዚህም ላይ ኪዳኔን ያዛችሁምን» አላቸው። «አረጋገጥን» አሉ። «እንግዲያስ መስክሩ፤ እኔም ከእናንተ ጋር ከመስካሪዎቹ ነኝ» አላቸው።} [አሊ-ዒምራን 81]

## 41- የሁሉም መለኮታዊ ተልእኮዎች ግብ፡- እውነተኛው ሃይማኖት ወደ ሰው ልጅ እንዲሰርፅ ብሎም ለዓለማት ጌታ አላህ ንጹሕ ባርያ ይሆን ዘንድ፤ የሰው ልጅን ከአጉል ባህል ወይም ከአጉል እምነት ወይንም ከቁሳዊ ባርነት ነፃ ያውጣው ዘንድ ነው። ይኸውና

## እስልምና የሰዎችን ፍፁምነትንም አይሞግትም ካላቸው ሰብአዊ ደረጃ በላይ አንስቶም ጌቶች እና አማልክት አያደርጋቸውም።

የሁሉም መለኮታዊ ተልእኮዎች ግብ፦ እውነተኛው ሃይማኖት በሰው ልጅ ሰርፆ ጥርት ያለ የአለማት ጌታ አላህ ባርያ ይሆን ዘንድ ነው። እስልምና የሰውን ልጅ የቁሳዊ አምልኮ ወይንም የእንቶፈንቶ ባርያ ከመሆን ይታደገዋል። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

«تَعِسَ عَبْدُ الدِّينَارِ وَالدِّرْهَمِ وَالقَطِيفَةِ وَالخَمِيصَةِ إِنْ أُعْطِيَ رَضِيَ وَإِنْ لَمْ يُعْطَ لَمْ يَرْضَ»

"የገንዘብ ባርያ ጠፋ! የልብስ ባርያ ያጥፋው! ሲሰጠው ይደሰታል፤ (በምንም ነገር ላይ ገንዘብ) ካልተሰጠው ደግሞ አይመቸውም።" ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 6435 የነቃ ሰው ለአላህ ብቻ ነው የሚያገበድደው፤ በገንዘብ አይገዛ፣ በክብር ወይንም በሥልጣን አይገዛ፤ ወይም ለዘረኝነት አያጎበድድም። በዚህ በተከታዩ ክስተት ሰዎች ከነብያዊ ተልዕኮ በፊትና በኋላ የነበራቸውን ሁኔታ ግልፅ የሚያደርግ እውነታ አለው፦

የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ወደ ሐበሻ ሲሰደዱ የጊዜው የሐበሻ ንጉስ የነበረው ነጃሺ እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው፦ "ከሕዝባችሁ የተለያችሁበትና ወደ እኔ ሃይማኖትም ሆነ ወደ ሌሎች ሃይማኖቶች ያልገባችሁበት ይህ ሃይማኖት ምንድን

ነው?" ጃዕፈር ኢብን አቢ ጧሊብም እንዲህ በማለት መለሱ፡- “ንጉሥ ሆይ! እኛ በድንቁርና እና በአረመኔነት ጥልቀት ውስጥ ወድቀን ነበርን። ለጣዖታት የምንሰገድ፣ የበከተን የምንበላ፣ አስጸያፊ ነገሮችን የምንፈፅም፣ ዝምድናን የምንቆርጥ፣ ለጉርብትና የምናስቸግር፣ ከኛ መካከል ብርቱዎቹ ደካማውን የሚበዘብዙበት ማህበረሰቦች ነበርን። ውልደቱን፣ እውነተኛነቱን፣ አደራ ጠባቂነቱን፣ ጥብቅነቱን የምናውቅለትን ሰው አላህ በመካከላችን አስነሳልን፤ ከዚያም ይህ የአላህ መልዕክተኛ እኛም ወላጆቻችንም ከአላህ ጋር የምናጋራቸውን ድንጋዮችንና ዛፎችን እርግፍ አድርገን ትተን አንዳችም ሳናጋራ አላህን በብቸኝነት እንድናመልክ ጥሪ አደረገልን። እርሱ እውነትን እንድንናገር፣ ቃል ኪዳኖቻችንን እንድናከብር፣ በመስተጋብራችን ደግ እንድንሆን፣ ጎረቤቶቻችንን እንድንረዳ፣ የተከለከሉ ድርጊቶችን ሁሉ እንድናቆም፣ ከደም መፍሰስ እንድንርቅ፣ ጸያፍ ድርጊቶችን እና የሐሰት ምስክሮችን እንድናስወግድ፣ ወላጅ አልባ ህፃናትን ንብረት ከመብላት እንድንቆጠብ፣ የንፁህ ሴቶችን ስም ከማጥፋት እንድንታቀብ አዘዘን። አላህንም በብቸኝነት እንድንገዛው፣ ሶላት እንድንሰግድ፣ ዘካ እንድንሰጥ፣ ፆምም እንድንፆም አዘዘን። እንዲሁ በርካታ የእስልምና ጉዳዮችን ዘረዘረልን እኛም እውነት ብለን አፀደቅን፤ አመንንም፤ ይዞት በመጣው ነገር ተከተልነውም የከለከለንን ተከልክለን የፈቀደልንን ፈቅደን በአላህ ምንንም ሳናጋራ በብቸኝነት አመለክን።" አሕመድ (1740) በተወሰነ ልዩነት ጋ ፤ አቡ ኑዐይም በ

(ሒልየቱል አውሊያእ) 1/115 ላይ አጠር ባለ መልኩ ዘግበውታል። እስልምና ማንንም ግለሰብ ከደረጃው በላይ ሰጥቶ ፍፁም አድርጎ አይቆጥርም፤ አምላክና ጣኦትም አያደርግም። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ يَا أَهْلَ الْكِتَابِ تَعَالَوْا إِلَىٰ كَلِمَةٍ سَوَاءٍ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا اللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِ شَيْئًا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضًا أَرْبَابًا مِّن دُونِ اللَّهِ ۚ فَإِن تَوَلَّوْا فَقُولُوا اشْهَدُوا بِأَنَّا مُسْلِمُونَ}

{የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ። (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው። እምቢ ቢሉም፦ እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው።} [አሊ-ዒምራን 64] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا يَأْمُرَكُمْ أَن تَتَّخِذُوا الْمَلَائِكَةَ وَالنَّبِيِّينَ أَرْبَابًا ۗ أَيَأْمُرُكُم بِالْكُفْرِ بَعْدَ إِذْ أَنتُم مُّسْلِمُونَ}

{መላእክትንና ነቢያትንም አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ (አይገባውም)። እናንተ ሙስሊሞች ከኾናችሁ በኋላ በክህደት ያዛችኋልን።} [አሊ-ዒምራን 80] የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን እንዲህ ብለዋል፦

«لاَ تُطْرُونِي كَمَا أَطْرَتْ النَّصَارَى ابْنَ مَرْيَمَ فَإِنَّمَا أَنَا عَبْدُهُ فَقُولُوا عَبْدُ اللَّهِ وَرَسُولُهُ»

“እኔ ክርስቲያኖች የማርያምን ልጅ እንዳሞገሱኝ እኔን በማድነቅ አታጋንኑኝ፣ እኔ ባሪያ ብቻ ነኝ። ስለዚህ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛው በሉኝ።” ሰሒሕ ቡኻሪይ፡ 3445

## 42- አላህ በእስልምና ንስሀን (ተውባን) ደንግጓል፡ ይህም - አንድ ሰው ባጠፋ ጊዜ ወደ ጌታው መመለሱ እና ኃጢአቱን መተው ነው፤ እስልምና ከእርሱ በፊት የነበሩትን ኃጢአቶች ያጠፋል (ያስምራል)፤ ንስሐም ከዚህ በፊት የነበሩትን ኃጢአቶች ሁሉ ይሰርዛል፤ ለዚህም ማንም ኋጢአቱን በሰው ፊት መናዘዝ አያስፈልገውም።

አላህ በእስልምና ንስሀን (ተውባን) ደንግጓል፡ ይህም - አንድ ሰው ባጠፋ ግዜ ወደ ጌታው መመለሱ እና ኃጢአቱን መተው፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَتُوبُوا إِلَى اللَّهِ جَمِيعًا أَيُّهَ الْمُؤْمِنُونَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

{ምእመናኖች ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አላህ (በመመለስ) ተጸጸቱ።} (አን-ኑር 31) ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{أَلَمْ يَعْلَمُوا أَنَّ اللَّهَ هُوَ يَقْبَلُ التَّوْبَةَ عَنْ عِبَادِهِ وَيَأْخُذُ الصَّدَقَاتِ وَأَنَّ اللَّهَ هُوَ التَّوَّابُ الرَّحِيمُ}

{አላህ እርሱ ከባሮቹ ንስሓን የሚቀበል ምጽዋቶችንም የሚወስድ መሆኑን አላህም እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ

መኾኑን አያውቁም} [አት-ተውባህ: 104] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{وَهُوَ الَّذِي يَقْبَلُ التَّوْبَةَ عَنْ عِبَادِهِ وَيَعْفُو عَنِ السَّيِّئَاتِ وَيَعْلَمُ مَا تَفْعَلُونَ }

{እርሱም ያ ከባሮቹ ንስሓን የሚቀበል፣ ከኃጢአቶችም ይቅር የሚል፣ የምትሠሩትንም ሁሉ የሚያውቅ ነው።} [አሽ-ሹራ: 25] የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፡-

«لَلَّهُ أَشَدُّ فَرَحًا بِتَوْبَةِ عَبْدِهِ الْمُؤْمِنِ مِنْ رَجُلٍ فِي أَرْضٍ دَوِّيَّةٍ مَهْلِكَةٍ مَعَهُ رَاحِلَتُهُ عَلَيْهَا طَعَامُهُ وَشَرَابُهُ فَنَامَ فَاسْتَيْقَظَ وَقَدْ ذَهَبَتْ فَطَلَبَهَا حَتَّى أَدْرَكَهُ الْعَطَشُ ثُمَّ قَالَ: أَرْجِعُ إِلَى مَكَانِيَ الَّذِي كُنْتُ فِيهِ فَأَنَامُ حَتَّى أَمُوتَ فَوَضَعَ رَأْسَهُ عَلَى سَاعِدِهِ لِيَمُوتَ فَاسْتَيْقَظَ وَعِنْدَهُ رَاحِلَتُهُ وَعَلَيْهَا زَادُهُ وَطَعَامُهُ وَشَرَابُهُ فَاللهُ أَشَدُّ فَرَحًا بِتَوْبَةِ الْعَبْدِ الْمُؤْمِنِ مِنْ هَذَا بِرَاحِلَتِهِ وَزَادِهِ»

"አላህ በባርያው ተውባ የሚደሰተው፡- ከአማኞች አንዱ ሙሉ ስንቁን አሸክሞ የሚጋልበው ግመሉ ጭኖ ደክሞት ካረፈበት ሲነቃ ግመሉ ጠፍታበታለች። ለፍለጋ ብዙ ኳተነ በመጨረሻም በውኋ ጥም ሲንገላታ፤ ከዚያ "ቀድሞ ወደነበርኩበት ቦታ ልመለስና እዛው ሆኜ ልሙት" ብሎ ለሞት ራሱን አሳምኖ ሊተኛ ራስጌውን ትራስ ላይ አሳርፎ ሳለ፤ ድንገት ሲነቃ የሚጋልበው ግመሉ ከሙሉ ስንቁ ጋር በፊትለፊቱ ቆማ አያት። ይህ መንገደኛ ስንቁን ሲያገኝ ከተደሰተው በላይ አላህ በባርያዎቹ ተውባ ይበልጡን ይደሰታል።" ሰሒሕ ሙስሊም 2744

ኢስላም ከእርሱ በፊት የነበሩትን ኃጢአቶችን ያጠፋል (ያስምራል)፣ ንስሐም ከእርሱ በፊት የነበሩትን ኃጢአቶች ያስሰርዛል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ قُل لِّلَّذِينَ كَفَرُوا إِن يَنتَهُوا يُغْفَرْ لَهُم مَّا قَدْ سَلَفَ وَإِن يَعُودُوا فَقَدْ مَضَتْ سُنَّتُ الْأَوَّلِينَ }

{ለነዚያ ለካዱት በላቸው፡- ቢከለከሉ ለእነሱ በእርግጥ ያለፈውን (ሥራ) ምሕረት ይደረግላቸዋል። (ወደ መጋደል) ቢመለሱም (እናጠፋቸዋለን)። የቀድሞዎቹ ሕዝቦች ልማድ በእርግጥ አልፋለችና።} [አል-አንፋል: 38] አላህ ክርስትያኖችንም ለተውባ ጠርቷቸዋል፤ እንዲህም ብሏል፦

{ أَفَلَا يَتُوبُونَ إِلَى اللَّهِ وَيَسْتَغْفِرُونَهُ ۚ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ }

{ወደ አላህ አይመለሱምና ምሕረትን አይለምኑትምን አላህም መሓሪ አዛኝ ነው።} [አል-ማኢዳህ:74] አመፀኞችና ወንጀለኞችን ሁሉ በተውባ ወደ አላህ እንዲመለሱ አበረታትቷል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ قُلْ يَا عِبَادِيَ الَّذِينَ أَسْرَفُوا عَلَىٰ أَنفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا مِن رَّحْمَةِ اللَّهِ ۚ إِنَّ اللَّهَ يَغْفِرُ الذُّنُوبَ جَمِيعًا ۚ إِنَّهُ هُوَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ }

{በላቸው «እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ። አላህ ኃጢኣቶችን በመላ ይምራልና። እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና።} [አዝ-ዙመር: 53] ዐምር ኢብኑል ዓስ እስልምናን ለመቀበል ቆርጦ በወሰነ ጊዜ ምናልባት የቀድሞ ወንጀሉ እማይማርለት እንዳይሆን የሚል ስለተፈጠረበት ስጋት እንዲህ ሲል ይተርካል፦

(لَمَّا أَلْقَى اللهُ عَزَّ وَجَلَّ فِي قَلْبِي الْإِسْلَامَ قَالَ: أَتَيْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ لِيُبَايِعَنِي فَبَسَطَ يَدَهُ إِلَيَّ فَقُلْتُ: لَا أُبَايِعُكَ يَا رَسُولَ اللهِ حَتَّى تَغْفِرَ لِي مَا تَقَدَّمَ مِنْ ذَنْبِي قَالَ: فَقَالَ لِي رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: يَا عَمْرُو أَمَا عَلِمْتَ أَنَّ الْهِجْرَةَ تَجُبُّ مَا قَبْلَهَا مِنَ الذُّنُوبِ يَا عَمْرُو أَمَا عَلِمْتَ أَنَّ الْإِسْلَامَ يَجُبُّ مَا كَانَ قَبْلَهُ مِنَ الذُّنُوبِ)

"አላህ እስልምናን በልቦናየ ሲያሳርፍ ለሙባየዓህ (ለቃል ኪዳን) ወደ ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሄድኩና እጃቸውን ሲዘረጉልኝ እንዲህ አልኳቸው፤ "የቀድሞ ወንጀሌ እስካልተሰረዘ ድረስ ሙባየዓህ አልገባም።" እርሳቸውም: "ዓምር ሆይ! ሂጅራም የቀድሞ ወንጀል የምታጠፋ (የምታስምር) መሆኗን አላወቅክም እንዴ? እስልምናስ ከበፊቱ ያለን ወንጀል ሁሉ ጥርግ አድርጎ እንደሚያጠፋስ (እንደሚያስምር) አታውቅምን?" አሉኝ። ሙስሊም በረዥሙ ሙሉ ሰነዱን ዘግበውታል (121)፤ አሕመድም (17827) ዘግበውታል፤ ይህ የቃላት አወቃቀርም የዚሁ ዘገባ ነው።

## 43- በእስልምና በሰው እና በአላህ መካከል ያለው ቁርኝት ቀጥተኛ ነው። በአንተና በአላህ መካከል ምንም አማላጅ አያስፈልግህም። የእስልምና ሃይማኖት የሰውን ልጅ አማልክት ወይም በጌትነት ወይም በአምላክነት የአላህ ተጋሪ እንዳናደርግ ይከለክለናል።

በእስልምና ወደ አላህ በተውባ ለመመለስ በሰው ፊት ኃጢአትን መናዘዝ አያስፈልግም። በእስልምና ውስጥ በሰው

እና በአምላክ መካከል ያለው ግንኙነት ቀጥተኛ ነው። በመሆኑም በአንተ እና በአላህ መካከል ማንም አማላጅ እንዲሆንልህ አያስፈልግህም። ልክ በአንቀፅ (36) እንዳሳለፍነው ማለት ነው። የላቀው አላህ ሰዎች ሁሉ ተውባ እንዲያደርጉና ወደ እርሱም እንዲመለሱ ጥሪ ያደረገ በመሆኑ በእርሱ እና በአገልጋዮቹ መካከል ሰዎችን፣ ነቢያትን ወይም መላእክትን አማላጅ ማድረጋቸውን ከልክሏል። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا يَأْمُرَكُمْ أَن تَتَّخِذُوا الْمَلَائِكَةَ وَالنَّبِيِّينَ أَرْبَابًا ۗ أَيَأْمُرُكُم بِالْكُفْرِ بَعْدَ إِذْ أَنتُم مُّسْلِمُونَ}

{መላእክትንና ነቢያትንም አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ (አይገባውም)። እናንተ ሙስሊሞች ከኾናችሁ በኋላ በክህደት ያዛችኋልን?} [አሊ-ዒምራን 80] እስልምና - እንዳየሀው - በጌትነቱ ወይም በአምላክነቱ የሰው ልጆችን አማልክት ወይም ከአላህ ጋር አጋር አድርጎ መያዝን ይከለክላል። የላቀው አላህ ክርስትያኖችን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

{اتَّخَذُوا أَحْبَارَهُمْ وَرُهْبَانَهُمْ أَرْبَابًا مِّن دُونِ اللَّهِ وَالْمَسِيحَ ابْنَ مَرْيَمَ وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا إِلَٰهًا وَاحِدًا ۖ لَّا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۚ سُبْحَانَهُ عَمَّا يُشْرِكُونَ}

{ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲኾኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን፣ የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።} [አት-ተውባህ: 31] አላህ ከሓዲዎች በእርሱና በእነርሱ

መካከል አማላጆች መያዛቸውን አውግዞበቸዋል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{أَلَا لِلَّهِ الدِّينُ الْخَالِصُ ۚ وَالَّذِينَ اتَّخَذُوا مِن دُونِهِ أَوْلِيَاءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللَّهِ زُلْفَىٰ إِنَّ اللَّهَ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ فِي مَا هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي مَنْ هُوَ كَاذِبٌ كَفَّارٌ}

{ንቁ! ፍጹም ጥሩ የኾነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው። እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች የያዙት «ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም» (ይላሉ)። አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል። አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም።} [አዝ-ዙመር: 3] ጣኦት አምላኪያን -የጃሂሊያ ሰዎች- በእነርሱና በአላህ መካከል አማላጅ መያዛቸውንና ወደ አላህ ያቃርቡናል ብለው እንደሚያስቡ ግልፅ አድርጓል።

አላህም ሰዎች በእርሱና በአገልጋዮቹ መካከል ነቢያትን ወይም መላእክትን አማላጅ መደረጋቸውን ከከለከለ፤ ለሌሎቹማ ይበልጥ የሚከለከሉ ይሆናል፤ ይህ የተባለው ነቢያትና መልእክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም ወደ አላህ ለማቃረብ የሚጣደፉ ከመሆናቸውም ጋ ነው። የነብያቶችንና የመልዕክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም ሁኔታ በማስመልከት አላህ እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّهُمْ كَانُوا يُسَارِعُونَ فِي الْخَيْرَاتِ وَيَدْعُونَنَا رَغَبًا وَرَهَبًا ۖ وَكَانُوا لَنَا خَاشِعِينَ }

{እነርሱ በበጎ ሥራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ኾነው የሚለምኑንም ነበሩ። ለእኛ ተዋራጆችም ነበሩ።} [አል-አንቢያእ: 90] ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{أُولَٰئِكَ الَّذِينَ يَدْعُونَ يَبْتَغُونَ إِلَىٰ رَبِّهِمُ الْوَسِيلَةَ أَيُّهُمْ أَقْرَبُ وَيَرْجُونَ رَحْمَتَهُ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُ ۚ إِنَّ عَذَابَ رَبِّكَ كَانَ مَحْذُورًا}

{እነዚያ እነርሱ የሚግገዟቸው ማንኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን (ሥራ) ይፈልጋሉ። እዝነቱንም ይከጅላሉ። ቅጣቱንም ይፈራሉ። የጌታህ ቅጣት የሚፈራ ነውና።} [አል-ኢስራእ: 57] እነዚያ ከአላህ ውጭ የምትጠሯቸው ራሳቸው - ነቢያትና ሷሊሖች - ወደ አላህ በመቃረብ ምሕረቱን ተስፋ ያደርጋሉ፤ ቅጣቱን ይፈራሉ። ታድያ እንዴት ከአላህ ውጭ አማላክት ተደርገው ይጠራሉ?

## 44- በዚህ ፅሁፍ መጨረሻ ላይ ማውሳት የምንፈልገው ነገር ቢኖር፡ ሰዎች በተለያዩ ጊዜዎች፣ ብሄረሰቦች እና ሀገሮች መሆናቸውን እናስተውላለን፤ ኧረ እንደውም መላው የሰው ልጅ ማህበረሰብ በሀሳቡ እና በአላማው የተለያየ በአከባቢው እና በድርጊቱም የተለያየ በመሆኑ አንድ የሚያደርግ ሥርዓት እና ጥበቃን የሚያደርግለት ገዥ ወደ ጥሩ የሚመራው መመሪያ ጋር ግዴታ ያስፈልገዋል። የአላህ ሰላትና ሰላም በእነርሱ

**ላይ ይስፈን የተከበሩት የአላህ መልእክተኞችም ከአላህ -ሱብሓነሁ ወተዓላ- በሚወርድላቸው ወሕይ በአላህ ሸሪዓ በማሰባብሰብ፣ በሰዎች መካከል በእውነት በመፍረድ ሰዎችን ወደ መልካምና ቀና ጉዳና የመምራት ኋላፊነትን ተሸክመው ነበር። ሰዎች ለእነኝህ የአላህ መልእክተኞች ተልእኮ ባላቸው ምላሽ ሰጭነት እንዲሁም ለመለኮታዊው ጥሪም ባላቸው የጊዜ ቅርበትም ልክ ሁኔታቸው ይስተካከል ነበር። ጥራት ይገባውና አላህ መልእክተኛውን ሙሐመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በመላክ ለሰው ልጆች የሚያስተላልፈውን ተልእኮ ደመደመና ለነብያችን ሙሐመድ ተልእኮም ዘለቄታን ፃፈላት (ደነገገለት)፤ ለሰው ልጆችም ምሪቻ፣ እዝነት፣ ብርሃን፣ ጥራት ወደ ተገባው አላህ የምትመራም ቅን ፈለግ አደረጋት።**

በዚህ ፅሁፍ መጨረሻ ላይ ማውሳት የምንፈልገው ነገር ቢኖር፡ ሰዎች በተለያዩ ጊዜዎች፣ ብሄረሰቦች እና ሀገሮች መሆናቸውን እናስተውላለን፤ ኧረ እንደውም መላው የሰው ልጅ ማህበረሰብ በሀሳቡ እና በአላማው የተለያየ በአከባቢው እና በድርጊቱም የተለያየ በመሆኑ አንድ የሚያደርግ ሥርዓት

እና ጥበቃን የሚያደርግለት ገዥ ወደ ጥሩ የሚመራው መመሪያ ጋር ግዴታ ያስፈልገዋል። የአላህ የአላህ ሰላትና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈን የተከበሩት የአላህ መልእክተኞችም ከአላህ -ሱብሓነሁ ወተዓላ- በሚወርድላቸው ወሕይ በአላህ ሸሪዓ በማሰባብሰብ፣ በሰዎች መካከል በእውነት በመፍረድ ሰዎችን ወደ መልካምና ቀና ጉዳና የመምራት ኋላፊነትን ተሸክመው ነበር። ሰዎች ለነኝህ የአላህ መልእክተኞች ተልእኮ ባላቸው ምላሽ ሰጭነት እንዲሁም ለመለኮታዊው ጥሪም ባላቸው የጊዜ ቅርበትም ልክ ሁኔታቸው ይስተካከል ነበር። ጥመት ሲበዛ፣ ድንቁርና ሲበረታ፣ ለጣዖታትም ሊሰገድላቸው በጀመረ ጊዜ አላህ ነብዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሰዎችን ከክህደት፣ ከድንቁርናና ከጣዖት አምልኮ ጨለማ ወደ እምነት እና ወደ ቀና ጎዳና ለማውጣት በቀና መመርያና በቀጥተኛ ሃይማኖት ላካቸው።

## 45- ስለዚህም የሰው ልጅ ሆይ! ከአጉል ባህልና ከልምድ እንዲሁም ከድንቁርና በመላቀቅ እስልምናን ተቀብለህ በሐቀኝነት ለአላህ እንድትቆም ከሞትክም በኋላ ወደ ጌታህ ተመላሽ መሆንህን እንድታውቅ፤ ራስህንም በዙሪያህ ያለውንም አድማስ እንድትመለከት አደራ እያልኩ እጋብዝሃለሁ። ያኔ በሃይማኖታዊም በአለማዊም ጉዳይህ ደስተኛ

**ትሆናለህ። ወደ እስልምና ሃይማኖት ለመግባት የፈለገ "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ እንደሆኑ" ለመመስከር "ላ ኢላሃ ኢለሏህ ሙሓመዱን ረሱሉሏህ" ብሎ መመስከር ብቻ ነው የሚጠበቅበት። ይህችን የምስክርነት ቃል ከሰጡ ሙስሊም ሆነዋል። ከዚህ በኋላ አላህ በደነገገው መልኩ ሶላትንም እየሰገዱ፣ ፆሞን እየፆሙ፣ ከቻሉም ሓጅ በማድረግ አላህን ማምለክ ላይ አደራ።**

ስለዚህም የሰው ልጅ ሆይ! ከአጉል ባህልና ከልምድ እንዲሁም ከድንቁርና በመላቀቅ እስልምናን እንድትቀበል እጋብዝሀለሁ፤ ልክ የላቀው አላህም በተከታዩ አንቀፅ እንደጠራህ፦

{قُلْ إِنَّمَا أَعِظُكُم بِوَاحِدَةٍ ۖ أَن تَقُومُوا لِلَّهِ مَثْنَىٰ وَفُرَادَىٰ ثُمَّ تَتَفَكَّرُوا ۚ مَا بِصَاحِبِكُم مِّن جِنَّةٍ ۚ إِنْ هُوَ إِلَّا نَذِيرٌ لَّكُم بَيْنَ يَدَيْ عَذَابٍ شَدِيدٍ}

{«የምገስጻችሁ ባንዲት ነገር ብቻ ነው። (እርሷም) ሁለት ሁለት አንድ አንድም ሆናችሁ ለአላህ እንድትነሱ ከዚያም በጓደኛችሁ (በሙሐመድ) ምንም ዕብደት የሌለበት መሆኑን መርምራችሁ እንድትረረዱ ነው። እርሱ ለእናንተ ከብርቱ ቅጣት በስተፊት አስጠንቃቂ ነው እንጂ ሌላ አይደለም» በላቸው።} [ሰባእ: 46] ከሞትክ በኋላም ወደ ጌታህ

እንደምትመለስ ልታውቅ ይገባሀል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَأَن لَّيْسَ لِلْإِنسَانِ إِلَّا مَا سَعَىٰ (39) وَأَنَّ سَعْيَهُ سَوْفَ يُرَىٰ (40) ثُمَّ يُجْزَاهُ الْجَزَاءَ الْأَوْفَىٰ (41) وَأَنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ الْمُنتَهَىٰ (42) }

{ለሰውም ሁሉ የሠራው እንጅ ሌላ የለውም።} (39)

{ሥራውም ሁሉ ወደ ፊት ይታያል።}

{ከዚያም ሙሉውን ምንዳ ይመነዳዋል።}

{መጨረሻውም ወደ ጌታህ ብቻ ነው።} [አን-ነጅም: 39-42] ራስክንም በዙርያህ ያለውንም ትመለከት ዘንድ እጋብዝሀለሁ፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ أَوَلَمْ يَنظُرُوا فِي مَلَكُوتِ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَا خَلَقَ اللَّهُ مِن شَيْءٍ وَأَنْ عَسَىٰ أَن يَكُونَ قَدِ اقْتَرَبَ أَجَلُهُمْ ۖ فَبِأَيِّ حَدِيثٍ بَعْدَهُ يُؤْمِنُونَ}

{በሰማያትና በምድር ግዛት ውስጥ ከማንኛው ነገር አላህ በፈጠረውም ሁሉ የሞት ጊዜያቸውም በእርግጥ መቅረቡ የሚፈራ መኾኑን አያስተውሉምን ከእርሱም (ከቁርኣን) ወዲያ በየትኛው ንግግር ያምናሉ።} [አል-አዕራፍ: 185]

እስልምናን ተቀበልና በዚህም በቀጣዩ አለምም ደስተኛ ትሆናለህ፤ ወደ እስልምና ከገባህም "ላ ኢላሀ ኢለሏህ ሙሐመዱን ረሱሉሏህ" ብለህ በአላህ አንድነትና በነብዩ ሙሐመድ ከመስከር ውጭ የሚጠበቅብህ ነገር የለም። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሙዓዝን ወደ የመን በላኩት ጊዜ እንዲህ ብለውት ነበር፦

«إِنَّكَ تَأْتِي قَوْمًا مِنْ أَهْلِ الْكِتَابِ فَادْعُهُمْ إِلَى شَهَادَةِ أَنَّ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَأَنِّي رَسُولُ اللهِ فَإِنْ هُمْ أَطَاعُوا لِذَلِكَ فَأَعْلِمْهُمْ أَنَّ اللهَ افْتَرَضَ عَلَيْهِمْ خَمْسَ صَلَوَاتٍ فِي كُلِّ يَوْمٍ وَلَيْلَةٍ فَإِنْ هُمْ أَطَاعُوا لِذَلِكَ فَأَعْلِمْهُمْ أَنَّ اللهَ افْتَرَضَ عَلَيْهِمْ صَدَقَةً تُؤْخَذُ مِنْ أَغْنِيَائِهِمْ فَتُرَدُّ فِي فُقَرَائِهِمْ فَإِنْ هُمْ أَطَاعُوا لِذَلِكَ فَإِيَّاكَ وَكَرَائِمَ أَمْوَالِهِمْ»

"አንተ የምትሄድባቸው ሰዎች የመጽሐፉ ባለቤት ወደሆኑ ህዝቦች ነው፤ በመሆኑም በ "ላ ኢላሃ ኢለሏህ" እና በኔም የአላህ መልዕክተኝነት እንዲመሰክሩ ጥሪ አድርግላቸው፤ ለዚህ ጥሪህ ተገቢውን ምላሽ ከሰጡህ ልእል ኀያሉ አላህ በየቀኑ አምስት ግዜ የምትሰገድ ሶላትን ግዴታ እንዳደረገባቸው አስተምራቸው፤ ለዚሁ ጥሪህም ተገቢውን ምላሽ ከሰጡህ ልእለ ኀያሉ አላህ በገንዘባቸው ላይ ከሀብታሞቻቸው ተይዞ ወደ ድሆቻቸው የምትመለስ የሆነችን ሶደቃ ግዴታ እንዳደረገባቸው አስተምራቸው፤ ለዚህም ተገቢውን ምላሽ ከሰጡህ አደራ ውድ ንብረቶቻቸውን ተጠንቀቅ (አትንካባቸው)።" ሰሒሕ ሙስሊም 19 እንዲሁም ከአላህ ውጭ የሚመለከውንም ሁሉ እንድትተው አደራ እልሀለሁ፤ ከአላህ ውጭ ከሚመለክ ሁሉ መጥራራት ይገባል፤ ቀና የሆነችዋ የነብዩሏህ ኢብራሂም ፈለግ ማለት እርሷ ነች። የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{قَدْ كَانَتْ لَكُمْ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ فِي إِبْرَاهِيمَ وَالَّذِينَ مَعَهُ إِذْ قَالُوا لِقَوْمِهِمْ إِنَّا بُرَآءُ مِنكُمْ وَمِمَّا تَعْبُدُونَ مِن دُونِ اللَّهِ كَفَرْنَا بِكُمْ وَبَدَا بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمُ الْعَدَاوَةُ وَالْبَغْضَاءُ أَبَدًا حَتَّىٰ تُؤْمِنُوا بِاللَّهِ وَحْدَهُ}

{በኢብራሂምና በእነዚያ ከእርሱ ጋር በነበሩት (ምእምናን) መልካም መከተል አለቻችሁ። ለሕዝቦቻቸው

«እኛ ከእናንተ ከአላህ ሌላ ከምትግገዙትም ንጹሖች ነን። በእናንተ ካድን። በአላህ አንድ ብቻ ሲኾን እስከምታምኑ ድረስ በእኛና በእናንተ መካከል ጠብና ጥላቻ ዘወትር ተገለጸ።» ባለ ጊዜ (መልካም መከተል አለቻችሁ)።} [አል-ሙምተሒናህ: 4] አላህ በቀብር ውስጥ ያሉትን ሙታኖችንም እንደሚቀሰቅስም ልታምን ይገባሀል፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{ذَٰلِكَ بِأَنَّ اللَّهَ هُوَ الْحَقُّ وَأَنَّهُ يُحْيِي الْمَوْتَىٰ وَأَنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ (6) وَأَنَّ السَّاعَةَ آتِيَةٌ لَّا رَيْبَ فِيهَا وَأَنَّ اللَّهَ يَبْعَثُ مَن فِي الْقُبُورِ (7) }

{ይህ አላህ እርሱ መኖሩ የተረጋገጠ፣ እርሱም ሙታንን ሕያው የሚያደርግ፣ እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ በመሆኑ ነው።}

{ሰዓቲቱም መጪ፣ በእርሷ ፈጽሞ ጥርጣሬ የሌለባት በመሆኗ፣ አላህም በመቃብሮች ውስጥ ያለን ሁሉ የሚቀሰቅስ በመሆኑ ነው።} [አል-ሓጅ: 6-7] መተሳሰብና ምንዳ እውነት ነው፤ የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

{وَخَلَقَ اللَّهُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ بِالْحَقِّ وَلِتُجْزَىٰ كُلُّ نَفْسٍ بِمَا كَسَبَتْ وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ }

{አላህም ሰማያትንና ምድርን (ለችሎታው እንደሚያመለክትባቸውና) ነፍስም ሁሉ በሠራችው ሥራ ትምመነዳ ዘንድ በትክክል ፈጠረ። እነርሱም አይበደሉም።} [አል-ጃሢያህ: 22]

ይህንን የምስክርነት ቃልህን ከሰጠህ ሙስሊም ሆንክ ማለት ነው፤ ስለዚህም ከዚያ በኋላ ሶላት ላይ፣ ዘካ መስጠት

ላይ፣ ጾም መጾም ላይና የጉዞ ጣጣውን ከቻልክ ደግሞ ሐጅ ማድረግ ላይና መሰል የተደነገጉ አምልኮዎች ላይ አደራህን።

የቀን 19-11-1441 ቅጂ

ጸሐፊ መምህር ዶክተር ሙሐመድ ቢን ዐብደላህ ሱሐይሚ

በኢስላማዊ አስተምህሮ ክፍል ነባር የዓቂዳ አስተማሪ

መሊክ ሰዑድ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ክፍል

በሳዑዲ ዓረቢያ ግዛት፡ ሪያድ

# ማውጫ

እስልምና......2
ስለ እስልምና አጭር ገለፃ፤ በተከበረው ቁርአን እና በነብያዊ ሐዲሥ በመጣበት መልኩ......2
1- እስልምና ወደ ሰው ልጆች ሁሉ የተላከ የአላህ መልዕክት ነው። እንዲሁም ዘውታሪ የሆነ አምላካዊ የመጨረሻ መልዕክቱም ነው። ......2
2- እስልምና ለተወስኑ ነገዶች ወይንም ህዝቦች ብቻ የተወሰነ ሃይማኖት ሳይሆን አምላካዊ የሰው ልጆች ሁሉ ሃይማኖት ነው። ......4
3- እስልምና የአላህ ሰላት እና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና የቀደምት ነብያትንና መልእክተኞችን መልእክት ለማሟላት የመጣ መለኮታዊ መልእክት ነው። ......5
4- ነብያቶች ሁሉ የአላህ ሰላት እና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና ሃይማኖታቸው አንድ ሲሆን መመርያ ድንጋጌያቸው ግን የተለያየ ነው። ......7
5- እስልምና የሚጣራው፡- ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ሱለይማን፣ ዳውድ፣ ዒሳ የአላህ ሰላት በእነርሱ ላይ ይስፈንና ~ሁሉም ነብያቶች ወደተጣሩበት ብቸኛ ጌታ፣ ፈጣሪ፣ ሲሳይ ለጋሽ፣ ህይወት ሰጪ ህይወት ነሺ፣ ንጉሰ ነገስት፣ የጉዳዮችም አስተናባሪ በሆነው አላህ ወደ ማመን ነው። ......8
6- ጥራት ይገባውና ከፍ ያለው አላህ ፈጣሪ እና ለአምልኮ ብቸኛው ተገቢ የሆነ ከእርሱም ሌላ አብሮት ሊመለክ የማይገባው ነው። ......15

7- በፍጠረተ አለሙ ያለውን ሁሉ የምናየውንም የማናየውንም ፈጣሪ አላህ ነው። ከእርሱ ውጪ ያለው ሁሉ ከፍጥረታቱ መካከል የሆነ ፍጡር ብቻ ነው። አላህ ሰማያትንና ምድርንም በሰባት ቀናት ፈጠረ።..........................................................................................23

8- ጥራት የተገባው አላህ በንግስናውም ሆነ በመፍጠሩ፤ በማስተናበሩም ሆነ በአምልኮው ተጋሪ የለውም። ....................25

9- ጥራት የተገባው አላህ አልወለደም አልተወለደም ብጤም ሆነ አምሳያም የለውም።.................................................................29

10- ጥራት የተገባውና ከፍ ያለው አላህ በአንዳች ፍጡራኑ ላይ የሚሰርፅም የሚዋሃድም አይደለም። ........................................31

11- ጥራት የተገባውና ከፍ ያለው አላህ ርህሩህና አዛኝ በመሆኑ መልዕክተኞችን ላከ መጽሐፍቶችንም አወረደ። .........................34

12- ጌታችን አላህ እጅግ በጣም አዛኙ በእለተ ትንሳኤ ፍጥረታትን የሚተሳሰብ ብቸኛው ጌታ ነው። የዚያኔ ሁሉንም ባጠቃላይ ከቀብራቸው እንዲቀሰቀሱ አድርጎ እያንዳንዱን ግለሰብ ከሰራው መልካምና ክፉ ስራው አንፃር ይመነዳዋል። አማኝ ሆኖ መልካምን የሰራ ዘውታሪ ፀጋ አለለት፤ የካደና መጥፎንም የሰራ ደግሞ በእለተ ትንሳኤ ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል።................................35

13- ከፍ ያለው አላህ አደምን ከፈጠረ በኋላ ዝርያዎቹ ከእርሱ በኋላ እንዲባዙ አደረገ። የሰው ልጆች ሁሉ አላህን በመፍራታቸው ካልሆነ በቀር በመሰረታዊ ማንነታቸው አንዱ ዝርያ ከሌላኛው ዝርያ አንዱ ህዝብ ከሌላኛው ህዝብ በማይበላለጥበት መልኩ እኩል ናቸው።..........................................................................39

14- ሁሉ ልጅ በተፍጥሯዊው ሃይማኖት (እስልምና) ላይ ሆኖ ነው የሚወለደው። .........................................................................42

15- ማንኛውም ሰው ሲወለድ ኋጢአተኛ ሆኖ ወይንም የሌላን ኋጢአት ወርሶ አይወለድም። ....................................................44

16 - የሰው ልጆች የመፈጠራቸውም አላማ አላህን በብቸኝነት ለማምለክ ነው። ......................................................................46

17 - እስልምና የሰውልጆችን –ወንዶቹንም ሆነ ሴቶቹን- ክብርን አጎናፀፋቸው፤ ለተሟላ መብታቸውም ዋስትናውን አረጋገጠላቸው፤ በተቀሩት ምርጫዎች፣ ድርጊቶችም ሆኑ ክንውኖች ተጠያቂነትን አደረገባቸው፤ ራሱንም ይሁን ሌላን ለሚጎዱ ድርጊቶች የተጠያቂነት ኋላፊነት ጣለባቸው። .............47

18- እስልምና ወንዶችንና ሴቶችንም ከተጠያቂነት፣ ከቅጣት፣ ከምንዳም ሆነ ከሽልማት አንፃር እኩል አደረጋቸው። ................53

19- እስልምና ሴትን ልጅ አከበረ፤ ሴቶቹን የወንዶቹ ክፋይ አድርጎም ቆጠረ፤ ወንድ እስከቻለ ድረስ ለሴት ይለግሳት ዘንድ ግዴታን ጣለበት፤ በመሆኑም አባት የሴት ልጁን ወጭ የመቻል ግዴታ አለበት፤ እናትም ወጭዋን ለመቻል የደረሰ ልጅ ካላት፤ ሚስትም ባሏ ወጭዋን ሊችሉ ግዴታ አለባቸው። ....................55

20- ሞት ብሎ ማለት ሙሉ በሙሉ አልቆ መጥፋት ማለት ሳይሆን ከስራ አለም ወደ ምንዳ አለም መሸጋገር ነው። ሞት አካልንም ሩሕንም የሚመለከት ነው። የሩሕ ሞት ስንል ግን ከአካል መለየቷን ማለታችን ነው። ከዚያም በእለተ ትንሳኤ ከተቀሰቀሱ በኋላ ሩሕ ወደ አካሏ ትመለሳለች። ሰው ከሞተ በኋላ ሩሑ ወደ ሌላ አካልም አትሸጋገርም ወደሌላም አካል አትሰርፅም። ........................................................................................................59

21- እስልምና በታላላቅ የእምነት መሰረቶች ወደ ማመን ይጣራል። እነኝህም፡ በአላህ ማመን፤ በመላእክቶች ማመን፤ በመለኮታዊ መጽሐፍት በነ ተውራት፣ ኢንጂል፣ ዘቡር –

ከመበረዛቸው በፊት- ማመን እንዲሁም በቁርአን ማመን፤ የአላህ ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈንና በሁሉም ነብያቶች እና መልዕክተኞች ማመን እንዲሁም በመጨረሻቸውና የነብያቶችም የሩሱሎችም መደምደሚያ በሆኑት የአላህ መልዕክተኛ በሙሐመድ ማመን፤ በመጨረሻው ቀን ማመን –የዱንያ ህይወት ብቻ እንጂ ሌላ አለም የሌለ ቢሆን ኖሮ ህይወትም ሆነ ህልውና ጥርት ያለ ተላላነት በሆነ ነበር- በቀዷና በቀደር ማመን ላይ የተመሰረተ ነው።..........................................................................61

22- ነብያቶች ከአላህ በሚያደርሱት ተልእኳቸው ጥብቆች ናቸው፤ ህሊና ጋ ከሚጋጭም ሆነ ጥሩ ስነምግባር ከማይቀበለውም ነገር ሁሉም የተጠበቁ ናቸው፤ የአላህን ትእዛዞች ለባርያዎቹ የማድረስ ኋላፊነት የተሰጣቸው ነብያቶቹ ናቸው። ነብያቶች ለአላህ ብቻ ካሉት አምላካዊም ሆነ ጌታዊ ማንነት ድርሻ የላቸውም። ይልቅ እነርሱም እንደሌላው ሰው ሲሆኑ አላህ ተልእኮውን የሚገልፅላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው።............................................80

23- እስልምና በታላላቅ መሰረቶች ባላቸው አምልኮ አላህን በብቸኝነት ወደ ማምልከ ጥሪ ያደርጋል፤ እነኝህም፡- ሶላት እርሷም መቆምና ማጎብደድ በግንባር መደፋትም (ሱጁድ) አላህን ማወደስና መማፀንንም ያካተተች ስትሆን በየዕለቱ እያንዳንዱ ግለሰብ አምስት ጊዜ የሚሰግዳት እንዲሁም በሰው ልጆች መካከል ያሉ ልዩነቶችንም የምታስወግድ ሃብታሙም ሆነ ድሃው መሪውም ሆነ ተመሪው በአንድ መስመር ገጥመው የሚሰግዷት ግዴታ ነች። ዘካ፡- አላህ ባስቀመጠው ጥቂት የገደብ መጠን በአመት አንድ ጊዜ ከሃብታም ንብረት ተቀንሶ ለድሃውና ለመሳሰሉት የምትሰጥ ግዴታ ነች። ፆም፡- በወርሃ ረመዷን የቀኑ ክፍለ ጊዜ ፆምን ከሚያፈርሱ ነገሮች ታቅቦ መዋል ሲሆን ነፍስን፣ ፍላጎትንና ትእግስትን የሚያሰለጥን ነው። ሐጅ፡- አቅም ባለው

ሰው ላይ ሁሉ በእድሜ ልክ አንድ ጊዜ በተከበረው መካ የሚገኘውን የአላህን ቤት መጎብኘት ሲሆን በዚህ በስርአተ ሐጅ ሁሉም ወደ ፈጣሪ በመቅጣጨት እኩል በመሆናቸው ልዩነቶች እና መከፈሻዎች ሁሉ ይወገዳሉ። ....................................................88

24- ኢስላማዊ አምልኮ ከሚለይባቸው መለያዎች መካከል ሁኔታውንም ሆነ ጊዜው ብሎም ቅድመ መስፈርቱን ሁሉ ያስቀመጠው አላህ ሲሆን ያደረሱት ስውግሞ የአላህ ሶለዋትና ሰላም ይስፈንባቸውና መልእክተኛው መሆናቸው ነው። ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬም ድረስ በመጨመሩም ሆነ በመቀነሱ የማንም ጣልቃ ገብነት የለበትም። እነኝህ ከፍ ብለን የጠቀስናቸው ታላላቅ አምልኮዎችም ቢሆኑ ነብያቶችም ሁሉ የተጣሩባቸው አምልኮዎች ናቸው። .......................................................................................96

25- የኢስላምን መልዕክት (ለዚህ ህዝብ ያደረሱት) የኢብራሂም ልጅ ኢስማዒል ዝርያ የሆኑት ነብዩ ሙሐመድ ቢን ዐብደሏህ ናቸው። በመካ እ. ኣ. አ. በ 571 ተልከው እዛው ተልእኮው የተሰጣቸው ሲሆን ወደ መዲና ሂጅራ አድርገዋል (ተሰደዋል)። ህዝባቸውንም በጣኦታዊ ጉዳያቸው አልተጋሯቸውም (ድጋፍ አልሰጡም)። ይልቅ ህዝባቸውን ይደግፉ የነበሩት በታላላቅ ስራዎች ላይ ነበር። ከመላካቸውም በፊት ባማረ ታላቅ ስነምግባር ላይ ነበሩ፤ ህዝቦቻቸውም አል አሚን (ታማኙ) ይሏቸው ነበር፤ እድሜያቸውም አርባ አመት በሞላ ጊዜ አላህ መልዕክተኛው አድርጎ ላካቸውና በታላላቅ ተአምራቶችም አጠነከራቸው፤ ይበልጥ ታላቁ ተዓምር የተከበረው ቁርአን ነው። ይኸውም የቁርአን ተአምርነት ከነብያቶች ተአምር ሁሉ እጅግ በጣም ታላቁ ተአምር ሲሆን ከነብያቶች ተአምር ሁሉ እስከዛሬ ድረስ የዘለቀውም ተአምር እርሱው ነው። አላህ ለእርሳቸው ዲኑን ባሟላላቸው ጊዜ መልእክተኛውም ተልእኳቸውን በተሟላ መልኩ

ያደረሱ ሆነው እድሜያቸው 63 አመት በሞላ ጊዜ ከዚህ አለም በሞት ተለዩ። በነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከተማ መዲና ተቀበሩ። የአላህ መልእክተኛ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የነብያቶችና የመልእክተኞችም መጨረሻ ሲሆኑ አላህ የሰው ልጆችን ሁሉ ከጣኦታዊ የክህደትና የድንቁርና ጨለማዎች ወደ የተውሒድና የኢማን ብርሃን ሊያወጡ ላካቸው። አላህም በእርሱ ፈቃድ ወደ እርሱ የሚጣሩ መሆናቸው መሰከረላቸው።...............................99

26- ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ይዘውት የመጡት የእስልምና ድንጋጌ የአምላካዊ ተልእኮዎችና የጌታቻን አላህ ድንጋጌዎች መጨረሻ ነው። ይህችም የሙሉነት ድንጋጌ ስትሆን በውስጧም የሰው ልጆች ዲናዊም ሆነ ዱንያዊ መስተካከል የያዘች ነች። ይህች ሸሪዓ በመጀመርያ ደረጃ የሰው ልጆችን ሃይማኖት፣ ደማቸውንም፣ ንብረታቸውንም፣ አእምሯቸውንም፣ ዝርያቸውንም፣ ትጠብቅላቸዋለች። የቀደሙት ሸሪዓዎች ከፊሉ ከፊሉን ሲሽር እንደነበረው ሁሉ የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሸሪዓም ቀደምት ድንጋጌዎችን ሁሉ የምትሽር ነች።............................................105

ጥራት የተገባውና ከፍ ያለው አላህ መልዕክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ይዘውት ከመጡት ሃይማኖት ውጪ ሌላን ሃይማኖት አይቀበልም። በመሆኑም ከእስልምና ውጪ ያለን ሃይማኖት አድርጎ የያዘን አላህ አይቀበለውም።..........................................................................109

28- የተከበረው ቁርአን ከፍ ያለው አላህ ለመልዕክተኛው ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በወሕይ መልኩ ያወረደለት መጽሐፍ የአላህ ቃል ነው። የእርሱን አምሳያ

ወይንም ከአምሳያው የአንዲቷን ምእራፍ አምሳያ እንኳ እንዲያመጡ አላህ የሰው ልጆችንም ይሁን አጋንንቶችን ሁሉ ያፎካከረበት ነው። ማፎካከሩ ዛሬም ድረስ ያለ ነው። ይህ ታላቁ ቁርአን ብዙ እልፍ አእላፍ ሰዎችን የሚያሳስቡ በርካታ ጥያቄዎችን ይመልሳል። ይህ ታላቁ ቁርአን የወረደበት በሆነው የዐረብኛ ቋንቋ የአንዲት ሆሄ እንኳ መጨመር እና መቀነስ ሳይኖርበት እንደተጠበቀ ነው ያለው። ታትሞ የተሰራጩና ተአምራዊ ሲሆን መቅራቱም ሆነ የተተረጎመውን ማንበቡ የሚገባው የሆነ ታላቅ ኪታብ ነው። ልክ የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ፈለግ፣ አስተምህሮትና ታሪካቸውም የተጠበቀ እና በታማኝ ዘጋቢዎች ሰንሰለት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ እንዲሁም እሳቸው ሲናገሩበት በነበረው የዐረብኛ ቋንቋም የታተመ ብሎም ወደ በርካታ ቋንቋ የተተረጎመ እንደሆነው ሁሉ። የተከበረው ቁርአን እና የነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ሱና ለዲነል ኢስላም ህግጋትና ድንጋጌዎች ብቸኞቹ ምንጮች ናቸው። የእስልምና ምንጩ ራሳቸውን ወደ እርሱ ከሚያስጠጉ ግለሰቦች ተግባር ሳይሆን ከአምላካዊ ወሕይ ነው የሚያዘው፤ ማለትም ከተከበረው ቁርአንና ከነብያዊ ሱና።... 111

29- እስልምና ሙስሊም እንኳ ባይሆኑ ለወላጆች በጎ መዋልን ያዛል ስለልጆችም መልካሙን አደራ ያስተላልፋል።................. 118

30- እስልምና ከጠላት ጋር እንኳ በተግባርም ሆነ በንግግር ፍትሃዊ መሆንን ያዛል።............................................................ 124

31- እስልምና ለፍጥረታቱ ሁሉ በጎ መዋልን የሚያዝ ሲሆን ወደ መልካም ስነምግባርና ወደ በጎ ስራዎችም ጥሪ ያደርጋል።..... 128

32- እስልምና እውነተኛነትን፣ አደራን መወጣትን፣ ጥብቅነትን፣ አይነ አፋርነትን፣ ጀግንነትን፣ ለጋስነትን፣ ቸርነትን፣ የተቸገረን

መርዳትንና የወደመበትን መታደግን፣ የተራበን ማብላትን፣ መልካም ጉርብትናን፣ ዝምድና መቀጠልን፣ ለእንስሳት እንኳ ማዘንን በመሰሉ ምስጉን የሆኑ ስነምግባሮች ሁሉ ያዛል።..... 131
33- እስልምና ከሚጠጣም ሆነ ከሚበላ ነገር ጥሩውን (መልካም የሆነውን) ፈቅዷል፤ ልበናንም ሆነ አካልን እንዲሁም መኖርያ ስፍራን ንፁህ ማድረግን አዟል፤ የአላህ ሰላትና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈን ነብያቶችም እንዳዘዙት ሁሉ ጋብቻን የተፈቀደ አድርጓል፤ እነርሱ በጥሩ ነገር ሁሉ የሚያዙ ናቸውና።............................ 139
34- እስልምና በአላህ ማጋራት፣ ክህደት፣ የጣኦት አምልኮ፣ በአላህ ላይ ያለ እውቀት መናገር፣ ልጅን መግደል፣ ክቡር የሆነችውን የሰውን ልጅ ነፍስ ማጥፋት፣ በምድር ላይ ማበላሸት፣ ድግምት፣ ግልፅም ይሁን ድብቅ ብልግና፣ ዝሙት፣ ግብረሰዶም፣ ወለድ መብላትንም ከልክሏል፣ የበከተን ስጋ፣ ለጣኦታትና ለቅርፃ ቅርፅ ተብሎ የታረደን ስጋ እና የአሳማ ስጋን መብላት እና ሌሎችም ርኩስና ቆሻሻን ሁሉ ከልክሏል፤ ወላጁን ያጣን (የቲም) ልጅ ንብረት መብላት፣ ሚዛንና መለኪያን ማዛባት፣ ዝምድና መቁረጥን የመሰሉ የሐራም (እርም) ነገሮች መሰረት የሆኑትን ይከለክላል። ሁሉም ነብያቶችም እነዚህ የተዘረዘሩት የተከለከሉ ሐራም መሆናቸው ላይ ይስማማሉ። ..................................... 142
35- እስልምና እንደ ውሸት፣ ማታለል፣ መካድ፣ ክፋትን ማመርቀዝ፣ ምቀኝነት፣ መጥፎ ተንኮል፣ ስርቆት፣ ድንበር ማለፍንና ሰዎችን መበደልን ከመሰሉ የተወገዙ ስነምግባሮችና መጥፎ ማንነቶች ሁሉ ይከለክላል። ......................................... 151
36- እስልምና ወለድ፣ የሰዎች ጉዳት፣ መሸወድ፣ ሰዎችን መበደል፣ ማጭበርበር ካለበትም ሆነ ማህበራዊም ይሁን ህዝባዊ ወይንም

ግለሰባዊ ጉዳት ወደ ማምጣት ሊያደርስ የሚችልን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴን ይከለክላል። .......................................................... 160
37- እስልምና የመጣው አእምሮን ለመጠበቅ እና አስካሪ መጠጥ መጠጣትን ከመሰሉ እርሱን ከሚያበላሹ ነገሮች በመከልከል ነው። እስልምና የአዕምሮንም ደረጃ ከፍ በማድረግ የፍርድ ማብሰልሰያ አድርጎ ከአጉል እምነትም ሆነ ከጣዖት አምልኮ ጭንቅ ገላገለው። በመሆኑም በእስልምና አንዱን የማህበረሰብ ክፍል ከሌላው የሚለዩ ምስጢሮች ወይም ፍርዶች የሉም፤ ሁሉም ፍርዶቹ እና ህጎቹ ጤናማ ከሆኑ አእምሮዎችም ጋር የሚስማሙ ናቸው፤ እነርሱም ከፍትህና ጥበብ ጋ የሚገጠሙ ናቸው። .... 165
38- ሐሰተኛ ሃይማኖቶች ተከታዮቻቸው በውስጣቸው ያሉትን እርስ በርስ መጣረሶች እና አዕምሯቸው የማይቀበሏቸውን ጉዳዮች ካልተረዱ የሃይማኖቱ አባቶች ሃይማኖትን ከምክንያታዊነት በላይ ነው ብለው ተከታዮቻቸውን ያታልላሉ። አእምሮም ሀይማኖትን መረዳትና መገንዘብን ለመቻል እድሉ የለውም ይሏቸዋል። እስልምና ግን ሃይማኖትን ለአእምሮ ጎዳና የሚያበራለት ብርሃን እንደሆነ አድርጎ የሚቆጥር ሲሆን የሐሰት ሃይማኖቶች ግን ፍላጎታቸው ሰው አእምሮውን ትቶ እነሱን እንዲከተል ነው። እስልምና ታድያ ሰው የነገሮችን እውነታ ባሉበት ተጨባጭ ያውቅ ዘንድ አዕምሮውን እንዲያነቃ ይፈልጋል። .. 169
39- እስልምና ትክክለኛ እውቀትን ያልቃል። ስሜትን ከመከተል የጠራ የሆነ ሳይንሳዊ ምርምርን ያበረታታል። ስለ ራሳችንም ሆነ በዙሪያችን ስላለው ፍጥረተ ዓለም በተመለከተ እንድናስተነትን ጥሪ ያደርጋል። እናም ትክክለኛ የሳይንስ ምርምር ውጤቶች ከእስልምና ጋር አይጋጩም። .................................................... 172

40- በአላህ አምነው ለታዘዙትና መልእክተኞቹንም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እውነት ብለው የተቀበሉትን ካልሆነ በቀር አላህ ከማንም ስራውን አይቀበለውም ለመልካም ስራውም አኺራ ላይ አይመነዳውም። የደነገገውንም ካልሆነ በቀር የትኛውንም አምልኮ አይቀበለም። የሰው ልጅ በአላህ ከካደ በኋላ አላህ መልካም ይመነዳኛል ብሎ እንዴት ያስባል?! ማንኛውም ሰው ቢሆን በሁሉም ነብያቶች ብሎም በነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የአላህ መልእክተኝነት አምኖ ካልተገኘ አላህ እምነቱን አይቀበለውም። ........................................................................................................ 176

41- የሁሉም መለኮታዊ ተልእኮዎች ግብ፡- እውነተኛው ሃይማኖት ወደ ሰው ልጅ እንዲሰርፅ ብሎም ለዓለማት ጌታ አላህ ንጹሕ ባርያ ይሆን ዘንድ፤ የሰው ልጅን ከአጉል ባህል ወይም ከአጉል እምነት ወይንም ከቁሳዊ ባርነት ነፃ ያውጣው ዘንድ ነው። ይኸውና እስልምና የሰዎችን ፍፁምነትንም አይሞግትም ካላቸው ሰብአዊ ደረጃ በላይ አንስቶም ጌቶች እና አማልክት አያደርጋቸውም። ................................................................ 180

42- አላህ በእስልምና ንስሀን (ተውባን) ደንግጓል፡ ይህም - አንድ ሰው ባጠፋ ጊዜ ወደ ጌታው መመለሱ እና ኃጢአቱን መተው ነው፤ እስልምና ከእርሱ በፊት የነበሩትን ኃጢአቶች ያጠፋል (ያስምራል)፤ ንስሐም ከዚህ በፊት የነበሩትን ኃጢአቶች ሁሉ ይሰርዛል፤ ለዚህም ማንም ኋጢአቱን በሰው ፊት መናዘዝ አያስፈልገውም። ................................................................ 184

43- በእስልምና በሰው እና በአላህ መካከል ያለው ቁርኝት ቀጥተኛ ነው። በአንተና በአላህ መካከል ምንም አማላጅ አያስፈልግህም።

የእስልምና ሃይማኖት የሰውን ልጅ አማልክት ወይም በጌትነት ወይም በአምላክነት የአላህ ተጋሪ እንዳናደርግ ይከለክለናል። 187

44- በዚህ ፅሁፍ መጨረሻ ላይ ማውሳት የምንፈልገው ነገር ቢኖር፡ ሰዎች በተለያዩ ጊዜዎች፣ ብሄረሰቦች እና ሀገሮች መሆናቸውን እናስተውላለን፤ ኧረ እንደውም መላው የሰው ልጅ ማህበረሰብ በሀሳቡ እና በአላማው የተለያየ በአከባቢው እና በድርጊቱም የተለያየ በመሆኑ አንድ የሚያደርግ ሥርዓት እና ጥበቃን የሚያደርግለት ገዥ ወደ ጥሩ የሚመራው መመሪያ ጋር ግዴታ ያስፈልገዋል። የአላህ ሰላትና ሰላም በእነርሱ ላይ ይስፈን የተከበሩት የአላህ መልእክተኞችም ከአላህ -ሱብሓነሁ ወተዓላ- በሚወርድላቸው ወሕይ በአላህ ሸሪዓ በማሰባብሰብ፣ በሰዎች መካከል በእውነት በመፍረድ ሰዎችን ወደ መልካምና ቀና ጉዳና የመምራት ኋላፊነትን ተሸክመው ነበር። ሰዎች ለእነኚህ የአላህ መልእክተኞች ተልእኮ ባላቸው ምላሽ ሰጭነት እንዲሁም ለመለኮታዊው ጥሪም ባላቸው የጊዜ ቅርበትም ልክ ሁኔታቸው ይስተካከል ነበር። ጥራት ይገባውና አላህ መልእክተኛውን ሙሐመድን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) በመላክ ለሰው ልጆች የሚያስተላልፈውን ተልእኮ ደመደመና ለነብያችን ሙሐመድ ተልእኮም ዘለቄታን ፃፈላት (ደነገገለት)፤ ለሰው ልጆችም ምራቻ፣ እዝነት፣ ብርሃን፣ ጥራት ወደ ተገባው አላህ የምትመራም ቅን ፈለግ አደረጋት። .................................. 190

45- ስለዚህም የሰው ልጅ ሆይ! ከአጉል ባህልና ከልምድ እንዲሁም ከድንቁርና በመላቀቅ እስልምናን ተቀብለህ በሐቀኝነት ለአላህ እንድትቆም ከሞትክም በኋላ ወደ ጌታህ ተመላሽ መሆንህን እንድታውቅ፤ ራስህንም በዙሪያህ ያለውንም አድማስ እንድትመለከት አደራ እያልኩ እጋብዝሃለሁ። ያኔ በሃይማኖታዊም በአለማዊም ጉዳይህ ደስተኛ ትሆናለህ። ወደ

እስልምና ሃይማኖት ለመግባት የፈለገ "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ እንደሆኑ" ለመመስከር "ላ ኢላሃ ኢለሏህ ሙሓመዱን ረሱሉሏህ" ብሎ መመስከር ብቻ ነው የሚጠበቅበት። ይህችን የምስክርነት ቃል ከሰጡ ሙስሊም ሆነዋል። ከዚህ በኋላ አላህ በደነገገው መልኩ ሶላትንም እየሰገዱ፣ ፆሞን እየፆሙ፣ ከቻሉም ሓጅ በማድረግ አላህን ማምለክ ላይ አደሩ። .................................................... 192

am180v1.0 - 03/09/2026